# ስንክሳር ዘወርኀ የካቲት

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ወርኀ ፡ የካቲት ፡ ቡሩክ ፡ መዓልቱ ፡ ፲ ፡ ወ፩ ፡ ወእምዝ ፡ ይትዌሰክ ። ወአመ ፡ ፩ ፡ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ማኅበረ ፡ ጉባኤ ፡ ቅዱሳን ፡ ፻ወ፶ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለቴዎዶስዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ዘየዓቢ ።

፪፤ ወኮነ ፡ ተጋብኦቶሙ ፡ በእንተ ፡ መቅዶንዮስ ፡ ዘኮነ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ዘክህዶ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወይቤ ፡ በእከየ ፡ ልቡ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ወካዕበ ፡ በእንተ ፡ ሰባልዮሳውያን ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ወሣልስ ፡ በእንተ ፡ አቡሊናርዮሳውያን ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ እስመ ፡ ወልድ ፡ ኢነሥአ ፡ ነፍሰ ፡ ነባቢተ ፡ ወለባዊተ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ መለኮቱ ፡ ኮኖ ፡ ህየንተ ፡ ነፍስ ፡ ወልቡና ።

፫፤ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ክሡተ ፡ ስሕተቶሙ ፡ ለእሉ ፡ ከሀድያን ፡ ሰአልዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ከመ ፡ ያስተጋብእ ፡ ሎሙ ፡ ማኅበረ ፡ ጉባኤ ፡ ውእቱኒ ፡ ተወክፈ ፡ ቃሎሙ ፡ ወሶቤሃ ፡ ፈነወ ፡ መልእክተ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ወኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ወኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ ወኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይምጽኡ ፡ ምስለ ፡ ኤጲስቆጶሳቲሆሙ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ምሁራነ ።

፬፤ ወተጋብኡ ፡ ወበጽሑ ፡ እሉ ፡ አበው ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ወኢመጽአ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ አላ ፡ ፈነወ ፡ ሰብአ ፡ ማእምራነ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ መልእክት ፡ እንተ ፡ ጸሐፋ ፡ በእዴሁ ።

፭፤ ፡ ወአፈ ፡ ጉባኤሆሙ ፡ ኮነ ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወጸውዖ ፡ ለመቅዶንዮስ ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ይትናገር ፡ ሃይማኖቶ ፡ ርኩስተ ፡ ወይቤ ፡ ውእቱ ፡ ከሐዲ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኵሎሙ ፡ ፍጡራን ፡ አውሥአ ፡ ጢሞቴዎስ ፡

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የተባረከ ፡ የየካቲት ፡ ወር ፡ መዓልቱ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው ፡ ከእንግዲህም ፡ ይጨምራል ፡ በዚችም ፡ በየካቲት ፡ አንድ ፡ የከበሩ ፡ የመቶ ፡ ሃምሳ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የአንድነት ፡ ስብሰባ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ በታላቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ተደረገ ።

፪፤ ስብሰባቸውም ፡ የሆነው ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ስለ ፡ ሆነው ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በክፋቱ ፡ ኀሳቡ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ካደው ፡ ስለ ፡ መቅዶንዮስ ፡ ሁለተኛም ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ስለሚሉ ፡ ስለ ፡ ሰባልዮሳውያን ፡ ሦስተኛ ፡ ወልድ ፡ ከብቻው ፡ ሥጋ ፡ በቀር ፡ ነባቢት ፡ ለባዊት ፡ ነፍስን ፡ አልነሣም ፡ መለኮቱ ፡ በነፍስና ፡ በልቡና ፡ ፈንታ ፡ ሆነው ፡ ስለሚሉ ፡ ስለ ፡ አቡሊናርዮሳውያን ፡ ነው ።

፫፤ የእሊህ ፡ ከሀድያንም ፡ ስሕተት ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አሰባስቦ ፡ የአንድነት ፡ ጉባኤ ፡ ያደርግላቸው ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስን ፡ ለመኑት ፡ እርሱም ፡ ቃላቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትም ፡ መልእክትን ፡ ላከ ፡ ምሁራን ፡ የሆኑ ፡ ኤጲስቆጶሶቻቸውንም ፡ ይዘው ፡ እንዲመጡ ፡ አዘዛቸው ።

፬፤ እሊህም ፡ አባቶች ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ ተሰበሰቡ ፡ የሮሜው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሰት ፡ ግን ፡ አልመጣም ፡ ምሁራን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎችን ፡ ላከ ፡ እንጂ ፡ ከእሳቸውም ፡ ጋር ፡ በእጁ ፡ የጻፋትን ፡ ደብዳቤ ፡ ላከ ።

፭፤ የጉባኤውም ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ነው ፡ መቅዶንዮስንም ፡ ጠርቶ ፡ የረከሰች ፡ ሃይማኖቱን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ፡ ያ ፡ ከሀዲም ፡ እንደ ፡ ፍጥረቶች ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተፈጠረ ፡ ነው ፡ አለ ። ጢሞቴዎስም ፡ መልሶ ፡ መንፈስ

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎ፡ኢተአምርኑ፡ከመ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
ሕይወቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እፎ ፡ ትሬሲ ፡
ፍጡረ፡ሕይወቶ፡ለእግዚአብሔር፡ወይእዜኒ፡
ይኄይሰከ ፡ ትትመየጥ ፡ እምዛቲ ፡ ክህደት ፡
ርኵስት ፡ እምቅድመ ፡ ትባእ ፡ ውስተ፡ እሳተ ፡
ገሃነም ፡ዘለዓለም፡ውእቱሰ፡ኢሰምዐ፡ወኢተ
መይጠ ፡ ወአውገዝዎ ፡ ወመተርዎ ፡ እምሢ
መቱ፡ወሰደድዎ፡እምቤተ፡ክርስቲያን።

፪፤ ወእምዝ ፡ ጸውዖሙ ፡ ለሰባልዮሳውያን ፡ ወይ
ቤሎሙ ፡ ምንተ ፡ ትብሉ ፡ አንትሙ ፡ በእንተ ፡
ሃይማኖትክሙ፡ተናገሩ፡አውሥኡ፡ወይቤሉ፡
እሙንቱ፡እስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡
ቅዱስ፡፩፡ገጽ፡ወ፩ዱ፡ህላዌ፡ወኢይሤለስ፡
በምንትኒ።

፫፤ አውሥአ ፡ አብ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወይቤሎሙ ፡
ተሥዕረኑ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ዘይቤ ፡ እስመ ፡
ወልድ ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወመ
ንፈስ፡ቅዱስ፡ወረደ፡በርእየተ፡ርግብ፡ፀዓዳ፡
ወነበረ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ወአብ ፡ እምውስተ ፡
ደመና፡ጸርሐ፡እንዘ፡ይብል፡ዝንቱ፡ውእቱ፡
ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ ዘኪያሁ ፡ ሠመርኩ ፡
ወሎቱ፡ስምዕዎ።ወበከመ፡ትቤሉ፡አንትሙ፡
ተሥዕረ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትናክሙ ፡ ዘተጠ
መቅሙ፡በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡
ቅዱስ ፡ ወይእዜኒ ፡ ኅድጉ ፡ ዘንተ ፡ ዕልወተ
ክሙ ፡ ወይኄይሰክሙ ፡ ትትመየጡ ፡ እስመ ፡
አርዮስ ፡ ቀዳሚ ፡ ክህዶ ፡ ለወልድ ፡ ወመቅዶ
ንዮስ ፡ ዝንቱ ፡ ክህዶ ፡ ለመንፈስ፡ ቅዱስ ፡
ወአንትሙ ፡ ኮንክሙ ፡ ሱቱፋነ ፡ ምስሌሆሙ ፡
እሙንቱሰ ፡ ኢሰምዑ ፡ ወኢተመይጡ ፡ ወማኅ
በረ፡ጉባኤ፡አውገዞሙ፡ወሰደዶሙ፡እምቤተ፡
ክርስቲያን።

፬፤ ወእምዝ፡ዓዲ፡አውገዘ፡ትምህርቶ፡ለአቡሊና
ርዮስ፡ዘይቤ፡እስመ፡ወልድ፡ኢነሥአ፡ነፍሰ፡
ነባቢተ፡ወለባዊተ፡ዘእንበለ፡ሥጋ፡ባሕቲቱ።

፭፤ ወእሉ፡ አበዊነ፡ ፫ወ፺፡ ኤጲስቆጶሳት፡ ወሰኩ፡
በዲበ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘይብል ። ወነአ
ምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእ ፡ ማሕየዊ ፡
ዘሠረፀ፡እምአብ፡ ንስግድ ፡ ሎቱ ፡ ወንስብሖ ፡
ምስለ፡አብ፡ወወልድ፡ዘነበበ፡በነቢያት።

ቅዱስ፡የእግዚአብሔር፡ሕይወቱ፡እንደሆነ፡
አታውቅምን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕይወት ፡
እንዴት ፡ ፍጡር ፡ ታደርገዋለህ ፡ አሁንም ፡
ከዚች ፡ ከረከሰች ፡ ሃይማኖትህ ፡ ተመለስ ፡
ወደ፡ዘላለማዊ፡እሳተ፡ገሃነም ፡ከመግባትህ፡
በፊት ፡ ንስሐ ፡ ግባ ፡ አለው ። እርሱ ፡ ግን ፡
ሰምቶ ፡ አልተመለሰም ፡ እነርሱም ፡ አወገ
ዙት ፡ ከሹመቱም ፡ ሻሩት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲ
ያንም፡አሳደዱት።

፪፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰባልዮሳውያንን ፡ ጠርቶ ፡
እናንተስ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ምን ፡ ትላ
ላችሁ ፡ ተናገሩ ፡ አላቸው ፡ ፡ እነርሱም ፡ አብ ፡
ወልድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡አንድ፡ገጽ፡አንድ፡
ህላዌ ፡ ነው ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ሦስት ፡
አይሆንም፡አሉ።

፫፤ አባት ፡ ጢሞቴዎስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡
አላቸው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውስጥ ፡ ወልድ ፡ ቁሞ፡
ሳለ ፡ በፀዓዳ ፡ ርግብ ፡ አምሳል ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡
አብም፡ከደመና፡ውስጥ፡ሁኖ፡በእርሱ፡ደስ፡
የሚለኝ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እር
ሱን ፡ ስሙት ፡ ብሎ ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ፡
ያለው፡የወንጌል፡ቃል፡ተሻረን።እናንተ፡እን
ደምትሉት፡ከሆነ፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈ
ስቅዱስ፡ ስም ፡ የተጠመቃችሁት ፡ የክርስት
ናችሁ፡ጥምቀት፡ተሽሮአል፡አሁንም፡ክህደ
ታችሁን፡ተዉ፡ብትመለሱም፡ይሻላችኋል።
አርዮስም፡አስቀድሞ፡ወልድን፡ካደው፡ይህ፡
መቅዶንዮስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ካደው ፡
እናንተም፡የእነርሱ፡ተሳታፊዎች፡ሆናችሁ።
እነርሱም ፡ ሰምተው ፡ አልተመለሱም ፡ የአን
ድነት ፡ ጉባኤም ፡ አውግዞ ፡ ከምእመናን ፡
አንድነት፡ለያቸው።

፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ወልድ ፡ ነባቢት ፡
ለባዊት፡የሆነች፡ነፍስን፡አልነሣም፡ሥጋን፡
ብቻ ፡ እንጂ ፡ የሚለውን ፡ የአቡሊናርዮስን ፡
ትምህርት፡አወገዘ።

፭፤ እሊህ ፡ መቶ ፡ ኃምሳ ፡ የሆኑ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡
አባቶቻችንም ፡ በጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡
ጌታ ፡ አዳኝ ፡ በሚሆን ፡ ከአብ ፡ በሠረፀ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እናምናለን ፡ እንሰግ
ድለት ፡ እናመሰግነውም ፡ ዘንድ ፡ ከአብና ፡
ከወልድ ፡ ጋራ ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ የተናገረ ፡
የሚለውን፡ጨመሩ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ወነአምን፡በአሐቲ፡ቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ እንተ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ጉባኤ፡ዘሐዋርያት።

፲፩፡ ወነአምን ፡ በአሐቲ ፡ ጥምቀት ፡ ለሥርየተ ፡ ኃጢአት ፡ ወንሴፎ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወሕ ይወተ፡ዘይመጽእ፡ለዓለመ፡ዓለም።

፲፪፡ እስመ ፡ ፫፻፲ ወ ፰ቱ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ አበዊነ፡ነበቡ፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ወአልቦ፡ ማኅለቅት፡ለመንግሥቱ።

፲፫፡ ወተጋብኡቶሙ ፡ ለእሉ ፡ ፪ወ፻ ፡ አበው ፡ በእ ንተ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ወከሠቱ፡በእንቲአሁ። ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ለአበዊነ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፡ ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ በምትሆን ፡ ሐዋርያት ፡ በሰበ ሰቧት ፡ በአንዲት ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያንም፡እናምናለን።

፲፩፡ ኃጢአትን ፡ ለማስተስረይ ፡ በአንዲት ፡ ጥም ቀት ፡ እናምናለን ። የሙታንንም ፡ መነሣት ፡ የሚመጣውንም ፡ ሕይወት ፡ ለዘላለሙ ፡ ተስፋ፡እናደርጋለን።

፲፪፡ ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንቱ ፡ አባቶቻችን ፡ የተናገሩት ፡ ለመንግሥቱ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ እስከሚል ፡ ነው።

፲፫፡ እሊህ ፡ መቶ ፡ ኃምሳው ፡ አባቶች ፡ የተሰበ ሰቡት ፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለሆነ፡ ስለርሱ ፡ የእርሱን ፡ ነገር ፡ አብራሩ ። ለእ ርሱም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ የአባቶቻችንም ፡ በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ማኅበረ፡ኢየሱስ፡ኬንያ።ጉቡአን፡ዘቊስጥንጥንያ።ምስለ፡ሰባልዮስ፡አብድ፡ለመቅ ዶንዮስ፡ሐራውያ። ታጽድፍዎ ፡ ውሳጤ ፡ ግብ ፡ ዘዕሙቅ ፡ ቀላያ ። ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ ኢይኪድ፡ ባሕርያ።

፲፬፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያኑ፡ለቅዱስ፡ጴጥሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወተፍ ጻሜተ ፡ ሰማዕት ፡ ዘአውገዞ ፡ ለአርዮስ ፡ ከሀዲ ፡ ወኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ በሀገረ ፡ እስክንድ ርያ፡በተፍጻሜተ፡መንግሥቱ፡ለዲዮቅልጥ ያኖስ፡ዕልው።

፲፭፡ ወሶበ ፡ ነግሠ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ጻድቅ ፡ አንሐለ፡ኵሎ፡አብያተ፡ጣዖታት፡ወሐነፃ፡ ለዛቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስሙ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በምዕራብ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወተቀደሰት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ወኮኑ ፡ በው ስቴታ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡ብዙኃን።

፲፮፡ ወነበረት ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ነግሡ ፡ ተንባላት ፡ በብሔረ ፡ ግብጽ፡ ወእምድኅረ፡ ነግሡሂ ፡ ነበረት ፡ ከዊና ፡ ዕው ቅተ፡ወእምዝ፡ንሕለት፡ወበድወት።

፲፯፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑሰ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ፡ጽንዕት።

፲፬፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በከሀዲው ፡ ዲዮቅልጥያኖስ መንግሥት ፡ ፍጻሜ ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞተ ፡ ከሀዲ፡አርዮስንም፡ያወገዘ፡የሰማዕታትም፡ ፍጻሜ ፡ የሆነ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የከበረችበት ፡ ነው።

፲፭፡ ጻድቁ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ የጣ ዖታትን ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ አፈረሰ ፡ ይችንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ከተማ ፡ በምዕራብ፡በኩል፡በቅዱስ፡ጴጥሮስ፡ስም፡ አነፃት ፡ በዛሬዋም ፡ ዕለት ፡ ከበረች ፡ በው ስጧም ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራ ቶች፡ተገለጡ።

፲፮፡ ያቺም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስላሞች ፡ በግ ብጽ ፡ እስከ ፡ ነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ኖረች ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ የታወቀች ፡ ሁና ፡ ትኖር ፡ ነበር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈረሰችና ፡ ምድረ፡በዳ፡ሆነች።

፲፯፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እጅ ፡ የተያ ዘችና፡የተጠበቀች፡ናት።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፲፰፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለቅዳሴ ፡ ቤትከ ፡ እንተ ፡ ሐነፅዋ ፡ ሕዝባ ። ለእስክንድርያ ፡ መንገለ ፡ ምዕራባ ። ጴጥሮስ ፡ ዘኮንከ ፡ ለስምዐ ፡ ሃይማኖት ፡ መክብባ ። ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ከመ ፡ ለብእሲት ፡ ነበባ ። ለማኅደርከ ፡ ዘትነብር ፡ ቅሩባ ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲፱ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ለንጊኖስ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ ዘደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ዘአፍአ ፡ ሀገረ ፡ እስክን ድርያ ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምሀገረ ፡ ኪልቅያ ፡ ወበህየ ፡ መንኰሰ ፡ መምህሩሰ ፡ መፍቀሬ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘይጐይይ ፡ እምክብረ ፡ ሰብእ ፡ ወበውእቱ ፡ ጊዜ ፡ አዕረፈ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ዘደብረ ፡ ዚአሆሙ ፡ ወፈቀዱ ፡ አኃው ፡ ይሢምዎ ፡ ለአረጋዊ ፡ መምህሩ ፡ ዘስሙ ፡ ሉክያኖስ ፡ ወነሥአ ፡ በጽሚት ፡ ለረድኡ ፡ ለንጊኖስ ፡ ወወጽአ ፡ እምኪልቅያ ፡ ወሖረ ፡ ብሔረ ፡ ሶርያ ፡ ወነበሩ ፡ ኀቡረ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይግበር ፡ ዲበ ፡ እደዊሆሙ ፡ ተአምራተ ፡ ወመን ክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወኮነ ፡ ሎሙ ፡ ውዳሴ ፡ ወክብር ፡ እምኀበ ፡ ሰብእ ።

፫፤ ወወጽአ ፡ አባ ፡ ለንጊኖስ ፡ በምክረ ፡ መምህሩ ፡ ወሖረ ፡ ወበጽሐ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወሶበ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ተቀበልዎ ፡ በፍሥሓ ፡ ወነበረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወበእንተ ፡ ዘአእምሩ ፡ ገድሎ ፡ ወት ሩፋቶ ፡ ወጽድቆ ፡ ሤምዎ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ለአባ ፡ ለንጊኖስ ፡ ላዕለ ፡ ደብረ ፡ ዝጋግ ።

፬፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ መጽአ ፡ መምህሩ ፡ አባ ፡ ሉክያኖስ ፡ ወነበሩ ፡ ኅቡረ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ተድባባተ ፡ አሕማር ፡ ወይሴሰዩ ፡ እምግብረ ፡ እደዊሆሙ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ በ፩ልብ ፡ ወገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእደዊሆሙ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወእምዝ ፡ አባ ፡ ሉክያኖስ ፡ አዕረፈ ።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሁለት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ውጭ ፡ የደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ገዳም ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ለንጊኖስ ፡ አረፈ ።

፪፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከኪልቅያ ፡ አገር ፡ ነው ፡ በዚያም ፡ መነኰሰ ፡ መምህሩም ፡ ክርስቶስን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ከሚሰጠውም ፡ ክብር ፡ የሚ ሸሽ ፡ ነበር ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የገዳማቸው ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አረፈ ፡ ይህንንም ፡ ስሙ ፡ ሉክያኖስ ፡ የተባለ ፡ አረጋዊ ፡ መምህሩን ፡ አበ ፡ ምኔትነት ፡ ሊሾሙት ፡ መነኰሳቱ ፡ ወደዱ ፡ እርሱም ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ ለንጊኖስን ፡ ይዞ ፡ በጭልታ ፡ ከኪልቅያ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ አገር ፡ ሔደ ፡ በአንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ግቢ ፡ በአን ድነት ፡ ተቀመጡ ፡ በእጆቻቸውም ፡ ብዙዎች ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ወደደ ፡ ከሰዎችም ፡ ዘንድ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴና ፡ ክብር ፡ ሆነባቸው ።

፫፤ አባ ፡ ለንጊኖስም ፡ በመምህሩ ፡ ምክር ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገር ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ገዳምም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉትና ፡ ከእሳቸው ፡ ጋራ ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አበ ፡ ምኔቱ ፡ አረፈ ፡ ተጋድሎውን ፡ ትሩፋቱንና ፡ ደግነቱን ፡ ስለ ፡ አወቁ ፡ በደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ገዳም ፡ ላይ ፡ አባ ፡ ለንጊኖስን ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አድርገው ፡ ሾሙት ።

፬፤ ከጥቂትም ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ መምህሩ ፡ አባ ፡ ሉክያኖስ ፡ መጣ ፡ የመርከቦችን ፡ ጣሪያዎች ፡ እየሠሩ ፡ በእጆቻቸውም ፡ ከሚሠሩት ፡ እየተ መገቡ ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ በመሆንም ፡ በአን ድነት ፡ ኖሩ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእጆቻቸው ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አደረገ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ሉክያኖስ ፡ አረፈ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፭፤ ወበመዋዕሊሁ፡ለመርቅያኖስ፡ዐላዊ፡ዘአስተ
ጋብአ፡ማኅበረ፡ኬልቄዶን፡ወፈነወ፡ላእካነ፡
ውስተ፡ ኵሎን፡ በሐውርት፡ ወምስሌሆሙ፡
ጦማረ፡ሃይማኖት፡ርኵስት፡ዘትሬስዮ፡ለክር
ስቶስ፡ ፩ዱ፡ ክልኤተ፡ ጠባይዓተ። ወሶበ፡
በጽሑ፡ኀበ፡ደብረ፡ዝጋግ፡ሠለስቱ፡እምላእ
ካኒሁ፡ለንጉሥ፡ወወሀብዎ፡ውእተ፡ጦማረ፡
ለአባ፡ለንጊኖስ፡ወይቤልዎ፡ንጉሥ፡መር
ቅያኖስ፡ አዘዘ፡ ከመ፡ ትእመኑ፡ በዝንቱ፡
ጽሑፍ፡ ወትጽሐፉ፡ ውስተ፡ ዝንቱ፡
መጽሐፍ።

፳፮፤ ወይቤ፡ አባ፡ ለንጊኖስ አንስ፡ ኢይክል፡ እግ
በር፡ምንተኒ፡ዘእንበለ፡ምክሮሙ፡ለአበውየ፡
ቀዱሳን፡ ወአንትሙ፡ ንዑ፡ ምስሌየ፡ ከመ፡
ንትማከር፡ ወአብአሙ፡ ውስተ፡ በዓት፡ ኀበ፡
ሀሎ፡ አብድንቲሆሙ፡ ለቅዱሳን፡ ወይ
ቤሎሙ፡ አ፡ አበውየ፡ ቅዱሳን፡ ኢትበሉ፡
ከመ፡ አንትሙ፡ ሰከብክሙ፡ ወአዕረፍክሙ፡
እስመ፡ ናሁ፡ አምጽኡ፡ ዘንተ፡ ጦማረ፡
ዘጽሑፍ፡ ውስቴቱ፡ ዘይሬስዮ፡ ለክርስቶስ፡
፩ዱ፡ክልኤተ፡ጠባይዓተ፡ትኤዝዙኒኑ፡ከመ፡
እመን፡ በቃሉ፡ ወእጽሐፍ፡ ውስቴቱ፡ አው፡
አልቦ፡ ወለእመ፡ ኢነገርክሙኒ፡ ዘእገብር፡
ሕየው፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፡አነ፡አወጽእ፡
አዕፅምቲክሙ፡እምዝንቱ፡መካን።

፳፯፤ አሜሃ፡ ወጽአ፡ ቃል፡ እምአብድንቲሆሙ፡
ኵሎሙ፡ ሰብእ፡ እንዘ፡ ይሰምዑ፡ ዘይብል፡
ኢትኅድግ፡ሃይማኖተከ፡ርትዕተ፡ዘአበዊነ፡
ሐዋርያት፡ ወዘአበዊነ፡ ፫፻፲ወ፰ቱ፡ ወኢት
ትሉ፡ ዘንተ፡ ጦማረ፡ ርኵሰ፡ አላ፡ አእትቶ፡
እመካነ፡ አብድንቲነ፡ ወሰሚያሙ፡ ላእካነ፡
ንጉሥ፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ አንከሩ፡ ፈድፋደ፡ ወበ
ጽሐ፡ ላዕሌሆሙ፡ ፍርሀት፡ ዐቢይ፡ ወኢተ
መይጡ፡ ኀበ፡ ንጉሥ፡ አላ፡ ላጸዩ፡ ርእሶሙ፡
ወመንኰሱ፡ ወነበሩ፡ ውስተ፡ ውእቱ፡ ደብር፡
እንዘ፡ ይትጋደሉ፡ ብዙኀ፡ አዝማነ፡ እስከ፡
አዕረፉ።

፳፰፤ ወቅዱስሰ፡ አባ፡ ለንጊኖስ፡ ፈጺሞ፡ ተጋድ
ሎቶ፡ ሠናየ፡ ወአሥመሮ፡ ለእግዚአብሔር፡
አዕረፈ፡በሰላም፡ወነሥአ፡አክሊለ፡ሕይወት።

፳፱፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይም
ሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፭፤ የኬልቄዶንን፡ ጉባኤ፡ በሰበሰበ፡ በከሀዲው፡
መርቅያኖስም፡ዘመን፡ወደ፡ሀገሮችም፡ሁሉ፡
መልእክተኞችን፡ ላከ፡ ከእርሳቸውም፡ ጋር፡
አንዱን፡ ክርስቶስን፡ ወደ፡ ሁለት፡ ባሕርይ፡
የምትከፍል፡የረከሰች፡የሃይማኖቱ፡ደብዳቤ፡
አለች። ከንጉሥ፡ መልእክተኞች፡ ሦስቱ፡
ወደ፡ ደብረ፡ ዝጋግ፡ በደረሱ፡ ጊዜ፡ ያንን፡
ደብዳቤ፡ ለአባ፡ ለንጊኖስ፡ ሰጡት፡ በዚህ
ጽሑፍ፡ እንድታምኑ፡ በውስጡም፡ እንድት
ፈርሙ፡ ንጉሥ፡ መርቅያኖስ፡ አዝዞአል፡
አሉት።

፳፮፤ አባ፡ ለንጊኖስም፡ ከቅዱሳን፡ አባቶቼ፡ ጋር፡
ሳልማከር፡ እኔ፡ ምንም፡ ምን፡ መሥራት፡
አልችልም፡እንድንማከርም፡እናንተም፡ከእኔ፡
ጋር፡ኑ፡አላቸውና፡የቅዱሳን፡በድኖች፡ወደ፡
አሉበት፡ ዋሻ፡ ውስጥ፡ አስገባቸውና፡ የከበ
ራችሁ፡ አባቶቼ፡ ሆይ፡ እናንተ፡ ዐርፈን፡
ተኝተናል፡ አትበሉ፡ እነሆ፡ አንዱን፡ ክር
ስቶስን፡ ሁለት፡ ባሕርይ፡ የሚያደርግ፡ በው
ስጡ፡የተጻፈበትን፡ይህን፡ደብዳቤ፡አምጥተ
ዋልና፡ በቃሉ፡ አምን፡ ዘንድ፡ በውስጡም፡
እፈርም፡ዘንድ፡ታዙኛላችሁን፡ወይም፡አታ
ዙኝም፡ የምሠራውንም፡ ካልነገራችሁኝ፡
ሕያው፡ እግዚአብሔርን፡ ዐፅሞቻችሁን፡
ከዚህ፡ቦታ፡አወጣለሁ፡አላቸው።

፳፯፤ ያን፡ጊዜ፡ሰዎች፡ሁሉም፡እየሰሙ፡ከአስከሬ
ናቸው፡ የአባቶቻችንን፡ የሐዋርያትንና፡
የሦስት፡መቶ፡ዐሥራ፡ስምንቱን፡የቀናች፡
ሃይማኖትን፡ አትተው፡ ይህንንም፡ የረከሰ፡
ደብዳቤ፡ አትከተል፡ ከአስከሬናችን፡ ቦታ፡
አርቀው፡እንጂ፡የሚል፡ቃል፡ወጣ፡የንጉሥ፡
መልእክተኞችም፡ ይህን፡ ነገር፡ ሰምተው፡
እጅግ፡አደነቁ፡በላያቸውም፡ታላቅ፡ፍርሀት፡
አደረባቸው፡ ወደ፡ ንጉሥም፡ አልተመ
ለሱም፡ ራሳቸውን፡ ተላጭተው፡ መነኰሱ፡
እንጂ፡እስከ፡አረፉም፡ድረስ፡ብዙ፡ዘመን፡
እየተጋደሉ፡ኖሩ።

፳፰፤ የከበረ፡ አባ፡ ለንጊኖስም፡ ያማረ፡ ተጋድ
ሎውን፡ ጨርሶ፡ እግዚአብሔርንም፡ አገል
ግሎ፡ በሰላም፡ አረፈ፡ የሕይወት፡ አክሊል
ንም፡ተቀበለ።

፳፱፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በጸሎቱ፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡
ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

አርኬ
ሰላም፡እብል፡መዓልተ፡ወለያልየ። ትሩፋቲከ፡አቡየ።ለንጊኖስ፡አነክር፡ዘተውህበከ፡ዕበየ።ኀበ፡ኢሀሎከ፡ሶበ፡ቆብዓከ፡ርእየ።ሰይጣን፡ተኃፊሮ፡እፎኑመ፡ጐየ።

፲፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሊ ፡ ዘየዓቢ ፡ ርእሰ ፡ ኵሎሙ ፡ ገዳማውያን ፡ ወዘ ውገ፡መላእክት፡ ትጉሃን።

፲፩፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ እምሀገረ ፡ እስክን ድርያ፡ ወቦቱ ፡ እኁው ፡ ዘስሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወአቡሆሙ ፡ ባዕል ፡ ፈድፋደ ፡ ዘኢይት ኌለቍ ፡ ብዝኅ ፡ ንዋዩ ፡ ወብዕሉ ። ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ ወተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ኀዘኖሙ ፡ አኀዙ፡ይክፍሉ፡ርስተ፡አቡሆሙ፡ወንዋዮ፡ ወኮነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘይነሥእ ፡ ክፍለ ፡ ዘየዐቢ ፡ ወይሁቦ ፡ ለጳውሊ ፡ ዘይንእስ ፡ ክፍለ፡ ወበእ ንተዝ ፡ ኀዘነ ፡ ጳውሊ ፡ ወይቤሎ፡ ለእኁሁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለምንት ፡ ኢትሁበኒ ፡ እምርስተ ፡ አቡየ ፡ ክፍልየ ፡ ርቱዐ፡ ወአሥኦ ፡ ወይቤሎ፡ እኁሁ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ወሬዛ ፡ ወትዘሩ ፡ ንዋየ፡ወአነ፡አዐቅብ፡ለከ፡እስከ፡ ትልሕቅ።

፲፪፡ ወበእንተዝ ፡ተምዐ ፡ ጳውሊ ፡ ወተበአሱ ፡ በበ ናቲሆሙ ፡ ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ሎሙ ፡ ፍትሐ ፡ ወእንዘ ፡ እሙንቱ ፡ የሐውሩ ፡ ረከቡ ፡ ምውተ ፡ እንዘ ፡ ይፀውርዎ ፡ ሰብእ ፡ ወይወስድዎ ፡ ኀበ ፡ ይቀብርዎ ፡ ወብዙኃን ፡ ይተልውዎ ። ወተሰአለ ፡ ጳውሊ ፡ ፩ደ ፡ ብእሴ ፡ እምእለ ፡ ይተልውዎ ፡ ለምውት ፡ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘሞተ ፡ዮም ፡ ወአውሥኦ ፡ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ አእምር ፡ ኦ ፡ ወልድየ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ዘሞተ ፡ ዮም ፡ ባዕል ፡ ፈድፋደ ፡ በወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ወዘ ይትፌጋዕ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ወናሁ ፡ ኀደጎ ፡ ለዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ወየሐውር ፡ ዕራቆ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ወውስተ ፡ ፍኖት ፡ ዘኢይትመየጥ ፡ እምኔሃ ፡ እስመ ፡ ሞተ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ መዋግደ ፡ ኃጢአት ።

፲፫፡ ወይእዜኒ ፡ ኦ ፡ ወልድየ ፡ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንትጋደል ፡ በእንተ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍስነ ፡ እስመ ፡ ንሕነ ፡ ኢነአምር ፡ ከመ ፡ ማእዜ ፡ ንመውት ፡ ወባሕቱ ፡ ብዑዕ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወሥ ልጣን ፡ ዘዮኒድግ ፡ ኵሎ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡

፲፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የትጉሃን ፡ መላእክት ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ የገዳማውያን ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ የከበረ ፡ ታላቁ ፡ ጳውሊ ፡ አረፈ።

፲፩፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ጴጥ ሮስ፡ የሚባል ፡ ወንድም ፡ አለው ፡ አባታ ቸውም ፡ የገንዘቡ ፡ ብዛት ፡ ሊቈጠር ፡ የማይ ቻል ፡ እጅግ ፡ ባለጸጋ ፡ ነበር ፡ በአረፈም ፡ ጊዜ ፡ የኀዘናቸው ፡ ቀን ፡ ሲፈጸም ፡ ርስቱንና ፡ ገን ዘቡን ፡ ሊካፈሉ ፡ ጀመሩ ፡ ጴጥሮስም ፡ ታላቁን ፡ ክፍል ፡ ወደ ራሱ ፡ በመውሰድ ፡ የሚ ያንሰውን ፡ ለጳውሊ ፡ የሚሰጠው ፡ ሆነ ። ስለዚህም ፡ ጳውሊ ፡ አዘነና ፡ ከአባቴ ፡ ርስት ፡ በትክክል ፡ ለምን ፡ አትሰጠኝም ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ አንተ ፡ ወጣት ፡ ስለሆንክ ፡ ታባክነ ዋለህ ፡ እስከ ፡ ምታድግ ፡ እኔ ፡ እጠብቅል ሃለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት።

፲፪፡ ስለዚህም ፡ ጳውሊ ፡ ተቆጣና ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጣሉ ፡ ይፈርድላቸውም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሔዱ ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ሲሔዱ ፡ ሰዎች ፡ ተሸክመውት ፡ ወደ ፡ ሚቀብሩበት ፡ ሲወስ ዱት ፡ ብዙዎችም ፡ የተከተሉትን ፡ የሞተ ፡ ሰውን ፡ አገኙ ፡ ጳውሊም ፡ ከተከተሉት ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ዛሬ ፡ የሞተው ፡ ማን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ያም ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለ ሰለት ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ዕወቅ ፡ አስተውል ፡ ይህ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ እጅግ ፡ ባለጸጋ ፡ የሆነ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ የሚለው ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ እነሆ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ ራቁቱን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ወደማይመለስበት ፡ መን ገድ ፡ ይሔዳል ፡ በኃጢአት ፡ ማዕበል ፡ ውስጥ ፡ እያለ ፡ ሙቷልና።

፲፫፡ አሁንም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ ነፍሳችን ፡ድኅነት ፡ ልንታገል ፡ ይገባናል ፡ እኛ ፡ መቼ ፡ እንደም ንሞት ፡ አናውቅምና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ ኑሮት ፡ ሥልጣንም ፡ ኑሮት ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የተወ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ የቅዱሳን ፡ ሀገር ፡ በሆነች ፡ በኢየ

www.ethiopianorthodox.org

ይነሥእ ፡ ክብረ፡ዐቢየ፡በኢየሩሳሌም፡ሰማያ
ዊት፡ሀገሮሙ፡ለቅዱሳን።
፲፬፡ ወሰበ ፡ ሰምዐ ፡ ብፁዕ ፡ ጳውሊ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡
ገዐረ፡እምልቡ፡ወይቤ፡ምንት፡ብየ፡ንዋየ፡
ዝንቱ፡ዓለም፡ኃላፊ፡እምድኅረ፡ኅዳጥ፡መዋ
ዕል፡አኮኑ፡አኀድጎ፡ወአሐውር፡ዕራቅየ። ወእ
ምዝ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ እኁሁ   ሀይቤሎ ፡
ኦ ፡ እኁየ ፡ ንትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ቤትነ ፡
እምይእዜሰ፡ኢይትናገር፡ምስሌከ፡በእንተ፡
ንዋይ፡ወኢምንተኒ።

፲፭፡ ወእምዝ ፡ ጐየ ፡ እምእኁሁ ፡ ወወጽአ ፡
እምሀገሩ፡ወቦአ፡ውስተ፡መቃብር፡ወነበረ፡
ውስቴቱ ፡ ፫ተ ፡ መዓልተ ፡ ወ፫ተ ፡ ለያልየ ፡
እንዘ፡ይጼሊ፡ወያስተበቍዕ፡ኀበ እግዚአ
ብሔር፡ከመ፡ይምርሖ፡ፍኖቶ፡ወእኁሁ፡
ጴጥሮስ ፡ ነበረ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡
የዐውድ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወየኃሥሦ ፡ ወኢ
ረከቦ ፡ ወኀዘነ ፡ ዐቢየ ፡ ኀዘነ ። ወብፁዕሰ፡
ጳውሊ፡ሶበ፡ነበረ፡ውስተ፡ይእቲ፡መቃብር፡
ኢተዘከረ፡መብልዐ፡ወመስቴ፡መጠነ፡፫ቱ፡
መዋዕል ፡ ወኢበጽሖ ፡ ፍርሃት ፡ ወድንጋፄ ፡
እስመ፡ኃይል፡አምላካዊት፡ተዐቅቦ።
፲፮፡ ወበራብዕት ፡ ዕለት ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኀቤሁ ፡ መልአኮ ፡ ወመሠጦ ፡ እምህየ ፡
ወወሰዶ፡ውስተ፡ውሳጤ፡ገዳም፡ዘመንገለ፡
ምሥራቅ ፡ ወአንበሮ ፡ በህየ ፡ወሀሎ፡ ነቅዐ ፡
ማይ ፡ ወተአምኖ ፡ ወዐርገ ፡ ሰማየ ፡ ወረከበ ፡
ብፁዕ ፡ ጳውሊ ፡ ግበባተ ፡ ዘአራዊት ፡ ወቦአ ፡
ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ግብ ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡
መልበሶ ፡ እምቈጽለ ፡ በቀልት ፡ ወጸለየ ፡
ከመዝ ፡ ወይቤ ፡ ኦ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡
ዕቀበኒ ፡ ወአድኅነኒ ፡ እምእዴሁ ፡ ለጸላኢ ፡
ዘአልቦ ፡ ምሕረት ፡ ወትምጻእ ፡ ላዕሌየ ፡
ምሕረትከ ፡ ወታጽንዓኒ ፡ እስከ ፡ እፌጽም ፡
ገድልየ ፡ በሥምረትከ ፡ ኦ ፡ ንጉሠ ፡ ኵሉ ፡
ትውልድ ፡ እስመ ፡ ለከ ፡ ኃይል ፡ ወስብሐት ፡
ለዓለመ፡ዓለም።
፲፯፡ ወነበረ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ በዓት ፡ ፹ ዓመተ ፡
ወኢርእየ ፡ ግሙራ ፡ መነሂ ፡ እምሰብእ ፡
ወልብሱ ፡ ጸጕረ ፡ በቀልት ፡ ወኮነ ፡ ይፌኑ ፡
ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቋዐ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡

ሩሳሌም፡ ሰማያዊት ፡ ታላቅ ፡ ክብርን ፡ ይቀበ
ላልና።
፲፬፡ የከበረ ፡ ጳውሊም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡
ከልቡ ፡ አዘነ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ የዚህ ፡
የኃላፊው ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ምኔ ፡ ነው ፡ ምን ፡
ይጠቅመኛል ፡ ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡
ትቼው ፡ ራቁቴን ፡ የምሔድ ፡ አይደለሁምን ፡
አለ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ወንድሙ ፡
ተመልሶ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡
እንመለስ፡ከእንግዲህ፡ስለ፡ገንዘብ፡ምንም፡
ምን፡ከአንተ፡ጋር፡አልነጋገርም፡አለው።
፲፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከወንድሙ ፡ ሸሽቶ ፡ ከሀገሩ ፡
ወጣ ፡ ከመቃብር ፡ ቤት ፡ ውስጥም ፡ ሦስት ፡
ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ መንገዱን ፡ ይመ
ራው፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየጸ
ለየና፡ እየማለደ ፡ ኖረ ። ወንድሙ ፡ ጴጥ
ሮስም፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ እየዞረ ፡ ሲፈልገው ፡
ሰነበተ ፡ ግን ፡ አላገኘውም ፡ ታላቅ ፡
ኃዘንንም፡ አዘነ ። የተመሰገነ ፡ ጳውሊ ፡ ግን ፡
ሦስት ፡ ቀኖች ፡ ያህል ፡ በዚያች ፡ መቃብር ፡
ቤት ፡ ሲኖር ፡ መብልና ፡ መጠጥን ፡ አላሰበም ፡
ፍርሀትና ፡ ድንጋፄም ፡ አልደረሰበትም ፡ አም
ላካዊት ፡ ኃይል ፡ ትጠብቀው ፡ ነበርና።
፲፮፡ በአራተኛዩቱም ፡ ዕለት ፡ እግዚአብሔር ፡
ወደርሱ ፡ መልአኩን ፡ ላከ ፡ ከዚያም ፡ ነጥቆ ፡
ወሰደው ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በምትገኝ ፡
በረሀ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ፡ በዚያም ፡ የውኃ ፡
ምንጭ ፡ አለ ፡ መልአኩም ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥ
ቶት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ የከበረ ፡ ጳውሊም ፡
አራዊት ፡ የሚኖሩበትን ፡ ጕድጓዶች ፡ አግ
ኝቶ ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ፍርኩታ ፡ ገባ ፡ ልብ
ሱንም ፡ ሰኔል ፡ ሠርቶ ፡ ለበሰ ። እንዲህም ፡
ብሎ ፡ ጸለየ ፡ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡
ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ ፡ ርኅራኄ ፡
ከሌለው ፡ ጠላት ፡ እጅ ፡ ጠብቀኝ ፡ አድነኝም ፡
ተጋድሎዬን ፡ እስከምፈጽም ፡ ታጸናኝ ፡ ዘንድ ፡
ቸርነትህ ፡ ወደእኔ ፡ ትምጣ ፡ የትውልድ ፡ ሁሉ ፡
ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ኃይል ፡ ጌትነት ፡ ክብር ፡ ገን
ዘብህ ፡ ነውና ፡ ለዘላለሙ።
፲፯፡ በዚያችም ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡
ኖረ ፡ ከሰውም ፡ ከቶ ፡ ማንንም ፡ አላየም ፡
ልብሱም ፡ ከሰኔል ፡ ቅጠል ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡
እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በጊዜ ፡ ምሴት ፡ ወምስሌሁ ፡ መንፈቀ ፡
ኅብስት፡ወይሁቦ፡ኪያሁ፡ለብፁዕ፡ጳውሊ።

፲፰፡ ወሶበ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡
ስብሐት፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ ቅድስናሁ ፡
ወጽድቆ ፡ ፈነወ ፡ መልአኮ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡
ዐቢይ፡ እንጦንዮስ ፡ ወውእቱ ፡ እንጦንዮስ ፡
ይሔሊ ፡ በልቡ ፡ ከመ ፡ ቀደመ ፡ ኀዲረ ፡
ውስተ፡ገዳም፡ወይቤሎ፡መልአክ፡አ፡እንጦ
ንዮስ፡ዘርኁቅ፡እምኔከ፡መጠነ፡፪መዓልት፡
ሀሎ ፡ ብእሲ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ ዘኢይደ
ልዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ዓለም ፡ ይኩኑ ፡ ከመ ፡
አሐቲ ፡ እምክያደ ፡ እገሪሁ ፡ ወበእንተ ፡
ጸሎቱ ፡ ዓለም ፡ ረትዐ ፡ ወምድርኒ ፡ ትሁብ ፡
ፍሬሃ ፡ ወበእንቲአሁ ፡ ይወርድ ፡ ጠል ፡ ዲበ ፡
ምድር ፡ ወፀሐይ ፡ ይሠርቅ ፡ ላዕለ ፡ ኃጥአነ ፡
ምድር፡ ኵሎሙ ፡ ወይፀወር ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረተ ፡
ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአ
ብሔር።

፲፱፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡
ተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡
እንዘ ፡ የአምን ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡
ምስሌሁ ፡ ወይጸይሕ ፡ ሎቱ ፡ ፍኖቶ ፡ ወረከበ ፡
አሠረ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ አሠረ ፡ አራዊት ፡
ወተለወ ፡ ውእተ ፡ አሠረ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡
በዓቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሊ ፡ ወጐድጐደ ፡
ኆኅቶ፡ ወቅዱስሰ ፡ አባ ፡ ጳውሊ ፡ ሐለየ ፡
ከመ ፡ እምግብረ ፡ ሰይጣን ፡ ውእቱ ፡ ወነሥአ ፡
ዕብነ፡ ዐቢየ ፡ ወአንበሮ ፡ ድኅረ ፡ ማዕፆ ፡
ኆኅቱ ፡ ወአባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ጸርሐ ፡ ወይቤ ፡
ኃሠሥኩ ፡ ይትወሀብ ፡ ሊተ ፡ ሰአልኩ ፡
እርከብ ፡ ጐድጐድኩ ፡ ይትረኃው ፡ ሊተ ፡
ወሶቤሃ ፡ አርኃወ ፡ ሎቱ ፡ ወአብአ ፡ ወተ
አምኁ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ በአምኃ ፡ መንፈ
ሳዊት ፡ ወጸለዩ ፡ ኅቡረ ፡ ወነበሩ።

፳፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ መኑ ፡
ስምከ ፡ አውሥአ ፡ አባ ፡ ጳውሊ ፡ ወይቤሎ ፡
ለእመ ፡ ኮንከ ፡ አንተ ፡ ዘኢተአምር ፡ ስምየ ፡
ለምንት ፡ አንሶሰውከ ፡ እስከ ፡ ዛቲ ፡ መካን ፡
ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ አርኃወ ፡ እግዚአብሔር ፡
ልቦ ፡ ለእንጦንዮስ ፡ ወይቤ ፡ ብፁዕ ፡ አነ ፡
እስመ፡ ደለወኒ ፡ ከመ ፡ እርአይ ፡ ጳውሎስሃ ፡

ወደርሱ ፡ ቁራኝ ፡ ይልክለታል ፡ ከርሱም ፡
ጋር፡ግማሽ፡እንጀራ፡አለ፡ያንን፡ለከበረው፡
ጳውሊ፡ይሰጠዋል።

፲፰፡ የክብር፡ባለቤት፡እግዚአብሔርም፡ቅድስና
ውንና፡ጽድቁን፡ይገልጥ፡ዘንድ፡በወደደ፡
ጊዜ፡መልአኩን፡ወደ፡ታላቅ፡አባት፡ወደ፡
እንጦንዮስ ፡ ላከ ፡ ይህም ፡ እንጦንዮስ ፡ በበ
ረሀ፡ ውስጥ ፡ መኖርን ፡ የጀመረ ፡ እርሱ ፡
እንደሆነ፡በልቡ፡ያስብ፡ነበር፡መልአኩም፡
እንዲህ፡አለው፡እንጦንዮስ፡ሆይ፡ከአንተ፡
የሁለት፡ቀን፡ጎዳና፡ርቆ፡በበረሀ፡ውስጥ፡
ሰው ፡ አለ ፡ የዓለም ፡ ሰዎች ፡ ከሚረግጥ
ባቸው፡የእግሩ፡ጫማዎች፡እንደ፡አንዲቱ፡
ሊሆኑ፡የማይገባቸው፡ስለ፡ርሱም፡ጸሎት፡
ዓለም ፡ ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ምድርም ፡
ፍሬዋን ፡ የምትሰጥ ፡ ጠል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
የሚወርድ ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኃጢአ
ተኞች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ፀሐይ ፡ የሚወጣ ፡
የሰውም ፡ ፍጥረት ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡
ውስጥ፡ተጠብቆ፡የሚኖር።

፲፱፡ አባ፡እንጦንዮስም፡ይህን፡ቃል፡በሰማ፡ጊዜ፡
ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ በረሀው ፡ መካከል ፡ ተጓዘ ፡
እግዚአብሔርም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሁኖ ፡ ጎዳና
ውንም፡እንደሚጠርግለት፡አምኖ፡ሲጓዝ፡
የሰውና፡የአራዊትን፡ፍለጋ፡አገኘ፡ያንንም፡
ፍለጋ ፡ ተከትሎ ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሊ ፡ በዓት ፡
ደረሰ ፡ በሩንም ፡ አንኳኳ ፡ የከበረ ፡ አባ ፡
ጳውሊ፡ ግን፡ ከሰይጣን ፡ ሥራ ፡ እንደሆነ ፡
አስቦ ፡ ታላቅ ፡ ደንጊያ ፡ ወስዶ ፡ ከመዝ
ጊያው፡ ጀርባ፡ አኖረ ፡ አባ፡ እንጦንዮስም ፡
ይሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ፈለግሁ ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡
ለመንኩ ፡ ይከፈትልኝም ፡ ዘንድ ፡ በሩን ፡
አንኳኳሁ ፡ ብሎ ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ።
በዚያንም፡ጊዜ፡ከፈተለትና፡ገባ፡እርስ፡በር
ሳቸውም ፡ በመንፈሳዊ፡ ሰላምታ ፡ እጅ ፡ ተነ
ሣሥተው ፡ በአንድነትም፡ ጸልየው ፡
ተቀመጡ።

፳፡ አባ ፡ እንጦንዮስም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ስምህ ፡
ማነው፡ አለው ፡ አባ ፡ ጳውሊም ፡ አንተ ፡
ስሜን ፡ ካላወቅህ ፡ እስከዚች ፡ ቦታ ፡ ለምን ፡
ተጓዝክ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡
እግዚአብሔር ፡ የእንጦንዮስን ፡ ልቡን ፡ ገለ
ጠለትና ፡ ገዳማዊ ፡ ጳውሎስን ፡ አየው ፡ ዘንድ ፡
ስለተገባኝ ፡ እኔ ፡ ብፁዕ ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ ከዚህም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ገዳማዊ፡ወእምዝ፡አኀዘ፡ይዘያነው፡በበይና
ቲሆሙ፡ዕበያቲሁ፡ ለእግዚአብሔር፨ወበ
ጊዜ፡ምሴት፡መጽአ፡ቋዕ፡ወወገረ፡ሎቱ፡
አሐተ፡ኅብስተ፡ፍጹምተ፡ወይቤሎ፡አባ፡
ጳውሊ፡ለአባ፡እንጦኒ፡ይእዜ፡አእመርኩ፡
ከመ፡አንተ፡ገብሩ፡ ለእግዚአብሔር፡እንዘ፡
እነብር፡አነ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ገዳም፡እስከ፡
ዮም፡፹ዓመተ፡ይፌኑ፡ሊተ፡እግዚአብሔር፡
ኵሎ፡አሚረ፡መንፈቀ፡ ኅብስት፡ወናሁ፡
ፈነወ፡ለከ፡ሲሳየከ። ወእምዝ፡ተንሥኡ፡
ወጸለዩ፡ ወበልዑ፡ ወሰብሕዎ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ወኀደሩ፡ ኵላ፡ ሌሊተ፡ እንዘ፡
ይጼልዩ።

፳፩፤ ወሶበ፡ ኮነ፡ ጽባሐ፡ ወሠረቀ፡ ፀሐይ፡
ተአምኑ፡በበይናቲሆሙ፡ወይቤሎ፡አባ፡

እንጦኒ፡ለአባ፡ጳውሊ፡አ፡አቡየ፡እምኀበ፡
አይቴ፡ትትሜጦ፡ምሥጢራተ፡ቅድሳት፡
በዝንቱ፡ኵሉ፡መዋዕለ፡ወአውሥአ፡ወይ
ቤሎ፡ብፁዕ፡ጳውሊ፡እግዚአብሔር፡ይፌኑ፡
ሊተ፡ መልአኮ፡ ወይሜጥወኒ፡ እምሥ
ጢራተ፡ቅድሳት፡ለለኵሉ፡ዕለተ፡ቀዳሚት፡
ሰንበት፡ወበዕለተ፡እሑድ፡ሰንባት፡ወከ
መዝ፡ይገብር፡ሊተ፡በኵሉ፡መዋዕል።

፳፪፤ ወእምዝ፡ ይቤሎ፡ አባ፡ እንጦኒ፡ ለአባ፡
ጳውሊ፡አ፡አቡየ፡እፈቅድ፡ታይድዓኒ፡ከመ፡
ዝንቱ፡ አስኬማ'፡ይበዝኀኑ፡ዲበ፡ምድር፡
አው፡ አልቦ። ወብፁዕ፡ ጳውሊ፡ ነጸረ፡
ውስተ፡ ሰማይ፡ ወአክሞሰሰ፡ ወእምዝ፡
ኀዘነ፡ወገዐረ፡ወይቤሎ፡እንጦንዮስ፡ሶበ፡
ርኢኩከ፡እንዘ፡ ታክሞስስ፡ተፈሣሕኩ፡
ወሶበ፡ ኀዘንከ፡ ወገዐርከ፡ ኀዘንኩ።
አውሥአ፡ቅዱስ፡ጳውሊ፡ወይቤሎ፡እስመ፡
እሉ፡አድባራት፡ወገዳማት፡ይከውኑ፡ማኅደ
ሪሆሙ፡ለአርጋብ፡ንጹሐን፡እለ፡ኀረዮሙ፡
ወአስተጋብአሙ፡ እግዚአብሔር፡ እምኵ
ሎን፡አህጉር።

፳፫፤ ወካዕበ፡የኃልፍ፡ዝንቱ፡ስም፡ወይከውን፡
ስሞሙ፡ መነኰሳተ፡ እሙንቱሰ፡ ይት
ፌሥሑ፡ብዙኀ፡መዋዕለ፡ ወያፈልሶሙ፡
እግዚአብሔር፡እምቅድመ፡ዕለተ፡መዓቱ።

በኋላ፡እርስ፡በእርሳቸው፡የእግዚአብሔርን፡
ልዕልናውን፡ቸርነቱን፡ይነጋገሩ፡ጀመር፡
በመሽም፡ ጊዜ፡ ቍራ፡ መጥቶ፡ አንዲት፡
ሙሉ፡እንጀራ፡ጣለለት፡አባ፡ጳውሊም፡
አባ፡ እንጦኒን፡ አንተ፡ የእግዚአብሔር፡
አገልጋይ፡እንደሆንክ፡አሁን፡አወቅሁ፡
እስከ፡ዛሬ፡ሰማንያ፡ዓመት፡በዚህ፡በረሀ፡
ስኖር፡ እግዚአብሔር፡ሁልጊዜ፡ የሚል
ክልኝ፡ግማሽ፡እንጀራ፡ነበረ፡እነሆ፡አሁን፡
ምግብህን፡ላከልህ፡አለው።ከዚህም፡በኋላ፡
ተነሥተው፡ የማዕድ፡ ጸሎት፡ ጸለዩ፡
በልተውም፡እግዚአብሔርን፡አመሰገኑት፡
መላ፡ሌሊቱንም፡ሲጸልዩ፡አደሩ።

፳፩፤ ነግቶ፡ ፀሐይ፡ በወጣ፡ ጊዜም፡ እርስ፡
በርሳቸው፡ሰላምታ፡ተሰጣጡ፡አባ፡እንጦ
ኒም፡አባቴ፡ሆይ፡በዚህ፡ሁሉ፡ዘመን፡ሥጋ
ውንና፡ደሙን፡ከወዴት፡ትቀበላለህ፡አለው፡
የከበረ፡ ጳውሊም፡ እግዚአብሔር፡መልአ
ኩን፡ይልክልኛል፡በቀዳሚት፡ሰንበትና፡
በእሑድ፡ሰንበት፡በየሳምንቱ፡ከሥጋውና፡
ከደሙ፡ ያቀብለኛል፡ በዘመኑም፡ ሁሉ፡
እንዲህ፡ያደርግልኛል፡ብሎ፡መለሰለት።

፳፪፤ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡እንጦኒ፡አባ፡ጳውሊን፡
አባቴ፡ሆይ፡ይህ፡አስኬማ፡በምድር፡ላይ፡
ይበዛ፡እንደሆነ፡ወይም፡አለምብዛቱን፡
ትነግረኝ፡ዘንድ፡እሻለሁ፡አለው።የከበረ፡
ጳውሊም፡ወደ፡ሰማይ፡ተመለከተና፡ፈገግ፡
አለ። ከዚህም፡ በኋላ፡ አዘነ፡ ጩኸም፡
አለቀሰ፡አባ፡እንጦንዮስም፡ፈገግ፡ስትል፡
በአየውህ፡ጊዜ፡ደስ፡አለኝ፡በአዘንክም፡
ጊዜ፡አዘንኩ፡አለው። የከበረ፡ጳውሊም፡
እንዲህ፡ ብሎ፡ መለሰለት፡ እሊህ፡
ተራሮችና፡ በረሐዎች፡ እግዚአብሔር፡
ከሁሉ፡አገሮች፡መርጦ፡ለሚሰበስባቸው፡
ንጹሐን፡ርግቦች፡ማደሪያዎች፡ይሆናሉ።

፳፫፤ ዳግመኛም፡ ይህ፡ ስም፡ ያልፋል፡
ስማቸውም፡ መነኰሳት፡ ይባላሉ፡
እነርሱም፡ብዙ፡ዘመናት፡ደስ፡ይላቸዋል፡
እግዚአብሔርም፡ ከቁጣው፡ ቀን፡
አስቀድሞ፡ከዚያ፡ያፈልሳቸዋል።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፤ ወእምድኅሬሆሙ ፡ ይትነሥኡ ፡ ትውልድ ፡
ዘኢይሰምዑ ፡ ወኢይትኤዘዙ ፡ ለመምህራ
ኒሆሙ ፡ ወእለ ፡ ኢይትገሀሡ ፡ ለጸሎት ፡
በመዓልት ፡ ወበሌሊት ፡ በእንተ ፡ መድ
ኃኒተ፡ነፍሶሙ።

፳፭፤ አሜሃ ፡ ይትመዐዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይት
ነሥኡ ፡ ሕዝብ ፡ ዐላውያን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡
ልብ ፡ ወሕግ ፡ ወያመዘብርዎሙ፡ ለገዳማት ፡
ወአድባራት፡ ወይከውኑ ፡ በድወ ፡ ብዙኀ ፡
መዋዕለ፡ ተዝካሮሙሰ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኢየኀ
ልቅ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ይወዲ ፡ ሣህለ ፡
ውስተ ፡ አልባቢሆሙ ፡ ለካልአን ፡ ሰብእ ፡
ወእሉ፡ የሐውሩ ፡ አድባራተ ፡ ወገዳማተ ፡
ወየኀድሩ ፡ ውስቴቶን ፡ ምእረ ፡ ዳግመ፡
ሰይጣንሰ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ አድባራት ፡
ወይሬሲ ፡ ጸብአ፡ ወእሙንቱ ፡ የኀድጉ ፡
አስኬማ ፡ ምንኵስና ፡ ወይወርዱ፡ ውስተ ፡
ዓለም፡ እስመ ፡ ኢነሥኡ ፡ ጥብዓተ፡ ፍቅረ፡
እግዚአብሔር ፡ ወኢተዓገሡ ፡ ባቲ ፡ እስመ ፡
ኢለበው፡ ጽሑፈ፡ ዘይብል፡ ወበትዕግሥ
ትክሙ ፡ ታጠርይዋ ፡ ለነፍስክሙ።

፳፮፤ ወይቤ ፡ እንጦንዮስ ፡ ቡርክት ፡ ይእቲ ፡ ሰዓት ፡
እንተ ፡ ባቲ ፡ ደለወኒ ፡ ከመ፡ እርአይ፡ ገጸከ ፡ አ፡
አቡየ፡ ብፁዕ ፡ ጳውሊ።

፳፯፤ ወይቤሎ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ጳውሊ ፡ ይእዜኒ ፡ ሑር፡
ኀበ ፡ ማኅደርከ ፡ ወአምጽእ ፡ ምስሌከ ፡ ልብሰ፡
ዘወሀቦ ፡ ቈስጠንጢኖስ፡ ለአባ ፡ አትናቴዎስ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአልበሰከ ፡ ለከ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ፡
ትግንዝ፡ ባቲ ፡ ሥጋየ ፡ ወእንጦንዮስ ፡
አንከረ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ አእምሮቱ ፡
ኅቡአተ፡ ወአምነ ፡ ኵሎ፡ ትንቢታቲሁ፡
ዘተነበየ፡ ሎቱ ። ወይቤሎ ፡ ካዕበ ፡ አፍጥን ፡
ወኢትቁም ፡ እስመ፡ ጊዜ ፡ ጸአትየ፡ ቀርበ፡
ዘሥሩዕ ፡ ላዕለ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወሰሚዖ ፡ አባ፡
እንጦኒ ፡ ኀዘነ ፡ ወበከየ፡ ወወጽአ ፡
እምኀቤሁ፡ ወአንሶሰወ ፡ ፪ተ ፡ መዋዕለ ፡
እስከ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ በዓቱ፡ ወነሥአ፡ ለይእቲ፡
ልብስ ፡ ወተመይጠ ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ፡ ውስተ፡
ፍኖት ፡ ርእዮ ፡ ለአባ ፡ ቡላ ፡ ወለማኅበረ ፡
መላእክት ፡ እንዘ ፡ ይሴብሑ ፡ ውስተ ፡ አየር፡
ወይብሉ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ወካዕበ ፡ ይብሉ ፡ ሰላም ፡ ለከ ፡ አ ፡ ኅሩዩ ፡ ለእግ

፳፬፤ ከእነርሱም፡ በኋላ ፡ ሰምተው ፡ ለመምህሮ
ቻቸው፡ የማይታዘዙ ፡ ትውልድ ፡ ይነሣሉ ፡
ስለ ፡ ነፍሳቸውም ፡ ድኅነት ፡ በቀንና ፡
በሌሊት ፡ የማይተጉና ፡ የማይጸልዩ ፡ ናቸው።

፳፭፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቆጥቶ ፡
ይፈርዳል ፡ የማያስተውሉ ፡ ሕግ፡ የሌላቸው፡
አረማውያንም ፡ ተነሥተው ፡ ገዳማቱንና ፡
አድባራቱን ፡ ያጠፉሉ፡ ብዙ፡ ዘመናትም ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሆናሉ ፡ የቅዱሳን ፡ መታሰቢ
ያቸው ፡ አይጠፋም፡ እግዚአብሔርም ፡
በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ልቡና፡ ይቅርታውን ፡ ያሳ
ድርባቸዋል ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ገዳማቱና ፡
ወደ ፡ አድባራቱ ፡ በመሔድ ፡ በውስጣቸው ፡
ዳግመኛ ፡ ይኖራሉ ፡ ሰይጣንም ፡ ወደ ፡
ገዳማት ፡ ሔዶ ፡ በመካከላቸው ፡ ጸብን ፡
ይዘራል ፡ እነርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ፍቅር፡ ገንዘብ ፡ በማድረግ፡ ጨክነው ፡ አልታ
ገሡባትምና ፡ ምንኵስናቸውን ፡ አስኬማታ
ቸውን፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ይወርዳሉ ፡ በት
ዕግሥታችሁ ፡ ነፍሳችሁን፡ ገንዘብ ፡ ታድርጓ
ታላችሁ ፡ የሚለውን ፡ ጽሑፍ ፡ አላስተዋ
ሉምና።

፳፮፤ እንጦንዮስም ፡ የከበርክ ፡ አባቴ ፡ ጳውሊ ፡
ሆይ፡ ፊትህን ፡ አይ፡ ዘንድ ፡ የታደልኩባት፡
ሰዓት ፡ የተባረከች ፡ ናት ፡ አለ።

፳፯፤ የከበረ ፡ አባ ፡ ጳውሊም ፡ አሁን ፡ ወደ፡
ማደሪያህ ፡ ሒድ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ለሊቀ ፡
ጳጳሳት ፡ አትናቴዎስ ፡ የሰጠውን ፡ ልብስ ፡
እርሱም፡ አንተን ፡ ያለበሳትን ፡ ያቺን ፡
ከአንተ ፡ ጋር ፡ ይዘሃት ፡ና ፡ ሥጋዬን ፡ በርሷ፡
ትገንዝ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ የተሠወ
ረውን ፡ በማወቁ፡ እጅግ ፡ አደነቀ ፡ የተነበየለ
ትንም ፡ ትንቢት ፡ ሁሉ ፡ አመነ ። ዳግመኛም፡
እንዲህ ፡ አለው ፡ በሰው ፡ ሁሉ፡ ላይ ፡ እንደ
ተሠራ ፡ ከዓለም ፡ የምወጣበት፡ ጊዜዬ ፡
ቀርቧልና፡ ፈጥነህ፡ ሒድና፡ ተመለስ፡ እርሱም፡
ከአባ ፡ ጳውሊ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ፡ በዓቱ ፡
እስኪደርስ ፡ የሁለት ፡ ቀን ፡ ጎዳና ፡ ተጓዘ ፡
ያቺንም ፡ ልብስ ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ ፡ በመን
ገድም፡ እየተጓዘ፡ ሳለ፡ በአየር ፡ ውስጥ ፡ አባ፡
ቡላን፡ የመላእክትንም ፡ ማኅበር ፡ አየ፡ ለእግ
ዚአብሔር፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ይሉ ፡ ነበር ።
ሁለተኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ወብፁዕ ፡ አንተ ፡ ጳውሊ ፡ ብእሴ፡ እግዚአብሔር ፡ እንከሰ ፡ ተፈሣሕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ እስመ ፡ ኀደገ ፡ ጽልመተ ፡ ዓለም ፡ ወነሣእከ ፡ ሀገረ ፡ ብርሃን ፡ ወይወ ስዱከ ፡ ውስተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘለዓለም ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ኮንከ ፡ ብፁዐ ፡ በትውልድከ ፡ አንተ፡ ጳውሊ ፡ ገዳማዊ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወእንዘ ፡ ከመዝ ፡ ይብሉ ፡ ተኀብኡ።

፳፰፡ ወይቤ ፡ ብፁዕ ፡ እንጦኒ ፡ ዛቲ ፡ ነፍሱ ፡ ለአቡየ ፡ ጳውሊ ፡ ዘያዐርግዋ ፡ ሰማያተ ፡ ወበዊአ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ፡ ረከቦ ፡ ሰጉደ ፡ ለአባ ፡ ጳውሊ ፡ ወእደዊሁ ፡ ስፉሐት ፡ አምሳለ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወነሥአ፡ አባ ፡ እንጦኒ ፡ ወከደኖ ፡ ወበከየ ፡ ላዕሌሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተዘከረኒ ፡ ኦ ፡ አቡየ ፡ በውስተ ፡ ማኅደርከ ፡ ሰማያዊ።

፳፱፡ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ወገነዘ ፡ ሥጋሁ ፡ በይእቲ፡ ልብስ ፡ ወፈጸመ ፡ ላዕሌሁ ፡ ቀኖና፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእምዝ ፡ ይቤ ፡ ምንተ፡ እገብር ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ቆክርየ፡ ምስሌሁ ፡ ወሶቤሃ ፡ መጽኡ ፡ አ ናብስት ፡ ወተአምኅዎ ፡ ወአድነኑ ፡ ወለሐሱ ፡ እገሪሁ ፡ ከመ፡ ዘየአምርዎ ፡ ቀዳሚ ፡ ወአመርዎ ፡ ከመ ፡ ዘይቤልዎ ፡ በአይ ፡ መካን ፡ ንከሪ ፡ ሎቱ ፡ መቃብሮ ፡ ወአእመረ፡ አባ ፡ እን ጦንዮስ፡ ትእምርቶሙ፡ ወሰፈረ ፡ ሎሙ፡ በመጠነ ፡ ቆሙ ፡ ወከረዩ፡ ፩ዱ ፡ በትርአስ ፡ ወ፩ዱ ፡ በትርጋፅ ። ወሶበ፡ አብጽሑ ፡ አመሮሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አከለክሙ ፡ ወወጽኡ ፡ እሉ ፡ አናብስት ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ፡ ውእቱኒ ፡ ባረከ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወሐሩ፡ መካ ኖሙ ፡ ወቅዱስ ፡ እንጦኒ ፡ ወደዮ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መቃብር ፡ ወኀተሞ ፡ ወነሥአ ፡ ዐጽፎ፡ ዘጸጕረ ፡ በቀልት ፡ በከመ፡ ወልድ ፡ ዘይወርስ ፡ ንዋየ ፡ አቡሁ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወቦአ፡ ኀበ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ ወነገሮ፡ ኵሎ፡ ዘኮነ ፡ እምነ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ጳውሊ ፡ ወመጠዎ ፡ ይእተ ፡ ልብሰ ፡ ዘጸጕረ ፡ በቀልት።

ክርስቶስ ፡ የመረጠህ ፡ ሰላምታ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይገባሃል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ጳውሊ፡ የተመሰገንክ ፡ ነህ ፡ እንግ ዲህስ ፡ በሰማያዊ ፡ መንግሥት ፡ ከመላእክት ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ የጨለማውን ፡ ዓለም ፡ ትተህ ፡ የብርሃን ፡ ሀገርን ፡ አግኝተሃልና ፡ ወደ፡ ዘላለማዊ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ይወስዱ ሃልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ የሆንክ ፡ አንተ ፡ ገዳማዊ ፡ ጳውሎስ ፡ በትውልድህ ፡ የከ በርክና ፡ የተመሰገንክ ፡ ነህ ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ተሠወሩ።

፳፰፡ የከበረ ፡ እንጦኒም ፡ ይህች ፡ ወደ፡ ሰማይ ፡ የሚ ያሳርጓት ፡ የአባቴ ፡ የጳውሊ ፡ ነፍስ ፡ ናት ፡ አለ፡ ወደ፡ በዓቱም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሰገደ፡ ሁኖ ፡ እጆቹም ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ ተዘር ግተው ፡ አገኘው፡ አንሥቶም ፡ ሸፈነው ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ በሰማያዊ ፡ ማደሪያህ ፡ ሁነህ ፡ አስበኝ ፡ ብሎ ፡ በላዩ ፡ አለቀሰ።

፳፱፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ በዚያች፡ ልብስ፡ ሥጋውን ፡ ገነዘና ፡ በላዩ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲ ያንን ፡ የጸሎት ፡ ሥርዓት ፡ ፈጸመ ፡ አደረሰም ፡ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ከእርሱ፡ ጋር ፡ የተማከ ርኩት ፡ ነገር ፡ የለም፡ ምን ፡ ላድርግ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ አንበሶች ፡ መጡ ፡ እጅ ፡ ነሡትም ፡ ቀድሞ፡ እንደሚያው ቁትም፡ ዘንበል ፡ ብለው ፡ የእግሩን ፡ ትቢያ ፡ ላሱ ፡ መቃብሩን ፡ በየት ፡ ቦታ ፡ እንቆፍርለት ፡ እንደሚሉ ፡ አመለከቱት ፡ እርሱም ፡ ምልክ ታቸውን ፡ አውቆ፡ በቁመቱ ፡ ልክ ፡ ለክቶ ፡ ሰጣቸው ፡ አንዱ ፡ በራስጌ ፡ አንዱ ፡ በግርጌ፡ ሁነው ፡ ቆፈሩ ፡ በአደረሱም ፡ ጊዜ ፡ በቃችሁ ፡ ብሎ ፡ አመለከታቸው ፡ እሊህ ፡ አንበሶችም ፡ ወጥተው ፡ ሰገዱለት ። እርሱም ፡ ባረካቸውና፡ ወደ ፡ ቦታቸው ፡ ሔዱ ፡ የከበረ ፡ እንጦኒ ፡ ወደ፡ መቃብር ፡ አስገብቶ ፡ ዘጋው። ከሰኔል ፡ ቅጠልም ፡ የተሠራች ፡ ዐጽፉን ፡ ወሰደ፡ የአባቱን ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚወርስ ፡ ልጅ፡ ነውና ፡ ወደ፡ እስክንድርያም ፡ ሔደ። ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ አትናቴዎስም ፡ ገብቶ ፡ ከከበረ፡ አባ ፡ ጳውሊ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረውና ፡ ያቺን ፡ ከሰኔል ፡ የተሠራች ፡ ዐጽፍ፡ ሰጠው።

www.ethiopianorthodox.org

፴፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አትናቴዎስ ፡ ዜናሁ ፡ ለብፁዕ ፡ ጳውሊ ፡ ተፈሥሐ ፡ ዐቢየ፡ ፍሥሓ፡ወነሥአ፡ለይእቲ፡ልብስ፡ወረሰያ፡ በኀቤሁ፡ወይትዓጸፋ፡ለለዓመት፡፫ተ፡ጊዜ፡ በበዓለ፡ልደት፡ስቡሕ፡ወበበዓለ፡ጥምቀት፡ ወበበዓለ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ክርስቶስ፡፡

፴፩፤ ወፈቀደ ፡ እግዚእነ ፡ ይክሥት ፡ ክብረ ፡ ልብሱ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሊ፡ ወይእተ ፡ አሚረ፡ ሞተ ፡ ፩ወልድ፡ወሬዛ፡ወአባ፡አትናቴዎስ፡ አንበራ ፡ ለይእቲ ፡ ልብስ ፡ ላዕለ ፡ ምውት ፡ ወተንሥአ ፡ በጊዜሃ ፡ ወዘንተ ፡ ዘርእየ ፡ አባ፡ ኢስድሮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ ወተሰምዐት ፡ ዛቲ ፡ ተአምር ፡ ውስተ ፡ ኵሎን ፡ በሐውርት።

፴፪፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለብፁዕ ፡ ጳውሊ ። ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፴፤ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አትናቴዎስም ፡ የከበረ ፡ ጳውሊን ፡ ዜና ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ፡ አለው፡ ያቺንም ፡ ዐጽፍ፡ ተቀብሎ ፡ በእርሱ፡ ዘንድ ፡ አኖራት ፡ በየዓመቱም ፡ በከበረ ፡ በልደት ፡ በዓል ፡ በጥምቀትም ፡ በዓል ፡በመድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ፡ ትንሣኤ ፡ በዓልም ፡ ሦስት፡ጊዜ፡ይለብሳት፡ነበር፡፡

፴፩፤ ጌታችንም ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሊን ፡ የልብሱን፡ ክብር ፡ ሊገልጥ ፡ ወደደ፡ በዚያችም ፡ ወቅት፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ሞተ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስም ፡ ያቺን ፡ ልብስ ፡ በሞተው ፡ ላይ ፡ አኖራት፡ወዲያውኑ፡ተነሣ፡ይህንንም፡ያየ፡ ኤጲስቆጶስ፡አባ፡ኤስድሮስ፡ምስክር፡ሆነ፡ ይችም፡ተአምር፡በአገሮች፡ሁሉ፡ተሰማች።

፴፪፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በከበረ፡ ጳውሊ ። ጸሎት ፡ ይማረን፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጳውሊ ፡ በውሳጤ ፡ ገዳም ፡ ዘተጸምደ ። እንዘ፡ ኢይሬኢ ፡ እምሰብእ፡ መነሂ ፡ አሐደ። ፃመወ። ብዙኀ ፡ ወተጋደለ፡ ፈድፋደ። ድኀረ ፡ ሞቱሂ ፡ ከመ፡ በሕይወቱ ፡ ለመደ።ለእግዚአብሔር፡ ተረክበ ፡ ከዊኖ ፡ ስጉደ።

፴፫፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ገብረ ፡ ተአምረ፡ ሐዋርያ ፡ ቅዱስ፡ቶማስ፡ ወሶበ፡ወጽአ፡ከመ፡ይስብክ፡ ኀበ፡ አዘዞ ፡እግዚእነ፡ ወተግኀሠ፡ ንስቲተ ፡ እምፍኖት፡ወርእየ፡ድንቀተ፡ወሬዛ፡ምውተ፡ ዘልሑይ፡ጥቀ፡አርአያሁ፡ወይቤ፡ሐዋርያ፡ እግዚኦ፡በእንተ፡ዝንቱ፡አምጻእከኒኑ፡ዝየ፡ ከመ ፡ እርአይ ፡ ዘንተ ፡ መንሱተ ፡ ወባሕቱ ፡ ፈቃድከ፡ይኩን።

፴፬፤ ወእምዝ ፡ ጸለየ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ምውት ፡ ሶቤሃ ፡ ወጽአ፡ ከይሲ፡ ዐቢይ ፡ እምውስተ ፡ አዕባን ፡ እንዘ ፡ ይዘብጥ ፡ ምድረ ፡ በዘነቡ፡ ወጸርሐ ፡ በቃል ፡ ዐቢይ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ምንት ፡ ብየ ፡ ምስሌከ፡ ሐዋርያሁ፡ ለክርስቶስ፡ እስመ፡መጻእከ፡ትዝልፍ፡ምግባርየ። ወይቤሎ፡ሐዋርያ፡እወ፡ተናገር፡ግብረከ።

፴፭፤ ወይቤ ፡ ከይሲ ፡ ብእሲት ፡ ሠናይተ ፡ ላሕይ፡ ሀለወት ፡ በአንጻረ ፡ ውእቱ ፡ ዐፀድ፡ ዘአነ ፡ አፈቅራ ፡ ወዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ እንዘ ፡ ይስዕማ፡

፴፫፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ቶማስ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ፡ ጌታችን ፡ ወደ፡ አዘዘው ፡ ሊአስተምር ፡ በወጣ፡ ጊዜ ፡ ከመንገድ ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ አለ፡ ድንገትም፡ የሞተ ፡ ጐልማሳ ፡ አየ ፡ መልኩ ፡ እጅግ ፡ የሚያምር ፡ ነበር ፡ ሐዋርያውም ፡ አቤቱ ፡ ይህን ፡ ጥፋት ፡ አይ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ አመጣህኝን፡ነገር፡ግን፡ፈቃድህ፡ይሁንአለ።

፴፬፤ከዚህም፡በኋላ፡ስለሞተው፡ሰው፡ጸለየ፡ያን፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ከይሲ ፡ ከድንጊያዎች ፡ ውስጥ፡ ወጥቶ ፡ በጅራቱ ፡ ምድሩን ፡ እየደበደበ ፡ መጣ፤ክርስቶስ፡ ሐዋርያ፡ሆይ፡እኔ፡ካንተ፡ ጋር ፡ ምን ፡ አለኝ ፡ ሥራዬን ፡ ልትዘልፍ ፡ መጣህን ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ፡ ጮኸ፡ ሐዋርያውም ፡ አዎን ፡ ሥራህን ፡ ተናገር ፡ አለው።

፴፭፤ከሲውም፡እንዲህ፡አለ፡በዚህ፡ቦታ፡አንጻር፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ሴት ፡ ነበረች፡ እኔ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ርኢክዎ፡ ወበዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ተደመረ ፡ ምስሌሃ፡ወበእንተዝ፡ነሰክዎ፡ወቀተልክዎ፡ በሕምዝየ፡ ወይቤሎ ፡ ሐዋርያ፡ እኤዝዘከ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእየ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣእ፡ ሕምዘከ፡ እምኔሁ ። ወሖረ፡ አሜሃ፡ ወነሥአ፡ ሕምዞ ፡ እምነ፡ ውእቱ ፡ ምውት ፡ አሜሃ ፡ ተነፍሐ፡ ወሐበጠ ፡ ኰለንታሁ ፡ ወነቅዐ ፡ ወሞተ ፡ ወመዋቲ ፡ ተንሥአ፡ ሕያዎ። ወበእንተ ፡ ዛቲ ፡ ትእምርት ፡ አምኑ ፡ ብዙኃን ፡ በእግዚእነ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ውእቱኒ፡ መሀሮሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወአጥ መቆሙ፡ጥምቀተ፡ክርስትና፡

፴፮፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለሐዋርያ ፡ ቶማስ ፡ አቡነ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

የምወዳት፡ናት፡ይህም፡ጕልማሳ፡ሲስማት፡ አየሁት ፡ በሰንበት ፡ ቀንም ፡ ከርሷ ፡ ጋር ፡ አደረ፡ ስለዚህም ፡ ነክሼ በመርዝ ፡ ገደልኩት፡ ሐዋርያውም ፡ መርዝህን ፡ ከሱ ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡ በጌታዬ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አዝዝሃለሁ ፡ አለው ።

ሔዶም ፡ ከዚያ ፡ ከሞተው ፡ መርዙን ፡ መጠጠና ፡ ወሰደ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተነፍቶ ፡ አበጠ፡ ተሠንጥቆም፡ ሞተ ፡ የሞተውም ፡ ሰው ፡ ድኖ ፡ ተነሣ። ስለዚች ፡ ምልክትም ፡ ብዙዎች ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ አመኑ፡ እርሱም ፡ ሃይማኖትን ፡ አስተምሮ ፡ የክርስትና፡ጥምቀትን፡አጠመቃቸው።

፴፮፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በሐዋርያው ፡ በአባታችን ፡ ቶማስ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለቶማስ ፡ ዘአርአየ ፡ እዘዞ ። ኀበ ፡ ሖረ ፡ ይስብክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዞ ። እስመ ፡ ለመዋቲ ፡ አብጽሖ፡እስከ፡አንከሮ፡ወአስያዘዞ።በስመ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለከይሲ፡ሶበ፡አውገዞ።እምላዕለ፡ብእሲ፡ ምውት፡ከመ፡ይንሣእ፡ሕምዞ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፫ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ መስተጋድል ፡ መነ ኰስ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ መነነ ፡ እምንእሱ ፡ ዘንተ ፡ ዓለመ ፡ ወመንኰሰ ፡ ወኮነ ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ በዓት ፡ ወይትጋደል ፡ በጾም ፡ ወበ ጸሎት ፡ ወበሰጊድ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ወትረ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዓት ፡ ወኢይወጽእ ፡ እምበዓቱ ፡ ወኢይበውእ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወኢይሬኢ ፡ ገጸ ፡ ብእሲት ፡ ወነበረ ፡ ከመዝ ፡ መጠነ ፡ ፲ወ፭ዓመት።

፫፤ ወእምዝ ፡ ተመክነዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰብእ ፡ እኩያን ፡ እምእለ ፡ ይተልውዎ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ወረሰይዋ፡ ለአሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘማ ፡ ትባእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይእቲ ፡ በዊአ ፡ አኀዘት ፡ ትትዋነይ ፡ ቅድሜሁ ፡ እንዘ ፡ ታዜክር ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወገሠጻ ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ ወአዘከራ ፡ እሳተ ፡ ገሀነም ፡ ዘለዓለም ። ወደንገፀት ፡ ሶቤሃ ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሦስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ተጋዳይ ፡ የሆነ ፡ መነኰስ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ አረፈ።

፪፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ትቶ ፡ መነኰሰና ፡ በአንዲት ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ ሆነ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥም ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይጾማል ፡ ይጸልያል ፡ በመስገድም ፡ ይተጋ ፡ ነበር ፡ ከበዓቱም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ አይገባም ፡ የሴት ፡ ፊትም ፡ አያይም ፡ እንዲህም ፡ ሁኖ ፡ ዐሥራ፡አምስት፡ዓመት፡ኖረ።

፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዲያብሎስን ፡ ከሚከተሉት ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ምክንያት ፡ ፈጥ ረው ፡ አንዲቷን ፡ አመንዝራ ፡ ሴት ፡ ወደርሱ ፡ እንድትገባ ፡ አደረጓት ፡ በገባችም ፡ ጊዜ ፡ የኃ ጢአትን ፡ ሥራ ፡ እያስታወሰች ፡ በፊቱ ፡ መጫ ወት ፡ ጀመረች ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብም ፡ ገሠጻት ፡ በገሀነም ፡ እሳትም ፡ ዘላለም ፡ ሲቃጠሉ ፡ መኖ

www.ethiopianorthodox.org

ወነስሐት ፡ ወኮነት ፡ ዘታሠምሮ ፡ ለእግዚአ
ብሔር።
፬፤ ወኢኀደጎ ፡ ሰይጣን ፡ ወቦአ ፡ ላዕለ ፡ ወለተ ፡
አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ እምልሒቃነ ፡ ሀገር ፡ ወኮነ ፡
ያወድቃ ፡ ወያንገረግራ ፡ ወአሕለዮ ፡ ለአቡሃ ፡
ከመ ፡ ይሰዳ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ወከመ ፡
ውእቱ ፡ ይክል ፡ ፈውሶታ ፡ ወነሥአ ፡ አቡሃ ፡
ወአብጽሓ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ወሰአሎ ፡
ከመ፡ ይጸሊ ፡ ላዕሌሃ ፡ ውእቱኒ ፡ ሶበ ፡ ጸለየ ፡
ላዕሌሃ፡ ተፈወሰት ፡ አቡሃሰ ፡ ኀደጋ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡
ያዕቆብ፡ ምስለ ፡ እኁሃ ፡ ሕፃን ፡ ንዑስ ፡ ከመ ፡
ኢይትመየጥ ፡ ላዕሌሃ ፡ ውእቱ ፡ ሰይጣን።

፭፤ ወእምዝ ፡ አኀዘ ፡ ሰይጣን ፡ ይጽብአ ፡ ባቲ ፡
በሌሊት ፡ ወበመዓልት ፡ እስከ ፡ አውደቆ ፡
በኃጢአት ፡ ምስሌሃ ፡ ወሶበ ፡ ወድቀ ፡ በኃ
ጢአት ፡ ፈርሀ ፡ ከመ ፡ ኢይትከሠት ፡ ኃጢ
አቱ ፡ ወኢይቅትልዎ ፡ በእንቲአሃ ፡ ወበእ
ንተዝ ፡ ቀተላ ፡ ምስለ ፡ እኁሃ ፡ ወወደየ ፡ ዓዲ ፡
ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ቀቢጸ ፡ ተስፉ ፡
ወወጽአ፡ አምበዓቱ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ውስተ ፡
ዓለም።
፮፤ ወእግዚአብሔር፥ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ዘኢ
ይፈቅድ ፡ ሞቶ ፡ ለኃጥእ ፡ ፈነወ ፡ ኀቤሁ ፡
ጻድቀ፡ መነኰሰ ፡ ወተራከቦ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡
እንዘ ፡ የሐውር ፡ ወተአምኖ ፡ ወተሰአሎ ፡
ወይቤሎ ፡ ምንተ ፡ ኮንከ ፡ ኦ ፡ እኁየ ፡ እስመ ፡
እሬእየከ ፡ ኀዙነ ፡ ወትኩዘ ፡ ወምንትኑ ፡
ዘበጽሐከ ፡ ውእቱኒ ፡ አይድዖ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡
ዘከመ ፡ ወድቀ ፡ በኃጢአት ፡ ምስለ፡ ይእቲ ፡
ወለት ፡ ወዘከመ ፡ ቀተላ ፡ ምስለ ፡ እኁሃ ፡
ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ መነኰስ ፡ ጻድቅ ፡ ኢት
ፍራህ ፡ ወኢትምትር ፡ ተስፉ ፡ እስመ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ወብዙኀ፡
ምሕረት ። ወእምዝ ፡ አንበረ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጾመ ፡
ወጸሎተ ፡ ወሰጊደ።

፯፤ ውእቱኒ ፡ ተመይጠ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ ግብ ፡
ወሞቅሐ ፡ ርእሶ ፡ ውስቴቱ ፡ ወተዓገሠ ፡ ላዕለ ፡
ፃማ ፡ ዐቢይ ፡ ወምንዳቤ ፡ ብዙኅ ፡ ወይተግህ ፡
ወትረ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወበሰጊድ ፡ ብዙኅ ፡
ወኮነ ፡ ዘይሴሰይ ፡ ሣዕረ ፡ ወበቍላተ ፡ ምድር ፡
ወየኀዝን ፡ ብዙኀ ፡ ወይብል ፡ ይትቄከፈኒኑ ፡

ርን ፡ አሳሰባት ፡ ደንግጣም ፡ ንስሐ ፡ ገባች ፡ እግ
ዚአብሔርንም፡ የምታገለግል ፡ ሆነች።
፬፤ ሰይጣንም ፡ መፈታተኑን ፡ አልተወውም ፡
ከሀገር ፡ ታላላቆችም ፡ በአንዱ ፡ ሰው ፡ በሴት ፡
ልጁ ፡ ላይ ፡ አደረ ፡ የሚጥላትና ፡ የሚያንከባ
ልላት ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ያዕቆብም ፡ ይወስዳት ፡
ዘንድ ፡ እርሱም ፡ ሊያድናት ፡ እንደሚችል ፡
አሳሰበው ፡ አባቷም ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ አደረ
ሳትና ፡ በላይዋ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፡
እርሱም ፡ በላይዋ ፡ ሲጸልይ ፡ ዳነች ፡ አባቷም ፡
ያ ፡ ሰይጣን ፡ እንዳይመለስባት ፡ ብሎ ፡
ከታናሽ፡ ብላቴና ፡ ወንድሟ ፡ ጋር ፡ ከአባ ፡
ያዕቆብ ፡ ዘንድ ፡ ተዋት።
፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ በኃጢአት ፡
እስከ ፡ ጣለው ፡ ድረስ ፡ እርሷን ፡ በማሳሰብ ፡
በሌሊትም ፡ በቀንም ፡ በዝሙት ፡ ጦር ፡
ሰይጣን፡ ተዋጋው ፡ በኃጢአትም ፡ በወደቀ ፡
ጊዜ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ እንዳይገድሉት ፡ ፈርቶ ፡
ኃጢአቱ ፡ እንዳይገለጥ ፡ ከወንድሟ ፡ ጋር ፡
ገደላት ፡ ሰይጣንም ፡ ደግሞ ፡ ቀቢጸ ፡
ተስፋ ፡ በልቡ ፡ አሳደረበት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡
ሊሔድ ፡ ከበዓቱ ፡ ወጣ።
፮፤ የኃጢአተኛውን ፡ ሞት ፡ የማይወድ ፡ መሐሪ ፡
ይቅር ፡ ባይ ፡ እግዚአብሔርም፥ ጻድቅ ፡ የሆነ ፡
መነኰስ ፡ ወደርሱ ፡ ላከ ፡ በጐዳናም ፡ ሲጓዝ ፡
ተገናኘውና ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠው ፡ እንዲህም ፡
ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡
ሁነሃል፡ አዝነህ ፡ ተክዘህ ፡ አይሃለሁና ፡ የደረሰ
ብህስ ፡ ምንድን ፡ ነው። እርሱም ፡ የሆነውን ፡
ሁሉ ፡ ከዚያች ፡ ብላቴና ፡ ጋር ፡ በኃጢአት ፡
እንደ ፡ ወደቀና ፡ ከወንድሟ ፡ ጋር ፡ እንደገ
ደላት፡ ነገረው ። ያ ፡ ጻድቅ ፡ መነኰስም ፡
አትፍራ ፡ ተስፋም ፡ አትቁረጥ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ መሐሪ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ምሕረቱ ፡ የበዛ ፡
ነውና ፡ አለው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጾም ፡
የጸሎት ፡ የስግደት ፡ ቀኖናን ፡ እንዲይዝ ፡
አዘዘው።
፯፤ እርሱም ፡ ተመልሶ ፡ ከአንድ ፡ ፍርኩታ ፡ ውስጥ ፡
ገባ ፡ በውስጡም ፡ ራሱን ፡ እሥረኛ ፡ አደረገ ፡
በታላቅ ፡ ድካምና ፡ በብዙ ፡ ችግርም ፡ ላይ ፡
ታገሠ ፡ በመጾም ፡ በመጸለይ ፡ አብዝቶ ፡ በመስ
ገድም ፡ ሁልጊዜ ፡ ይተጋል ፡ ከምድር ፡ የሚበ
ቅል ፡ ሣርንም ፡ የሚመገብ ፡ ሆነ ፡ አብዝቶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ፡ ወየኃድግ ፡ ሊተ ፡ አበሳየ ፡ ብዙኀ፡ወነበረ፡ከመዝ፡እንዘ፡ይኔስሕ፡ወይት ጋደል፡፴ ዓመተ።

፰፤ ወፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ ከመ፡ ተወክፈ ፡ ሎቱ ፡ ንስሐሁ ፡ አምጽአ ፡ ረኃበ፡ውስተ፡ሀገር፡ወይቤሎ፡ለኤጲስቆጶስ፡ ዘይእቲ ፡ ሀገር ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ረኃብ ፡ ኢየኀልፍ ፡ ዘእንበለ ፡ በጸሎቱ ፡ ለያዕቆብ ፡ መነኰስ፡ዘውስተ፡ግብ።

፱፤ ወሶቤሃ፡ተንሥአ፡ኤጲስቆጶስ፡ወነሥአሙ፡ ምስሌሁ፡ለካህናት፡ወለሰብአ፡ይእቲ፡ሀገር፡ ወበጽሑ፡ኀበ፡ቅዱስ፡ያዕቆብ፡ወሰአልዎ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ ይሣሃሎሙ ፡እግዚአብሔር፡ ወያውርድ፡ሎሙ፡ ዝናመ፡ወይቤሎሙ፡አባ፡ያዕቆብ፡እስመ፡ አነ፡ብእሲ፡ኃጥእ፡ወአባሲ፡ዘአማዕዕክዎ፡ ለእግዚአብሔር።በኃጢአትየ፡ወነገሮ፡ኤጲስ ቆጶስ፡ዘይቤሎ፡እግዚአብሔር፡በእንቲአሁ።

፲፤ ወእምዝ ፡ ወጽአ ፡ ማዕከለ ፡ ሕዝብ ፡ ወጸለየ ፡ እንዘ፡ ይበኪ ፡ ወይቤ ፡ እፎ ፡ እከሥት ፡ አፉየ ፡ ርኩስተ ፡ ቅድመ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ፡ እግዚኦ ፡ ወእፎ ፡ አሌዕል ፡ ገጽየ ፡ ዘጸልመ ፡ በብዝኀ ፡ ኃጢአት ፡ ወባሕቱ ፡ ተሣሃል ፡ ሕዝበከ ፡ በከመ ፡ ዕበየ ፡ ሣህልከ ፡ ወበከመ ፡ ብዝኀ ፡ ምሕረትከ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ወሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ ዝናም ፡ ብዙኀ ፡ ውእቱኒ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ተወክፈ፡ጸሎቶ፡ወንስሓሁ፡ወሰረየ፡ ሎቱ፡ኃጢአቶ።

፲፩፤ ወእምድኅረዝ፡ኢያንተገ፡ጸሎቶ፡ወትጋሆ፡ ወስግደቶ ፡ ዘከመ ፡ ይገብር ፡ ቀዳሚ ፡ ወይጌሥጽ፡ለነፍሱ፡ወይብላ፡ተጋደሊ፡ወተዐቀቢ፡ ከመ ፡ ኢትደቂ ፡ ውስተ ፡ ኃጢአት ፡ ዳግመ ፡ ወእምዝ ፡ ፈጺሞ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወአዕረፈ፡በሰላም።

፲፪፤ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እያዘነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀበለኝ ፡ ይሆን ፡ ብዙ ፡ በደሌንስ ፡ ይተውልኝ ፡ ይሆን ፡ ይላል ፡ እንዲህም ፡ በመጸጸት ፡ እየተጋደለ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት፡ኖረ።

፰፤ እግዚአብሔርም ፡ ንስሐውን ፡ እንደተቀበለለት ፡ ሊገልጥ ፡ ወዶ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ረኃብን፡ አመጣ ፡ ለዚያች ፡ አገር ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ በፍርኩታ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖር ፡ ከመነኰስ ፡ ያዕቆብ ፡ ጸሎት ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ረኃብ፡ አያልፍም ፡ አለው።

፱፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ካህናቱንና ፡ የዚያችን ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ ተነሣ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብም ፡ ደርሰው ፡ ስለርሳቸው ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ለመኑት ፡ እግዚአብሔር፡ይቅር፡እንዲላቸውና፡ዝናምንም፡እንዲአወርድላቸው ፡ አባ ፡ ያዕቆብም ፡ እኔ ፡እግዚአብሔርን ፡ በኃጢአቴ ፡ ያሳዘንሁት ፡ ኃጢአተኛና ፡ በደለኛ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ አላቸው ፡ ኤጲስቆጶሱም ፡ ስለርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ነገረው።

፲፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፡ እያለቀሰ፡ጸለየ፡እንዲህም፡አለ፡አቤቱ፡በጌትነትህ ፡ ክብር ፡ ፊት ፡ የረከሰች ፡ አፌን ፡ እንዴት፡ እገልጣለሁ ፡ በኃጢአት ፡ ብዛት ፡ የጠቆረ፡ፊቴንስ፡እንዴት፡ቀና፡አደርጋለሁ፡ ነገር፡ግን፡እንደ፡ይቅርታህ፡ገናናነት፡እንደ፡ ቸርነትህም ፡ ብዛት ፡ ሕዝብህን ፡ ይቅር ፡ በል ፡ አንተ ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነህና ፡ በዚያንም፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዝናም ፡ ወረደ ፡ እርሱም፡ ጸሎቱንና ፡ ንስሓውን፡ እግዚአብሔር ። እንደ ተቀበለው ፡ ኃጢአቱንም ፡ እንደ፡ ተወለት ፡ አወቀ።

፲፩፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚሠራው ፡ ተግቶ ፡ መጸለዩንና ፡ መስገዱን ፡ አላጐደለም ፡ ነፍሱንም ፡ ዳግመኛ ፡ በኃጢአት ፡ ውስጥ ፡ እንዳትወድቂ ፡ ተጠበቂ ፡ በማለት ፡ ይገሥጻት ፡ ነበር ፡ ከዚህም፡በኋላ፡ዕድሜውን፡አድርሶ፡እግዚአብሔርንም፡ አገልግሎ፡በሰላም፡አረፈ።

፲፪፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ ለያዕቆብ፡ በደዌ፡ ኃጢአት፡ ዘሐመ። ሶበ፡ አመከሮ፡ ሰይጣን፡ እንዘ፡ ይነብር፡ ገዳመ። እግዚአ ብሔር፡ ምክሮ፡ ውስተ፡ ሕሊናሁ፡ ዓቀመ። እምቀቢጸ፡ ተስፋ፡ ከመ፡ ይነስሕ፡ ዳግመ። እስከ፡ በጸሎቱ፡ አውረደ፡ እምሰማይ፡ ዝናመ።

፲፫፤ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ ርእሰ፡ ባሕታውያን፡ አባ፡ ዕብሎይ። ዘይመስል፡ ሕይወቱ፡ አምሳለ፡ መላእክት፡ ወእምትሩፋቲሁ፡ ዘሠረፀ፡ ፍሬ፡ ሃይማኖት።

፲፬፤ ወአመ፡ ገብአ፡ ቅዱስ፡ አትናቴዎስ፡ እምኀበ፡ ተሰደ፡ መጽአ፡ ኀበ፡ አባ፡ ባስልዮስ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ ዘቂሣርያ፡ ወቤቱ፡ ፪ሆሙ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዘአቡቂር፡ ወአኀዙ፡ ይትናገሩ፡ በበይናቲሆሙ፡ በእንተ፡ ቅዱሳን፡ እለ፡ ሀለዉ፡ ውስተ፡ ምኔታተ፡ ግብጽ፡ ይቤ፡ አብ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አትናቴዎስ፡ ሀሎ፡ አባ፡ ጳኵሚስ፡ ወአባ፡ ባስልዮስ፡ ይቤ፡ ሀለዉ፡ እንጦንዮስ፡ ወአባ፡ አሞኒ፡ ወእንዘ፡ ሀለዉ፡ በዘከመዝ፡ ነገር፡ ወይፈቅዱ፡ ይጠይቁ፡ ዘይልሕቅ፡ እምኔሆሙ፡ ወርእየ፡ ራእየ፡ አትናቴዎስ፡ አመ፡ ፳ ለየካቲት፡ ጊዜ፡ መንፈቀ፡ ሌሊት፡ ዕፀ፡ ዐባየ፡ ዘትበጽሕ፡ እስከ፡ ሰማይ፡ ወአዕጹቂሃኒ፡ እስከ፡ ባሕር፡ ወብዙኃን፡ ሰብእ፡ ያጸልሉ፡ ታሕተ፡ አዕጹቂሃ፡ ወታቦት፡ ዘምሥዋዕ፡ ማዕከሌሃ፡ ወእንዘ፡ ይዴመም፡ እምዝንቱ፡ ራዕይ፡ ናሁ፡ ወረደ፡ እምሰማይ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ሊቀ፡ መላእክት፡ ወይቤሎ፡ ለአባ፡ አትናቴዎስ፡ ተናገር፡ ዘንተ፡ ዘርኢከ፡ ምስለ፡ ባስልዮስ፡ ወአነ፡ እከሥት፡ ለክሙ።

፲፭፤ ወተርጐመ፡ ሎሙ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ዕፅ፡ ዘርኢከ፡ ደብር፡ ውእቱ፡ ዘይትሐነፅ፡ በደወለ፡ ግብጽ፡ ወአዕጹቂሃኒ፡ መነኰሳት፡ ወምሥዋዕኒ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ዘይሔውጽዎ፡ መላእክት፡ ወውእቱ፡ አባ፡ ዕብሎይ፡ አምሳሊሁ፡ ለጴጥሮስ፡ ሊቀ፡ ሐዋርያት፡ ዘይሥዕር፡ መናፍስተ።

፲፮፤ ወሰምዐ፡ ዜናሁ፡ ለአባ፡ ዕብሎይ፡ ፩ዱ፡ ሀቤ፡ ፻ት፡ ዘሀገረ፡ እስክንድርያ፡ አስተብቍዖ፡ ለሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አትናቴዎስ፡ ከመ፡ ይፈንዎ፡ ኀበ፡ አባ፡ ዕብሎይ፡ ከመ፡ ይንሣእ፡ በረከቶ፡ ውእቱኒ፡ ፈነዎ፡ ምስለ፡ ሰብዓቱ፡ መነኰሳት፡ ዘውእቶሙ፡ አባ፡ ኤስድሮስ፡ ወዮሐንስ፡ ወብሶይ፡ ወአሞኒ፡ ወፊቅጦር፡ ወአግሮኒኮስ፡

፲፫፤ በዚችም፡ ዕለት፡ የባሕታውያን፡ አለቃ፡ ኑሮው፡ የመላእክትን፡ ኑሮ፡ የሚመስል፡ ከትሩፋቱም፡ የሃየማኖት፡ ፍሬ፡ የተገኘ፡ የከበረ፡ አባት፡ ዕብሎይ፡ አረፈ።

፲፬፤ ቅዱስ፡ አትናቴዎስም፡ ከተሰደደበት፡ በተመለሰ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቂሣርያ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ወደ፡ አባ፡ ባስልዮስ፡ ዘንድ፡ መጥቶ፡ ሁለቱም፡ በአቡቂር፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ አደሩ፡ በግብጽ፡ ገዳማት፡ ስለሚኖሩ፡ ቅዱሳን፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ሊነጋገሩ፡ ጀመሩ፡ አባት፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አትናቴዎስ፡ አባ፡ ጳኵሚስ፡ አለ፡ ብሎ፡ ተናገረ፡ አባ፡ ባስልዮስም፡ አባ፡ እንጦንዮስና፡ አባ፡ አሞኒ፡ አሉ፡ አለ፡ በእንዲህ፡ ያለ፡ ነገርም፡ ከእርሳቸው፡ የሚልቀውን፡ ሊረዱ፡ ሽተው፡ ሳሉ፡ የካቲት፡ አምስት፡ ቀን፡ በመንፈቀ፡ ሌሊት፡ አባ፡ አትናቴዎስ፡ ራዕይን፡ አየ። እስከ፡ ሰማይ፡ የምትደርስ፡ ታላቅ፡ ዛፍ፡ ነበረች፡ ቅርንጫፎቿም፡ እስከ፡ ባሕር፡ ደርሰዋል፡ ብዙ፡ ሰዎችም፡ ከቅርንጫፎቿ፡ በታች፡ ተጠልለዋል፡ በመካከሏም፡ ታቦት፡ መሠዊያ፡ አለ፡ ከዚህም፡ ራእይ፡ የተነሣ፡ እየተደነቀ፡ ሳለ፡ እነሆ፡ የመላእክት፡ አለቃ፡ የከበረ፡ ሚካኤል፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ ይህን፡ ያየኸውን፡ ከባስልዮስ፡ ጋር፡ ተነጋገር፡ እኔም፡ እገልጥላችኋለሁ፡ አለው።

፲፭፤ እንዲህ፡ ብሎ፡ ተረጐመላቸው፡ ያየሃት፡ ዛፍ፡ በግብጽ፡ አውራጃዎች፡ ውስጥ፡ የሚሠራ፡ ገዳም፡ ነው፡ ቅርንጫፎቿም፡ መነኰሳት፡ ናቸው፡ መሠዊያውም፡ መላእክት፡ የሚጐበኙት፡ የእግዚአብሔር፡ ማደሪያ፡ ይህ፡ ርኵሳን፡ መናፍስትን የሚሽር፡ የሐዋርያት፡ አለቃ፡ የጴጥሮስ፡ አምሳል፡ የሆነ፡ አባ፡ ዕብሎይ፡ ነው።

፲፮፤ በእስክንድርያ፡ የሚኖር፡ አንድ፡ የመቶ፡ አለቃ፡ የአባ፡ ዕብሎይን፡ ዜና፡ ሰምቶ፡ በረከቱን፡ ይቀበል፡ ዘንድ፡ ወደ፡ አባ፡ ዕብሎይ፡ እንዲልከው፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አትናቴዎስን፡ ማለደው። እርሱም፡ ከሰባት፡ መነኰሳት፡ ጋር፡ ሰደደው፡ እነርሱም፡ አባ፡ ኤስድሮስ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ አባ፡ ብሶይ፡ አባ፡ አሞኒ፡ አባ፡ ፊቅጦር፡ አባ፡ አግሮኒ

www.ethiopianorthodox.org

ወካሉናስ ፡ ወበጺሖሙ ፡ ተራከቦሙ ፡ አባ ፡
ዕብሎይ ፡ በፍሥሓ ። ሀቤሰ ፡ ፪ት ፡ ዘመጽአ ፡
ምስለ ፡ አኃው ፡ ዘአሐቲ ፡ ዐይኑ ፡ ዕውርት ፡
ወሶበ፡ ተአምኖ ፡ ለአባ ፡ ዕብሎይ ፡ ተከሥተት ፡
ዐይኑ ፡ ወጸርሐ ፡ ወይቤ ፡ ኮከብ ፡ ብሩህ ፡
ዘውስተ ፡ ዓለም ።
፲፯ ወዓዲ ፡ ሰአሎ ፡ ለአባ ፡ ዕብሎይ ፡ ወይቤሎ ፡
ብእሲትየ ፡ ትፃሙ ፡ በደዌ ፡ ለምጽ ፡ ወይእቲ ፡
ታሕተ ፡ አስኬማከ ፡ ወይርከባ ፡ ጸጋከ ፡ እንተ ፡
ረከበኒ ፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ዕብሎይ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡
ፈውስ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡
እምከመ ፡ ወጽአ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ እምአፉሁ ፡
ረከበት ፡ ጥዒና ።

፲፰ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ቆመ ፡ አባ ፡ ዕብሎይ ፡
ማዕከለ ፡ መነኰሳት ፡ ወይቤሎሙ ፡ የሀሉ ፡
ዝየ ፡ ፩፩ እምኔክሙ ፡ እስመ ፡ መድኃኒነ ፡
ክርስቶስ ፡ ይመጽእ ፡ ወአርዳኢሁ ፡ ምስሌሁ ፡
ከመ ፡ ያለብወነ ፡ ንብረታ ፡ ለቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ።
፲፱ ወሶቤሃ ፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ በውእቱ ፡ መካን ፡
ወመጽአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ምስለ ፡ አርዳኢሁ ፡ ወመላእ
ክቲሁ ፡ ቅዱሳን ፡ ወአርአዮሙ ፡ መሠረተ ፡
ሕንፄሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።
፳ ወውእቱ ፡ ይምዕዶሙ ፡ ለደቂቁ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡
ፍጹማነ ፡ በኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ወያጽንዑ ፡
ተፋቅሮ ፡ ወእንዘ ፡ ይምዕዶሙ ፡ ተወለጠ ፡
ገጹ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ገጸ ፡ መልአከ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወኵለንታሁ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ዘይነ
ድድ ፡ ወፈርህዎ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ኢትፍርሁ ፡
ኦ ፡ ደቂቅየ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ እሰነአለክሙ ፡
አንሰ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ተመሥጠት ፡ ነፍሱ ፡
ወጼነወ ፡ ጼና ፡ ሠናይ ፡ ወበጊዜሃ ፡ ተከሥተ ፡
ዐይኑ ፡ ወይቤ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ርድአኒ ፡ ወተወከፍ ፡ ነፍስየ ፡ ኀቤከ ፡ ወዘንተ ፡
ብሂሎ ፡ አዕረፈ ፡ ወዘተርፈ ፡ ዜናሁ ፡ ቦ ፡ አመ ፡
፳ወ፩ለጥቅምት ።
፳፩ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ኮስና ፡ አባ ፡ ካሉናስ ፡ ናቸው ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡
አባ ፡ ዕብሎይ ፡ በደስታ ፡ ተቀበላቸው ፡ ከመነኰ
ሳቱም ፡ ጋር ፡ የመጣው ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ አንዲቷ ፡
ዐይኑ ፡ የታወረች ፡ ናት ፡ አባ ፡ ዕብሎይን ፡ በተማ
ለመው ፡ ጊዜ ፡ ዐይኑ ፡ ተከፈተች ፡ እርሱም ፡
በዓለም ፡ የሚያበራ ፡ ኮከብ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።
፲፯ ዳግመኛም ፡ አባ ፡ ዕብሎይን ፡ ለመነው ፡ እን
ዲህም ፡ አለው ፡ ሚስቴ ፡ በለምጽ ፡ ደዌ ፡ ትጨነ
ቃለች ፡ እርሷም ፡ በአስኬማህ ፡ የተማጸነች ፡ ናት ፡
እኔ ፡ ያገኘሁት ፡ ጸጋህ ፡ ለርሷም ፡ ይድረ
ሳት ። አባ ፡ ዕብሎይም ፡ በክብር ፡ ባለቤትም ፡
ጌታችን ፡ ስም ፡ ፈውስ ፡ ይሁንላት ፡ አለ ፡ ይህም ፡
ቃል ፡ ከአፉ ፡ እንደወጣ ፡ ድና ፡ ጤንነትን ፡
አገኘች ።
፲፰ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ አባ ፡ ዕብሎይ ፡ ከመነ
ኰሳት ፡ መካከል ፡ ቁሞ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምት
ሠራበትን ፡ ያስገነዝበን ፡ ዘንድ ፡ መድኃኒታችን ፡
ክርስቶስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ ይመጣልና ፡
አንዱም ፡ አንዱ ፡ ከእናንተ ፡ አይሒድ ፡ ከዚህ ፡
ይኑር ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።
፲፱ ያን ፡ ጊዜም ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ብርሃን ፡ ወጣ ፡ የክብር ፡
ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከከበሩ ፡
ደቀ ፡ መዛሙሩቱና ፡ ከመላእክቶቹ ፡ ጋር ፡ መጣ ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ሕንፃዋ ፡ የሚመሠረትበ
ትንም ፡ አሳያቸው ።
፳ እርሱም ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ፍጹማን ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ፍቅርንም ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ልጆ
ቹን ፡ ይመክራቸው ፡ ነበር ፡ እየመከራቸውም ፡
ፊቱ ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መል
አክ ፡ ፊት ፡ ሆነ ፡ ሁለመናውም ፡ እንደሚነድ ፡
እሳት ፡ ሆነ ፡ እነርሱም ፡ ፈሩ ። እርሱም ፡ ልጆቼ ፡
አትፍሩ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ እሰናበታችኋለሁ ፡ አላ
ቸው ። ይህንንም ፡ ብሎ ፡ ነፍሱ ፡ ተመሠጠች ፡
በጎ ፡ መዓዛም ፡ ሸተተ ፡ ወዲያውኑ ፡ ዐይኑ ፡
ተገለጠና ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ርዳኝ ፡
ነፍሴንም ፡ ወዳንተ ፡ ተቀበል ፡ አለ ፡ ይህንንም ፡
ብሎ ፡ አረፈ ። የቀረውም ፡ ዜናው ፡ ጥቅምት ፡ ሃያ ፡
አምስት ፡ ቀን ፡ ተጽፎአል ።

፳፩ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡
በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለዕብሎይ፡መምህረ፡ሥርዓት፡ወሕግ፡ዘደገለ፡ብሎግ። ምግባሩ፡ሠናይ፡ምስለ፡ሃይማኖት፡በደርግ። ያስተፌሥሕ፡ልበ፡ደቂቅ፡ወሕሊና፡ኵሉ፡አእሩግ። ከመ፡ያስተፌሥሕ፡አህጉራተ፡ዘይውኅዝ፡ፈለግ።

፳፪፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ፍልሰተ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ፡ኤፍሬም፡ሶርያዊ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

፳፪፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የሶርያዊ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ የሥጋው ፡ ፍልሰት ፡ ሆነ ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ፍልሰተ፡ሥጋከ፡ማሕየዊ። ለዘሐመ፡ብእሲ፡ወለዘይደዊ። ምሉእ፡ጥበበ፡ወምክር፡ኤፍሬም፡ሶርያዊ። አመ፡አስተርአይከ፡ማዕከለ፡ሕዝብ፡ሐሳዊ። በተዋሥኦትከ፡ጽድቀ፡ተሞዐ፡ዐላዊ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ አጋቦስ ፡ ሐዋርያ ፡ ፩ እምሮወ፪፡አርድእት።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለሰብዓ ፡ ወክልኤቱ ፡ አርድእት ፡ እለ ፡ ኀረዮሙ ፡ እግዚእነ ፡ ወፈነዎሙ ፡ ከመ ፡ ይስብኩ ፡ እምቅድመ፡ሕማማቲሁ።

፫፤ ወሶበ ፡ ወረደ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነሥአ ፡ ጸጋሁ ፡ ምስለ ፡ ሐዋርያት ፡ ወወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ እስመ ፡ ነሥአ ፡ ቅናቶ ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወአሠረ ፡ ባቲ ፡ እገሪሁ ፡ ለሊሁ ፡ ወይቤ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡ለበዓለ፡ዛቲ፡ቅናት፡ሀለዎ፡ ከመ ፡ ይእሥርዎ ፡ አይሁድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወተፈጸመት፡ዛቲ፡ትንቢቱ።

፬፤ ወእምዝ፡ወጽአ፡ይስብክ፡በስብከተ፡ወንጌል፡ ማሕየዊ ፡ ምስለ ፡ ሐዋርያት ፡ ወዖደ ፡ አህጉራተ፡ብዙኃተ፡እንዘ፡ይሜህር፡ወይመርሕ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርቱዐ ፡ ወሜጠሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እምአይሁድ ፡ ወእምየናናውያን ፡ ወአብአሙ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ዘእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወአንጽሖሙ፡በጥምቀተ፡ክርትና፡ቅድስት።

፭፤ አይሁድሰ፡ምሉአነ፡ቅንአት፡አኀዝዎ፡ግብተ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ አራት ፡ በዚች፡ቀን፡ከሰባ፡ሁለቱ፡አርድእት፡አንዱ፡ ሐዋርያ፡የከበረ፡አጋቦስ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፪፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ጌታችን ፡ ከመረጣቸውና ፡ ይሰብኩ፡ዘንድ፡ከመከራው፡በፊት፡ከላካቸው፡ ከሰባ፡ሁለቱ፡አርድእት፡ውስጥ፡ነው።

፫፤ በጽርሐ ፡ ጽዮንም ፡ አጽናኝ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋር ፡ ስጦታውን ፡ ተቀብሏል። እግዚአብሔርም ፡ የትንቢትን ፡ ሀብት ፡ ሰጠው ፡ ስለርሱ ፡ በሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ መታጠቂያ ፡ አንሥቶ ፡ ራሱ ፡ እግሮቹን ፡ አሠረባትና ፡ የዚችን ፡ መታጠቂያ ፡ ባለቤት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አይሁድ ፡ እንዲህ ፡ ያሥሩታል፡ አለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት፡ተናገረ፡ትንቢቱም፡ተፈጸመች።

፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሕይወት ፡ በሆነ ፡ በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ሊአስተምር ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋር ፡ ወጣ ፡ እያስተማረና ፡ ቀና ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔርን፡መንገድ፡እየመራ፡ብዙ፡አገሮችን፡ዞረ፡ ከአይሁድና፡ከዮናናውያንም፡ብዙዎችን፡የክብር፡ባለቤት፡ወደሆነ፡ወደ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ ፡ ቀን ፡ ሃይማኖት ፡ አስገባቸው ፡ በከበረች፡በክርስትና፡ጥምቀትም፡አነፃቸው።

፭፤ ቅናትን፡የተመሉ፡አይሁድም፡ብቻውን፡በኢየ

www.ethiopianorthodox.org

በኢየሩሳሌም ፡ ባሕቲቶ ፡ ወቀሠፍዎ ፡ መቅሠፍተ ፡ ዐቢየ ፡ ወእምዝ ፡ ገብሩ ፡ ውስተ ፡ ከሣዱ ፡ ሐብለ፡ወሰሐብዎ፡እስከ፡አፍአ፡ሀገር፡ወበህየ፡ ወገርዎ ፡ በአዕባን ፡ እስከ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ወሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ ብርሃን ፡ እምሰማይ ፡ ወኮነ ፡ ትኩለ፡ከመ፡ዓምድ፡ላዕለ፡ሥጋሁ፡ዘይበጽሕ፡ እስከ፡ሰማይ፡እንዘ፡ይኔጽሩ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ ኀቤሁ።

፯ ወከሠተ፡እግዚአብሔር፡ልበ፡አሐቲ፡ብእሲት፡ አይሁዳዊት ፡ ወይእቲ ፡ ዘአልባ ፡ ጽልሑት ፡ ውስቴታ፡ወኢ፡ቅንአት፡ወጽልእ፡ወተዓቅብ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ። ወርእያ ፡ ዘንተ ፡ ብርሃነ ፡ ትቤ ፡ እስመ፡ዝንቱ፡በእሲ፡ጻድቅ፡ውእቱ፡ወሶቤሃ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሃ ፡ ብርሃን ፡ ወጸርሐት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ አነ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ዘአአምን ፡ በእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ቅዱስ ፡ አጋቦስ ፡ ወእንዘ ፡ ታዓብዮ ፡ ወተአኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወገርዋ ፡ በአዕባን ፡ ወመጠወት ፡ ነፍሳ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግዚአብሔር።

፰ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለሐዋርያ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ሩሳሌም ፡ በድንገት ፡ ያዙትና ፡ ታላቅ ፡ ግርፋትንም ፡ ገረፉት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአንገቱ ፡ ገመድ ፡ አስገብተው ፡ እስከ ፡ ከተማ ፡ ውጭ ፡ ጐትተው ፡ በዚያም ፡ ነፍሱን ፡ እስከአሳለፈ ፡ ድረስ ፡ በደንጊያ ፡ ወገሩት ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከሰማይ፡ብርሃን፡ወርዶ፡በሥጋው፡ላይ፡እንደ፡ ምሰሶ፡ተተከለ፡ወደ፡ሰማይም፡ደርሶ፡አሕዛብ፡ ሁሉ፡ወደርሱ፡ሲመለከቱ፡ነበር።

፯ እግዚአብሔርም፡የአንዲት፡አይሁዳዊት፡ሴት፡ ልቡናዋን ፡ ገለጠላት ፡ እርሷም ፡ በውስጥዋ ፡ ሽንገላና ፡ ቅናት ፡ ጠብ ፡ የሌለባት ፡ ናት ፡ የኦሪትንም፡ሕግ፡የምትጠብቅ፡ነበረች፡እርሷም፡ ይህን ፡ ብርሃን ፡ አይታ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ አለች ። ያን ፡ ጊዜም ፡ በላይዋ ፡ ብርሃን ፡ ወረደ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ጮኸች ፡ እኔ ፡ በቅዱስ ፡ አጋቦስ ፡ ፈጣሪ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ በሆነ ፡ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ የማምን ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ከፍ፡ከፍ፡እያደረገች፡ስታመሰግነው፡በደንጊያ፡ወገሩዋት፡ነፍሷንም፡በእግዚአብሔር፡እጅ፡ሰጠች።

፰ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በሐዋርያው ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአጋቦስ ፡ እምአርድእተ ፡ ክርስቶስ ፡ ዋሕድ ። አመ ፡ ወገርዎ ፡ በአዕባን ፡ ወቀተልዎ ፡ አይሁድ። ተተክለ ፡ ብርሃን ፡ በአምሳለ ፡ ዓምድ ። መልዕልተ ፡ ሥጋሁ ፡ ቅድመ ፡ ጉቡአን ፡ በዓውድ ። እስከ ፡ አይሁዳዊት ፡ ተመይጠት፡ወአምነት፡በወልድ።

፱ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ወፍድፋደ ፡ ገድል ፡ ወሎቱሰ ፡ አመ ፡ ጸአታ ፡ ለነፍሱ ፡ እምሥጋሁ ፡ ይቤሎ ፡ አባ ፡ሙሴ ፡ እኁየ ፡ ምንተ ፡ ትሬኢ ፡ ወይቤ ፡ ሊተሰ ፡ ይኄይሰኒ፡አርምሞ፡ወሶበ፡ወጽአት፡መንፈሱ፡ ርእየ ፡ አባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ሰማየ ፡ ርኅወ ፡ ወይቤሎ ፡ ተፈሣሕ ፡ ኦ ፡ ወልድየ ፡ ዘካርያስ ፡ እስመ ፡ ተርኅወ ፡ ለከ ፡ አንቀጸ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወከመዝ ፡ አዕረፈ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፱ በዚችም ፡ ቀን ፡ በምግባር ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ተጋድሎውም ፡ የበዛ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ አረፈ ፡ እርሱንም ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ በምትለይ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ታያለህ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ ለእኔስ ፡ ዝምታ ፡ ይሻለኛል ፡ አለ ፡ ነፍሱም ፡ ስትወጣ ፡ አባ ፡ ኤስድሮስ ፡ ሰማይ ፡ ተከፍቶ ፡ አየ ፡ ልጄ ፡ ዘካርያስ ፡ ሆይ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በር ፡ ተከፍቶልሃልና ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ አለው ፡ በእንዲህም ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ አረፈ ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዘካርያስ ፡ በኀሢሥ ፡ ዓለመ ፡ ከሃ ፡ ዘሀሎ ። ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ዘኮነ ፡ ወፍድፋደ ፡ በተጋድሎ ። ጊዜ ፡ ጸአታ ፡ ለነፍሱ ፡ ዘይሬኢ ፡ ለዘተሰአሎ ። አምነቢብ ፡ አርምሞ ፡ ይኄይስ ፡ ይቤሎ ። እስመ ፡ ውዳሴ ፡ ሰብእ ፡ ጸልአ ፡ ዘያማስን ፡ ኵሎ።

www.ethiopianorthodox.org

፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፰ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አክርጽዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ፡ለአበው፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፲ቱ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ ወቅዱስ፡ውእቱ፡ወኮነ፡ቀሲስ፡በሀገረ፡እስክንድርያ። ወሶበ፡አዕረፈ፡አባ፡ከላድያኖስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት ፡ ዘእምቅድሜሁ ፡ ኀረይዎ ፡ ሕዝብ ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወኤጲስቆጳሳት ፡ ወሤምዎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ።

፫፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ሑረተ ፡ ሠናየ ፡ በከመ ፡ ሐዋርያት፡እንዘ፡ይሜህር፡ሃይማኖተ፡እግዚአብሔር፡ወሕጎ፡ማሕየዌ፡ወያነብብ፡ሎሙ፡መጻሕፍተ፡ቅዱሳተ፡ወይሜህሮሙ፡ለመርዔቱ ፡ ወየዐቅቦሙ ፡ ወይኤጽሮሙ ፡ ዘለሄ ፡ ወኢያጥረየ፡፩ደ፡ድርህመ፡ብሩር፡ወኢ፡፩ደ፡ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ሲሳየ ፡ ዕለት ፡ ወዓራዝ፡በዘይከድን፡ሥጋሁ፡በእንተ፡ቊር፡ወሐሩር፡ወኢዘገበ፡ምንተኒ።

፬፤ ወነበረ፡በዝንቱ፡ተጋድሎ፡፲ወ፪ተ፡ዓመተ፡ወአሥመሮ፡ለእግዚእነ፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፭፤ ወስብሐት፡ እግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ አምስት ፡ በዚች፡ቀን፡የእስክንድርያ፡አገር፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የከበረ ፡ አባት ፡ አክርጽዮስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ዐሥረኛ፡ነው።

፪፤ ይህም ፡ አባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ንጹሕ፡ቅዱስ፡ነው። በእስክንድርያ፡አገርም፡ቄስ፡ሁኖ፡የሚያገለግል፡ነበር፡ከእርሱ፡በፊት፡የነበረ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ከላድያኖስ፡በአረፈ፡ጊዜ ፡ የእስክንድር ፡ አገር ፡ ሕዝቡና ፡ ኤጲስቆጳሳቱ ፡ መረጡት ፡ በወንጌላዊ ፡ ማርቆስ ፡ ወንበርም፡ላይ፡ሊቀ፡ጵጵስና፡ሾሙት።

፫፤ ከዚህም፡በኋላ፡እንደ፡ሐዋርያት፡መልካም፡ጕዞን፡ተጓዘ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሃይማኖት ፡ ሕይወት ፡ የሆነ ፡ ሕጉንም ፡ እያስተማረ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትንም ፡ እያነበበላቸውና ፡ እያስተማራቸው፡መንጋዎቹን፡ይጠብቃቸው፡ነበር፡ሁል፡ጊዜም፡ይመለከታቸዋል፡አንድ፡የብር፡አላድን፡ወይም፡አንድ፡የወርቅ፡ዲናርን፡ጥሪት ፡ አላኖረም ፡ ከዕለት ፡ ምግቡ ፡ ከቁርና ፡ ከሐሩር ፡ ሥጋውን ፡ ከሚሸፍንበት ፡ ልብስ ፡ በቀር፡ምንም፡አላከማቸም።

፬፤ በዚህም፡ተጋድሎ፡ዐሥራ፡ሁለት፡ዓመት፡ኑሮ ፡ ጌታችንንም ፡ አገልግሎ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፭፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአክርጽዮስ ፡ ድኅረ ፡ ከላድያኖስ ፡ ዘቆመ ። ሞጣሕተ ፡ ጳጳሳት ፡ ይትዓጸፍ ፡ ዘበሃይማኖት ፡ እኑመ።ከዊኖ፡መሐሬ፡ወመስተሳልመ።እምእደ፡መርዔቱ፡ኢተሰቈቈ፡ፍጹመ።ተረፈ፡ሲሳዩ፡ወልብሱ፡አሐደ፡ድርህመ።

፮፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ መስተጋድል ፡ አባ ፡ ብሶይ ፡ ዘተሰምየ ፡ ጴጥሮስሃ ፡ ወዝንቱ ፡ እምላዕላይ፡ግብጽ፡እምሀገረ፡አክሚም።

፯፤ ወበጊዜ፡ውርዙቱ፡ኮነ፡ዘይገብር፡ምግባራተ፡ሕሱማተ ፡ ወይትፌጋዕ ፡ በመብልዕ ፡ ወበመስቴ ። ወፈቀዶ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒተ ፡ ነፍሱ ፡ አምጽአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ደዌ ፡ ዕፁበ ፡ ወቀርበ ፡ ለመዊት ፡ ወመሠጡ ፡ ነፍሶ ፡ ወአርአይዎ ፡ መከናተ ፡ ዘነኔ ፡ ወዓዘቅተ ፡ ዕምቅተ ፡

፮፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ተጋዳይ ፡ የሆነ ፡ አባት ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለ ፡ አባ ፡ ብሶይ ፡ አረፈ ፡ እርሱም፡ ከላይኛው ፡ ግብጽ ፡ አክሚም ፡ ከሚባል፡ከተማ፡ነው።

፯፤ በጐልማሳነቱም ፡ ጊዜ ፡ የከፉ ፡ ሥራዎችን ፡ የሚሠራ ፡ ሁኖ ፡ ነበር ፡ በመብላትና ፡ በመጠጣትም ፡ ይደሰት ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡ የነፍሱን ፡ ድኅነት ፡ ሽቶ ፡ ጽኑ ፡ ደዌ ፡ አምጣበትና ፡ ለመሞት ፡ ተቃረበ ። ነፍሱንም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወርእየ ፡ በህየ ፡ እለ ፡ ይለብሱ ፡ አልባሰ ፡ ብሩ
ሀነ ፡ ወበእደዊሆሙ ፡ በድነ ፡ ብእሲ ፡ ወፈለጥዎ ፡
፬ተ ፡ ክፍለ ፡ ወይቤልዎ ፡ ለብሶይ ፡ ከመዝ ፡
ይገብሩ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘይሰርቅ ፡ ንዋየ ፡ ሰብእ ፡
ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ገዐረ ፡ እምልቡ ፡
ወኀዘነ ፡ ወበከየ ፡ መሪረ ፡ ወእምዝ ፡ ተመይጠት ፡
ነፍሱ ፡ ወአንሥአ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ኀበ ፡ ሰማይ ፡
ወይቤ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ለእመ ፡ አሕየ
ውከኒ ፡ እምዝንቱ ፡ ደዌ ፡ አነ ፡ እኔስሕ ፡ እምኃጢ
አትየ ፡ ወአመልከከ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ፡ ወኢይ
ሬኢ ፡ እንከ ፡ ግሙራ ፡ ገጸ ፡ ብእሲት ፡ ለዓለም ።

፳፰፤ ወሶቤሃ ፡ አሕየዎ ፡ እምደዌሁ ፡ ወተንሥአ ፡
ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ብንዋይ ፡ ወአመከርዎ ፡
መንኰሳት ፡ ወአልበስዎ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡
ወተጋደለ ፡ ገድለ ፡ ዐቢየ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡
ወበሰጊድ ፡ እስከ ፡ ተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ውስተ ፡
ኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወተለዓለ ፡ ዲበ ፡
ኵሎሙ ፡ ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ወተግሣጻተ ፡
ወትምህርታተ ፡ ለመነኰሳት ፡ ዘይበቍዕ ፡
ወአሐተ ፡ ጊዜ ፡ ጾመ ፡ አሐደ ፡ ወርኃ ፡ እንዘ ፡
ኢይበልዕ ፡ ኅብስተ ፡ ወኢይሰቲ ፡ ማየ ፡
ወነበረ ፡ ከመዝ ፡ በተጋድሎ ፡ መጠነ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡
ዓመት ።

፳፱፤ ወኵላ ፡ ሌሊተ ፡ የኀድር ፡ ቀዊሞ ፡ እንዘ ፡
ይተግህ ፡ በሰጊድ ፡ ወበጸልዮ ፡ ወኮነ ፡ ሎቱ ፡
ክሡተ ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ምግባራ
ቲሆሙ ፡ ለሰብእ ፡ እመሂ ፡ ጻድቅ ፡ ወእመሂ ፡
ኃጥእ ፡ ወእምዝ ፡ ሐመ ፡ ንስቲተ ፡ ወአዕረፈ ፡
በሰላም ።

፴፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐ
ረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

በተመሥጦ ፡ አውጥተው ፡ የሥቃይ ፡ ቦታዎ
ችንም ፡ ጥልቅ ፡ የሆነች ፡ ጕድጓድንም ፡
አሳዩት ። በዚያም ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡
ሰዎች ፡ አሉ ፡ በእጆቻቸውም ፡ የሰው ፡ በድን ፡
ነበረ ፡ አራት ፡ ክፍል ፡ አድርገው ፡ ለያዩትና ፡
የሰውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰርቀውን ፡ ሁሉ ፡
እንዲህ ፡ ያድረጉበታል ፡ አሉት ። ይህንንም ፡
ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጮኸ ፡ ከልቡም ፡ አዝኖ ፡
አለቀሰ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነፍሱ ፡ ተመለሰች ፡
ዐይኖቹንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንቶ ፡ ጌታዬና ፡
ፈጣሪዬ ፡ ከዚህ ፡ ደዌ ፡ ከአዳንከኝ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡
ኃጢአቴ ፡ ንስሐ ፡ በመግባት ፡ በፍጹም ፡
ልቡናዬ ፡ አመልክሃለሁ ፡ ከእንግዲህም ፡ ከቶ ፡
ለዘላለሙ ፡ የሴት ፡ ፊት ፡ አላይም ፡ አለ ።

፳፰፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከደዌው ፡ አዳነውና ፡
ተነሥቶ ፡ ብንዋይ ፡ ወደሚባል ፡ ገዳም ፡ ሔደ ፡
መንኰሳቱም ፡ ከፈተኑት ፡ በኋላ ፡ የምንኵ
ስናን ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡
ሁሉ ፡ እስከሚሰማ ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን ፡
በጾም ፡ በጸሎት ፡ በመስገድም ፡ ተጋደለ ፡ ከሁሉ ፡
በላይም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ ለመነኰሳትም ፡
ትምርት ፡ የሚሆኑ ፡ የሚጠቅሙ ፡ ድርሳና
ትንና ፡ ተግሣጻትን ፡ ደረሰ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡
እንጀራ ፡ ሳይቀምስ ፡ ውኃ ፡ ሳይጠጣ ፡ አንድ ፡
ወር ፡ ጾመ ፡ እንዲህም ፡ እየተጋደለ ፡ ሠላሳ ፡
ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ኖረ ።

፳፱፤ መላዋንም ፡ ሌሊት ፡ በጸሎትና ፡ በሰግደት ፡
በመትጋት ፡ ቁሞ ፡ ያድራል ፡ ሰዎች ፡ የሚሠ
ሩት ፡ ሁሉ ፡ ጻድቅም ፡ ቢሆን ፡ ኃጢአተኛም ፡
ቢሆን ፡ በፊቱ ፡ ግልጥ ፡ ሆነ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
ጥቂት ፡ ታመመና ፡ በሰላም ፡ አረፈ ።

፴፤ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡
በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለብሶይ ፡ ጴጥሮስሃ ፡ ዘተሰምየ ። ኵነኔ ፡ ሰራቂ ፡ በሕልሙ ፡ ሶበ ፡ ነጸረ ፡ ወርእየ ። ኀዲጎ ፡ ዘትካት ፡ ምግባሮ ፡ እኩየ ። እንዘ ፡ ይፈዲ ፡ ብፅዓቶ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ ጸለየ ። በመዋዕለ ፡ ጾሙ ፡ ኢጥዕመ ፡ ኅብስተ ፡ ወማየ ።

፴፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ ኖብ ፡ ጻድቅ ፡
መነሳንሱ ፡ ዘወርቅ ። ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡
ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

፴፩፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ መነሳንሱ ፡ የወርቅ ፡ የሆነ ፡
ጻድቁ ፡ አባ ፡ ኖብ ፡ አረፈ ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡
ይገባል ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለኖብ ፡ መነሳንሱ ፡ ዘወርቅ ። ሰዳዴ ፡ አጋንንት ፡ በድድቅ ። ይጸሊ ፡ ለነ ፡ ይእዜ ፡ ምሕረተ ፡ ለውሉደ፡ ጥምቀት ፡ ደቂቅ ። አመ ፡ ምጽአቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወስብሐቲሁ ፡ መብረቅ ። ኢይርከበነ ፡ በፀጋም ፡ ወዲቅ።

፲፪፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ፍልሰተ፡ሥጋሆሙ፡ለ፵ወ፱፡ መነኰሳት ፡ ዘኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ በገዳመ፡ አስቄጥስ ፡ ወተዝካሩ ፡ ለአቡሊዲስ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡ዜናሁሰ፡ሀሎ፡ጽሑፈ፡አመ፡ ፮ ለዝ ፡ ወርኀ ፡ ወዓዲ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቡላ ፡ ወአሞኒ ፡ ወአበያ ፡ እሙ ፡ ለዕብሎይ ። በረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፲፪፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ባአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ ፡ የአርባ ፡ ዘጠኝ ፡ መነኰሳት ፡ መታሰቢያቸው፡ነው፡የሮሜ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ የአቡሊዲስም ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ ዜናውም ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ በስድስት ፡ ተጽፎአል። ደግሞ ፡ የቡላ ፡ የአሞኒ ፡ የዕብሎይ ፡ እናት ፡ የአበያ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ። በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ይገባል፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለፍልስተ፡ሥጋሆሙ፡ቅድስት።በደብረ፡መቃርዮስ፡አብ፡ኀበ፡ተሐንፀ፡በዓት።አርብዓ፡ ወተሰዓቱ፡ሰማዕታት።ሠረፀ፡ሎሙ፡ብንያሚን፡በመካኖሙ፡ዕውቅት።በዓለ፡ፍልሰቶሙ፡ዘገብረ፡በዛቲ፡ ዕለት።

ሰላም፡ለከ፡አቡሊዲስ፡አቡነ።ዘደለወከ፡ትሰመይ፡መምህረ፡ዓለም፡ካህነ።መልዕልተ፡ቀላይ፡በድንከ፡ ሶበ፡ጸለለ፡ዳኅነ።አስተኀፈረ፡ወአኅሠረ፡ዘወገሩከ፡ዕልዋነ።በውስተ፡እግርከ፡አሢሮሙ፡ዕብነ።

፲፫፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አባ፡ዕብሎይ፡መስተጋድል ፡ ጽኑዕ ፡ ዘአቅነየ ፡ ርእሶ ፡ ቀዳሚ ፡ ለኃጢአት፡ወዝንቱ፡ኖላዌ፡አባግዕ፡ወወሀበ፡ ርእሶ፡ለሰይጣን፡ወኢተርፎ፡ምንትኒ፡እምኃጣውዕ ፡ እስመ ፡ ይዜሙ ፡ ወይሰርቅ ፡ ወየኀይድ ፡ ወይቀትል ፡ ወነበረ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ፡ መጠነ፡፵ዓመት፡እንዘ፡ይፌጽም፡ምግባረ፡ ሰይጣን።

፲፬፤ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ምስለ ፡ አባግዒሁ ፡ በመንፈቀ፡ መዓልት ፡ ወናሁ ፡ ርእየ ፡ ብእሲተ፡ ዕንስተ ፡ ዘበጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ወሊዶታ ፡ ወወደየ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ሕሊና ፡ ወይቤ ፡ ዘተርፈተኒ ፡ እምኃጢአት ፡ አሐቲ ፡ ወይእቲ ፡ ከመ ፡ እሥጥቅ ፡ ከርሠ ፡ ብእሲት ፡ ወእርአይ ፡ ኀበ ፡ ይሰክብ ፡ ሕፃን ፡ በውስተ ፡ ከርሠ ፡ እሙ ፡

፲፭፤ ወሶቢሃ ፡ ሠረረ ፡ ወአኀዛ ፡ በሥዕርተ ፡ ርእሳ ፡ ወነጽሓ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወነሥአ ፡ መጥባሕተ ፡ ወሠጠቀ ፡ ከርሣ ፡ ወርእየ ፡ ለሕፃን ፡ ዘከመ ፡ ኮነ ፡ ሰኪቦቱ ፡ በውስተ ፡ ማሕፀን ፡ ወይእቲ ፡ ሞተት ፡ መቅድመ ፡ ተጽዒራ ፡

፲፫፤ በዚችም፡ቀን፡አስቀድሞ፡ራሱን፡ለኃጢአት፡ አስገዝቶ ፡ የነበረ ፡ ጽኑዕ ፡ ተጋዳይ ፡ አባ ፡ ዕብሎይ ፡ አረፈ ። ይህም ፡ የበጎች ፡ አርቢ ፡ ራሱን ፡ ለሰይጣን ፡ በማስገዛት ፡ ከኃጢአት ፡ ሥራ፡ምንም፡የቀረው፡የለም፡ያመነዝራል፡ ይሰርቃል፡ይቀማል፡ይገድላል፡በዚህም፡የሰይጣንን ፡ ሥራ ፡ እየፈጸመ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ያህል፡ኖረ።

፲፬፤ በአንዲትም፡ዕለት፡ከቀኑ፡እኩሌታ፡ከበጎቹ፡ ጋር፡በዱር፡ውስጥ፡ሳለ፡እነሆ፡የመውለጃዋ፡ ጊዜ፡የደረሰ፡ያረገዘች፡ሴትን፡አየ፡ሰይጣንም፡ በልቡ ፡ ክፉ ፡ ሐሳብን ፡ ጨመረ ፡ እንዲህም ፡ አለ፡የተረፈችኝ፡ኃጢአት፡አንዲት፡አለች፡ እርሷም ፡ ያረገዘች ፡ ሴት ፡ ሆዷን ፡ ሠንጥቄ ፡ በእናቱ ፡ ሆድ ፡ ሕፃኑ ፡ የሚተኛበትን ፡ አይ ፡ ዘንድ፡ነው።

፲፭፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ተወርውሮ ፡ ሔዶ ፡ በራስዋ ፡ ጠጕር ፡ ይዞ ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ጣላት ፡ ሾተልም ፡ አንሥቶ ፡ ሆዷን ፡ ሠነጠቀ ፡ ሕፃኑንም ፡ በማሕፀኗ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ሁኖ ፡ እነደተኛ ፡ አየው ፡ እርሷም ፡ በጻዕር ፡ ተጨ

www.ethiopianorthodox.org

ሕፃንስ ፡ ብዙኀ ፡ ጐንደየ ፡ እንዘ ፡ ይጼዓር ፡
በብዙኀ፡ፃማ፡ወሞተ።

፲፮፡ ወርእዮ፡ ኖላዌ፡ አባግዕ፡ ዘንተ፡ ዘገብረ፡ ዐቢየ፡
ኃጢአተ፡ ደንገፀ፡ ወኀዘነ፡ ፈድፋደ፡ ወበከየ፡
ብካየ ፡ መሪረ ፡ ወይቤ ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡
ገበርኩ ፡ ዐቢየ ፡ ኃጢአተ ።

፲፯፡ ወሶቢሃ ፡ ኀደገ ፡ አባግዒሁ ፡ ዝርዋነ ፡ ወነ
ሥአ ፡ በትረ ፡ በእዴሁ ፡ ወአንሶሰወ ፡ እንዘ ፡
ይበኪ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡
ወኢቦአ ፡ ኀበ ፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳት ፡
አላ፡ ቦአ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ ርኁቀ ፡ እምኔ
ሆሙ፡መጠነ፡፲ምዕራፍ፡ወኢኀደረ፡ውስተ
በዓት፡አላ፡ኮነ፡ዘየኀድር፡ምስለ፡አራዊት፡
ወይሴሰይ ፡ እምአቅማሀ ፡ ዕፀው ፡ ዘበ
በንስቲት፡ይጸርሕ፡ወይብል፡ዘምስለ፡ብካይ፡
አበስኩ ፡ እግዚኦ፡ ወገበርኩ ፡ እኩየ ፡ ስረይ ፡
ሊተ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ኃጥእ ፡ ወአባሲ ፡ ወገብር፡
እኩይ፡እስመ፡አንተ፡አምላክ፡ኄር፡ወመስተ
ሣህል፡አብ፡እስመ፡አልቦ፡ገብር፡ዘእንበለ፡
ኃጢአት ፡ ወአልቦ ፡ እግዚእ ፡ ዘእንበለ ፡
ምሕረት፡ወነበረ፡ከመዝ፡እንዘ፡ይትጋደል፡
፴ዓመተ።

፲፰፡ ወየብሰ፡ሥጋሁ፡ወጸልመ፡እምቍረ፡ሌሊት፡
ወእምሐሩረ፡ፀሐይ፡ወእምዋዕይ፡ወእምዝ፡
ሰምዐ፡ቃለ፡ዘይብሎ፡ሠረየ፡ለከ፡እግዚእ፡
በእንተ፡ደመ፡ብእሲት፡ጽናዕ፡ወተኀየል፡
ወዘንተኒ ፡ ዘይቤሎ ፡ ከመ ፡ ኢይትትኀከይ
ወኢይደቅ፡ውስተ፡ኃጢአት፡ዳግመ።

፲፱፡ወሶበ፡ሰምዐ፡ዘንተ፡ወሰከ፡ተጋድሎተ፡እንዘ፡
ይበኪ፡መሪረ፡እስከ፡ፈጸመ፡ይእተ፡ዓመተ፡
ዘእንበለ ፡ ፫ መዓልት ፡ ባሕቲቱ ፡ ወናሁ ፡
መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተርአዮ፡ ለ፩
ገዳማዊ፡ዘኮነ፡ርኁቀ፡እምኔሁ፡መጠነ፡፲ወ፫
ምዕራፍ፡ወዘነበረ፡ውስተ፡ይእቲ፡ገዳም፡፳
ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ኢይሬኢ ፡ ሰብአ ፡ ግሙራ ፡
ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ አፍአ ፡ እምኔከ ፡
ወትረክብ፡ብእሴ፡አረጋዌ፡ለእመ፡ተአመነ፡
ለከ፡ኃጢአቶ፡ናዝዞ፡ወበሎ፡ተኀድከ፡ለከ፡
ኵሉ፡ኃጢአትከ፡ቅትለተ፡ሕፃንኒ፡ተኃድገ፡
ለከ።

፳፡ ወሶቢሃ ፡ ሖረ ፡ ውእቱ ፡ ገዳማዊ ፡ ወተራከቦ ፡
ወተአምኁ፡በበይናቲሆሙ፡ውእቱሰ፡ይበኪ፡

ንቃ፡አስቀድሜ፡ሞተች፡ሕፃኑ፡ግን፡በጻዕር፡
እየተሠቃየ፡ብዙ፡ቆይቶ፡ሞተ።

፲፮፡ በግ፡አርቢውም፡የሠራውን፡ይህን፡ታላቅ፡
ኃጢአት ፡ ተመልክቶ ፡ ደነገጠ ፡ እጅግም ፡
አዘነ ፡ መራራ ፡ ልቅሶንም ፡ በማልቀስ ፡
ታላቅ፡ ኃጢአትን ፡ ሠርቻለሁና ፡ ወዮልኝ ፡
አለ ።

፲፯፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በጎቹን ፡ እንደተበተኑ ፡
ትቶ ፡ በእጁ ፡ በትሩን ፡ ብቻ ፡ ይዞ ወደ፡
አስቄጥስ፡ገዳም፡እስከሚደርስ፡እያለቀሰ፡
ተጓዘ ፡ ወደ ፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳትም ፡
አልገባም ፡ ከእርሳቸው ፡ ዐሥር ፡ ምዕራፍ ፡
ያህል፡ርቆ፡ወደ፡በርሀ፡ውስጥ፡ገባ፡እንጂ፡
በቤት ፡ ውስጥም ፡ አያድርም ፡ ነበር፡
ከአራዊት፡ጋር፡የሚኖር፡ሆነ፡እንጂ፡ከዕፀ
ዋትም ፡ ፍሬ ፡ በየጥቂቱ ፡ ይመገብ ፡ ነበር፡
ከዕንባ፡ጋርም፡እየጮኸ፡አቤቱ፡በደልኩ፡
ክፉ፡ሥራንም፡ሠራሁ፡ይቅር፡በለኝ፡እኔ፡
ኃጢአተኛ ፡ የሆንኩ ፡ ክፉ ፡ ባርያ ፡ ነኝና ፡
አንተም፡ቸር፡አምላክ፡ይቅር፡ባይ፡አባት፡
ነህና፡የማይበድል፡ባሪያ፡የማይምር፡ጌታ፡
የለምና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እንዲህም ፡ እየተ
ጋደለ፡አርባ፡ዓመት፡ኖረ።

፲፰፡ ከሌሊት ፡ ቍር ፡ ከቀን ፡ ፀሐይ ፡ ሐሩርና ፡
ትኩሳት፡የተነሣ፡ሥጋው፡ደርቆ፡ጠቆረ፡
ከዚህም፡በኋላ፡እንዲህ፡የሚለውን፡ቃል፡
ሰማ ፡ ስለ ፡ ሴቲቱ ፡ ደም ፡ ጌታ ፡ ይቅር ፡
ብሎሃል፡ጽና፡በርታ፡ይህንንም፡ያለው፡እን
ዳይታክትና፡ዳግመኛ፡በኃጢአት፡ውስጥ፡
እንዳይወድቅ፡ነው።

፲፱፡ ይህንም፡በሰማ፡ጊዜ፡ከሦስት፡ቀን፡ብቻ፡
በቀር ፡ ያቺን ፡ ዓመት ፡ እስከሚፈጽም ፡
መሪር፡ ልቅሶ ፡ እያለቀሰ ፡ ተጋድሎውን ፡
ጨመረ፡እነሆ፡የእግዚአብሔር፡መልአክ፡
ከእርሱ፡ዐሥራ፡አምስት፡ምዕራፍ፡ያህል፡
ርቆ፡ የሚገኝ፡ ከቶ፡ሰውን ፡ሳያይ ፡ በዚያች፡
በረሀ ፡ሰባ ፡ ዓመት ፡ የኖረውን ፡ አንዱን ፡
ገዳማዊ ፡ አንተ ፡ ካለህበት ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡
ውጭ ፡ ሒድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ታገኛለህ ፡
ኃጢአቱን ፡ ከአመነልህ ፡ አጽናናው ፡
ኃጢአትህ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሕፃኑም ፡ መገደል ፡
ተሠርዮልሃል፡በለው፡በማለት፡አዘዘው።

፳፡ በዚያንም፡ጊዜ፡ያ፡ገዳማዊ፡ሒዶ፡አገኘው፡
አርስበርሳቸውም ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘእንበለ፡ጽርዓት፡ወይቤሎ፡ገዳማዊ፡ንግረኒ፡
ዘገበርከ ። ወበእንተ ፡ ምንት ፡ ወጻእከ ፡ ዝየ ፡
ውእቱኒ፡ነገሮ፡ኵሎ፡ወዘከመ፡ሠጠቀ፡ከርሠ፡
ብእሲት፡ፅንስት፡ወይቤሎ፡ገዳማዊ፡ተኃደገ፡
ለከ፡ኃጢአትከ፡ወተፈሣሕ፡ኦ፡አቡየ፡እስመ፡
በሳኒታ፡ይመጽእ፡ኀቤከ፡መልአከ፡እግዚአ
ብሔር፡ወይሜጥወከ፡ሥጋሁ፡ወደሞ፡ለክር
ስቶስ።

፳፩፡ወሶበ፡ኮነ፡ጽባሐ፡ዕለተ፡ቀዳሚት፡ሰንበት፡
ጌነወ ፡ ጌና ፡ ምዑዝ ፡ ከኢኮነ ፡ ከማሁ ፡
ግሙራ፡ወይቤሎ፡አባ፡ዕሎይ፡ለገዳማዊ፡
ኦ፡ አቡየ ፡ ነፍስየ ፡ አልጸቀት ፡ ለወጺእ ፡
እምሥጋሃ፡እምፍርሃት፡ወሶበ፡ይቤ፡ዘንተ፡
ርእዮ፡ለመልአክ፡እንዘ፡ይቀውም፡ኀቤሁ፡
በአምሳለ ፡ መነኮስ ፡ ወውእቱ ፡ ይዜምር ፡
እንዘ፡ይብል፡እስመ፡ተመንደብኩ፡ወአድ
ኃነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግብኢ ፡ ነፍስየ ፡
ውስተ፡ዕረፍትኪ።እስመ፡እግዚአብሔር፡
ረደኢኪ፡እስመ፡አድኃና፡ለነፍስየ፡እሞት፡
ወለአዕይንትየኒ፡እምአንብዕ፡ወለእገርየኒ፡
እምዳኅፅ።ከመ፡አሥምሮ፡ለእግዚአብሔር፡
በብሔረ፡ሕያዋን።

፳፪፡ወሶበ፡ሰምዐ፡ዘንተ፡ነገረ፡አባ፡ዕብሎይ፡
ኖላዌ፡አባግዕ፡ወድቀ፡ዲበ፡ምድር፡ወኮነ፡
ከመ፡በድን፡ወሰፍሐ፡እዴሁ፡መልአክ፡
ወአንሥኦ፡በአምሳለ፡ብእሲ፡ወጸንዐ፡ልቡ፡
ወተመጠወ ፡ እምሥጢራተ ፡ ቅድሳት ፡
ዘወረደ፡ሎቱ፡እምሰማይ፡በእደ፡መልአክ።
ወዐርገ፡መልአክ፡ውስተ፡ሰማይ።

፳፫፡ወሶበሂ፡ተመጠወ፡ቍርባነ፡አባ፡ዕብሎይ፡
ኮነ፡ፀዓዳ፡ሥጋሁ፡ከመ፡በረድ፡ወብሩህ፡
ከመ፡ማኅቶት፡ወይእተ፡ዕለተ፡ወዐሉ፡
እንዘ፡ይትፌሥሑ፡፪ሆሙ፡ወይሴብሕዎ፡
ለእግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ምሴት ፡ አባ ፡
ዕብሎይሰ ፡ ኢያጽርዐ ፡ ዘትካት ፡ ጸሎቶ ፡
እንዘ፡ ይብል ፡ አበስኩ ፡ ስብዓ ፡ በበስብዕ ፡
አነ፡ገብር፡እኩይ፡ስረይ፡ሊተ፡ኦ፡አምላክ፡
ኄር፡ወአብ፡መሐሪ፡እስመ፡አልቦ፡ገብር፡
ዘእንበለ ፡ ጌጋይ ፡ ወአልቦ ፡ እግዚእ ፡
ዘእንበለ፡ምሕረት ። ወቤቱ፡በይቲ፡ዕለት፡
እንዘ፡ይሴብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡እስከ፡
መንፈቀ፡ሌሊት፡እንተ፡ይእቲ፡እሑድ ።

እርሱ፡ ዕብሎይ ፡ ግን ፡ ያለማቋረጥ ፡ ያለቅስ ፡
ነበር ፡ ገዳማዊውም ፡ የሠራኸውን ፡ ንገረኝ ፡
በምን፡ምክንያትስ፡ወደዚህ፡ወጣህ፡አለው።
እርሱም፡ሁሉንም፡ነገረው፡ያረገዘችዋንም፡
ሴት፡ሆድዋን፡እንደሠነጠቀ፡ነገረው፡ገዳማ
ዊውም ፡ ኃጢአትህ ፡ ሁሉ ፡ ተሠርዮልሃል ፡
አባቴ ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ ነገ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ መልአክ ፡ ወዳንተ ፡ መጥቶ ፡ የክርስ
ቶስን፡ሥጋና፡ደም፡ያቀብልሃል፡አለው።

፳፩፡የቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ዕለትም ፡ በነጋ ፡ ጊዜ ፡
ከቶ ፡ እንደርሱ ፡ ሁኖ ፡ የማያውቅ ፡ ጣፋጭ ፡
ሽታ ፡ ሸተተ ፡ አባ ፡ ዕብሎይም ፡ ገዳማዊውን ፡
አባቴ ፡ ሆይ ፡ ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ነፍሴ ፡
ከሥጋዋ ፡ ልትለይ ፡ ደረሰች ፡ አለው ።
ይህንንም፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በመነኰስ ፡ አምሳል ፡
ከአጠገቡ ፡ ቁሞ ፡ መልአኩን ፡ አየው ፡
እርሱም፡ ተቸገርኩ ፡ እግዚአብሔርም ፡
አዳነኝ ። ነፍሴ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ዕርፍትሽ ፡
ተመለሽ ። እግዚአብሔር ፡ ረዳትሽ ፡ ነውና ።
ነፍሴን ፡ ከሞት ፡ አድኗታልና ። ዐይኖቼንም ፡
ከእንባ ። እግሮቼንም ፡ በዳጥ ፡ ከመሰናከል ።
በሕያዋን ፡ አገር ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለ
ግለው፡ ዘንድ ፡ እያለ ፡ ይዘምር ፡ ነበር።

፳፪፡ የበጎች ፡ ጠባቂ ፡ የነበረ ፡ አባ ፡ ዕብሎይም ፡
ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ወድቆ ፡ እንደ ፡ በድን ፡ ሆነ ፡ መልአኩም ፡
በሰው ፡ አምሳል ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ አነሣው ፡
ልቡም፡ጸንቶ፡በመልአክ፡እጅ፡ከሰማይ፡የወ
ረደለትን፡ሥጋውንና፡ደሙን፡ተቀበለ፡መልአ
ኩም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ።

፳፫፡አባ፡ዕብሎይም፡ቍርባኑን፡በተቀበለ፡ጊዜ፡
ሰውነቱ፡ሁሉ፡እንደ፡በረድ፡ፀዓዳ፡እንደ፡
ፋናም ፡ ብሩህ ፡ ሆነ ፡ በዚያችም ፡ ዕለት ፡
ሁለቱም ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ እግዚአብሔ
ርንም፡ እያመሰገኑ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ዋሉ ።
እብሎይ ፡ ግን ፡ የቀድሞ ፡ ጸሎቱን ፡ አላቋ
ረጥም፡ እንዲህም ፡ እያለ ፡ እኔ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ፡
በየሰባቱ፡ሰባ፡ጊዜ፡በደልኩ፡ቸር፡ጌታ፡ሆይ፡
መሐሪ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ የማይ
በድል ፡ ባሪያ፡ የማይምር ፡ ጌታ ፡ የለምና ።
በዚችም፡ዕለት፡እስከ፡ሌሊቱ፡እኩሌታ፡እግ
ዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑ ፡ አደሩ ፡ እርሷም ፡
እሑድ ፡ ናት ። በዚያችም ፡ ጊዜ ፡ ከፊተኛው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይእተ፡ጊዜ፡ጼነወ፡ጼና፡ዕፍረት፡ምዑዝ፡ ዘይፈደፍድ ፡ እምቀዳሚ ፡ ወይቤሎ ፡ ገዳ ማዊ፡ ለአባ ፡ ዕብሎይ ፡ ነዓ ፡ እኊየ ፡ ተኀፀብ፡ በማይ ፡ ወተፈሣሕ ፡ እስመ ፡ በዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ተዓርፍ ፡ እምኵሉ ፡ ፃማ ፡ ዘተወከፍከ። ወሶቤሃ ፡ መጠዎሙ ፡ ቍርባነ ፡ ለክል ኤሆሙ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአዕ ረፈ፡ አባ ፡ ዕብሎይ ፡ ወፆርዋ ፡ ለነፍሱ ፡ መላእክት፡ወሠረሩ፡እስከ፡አርያም።

፳፬፡ ወኮነ፡ውእቱ፡ገዳማዊ፡ዘይሔሊ፡ወይብል፡ እስመ ፡ አነ ፡ አረጋዊ ፡ ወኢይክል ፡ ፀዊረ ፡ ሥጋሁ ፡ ወአልብየ ፡ በዘእከሪ ፡ መቃብሮ ፡ ወሶቤሃ፡መጽኡ፡፪ቱ፡አናብስት፡ወሰገዱ፡ ኀበ ፡ ሥጋሁ ፡ ወከረዩ ፡ መቃብሮ ፡ ወፆሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ወቀበርዎ ፡ ወተአ ምኅዎ፡ለገዳማዊ፡ውእቱኒ፡ባረኮሙ፡ወሖሩ፡ በሰላም።

፳፭፡ ወእምዝ ፡ ሐለየ ፡ ውእቱ ፡ ገዳማዊ ፡ ወይቤ ፡ ቦኑ፡እረክብ ፡ ዘይቀብር ፡ ሥጋየ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀቤሁ ፡ ዘይብል ፡ ኢትኅዝን ፡ አነ ፡ እቀብር ፡ ሥጋከ ፡ ወኢተርፈከ ፡ ዘእንበለ ፡ ሠለስቱ፡ዕለት፡ወናሁ፡እፌኑ፡ኀቤከ፡፫ተ፡ ዕደወ ፡ ወአንተ ፡ ንግሮሙ ፡ ዅሎ ፡ ገድሎ ፡ ለአባ፡ዕብሎይ፡ኖላዌ፡አባግዕ፡ወእሙንቱ፡ ይንግሩ ፡ ለካልአን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተስፋ ፡ ለእለ ፡ ወድቁ ፡ በኃጢአት ፡ ከመ ፡ ኢይም ትሩ፡ተስፋ፡እምሕረተ፡እግዚአብሔር።

፳፮፡ ወበሳኒታ ፡ በጽሑ ፡ ፫ቱ ፡ ዕደው ፡ ውእቱኒ ፡ ነገሮሙ ፡ ገድሎ ፡ ለአባ ፡ ዕብሎይ ፡ ኖላዌ ፡ አባግዕ ፡ ወእሉ ፡ አንከሩ ፡ ጥቀ ፡ ወጸሐፍዎ ፡ ወነበሩ ፡ ኀቤሁ ፡ ለገዳማዊ ፡ እስከ፡ ሠሉስ ፡ ዕለት ፡ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ ገዳማዊ ፡ ወጸለየ ፡ ወመጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአ ብሔር፡ወመጽኡ፡እሉ፡ክልኤቱ፡አናብስት፡ ወከረዩ ፡ሎቱ ፡ መቃብረ ፡ ወቀበርዎ ፡ ከመ ፡ ሰብእ፡ወሖሩ፡ምስለ፡እሉ፡ሠለስቱ፡ዕደው፡ ወመርሕዎሙ ፡ እስከ ፡ አብጽሕዎሙ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ፡ኀበ፡ደብረ፡አባ፡መቃርስ፡ ወነገርዎሙ እሉ ፡ ዕደው ፡ ዅሎ ፡ ዘኮነ ፡ ለመነ ኰሳት፡ ወእሙንቱ ፡ አንከሩ ፡ ጥቀ ፡ ወእሉ ፡ ጸሐፉ ፡ ገድሎ ፡ ለአባ ፡ እብሎይ ፡ ኖላዌ ፡ አባግዕ ፡ ወኮኑ ፡ ወትረ ፡ ዘያነብብዎ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ።

የሚበልጥ፡ የሽቱ ፡ መዓዛ ፡ ሸተተ ፡ ገዳማ ዊምም ፡ ወንድሜ ፡ ዕብሎይ ፡ ና ፡ በውኃ ፡ ታጠብ፡ደስ፡ይበልህም፡በዚች፡ሰዓት፡ከተቀ በልከው ፡ መከራ ፡ ታርፋለህና ፡ አለው ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ለሁለቱም ፡ ቍርባኑን ፡ አቀበ ላቸው፡አባ፡ዕብሎይም፡አረፈ፡መላእክትም፡ ነፍሱን፡ተሸክመው፡እስከ፡አርያም፡በረሩ።

፳፬፡ ያ፡ገዳማዊም፡እኔ፡ሽማግሌ፡ነኝ፡ሥጋውን፡ መሸከም ፡ አልችል ፡ የምቆፍርበትም ፡ የሌለኝ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚያስብ ፡ ሆነ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ አንበሶች ፡ መጥተው ፡ ለሥጋው ፡ ሰገዱ ፡ መቃብሩንም ፡ ቆፍረው ፡ ሥጋውን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ተሸክመው፡ ወስደው ፡ ቀበሩት፡ገዳማዊውንም፡እጅ፡ነሱት፡እርሱም፡ ባረካቸውና፡በሰላም፡ሔዱ።

፳፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ገዳማዊ ፡ የሚቀብረኝ ፡ አገኝ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡ ወደርሱም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ መጣ ፡ አትዘን ፡ ሥጋህን ፡ እኔ ፡ አስቀብራለሁ ፡ ያለ ፡ ሦስት ፡ ቀንም ፡ አልቀረህም ፡ ወዳንተም ፡ ሦስት ፡ ሰዎችን ፡ እልካለሁ ፡ የበግ ፡ ጠባቂው ፡ የአባ ፡ እብሎይን ፡ ገድል ፡ ንገራቸው ፡ እነርሱም ፡ ለሌሎች፡ይንገሩ፡ከእግዚአብሔር፡ምሕረት፡ ተስፋ ፡ እንዳይቆርጡ ፡ በኃጢአት ፡ ለወደቁ ፡ አለኝታ፡ይሆን፡ዘንድ።

፳፮፡ በማግሥቱም ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ መጡ ፡ እርሱም፡የበግ፡ጠባቂውን፡የአባ፡ዕብሎይን፡ ተጋድሎ ፡ ነገራቸው ፡ እነርሱም ፡ እጅግ ፡ አድንቀው ፡ ጻፉት ፡ ከገዳማዊውም ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ፡ገዳማዊው፡ተነሥቶ፡ጸለየ፡ነፍሱንም፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ሰጠ ፡ እነዚያ ፡ ሁለት ፡ አንበሶችም ፡ መጡ ፡ መቃብርንም ፡ ቆፍረው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ወስደው ፡ ቀበሩትና ፡ ከእነዚያ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ተጓዙ ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ እስከሚአደር ሷቸው ፡ መርተው ፡ ወሰዱአቸው ፡ ሰዎቹም ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለመነኰሳቱ ፡ ነገሩአቸው ። እነርሱም ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡ የበግ ፡ አርቢው ፡ የአባ ፡ ዕብሎይን ፡ ገድል ፡ ጻፉ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ በእሑድ ፡ ዕለት ፡ የሚያነቡት ፡ ሆኑ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፳፯፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡በቅዱሳን፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለዕብሎይ።አመ፡ሰይጣን፡አእቀፎ።እንተ፡ኢተገብረ፡ገብረ፡እምኃጢአት፡ዘተርፎ።እምድንጋፄ፡ዝንቱ፡ነገር፡አባግዒሁ፡ገዲፎ። ሶበ፡ነስሐ፡ወጸለየ፡እግዚአብሔር፡ ተወክፎ።እስከ፡አናብስት፡ከረዩ፡ለበድኑ፡ምዕራፎ።

***

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፩ አምላክ፡ አመ፡፮ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ ዕርገተ ፡ ሥጋሁ ፡ እምባሕር ፡ ለቅዱስ ፡አብ ፡ አቡሊዲስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ ሮሜ ፡ መምህረ፡ኵሉ፡ዓለም።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ክቡር ፡ ወማእምር ፡ ፍጹም፡ ወኅረዮ ፡እግዚአብሔር፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ እምድኅረ ፡ አብ፡ አውክዮስ ፡ ዝንቱኒ ፡ በቀዳሚ ፡ ዓመት ፡ እምዘተሠይመ ፡ ከላድያኑ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በሀገረ፡ እስክንድርያ ፡ ወኮነ ፡ ዘይሜህሮሙ ፡ ለሕዝብ፡ ወየዐቅቦሙ ፡ እምግዕዞሙ ፡ ለአረማውያን ፡ ወያጸንዖሙ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ስብሐት።

፫፤ ወተሰምዐ፡ዜናሁ፡በኀበ፡ንጉሥ፡ከላድያኖስ፡ ከሀዲ ፡ ወአኀዞ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሊዲስ፡ ወኰነኖ ፡ በብዙኅ ፡ መቅሠፍት ፡ ወበዝብጠት፡ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ እምኰንኖቱ ፡ አሠረ ፡ ውስተ ፡ እገሪሁ ፡ ዕብነ ፡ ዐቢየ ፡ ወአስጠሞ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ዕሙቅ ፡ አመ ፫ ለየካቲት ። ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሳኒታሁ ፡ አመ ፡ ፮ለየካቲት ፡ ተረክበ ፡ ሥጋሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ እንዘ ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፡ ወዕብን ፡ ውስተ ፡ እገሪሁ ፡ እሡር ፡ ወነሥአ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ምእመን ፡ ወአንበሮ ፡ በኀቤሁ ፡ ወገነንዞ ፡ በአልባስ ፡ ክቡራት ። ወኀብአ ፡ ወተሰምዐ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ውስተ ፡ ኵሎን ፡ አህጉራተ ፡ ሮሜ ፡ ወኃሠሦ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ያውዕዮ ፡ በእሳት ፡ ባሕቱ ፡ ኢረከቦ ፡ አስመ ፡ ኀብአ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ።

***

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ስም ፡ የካቲት ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ መምህር ፡ የሆነ ፡ የሮሜ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ አቡሊዲስ ፡ ሥጋው ፡ ከባሕር ፡ የወጣበት ፡ ነው።

፪፤ ይህም ፡ የከበረ ፡ በእውቀቱም ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ከአባት ፡ አውክዮስም ፡ በኋላ ፡ ለሮም ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ መንፈስቅዱስ ፡ መረጠው ፡ ይህም ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከላድያኑ ፡ በተሾመባት ፡ በመጀመሪያ ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ሕዝቡንም ፡ ከአረማውያን ፡ ጠባይ ፡ የሚጠብቃቸው ፡ የሚያስተምራቸውና ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያጸናቸው ፡ ሆነ።.

፫፤ በከሀዲውም ፡ ንጉሥ ፡ በከላድያኖስ ፡ ዘንድ ፡ ዜናው ፡ ተሰማ ፡ ይህንንም ፡ የከበረ ፡ አቡሊዲስን ፡ ይዞ ፡ በብዙ ፡ ግርፋትና ፡ ድብደባ ፡ አሠቃየው ፡ ማሠቃየቱንም ፡ በሰለቸ ፡ ጊዜ ፡ በእግሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ደንጊያ ፡ አሥሮ ፡ ከጥልቅ ፡ ባሕር ፡ የካቲት ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ አሰጠመው ። ማግሥትም ፡ ሲሆን ፡ የካቲት ፡ ስድስት ፡ በዛሬዋ ፡ ቀን ፡ የዚህ ፡ አባት ፡ ሥጋው ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ ተንሳፎ ፡ ተገኘ ፡ ደንጊያውም ፡ በእግሮቹ ፡ ውስጥ ፡ እንደታሠረ ፡ ነበር ፡ አንድ ፡ ምእመን ፡ ሰው ፡ ወስዶ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ አኖረው ፡ በከበሩ ፡ ልብሶችም ፡ገንዞ ፡ ሠወረው፡ ወሬውም ፡ በሮሜ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ተሰማ ፡ ንጉሡም ፡ ሊአቃጥለው ፡ ፈልጎት ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አላገኘውም ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ሠውሮታልና።

www.ethiopianorthodox.org

፬፤ ወደረሰ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ ድርሳናተ ፡ ብዙኃተ ፡ ቦ ፡ እምኔሆን ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወተሠግዎቱ ፡ ለቃል ፡ ወከዊኖቱ ፡ አሐደ ፡ ጠባይዐ ፡ በኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ወቦ ፡ ዓዲ ፡ ተግሣጻት ፡ ወትም ህታት፡ በእንተ ፡ ገቢረ ፡ ሠምረቱ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ወሠርዐ ፡ ቀኖና ፡ ሠላሳ ፡ ወሰመንተ ፡ በእንተ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእሉ ፡ ይትረከቡ ፡ ውስተ ፡ ኵሎን ፡ አብያተ ፡ ክርስ ቲያን።

፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፬፤ ይህም፡የከበረ፡አባት፡ስለ፡ቀናች፡ሃይማኖት፡ ብዙ፡ ድርሳናትን፡ደርሶአል፡ከእርሳቸውም፡ ስለ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ሰው ፡ መሆንና ፡ ከኃጢ አት፡በቀር፡በሥራው፡ሁሉ፡አንድ፡ባሕርይ፡ ስለ፡መሆኑ፡የደረሰው፡አለ።ዳግመኛም፡ እግ ዚአብሔር የሚወደውን፡ስለ፡መሥራት፡የደ ረሳቸው ፡ ተግሣጻትና ፡ ትምህርቶች ፡ አሉ ፡ ስለ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሕግ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት፡መመሪያዎችን፡ሠርቷል፡እሊህም፡ በሁሉ፡አብያተ፡ክርስቲያን፡ይገኛሉ።

፭፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ዕርገተ ፡ ሥጋሁ ፡ እምባሕር ። እንዘ ፡ ዕብን ፡ ክቡድ ፡ ውስተ ፡ እገሪሁ ፡ እሡር ። አቡሊዲስ፡ሊቅ፡ ዘበትውልዱ ፡ ማእምር ። ያምጽእ ፡ ሊተ ፡ በረከተ ፡ እምነ ፡ ገሪዛን ፡ ደብር ። ከመ ፡ ንዋየ ፡ ክብር፡ወብዕል፡ያመጽእ፡ሐመር።

፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱሳን ፡ አቡቂር፡ወዮሐንስ፡ወሠላስ፡ደናግል፡ምስለ፡ እሞን ፡ አትናስያ ። ወአስማቲሆን ፡ ለእላ ፡ ቴዎድራ ፡ ዘትርጓሜሁ ፡ ሀብተ ፡ እግዚአ ብሔር፡ወለካልዕታ፡ቴዎፍና፡ዘትርጓሜሁ፡ ሃይማኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ወሣልሲት ፡ ቴዎ ዶክስያ ፡ ዘትርጓሜሁ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወእሞን ፡ አትናስያ ፡ ዘትርጓሜሁ ፡ ሕይወት።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡቂር ፡ መነኮስ ፡ እምንእሱ፡ ጽሙድ ፡ በገድል ፡ ወቅዱስ ፡ ዮሐ ንስ ፡ ሐራ ፡ ውእቱ ፡ እምሠራዊተ ፡ ንጉሥ ፡ ወእሙንቱ ፡ እምሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወየኀ ድሩ ፡ በሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወተአመኑ ፡ በእግ ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ምስለ ፡ እላ ፡ ደናግል ፡ ወእሞን ፡ አትናስያ ፡ በቅድመ ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ውእቱኒ ፡ ተሰአለ ፡ ከመ ፡ እምአይቴ ፡ እሙንቱ ፡ ወሶበ ፡ ጠየቀ ፡ እምሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ እሙንቱ ፡ አዘዘ፡ይሰድዎሙ፡ህየ።

፫፤ ወሶበ ፡ በጽሑ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ቆሙ ፡ ቅድመ ፡ መኰንን ፡ ወተአመኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ መኰ ንንኒ፡ኰነኖሙ፡ኵነኔ፡ዐቢየ፡ወሶበ፡ደክመ፡

፩፤ በዚችም፡ዕለት ፡የከበሩ፡አቡቂርና፡ዮሐንስ፡ ሦስት፡ደናግልም፡ከእናታቸው፡ከአትናስያ፡ ጋር ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ። የእሊህም ፡ ስማ ቸው ፡ ቴዎድራ ፡ ትራጓሜው ፡ የእግዚአ ብሔር፡ስጦታ ፡ ነው ፡ ሁለተኛዋ ፡ ቴዎፍና ፡ ትርጓሜውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ሃይማኖት ፡ ሦስተኛይቱም፡ቴዎዶክስያ፡ትርጓሜውም፡ የእግዚአብሔር ፡ምስጋና ፡ የእናታቸውም ፡ አትናስያ፡ትርጓሜው፡ሕይወት፡የሆነ፡ነው።

፪፤ ይህም፡የከበረ፡አቡቂር፡ከታናሽነቱ፡በገድል፡ ተጠምዶ፡የሚኖር፡መነኰስ፡ነው፡የከበረ፡ ዮሐንስ፡ግን፡ከንጉሥ፡ሠራዊት፡ውስጥ፡ ወታደር፡ነበር፡የእነርሱም፡ሀገራቸው፡እስክ ንድርያ ፡ ሲሆን ፡ የሚኖሩት ፡ በአንጾኪያ ፡ ነው፡ በንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስም ፡ ፊት ፡ ቆመው፡ከእሊህ፡ደናግል፡ከእናታቸው፡ከአ ትናስያም፡ጋር፡በክብር፡ባለቤት፡በጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታመኑ ። እርሱም ፡ ከወዴት፡እንደሆኑ፡ጠየቀ፡ከእስክንድርያ፡ አገር፡እንደሆኑ፡በተረዳ፡ጊዜ፡ወደዚያ፡ይወ ስዷቸው፡ዘንድ፡አዘዘ።

፫፤ ወደ፡እስክንድርያ፡በደረሱ፡ጊዜ፡በመኰንኑ፡ ፊት፡ቆመው፡በክብር፡ባለቤት፡በጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ታመኑ ፡ መኰንኑም ፡ ጽኑዕ ፡ ሥቃይን ፡ አሠቃያቸው ፡ ማሠቃ

www.ethiopianorthodox.org

እምኰንኖቶሙ ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ አርእስ
ቲሆሙ ፡ በሰይፍ ፡ ወኮነት ፡ ቅድስት ፡
አትናስያ፡ ዘታጸንዖን ፡ ወታስተዔግሦን ፡ ለአ
ዋልዲሃ ፡ ደናግል ፡ ወታጤይቆን ፡ ከመ ፡
እማንቱ ፡ ይከውና ፡ መራዕያቲሁ ፡ ለመርዓዊ ፡
ክርስቶስ ፡ ሰማያዊ ፡ ለእመ ፡ ኮና ፡ ሰማዕተ ፡
በእንተ ፡ ስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ወከማሁ ፡ ቅዱስ ፡
አቡቂር ፡ ኮነ ፡ ይከሥት ፡ ሎን ፡ ዘበጽሐ ፡
ምንዳቤ፡ላዕለ፡ቅድስት፡ቴክላ፡ሐዋርያዊት፡
ወያጸንዖን።

፱፤ ወኮኑ ፡ ሐራ ፡ ያቄርብዎን ፡ ለደናግል ፡ ለለ
አሐቲ፡ እምድኅረ ፡ አሐቲ ፡ ለበዓለ ፡ ሰይፍ ፡
ወእምዝ ፡ መተርዋ ፡ ለእሞን ፡ ወለቅዱሳን ፡
አቡቂር ፡ ወዮሐንስ ፡ ወአዘዘ ፡ መኰንን ፡
ይግድፉ፡ሥጋሆሙ፡ለአራዊት፡ወለአዕዋፍ፡
ወመሃይምናን፡ነሥኡ፡ሥጋሆሙ፡በኅቡእ፡
ወገነዝዎሙ ፡ በክብር ፡ ወአንበርዎሙ ፡
ውስተ፡ሣፁን፡ወኀብእዎሙ፡እስከ፡የኀልፍ፡
መዋዕለ፡ ምንዳቤ ፡ ወእምዝ ፡ ተሐንፀት ፡
ሎሙ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአንበሩ ፡ ሥጋ
ሆሙ ፡ ውስቴታ ፡ ወኮና ፡ እምኔሆሙ ፡
ተአምራት ፡ ወመንክራት፡ ዐበይት ። ወበረ
ከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚ
አብሔር፡ አሜን።

የትንም፡በደከመ፡ጊዜ፡ራሶቻቸውን፡በሰይፍ፡
እንዲቆርጡ ፡ አዘዘ ፡ የከበረች ፡ አትናስያም ፡
ደናግል፡ ልጆቿን ፡ በከበረ ፡ ስሙ ፡ ምስክር ፡
ሁነው፡ከሞቱ፡ለሰማያዊ፡ሙሽራ፡ክርስቶስ፡
እነርሱ፡ሙሽሮቹ፡እንደሚሆኑ፡በማስረዳት፡
ታጸናቸውና ፡ ታስታግሣቸው ፡ ነበር ፡ እንዲ
ሁም ፡ የከበረ ፡ አቡቂር ፡ በከበረች ፡ ሐዋር
ያዊት፡ቴክላ፡ላይ፡የደረሰውን፡መከራ፡ይገል
ጥላቸውና፡ያጸናቸው፡ነበር።

፱፤ ወታደሮችም ፡ ለባለ ፡ ሰይፍ ፡ በማከታተል ፡
አንዲቱን ፡ ከአንዲቱ ፡ በኋላ ፡ የሚያቀርቡ ፡
ሆኑ ፡ ከዚያም ፡ እናታቸውን ፡ የከበሩ ፡ አቡ
ቂርና ፡ ዮሐንስንም ፡ ቆረጡ ፡ መኰንኑም ፡
ሥጋቸውን፡ለአራዊትና፡ለአዕዋፍ፡ይጥሉ፡
ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ምእመናንም ፡ ሥጋቸውን ፡
በሥውር ፡ ወሰዱ ፡ በክብርም ፡ ገነዙአቸው ፡
የመከራውም፡ዘመን፡እስቲያልፍ፡በሣጥን፡
አድርገው ፡ ሠወሩአቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠርቶላቸው ፡ ሥጋቸ
ውን፡ በውስጧ ፡ አኖሩ ፡ ከእርሳቸውም ፡
ታላላቅ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶች ፡ ተገለጡ ።
በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአ
ብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ ጽዱላነ፡ልብ፡እምጕህልያ። አቡቂር፡ወዮሐንስ፡ዘእስክንድርያ። ዘምስለ፡ሠላስ፡ ደናግል፡ወእሞን፡አትናስያ። ከመ፡አባግዕ፡እስከ፡በመጥባሕት፡ተወቅያ። ውስተ፡ጺዖተ፡ስምዕ፡ኅቡረ፡ ተርዕያ።

፲፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ ተዝካረ፡ዕረፍታ፡ለማርያም፡
ዘቀብዓቶ ፡ ዕፍረተ ፡ ለእግዚእነ፡ ወዛቲ ፡
ቅድስት፡ቀዳሚ፡ኃጥእት፡ዘፈጸመት፡ኵሎ፡
መንበርታ፡በዝሙት።

፲፩፤ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ኮነት ፡ ዘትሠረገው ፡
በዘዚአሁ፡ ሥርጋዌ ፡ ከመ ፡ ትጼውዎሙ ፡
ኀቤሃ፡ለወራዙት።

፲፪፤ ወአሐተ፡ዕለተ፡ተሠርገወት፡በከመ፡ልማዳ፡
ወተቀብዐት ፡ አፈወ ፡ ወርእየት ፡ ገጻ ፡
በመጽሔት፡ወአደማ፡ቂሐተ፡መላትሒሃ፡
ወላሕያ፡ወጸዳለ፡አዕይንቲሃ፡ ወጕንደየት ፡
መጠነ ፡ አሐቲ ፡ ሰዓት፡ እንዘ፡ ታነክር ፡
ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ ላዕሌሃ፡ ሕሊና፡ ሠናይ ፡

፲፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ጌታን ፡ ሽቱ ፡ ለቀባችው ፡
ማርያም ፡ የዕረፍቷ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡
ይችም፡ ቅድስት ፡ አስቀድማ ፡ ኑሮዋን ፡
በዝሙት፡ያሳለፈች፡ኃጢአተኛ፡ነበረች።

፲፩፤ እርሷም ፡ ጐልማሶችን ፡ ወደርሷ ፡ ትማር
ካቸው፡ ዘንድ ፡ በየራሱ ፡ በሆነ ፡ ሽልማትና፡
ጌጥ፡ትሸለም፡ነበር።

፲፪፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ እንደ ፡ ልማድዋ ፡
ተሸልማ፡አጊጣ፡ሽቱም፡ተቀብታ፡ፊቷን፡
በመስታዋት፡ተመለከተች፡የጉንጯ፡ቅላ
ትና ፡ ደም ፡ ግባቷ ፡ የዓይኗም፡ ወገግታና ፡
ጥራት ፡ ማማሩን ፡ አይታ ፡ እያደነቀች ፡
አንድ፡ሰዓት፡ያህል፡ቆየች፡ከዚህም፡በኋላ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወተዘከረት ፡ ሞተ ፡ ወኅልፈተ ፡ ዓለም ። ወሰሚዓ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይትዌከፍ፡ኃጥአነ፡ወይሰሪ፡አበሳ፡ነሥአት፡ ንዋያ፡ወተሣየጠት፡ቦቱ፡ዕፍረተ፡ዘአልባስ ጥሮስ፡ወሖረት፡ኀበ፡እግዚእነ፡እንዘ፡ሀሎ፡ ይረፍቅ፡በቤተ፡ስምዖን፡ዘለምጽ።

፲፫፡ ወሰገደት ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወቀብዓቶ ፡ ውእተ ፡ ዕፍረተ ፡ ወኀፀበት ፡ እገሪሁ ፡ በአንብዓ፡ወመዝመዘቶ፡በሥዕርተ፡ርእሳ፡ ወርእዮ ፡ እግዚእነ ፡ አፍቅሮታ ፡ ብዙኀ ፡ ኀደገ፡ ላቲ ፡ ኃጢአታ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይዝክሩ፡ ዘንተ ፡ ዘገብረት ፡ ኀበ ፡ ተሰብከ ፡ ወንጌለ ፡ መንግሥት። ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን።

በኃ፡ኀሳብ፡በላይዋ፡መጣ፡ሞትንና፡የዚህን፡ ዓለም ፡ ማለፍ ፡ አሰበች ። የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ኃጢአተኞችን ፡ እንደ ሚቀበልና ፡ ኃጢአትንም ፡ እንደሚአስተ ሰርይ፡ ሰምታ ፡ ገንዘቧን ፡ ወስዳ ፡ የአልባስጥ ሮስን፡ሽቱ፡ገዝታ፡በስምዖን፡ዘለምጽ፡ቤት፡ ለምሳ፡ተቀምጦ፡ሳለ፡ወደ፡ጌታችን፡ሔደች።

፲፫፡ ከእግሩ ፡ በታችም ፡ ሰግዳ ፡ ያንን ፡ ሽቱ ፡ ቀባችው ፡ እግሮቹን ፡ በዕንባዋ ፡ አጠበ ችውና፡ በራስዋ ፡ ጠጕር ፡ ወለወለችው ፡ ጌታችንም ፡ የፍቅርዋን ፡ ጽናት ፡ አይቶ ፡ ኃጢአቷን፡በደሏን፡ተወላት፡የመንግሥት፡ ወንጌልም ፡ በሚሰበክበት ፡ ይህን፡ ያደረገ ችውን፡እንዲአስቡ፡አዘዘ።በረከቷም፡ከኛ፡ ጋር ፡ ይኑር፡ ለእግዚአብሔርም ፡ምስጋና ፡ ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለማርያም፡በአንብዓ፡ዘተኀፅቡ።አእጋረ፡ክርስቶስ፡ርሱናት፡ለብርተ፡ሊባኖስ፡አምሳለ፡ ላህቡ።ወበእንተዝ፡አዘዘ፡እንዘ፡ይብል፡በቃለ፡ጥበቡ።ኀበ፡ተሰብከ፡ወንጌልየ፡ለዓለም፡በመክብቡ። ዛቲ፡ብእሲት፡ዘገብረት፡ያንብቡ።

***

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፯ ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡ አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡አባ፡እለእስክንድሮስ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡ወውእቱ፡ እምኍልቆሙ፡ለአበው፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፵ወ ፫ቱ።

፪፡ ወዝንቱ፡አብ፡መንኰሰ፡በደብረ፡ታሮን፡ዘበ ትርጓሜሁ፡ደብረ፡አበው፡ወበሥምረቱ፡ለእ ግዚእነ፡ተሠይመ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ላዕለ፡ሀገረ፡ እስክንድርያ፡እስመ፡ውእቱ፡ጻድቅ፡ወማእ ምር።

፫፡ ወበጽሐ፡ምንዳቤ፡ብዙኀ፡በመዋዕለ፡ሢመቱ፡ እስመ ፡ ንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ ሤሞ ፡ ለወልዱ ፡ ህየንቴሁ፡ላዕለ፡መንግሥቱ፡ወአሠልጠኖ፡ ወውእቱ፡አመዝበሮሙ፡ለአድባረ፡መነኰ ሳት፡ዘገዳመ፡አስቄጥስ፡ወእምብዝኀ፡እከዩ፡ ወዕልወቱ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ደብር፡ ዘመንገለ ፡ ሰሜን ፡ ምስር ፡ ወርእየ ፡ በህየ ፡ ሥዕላ፡ ለእግዝእትነ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወይእቲ ፡ ሥር ጉት፡ወዲበ፡አልባሲሃ፡ሐሪር፡ሠናይ፡ወይቤ፡ ምንት፡ይእቲ፡ዛቲ፡ወይቤልዎ፡ሥዕላ፡ለእግ

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሰባት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የእስክንድርያ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ እለእስክንድሮስ ፡ አረፈ፡እርሱም፡ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ አርባ፡ሦስተኛ፡ነው።

፪፡ ይህም ፡ አባት ፡ ታሮን ፡ በሚባል ፡ ገዳም ፡ መነኰሰ ፡ ትርጓሜውም ፡ የአባቶች ፡ ገዳም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በጌታችንም ፡ ፈቃድ ፡ በእስክን ድርያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ፡ እርሱ፡የተማረ፡አዋቂ፡ጻድቅ፡ሰው፡ነበረና።

፫፡ በሹመቱ፡ወራትም፡ብዙ፡መከራ፡ደረሰበት፡ የግብጽ፡ንጉሥ፡ልጁን፡ሹሞ፡በመንግሥቱ፡ ላይ ፡ አሠለጠነው ፡ እርሱም፡ በአስቄጥስ ፡ በረሀ፡ያለውን፡የመነኰሳቱን፡ገዳማት፡አፈረ ሳቸው።ከክፋቱና፡ከክህደቱ፡ብዛት፡የተነሣ፡ ከምስር፡በስተሰሜን፡ወዳለች፡ገዳም፡ገብቶ፡ በዚያ ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ የእመቤታ ችንን፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ሥዕሏን ፡ አየና ፡ ይች ፡ ምንድን ፡ ናት ፡ አለ ፡ እርሷም ፡ በሽልማት ፡ ሁሉ ፡ የተሸለመችና ፡ ያጌጠች ፡ ናት ፡ በልብሶቿም ፡ ላይ ፡ ያማረ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዝእትን፡ድንግል፡ማርያም፡እሙ፡ለክርስቶስ፡
ጸረፈ፡ላዕሌሃ፡ወተፍዐ፡ምራቀ፡ርኵሰ፡ውስተ፡
ገጸ ፡ ወይቤ ፡ ለእመ ፡ ኮንኩ ፡ ሕያወ ፡ እደመ
ስሶሙ፡ ለክርስቲያን ፡ ወአጠፍኦሙ ፡ ወጸረፈ ፡
ካዕበ ፡ ላዕለ ፡ እግዚእነ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብ
ሐት።

፬፤ ወሶበ ፡ ሌሊተ ፡ ኮነ ፡ ርእየ ፡ በንዋሙ ፡ ራእየ ፡
ግሩመ ፡ ወመደንግፀ ፡ ዐቢየ ፡ ወጊዜ ፡ ጽባሕ፡
ነገሮ ፡ ለአቡሁ ፡ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ በዛቲ ፡
ሌሊት ፡ በጽሐኒ ፡ ምንዳቤ ፡ ዐቢይ ፡ ወኵነኔ ፡
ብዙኅ ፡ ወርኢኩ ፡ ብእሴ ፡ ዘይነብር ፡ ዲበ ፡
መንበር ፡ ዐቢይ ፡ ወውእቱ ፡ መፍርህ ፡ ወመን
ደግፅ ፡ ወግሩም ፡ ፈድፋደ ፡ ገጹኒ ፡ ብሩህ ፡
ዘይበርህ ፡ እምፀሐይ ፡ ወየዐውድዎ ፡ አእላፈ፡
አእላፋት፡እንዘ፡ይፀውሩ፡ንዋየ፡ሀቅል፡ወኮነ፡
አንተ ፡ ወአነ ፡ እሡራነ ፡ በድኅሬሁ ፡ ወተሰ
አልኩ ፡ አነ፡ ወእቤ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡
ዘላዕለ ፡ መንበር ፡ ወይቤሉኒ ፡ ዝንቱ፡ ውእቱ ፡
ክርስቶስ፡ ንጉሠ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘአንተ ፡ ተሣ
ለቀ ፡ ላዕሌሁ ፡ ትማልም ፡ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡
ኀቤየ ፡ እምእለ ፡ ይፀውሩ፡ ንዋየ ፡ሀቅል ፡ ፩ዱ
ወረገዘኒ ፡ ገቦየ ፡ በኲናት ፡ ወኢያውጽኦ ፡
ለኲናት ፡ እምገቦየ። ወሰሚዖ፡ አቡሁ፡ ደንገፀ፡
ወኀዘነ ፡ ጥቀ ፡ ወሐመ ፡ በጊዜሃ ፡ ውእቱ ፡
ወልዱ ፡ ወብሕመ ፡ ልሳኑ ፡ ወሞተ ፡ በእኩይ ፡
ሞት ፡ ወእምድኅረ ፡ ፵ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ሞተ ፡
አቡሁ።

፭፤ ወተሠይመ ፡ ካልዕ ፡ ንጉሥ ፡ ህየንቴሁ ፡
ውእቱኒ ፡ አመንደቦሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ ፈድ
ፋደ ፡ ወአኀዞ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ እለእስክን
ድሮስ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወአመንዶቦ ፡ ብዙኀ ፡
እስከ ፡ ሰአለ ፡ እምሕዝቡ ፡ ፴ ፻ተ ፡ ዲናረ ፡
ወርቅ፡ወወሀቦ፡ኪያሁ፡ወአጥፍአ፡እግዚእነ፡
ለውእቱ፡ንጉሥ፡ፍጡነ።

፮፤ ወእምዝ ፡ ተሠይመ ፡ ናሁ ፡ ካልዕ ፡ ንጉሥ ፡
ውእቱኒ፡አኀዞ፡ለሊቀ፡ጳጳሳት፡ወኃሠሠ፡፴፻ተ፡
ዲናረ፡ ወርቅ ፡ ከመ ፡ ቀዲሙ ፡ ወዝንቱ ፡ አብ፡
ሰአሎ ፡ ወይቤሎ ፡ ተዓገሠኒ ፡ እስከ ፡ እስእል፡
እምእሊአየ ፡ ንጉሥኒ ፡ ወሀቦ ፡ ዕድሜ ፡
ወሶቤሃ፡ ዐርገ፡ ኀበ ፡ ላዕላይ ፡ ግብጽ፡ ከመ ፡
ይስአል።

የሐር ፡ ልብስ ፡ ነበረ ፡ ሰዎችም ፡ የክርስቶስ ፡
እናት ፡ የሆነች ፡ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡
**ማርያም** ፡ ሥዕል ፡ ናት ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡
ተሳድቦ ፡ የረከሰ ፡ ምራቁን ፡ በፊቷ ፡ ላይ ፡
ተፍቶ፡ ደኅና ፡ ከሆንኩ ፡ ክርስቲያኖችን ፡
ፈጽሜ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ አለ ፡ ዳግመኛም ፡
በክብር፡ባለቤት፡በጌታችን፡ክርስቶስ፡ላይ፡
የስድብ፡ቃልን፡ተናገረ።

፬፤ ሌሊትም፡በሆነ፡ጊዜ፡የሚያስፈራና፡የሚያስ
ደነግጥ፡ታላቅ፡ራእይን፡አየ፡በነጋም፡ጊዜ፡
ለአባቱ፡እንዲህ፡ብሎ፡ነገረው፡ዛሬ፡በዚች፡
ሌሊት ፡ ታላቅ ፡ መከራና ፡ ብዙ ፡ ቅጣት ፡
ደረሰብኝ፡ ታላቅ ፡ ዙፋንንም ፡ አየሁ፡ በላዩ ፡
የተቀመጠበት ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡
የሚያስደነግጥ ፡ ነው ፡ ፊቱም፡ ከፀሐይ ፡ ይበ
ራል ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ሠራዊት ፡ የጦር ፡
መሣሪያ፡ ይዘው ፡ በዙሪያው ፡ ቁመው ፡ ነበር ፡
እኔና ፡ አንተም ፡ እሥረኞች ፡ ሁነን ፡ በኋላው ፡
ቁመን ፡ ነበር ፡ እኔም ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ የተቀ
መጠው ፡ ማነው ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁ ፡ ትላንት ፡
አንተ ፡ የዘበትክበት ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡
ክርስቶስ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አሉኝ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ከተሸከሙት ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ መጥቶ ፡ ጐኔን ፡ በጦር ፡ ወጋኝ ፡ ጦሩንም ፡
ከጐኔ ፡ ውስጥ ፡ አላወጣውም ። አባቱም ፡
ሰምቶ ፡ ደነገጠ ፡ እጅግም ፡ አዘነ ፡ ያ ፡ ልጁም፡
ወዲያውኑ ፡ ታመመ ፡ አንደበቱም ፡ ተዘግቶ ፡
በክፉ ፡ አሟሟት ፡ ሞተ ። ዳግመኛም ፡ ከአርባ ፡
ቀን ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ ሞተ።

፭፤ በርሱም ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ተሾመ ፡ እር
ሱም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እጅግ ፡ አሠቃያቸው ፡
ይህንንም ፡ አባት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እለእስክንድ
ሮስን ፡ አብዝቶ ፡ አሠቃየው ፡ ከሕዝቡ ፡ ሦስት ፡
ሺህ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ለምኖ ፡ እስከ ፡ ሰጠው ፡
ድረስ ፡ ጌታችንም ፡ ይህን ፡ ንጉሥ ፡ ፈጥኖ ፡
አጠፋው።

፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አሁንም ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ተሾመ ፡
እርሱም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱን፡ ይዞ፡ እንደ፡ ቀድ
ሞው ፡ ሦስት ፡ ሺህ፡ የወርቅ ፡ ዲናር፡ እንዲ
ሰጠው ፡ ፈለገ ፡ እርሱም ፡ ከወገኖቹ ፡ እስከም
ለምን ፡ ታገሠኝ ፡ ብሎ ፡ ማለደው ፡ ንጉሡም ፡
ቀጠሮ ፡ ሰጠውና ፡ ይለምን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ወጣ።

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወሀሎ ፡ ፩ዱ፡ ብእሲ ፡ ገዳማዊ ፡ መልዕልተ ፡ ደብር ፡ ወምስሌሁ ፡ ፪ቱ ፡ አርድእቲሁ ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይኲስትሩ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ደብር ፡ ወረከቡ ፡ በሀየ ፡ ፫ተ ፡ ማኅበብታተ ፡ ምሉዓነ ፡ ወርቅ ፡ ወነብኡ ፡ ፩ደ ፡ ማኅበብተ ፡ ወርቅ ፡ ወ፬ተ ፡ አምጽኡ ፡ ኀበ ፡ ገዳማዊ ፡ መምህሮሙ ፡ ውእቱኒ ፡ ፈነዎሙ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ ከመ ፡ የሀብዎ ፡ እሎንተ ፡ ፬ተ፡ ማህበብታተ ፡ ወርቅ ፡ ከመ ፡ ይትረዳእ ፡ በሙ፡ እሙንቱሰ ፡ አርድእቱ ፡ ለገዳማዊ ፡ ነሥኡ ፡ ማኅበብታተ ፡ ወርቅ ፡ ወሖሩ ፡ ወገብኡ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወገደፉ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወአውሰቡ ፡ ብእሲተ ፡ ወተሣየጡ ፡ በውእቱ ፡ ወርቅ ፡ አግብርተ ፡ ወአእማተ ፡ ወእንስሳ ።

፰፤ ወመኰንነ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ አኀዞሙ ፡ ወሐተቶሙ ፡ ወቀሠፎሙ ፡ ከመ ፡ እምአይቴ፡ ረከቡ፡ ንዋየ ፡ ወአምኑ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ረከቡ ፡ ፫ተ፡ ማኅበብታተ ፡ ወርቅ ፡ ወመጠዎሙ ፡ መኰንን ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ሐራሁ፡ ውእቱኒ ፡ አብጽሖሙ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወአጠየቆ ፡ ከመ ፡ ረከቡ ፡ ማኅበብተ ፡ ወርቅ ፡ ፫ተ፡ ወፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ሐራሁ ፡ ወማህረከ ፡ ቤተ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወነሥአ ፡ ኵሎ ፡ ዘረከበ፡ እምንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ዘአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳትኒ ፡ ሞቅሖ ፡ ወይቤሎ ፡ አምጽእ ፡ ሊተ፡ ማኅበብተ ፡ ፬ተ ፡ ዘምሉዓነ ፡ ወርቀ ፡ ወ፴፻ተ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቤሎ ፡ አልብየ ፡ ምንትኒ ፡ እምንዋየ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም፡ ኃላፊ ፡ ወኢኀደጎ፡ እስከ ፡ ፈነወ ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወአምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ፴፻ተ ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ወወሀቦ ፡ ወአጥፍአ ፡ እግዚእነ ፡ ለዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡ እኩይ ።

፱፤ ወእምዝ ፡ ተሠይመ ፡ ካልዕ ፡ ንጉሥ ፡ ዘየአኪ፡ እምኔሁ ፡ ወአገበሮሙ ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን፡ ከመ ፡ ይኅትሙ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ፡ ስመ ፡ ነቢይ ፡ ሐሳዊ ፡ ወርኵሰ ፡ ህየንተ ፡ መስቀል ፡ ክቡር ፡ ወይእቲ ፡ ተእምርት ፡ ዘተነበየ ፡ በእንቲአሃ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ነባቢ ፡ መለኮት ፡ ወፈነወ ፡ ውእቱ፡ ንጉሥ ፡ እኩይ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡

፯፤ በተራራ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ገዳማዊ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አሉ ፡ በተራራውም ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ እንዲቆፍሩና ፡ እንዲጠርጉ ፡ አዘዛቸው፡ ወርቅን ፡ የተመላ ፡ አምስት ፡ ማሰሮ ፡ አገኙ ፡ አንዱን ፡ ሸሸገው ፡ አራቱን ፡ ወደ ፡ ገዳማዊ ፡ መምህራቸው ፡ አመጡ ፡ እርሱም ፡ ይረዳበት ፡ ዘንድ፡ እንዲሰጡት ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ላካቸው ። እነርሱ፡ ግን ፡ እነዚያን ፡ የወርቅ ፡ ማሰሮዎች ፡ ይዘው ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገቡ ፡ የምንኵስና፡ ልብሳቸውንም ፡ ጥለው ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፡ በዚያም ፡ ወርቅ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሮችን ፡ እንስሳትንም ፡ ገዙ ።

፰፤ የዚያቺም ፡ አገር ፡ አስተዳዳሪ ፡ ያዛቸው ፡ ገንዘብንም ፡ ከወዴት ፡ እንዳገኙ ፡ በመግረፍ፡ መረመራቸው ፡ እነርሱም ፡ አምስት ፡ የወርቅ፡ ማሰሮዎችን ፡ እንዳገኙ ፡ አመኑ ፡ መኰንኑም ፡ ለንጉሥ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ፡ አቀረባቸውና ፡ አምስት ፡ የወርቅ ፡ ማሰሮ ፡ እንዳገኙ ፡ አስረዳው ፡ ንጉሡም ፡ ጭፍሮቹን፡ ልኮ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ቤት ፡ በረበረ ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከሆነ ፡ ከንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱንም ፡ አሠረውና ፡ ወርቅን ፡ የተመሉ ፡ አራቱን ፡ ማሰሮዎች ፡ ደግሞም ፡ ሦስቱን ፡ ሽህ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ አምጣልኝ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የለኝም፡ አለው ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ልኮ ፡ ሦስቱን ፡ ሽህ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ አምጥተውለት ፡ እስከ ፡ ሰጠው ፡ ድረስ ፡ አልተወውም ፡ ይህንንም ፡ ክፉ ፡ ንጉሥ ፡ ጌታችን፡ አጠፋው ።

፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ የከፋ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ፡ ተሾመ ፡ እርሱም ፡ የሐሰተኛውንና ፡ የርኵሱን ፡ ነቢይ ፡ ስም ፡ በከበረ ፡ መስቀል ፡ ፈንታ ፡ በእጆቻቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዲአትሙ፡ የክርስቲያንን ፡ ወገኖች ፡ አስገደዳቸው ። ይችም ፡ ምልክት ፡ የመለኮትን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ የተናገራት ፡ ትንቢት ፡ ናት ፡ ይህም ፡ ክፉ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አህጉር ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ዘንተ ፡
ለሊቀ ፡ ጳጳሳትኒ ፡ አዘዞ ፡ ከማሁ ፡ ይግበር ፡
ወሰአሎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ስእለተ ፡ ብዙኀ ፡
ከመ፡ ይኅድጎ ፡ አበዮ ፡ ወካዕበ ፡ ሰአሎ ፡ ከመ፡
ይትዓገሦ ፡ እስከ ፡ ሠሉስ ፡ ዕለት ፡ ወእምዝ ፡
ዳግመ ፡ ሰአለ ፡ ወአስተብቍዐ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይግድፎ ፡ ወኢያግብኦ ፡
ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ርኩስ ፡ ወሰምዐ ፡
እግዚእነ ፡ ስእለቶ ፡ ወሐወጾ ፡ በደዌ ፡
ንስቲት፡ ወሰአሎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ለንጉሥ ፡
ከመ ፡ የአዝዝ ፡ ሎቱ ፡ ወይሑር ፡ ውስተ ፡
ቤቱ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወንጉሥ ፡ አበዮ ፡
እስመ ፡ መሰሎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይትመከነይ፡
በእንተ ፡ ኀትመተ ፡ እድ ። ወአስተርአዮ ፡
መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ወይቤሎ ፡ በሳኒታ ፡ ተዓርፍ ፡ ወይቤሎሙ ፡
ለአርድእቲሁ ፡ አስተዳልዉ ፡ ሐመረ ፡ እስመ ፡
በሳኒታ ፡ ይሔውጸኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአ
ዐርፍ ፡ ወአዕረፈ ፡ በሳኒታ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡
ወፆሩ ፡ ሥጋሁ ፡ በሐመር ፡ ወቀበርዎ ፡ ምስለ፡
ሥጋሆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት።

፲፤ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ እለእስክን
ድሮስ ፡ ኮነ ፡ ለመለካውያን ፡ እለ ፡ ብሔረ ፡
ግብጽ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘስሙ ፡ አንስጣ
ስዮስ፡ ወውእቱ ፡ ያፈቅሮሙ ፡ ለመሃይምናን፡
ያዕቆባውያን ፡ ወበእንተዝ ፡ ተጻብእዎ ፡
ሕዝበ ፡ ዚአሁ ፡ ወሐለየ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡
ያድኅን ፡ ነፍሶ ። ወመጽአ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡
አብ፡ እለእስክንድሮስ ፡ ወኮነ ፡ ታሕተ ፡
ትእዛዙ፡ ወእለእስክንድሮስኒ ፡ ሰአሎ ፡ ለአን
ስጣስዮስ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ህየንቴሁ ፡ ወይመግብ ፡ መርዔቶ ፡ ወኪያሁሰ ፡
ይኅድጎ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡
ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እመነኰሳት ፡ ወኢሠምረ ፡ አባ ፡
አንስጣስዮስ ፡ ወይቤ ፡ ለእመ ፡ ፈቀድኩ ፡
ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ አኮኑ ፡ አነ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አላ ፡ ፈቀድኩ ፡ እኩን ፡
ረድአከ ፡ ለከ ፡ ወእትለአከከ ፡ ወእምብዝኀ ፡
ስእለት ፡ ወተዋሥአ ፡ ዘኮነ ፡ ማዕከሌሆሙ ፡
ሠምረ ፡ አንስጣስዮስ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡
ወአንበሮ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ በሢመተ ፡
ኤጲስቆጶስና ፡ ወዐቀበ ፡ መርዔቶ ፡ በሠናይ ፡
በዘይደሉ ። ወአብ ፡ እለእስክንድሮስ ፡ ነበረ ፡

ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ እንዲአደርጉ ፡
አዘዛቸው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱንም ፡ እንዲሁ ፡
ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ። ሊቀ ፡ ጳጳሳትም ፡
ይተወው ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ለመነው ፡ አልተቀ
በለውም ፡ ዳግመኛም ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡
ይታገሠው ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፡ ከዚህም ፡
በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እንዳይጥለውና ፡ ወደዚህ ፡
ወደረከሰ ፡ ሥራ ፡ እንዳያስገባው ፡ ወደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ ማለደ ፡ ጌታችንም ፡፡
ልመናውን ፡ ተቀብሎ ፡ በጥቂት ፡ ደዌ ፡ ጐበ
ኘው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እስክንድርያ ፡ ይሔድ፡
ዘንድ ፡ እንዲአዝዝለት ፡ ንጉሡን ፡ ለመነው ።
ንጉሡም ፡ ከለከለው ፡ ስለ ፡ እጅ ፡ ኀትመት ፡
ምክንያት ፡ ለመፍጠር ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ የእግ
ዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ተገለጠለትና ፡ ነገ ፡
ታርፋለህ ፡ አለው ፡ እርሱም፡ አርድእቱን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ነገ ፡ ስለሚጐበኘኝ ፡ አርፋለሁና ፡
መርከብን ፡ አዘጋጁ ፡ አላቸው ። እንዳለውም ፡
በማግሥቱ ፡ አረፈ ፡ ሥጋውንም ፡ በመርከብ ፡
ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ ከአባቶች ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ ቀበሩት ።

፲፤ በዚህም ፡ አባት ፡ እለእስክንድሮስ ፡ ዘመን ፡
በግብጽ ፡ አገር ፡ ለሚኖሩ ፡ መለካውያን ፡
ስሙ ፡ አንስጣስዮስ ፡ የሚባል ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት፡ ነበራቸው ፡ ያዕቆባውያን ፡ ምእ
መናንን፡ ይወዳቸዋል ፡ ስለዚህም ፡ ወገኖቹ፡
መለካውያን ፡ ተጣሉት ። እርሱም ፡ ነፍሱን ፡
ያድን ፡ ዘንድ ፡ አሰቦ ፡ ወደ ፡ ዚህ ፡ አባት ፡ እለ
እስክንድሮስ ፡ መጥቶ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡
በመሆን ፡ የሚታዘዝ ፡ ሆነ ፡ እለእስክንድ
ሮስም ፡ አንስጣስዮስን ፡ በእርሱ ፡ ፈንታ ፡
የሊቀ ፡ ጵጵስናውን ፡ ሥልጣን ፡ ይዞ ፡
መንጋውን ፡ ይመራ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡
ከመነኰሳት ፡ እንዳንዱ ፡ ሁኖ ፡ በገዳም ፡
ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዲተወው ፡ ለመነው ።
አባ ፡ አንስጣስዮስም ፡ አልወደደም ፡ እን
ዲህም ፡ አለ ፡ ይህን ፡ የምሻ፡ ከሆነ ፡ እኔ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ እለነበርኩምን ፡
ላንተ ፡ ደቀ ፡ መዝሙርህ ፡ ሁኜ ፡ ላገለግልህ ፡
ወደድኩ ፡ እንጂ ፡ አለ ። በመካከላቸው ፡ ከተ
ደረገው ፡ ከብዙ ፡ ልመና ፡ ከብዙ ፡
ምልልስም ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሆን ፡
ዘንድ ፡ አንስጣስዮስ ፡ ፈቀደ ፡ በአንዲትም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዲበ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፳ወ፬ተ ፡ ዓመተ ፡ ወ፮ተ ፡ አውራኀ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእ ግዚአብሔር።

፲፩፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ሀገር ፡ ላይ ፡ ኤጲስቆጶስነትን ፡ ሾመው ። መን ጋውንም ፡ እንደሚገባ ፡ በጎ ፡ አጠባበቅን ፡ ጠበቀ ። አባት ፡ እለእስክንድሮስም ፡ በወን ጌላዊ ፡ ማርቆስ ፡ ወንበር ፡ የኖረው ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ነው ፡ እግ ዚአብሔርንም ፡ አገለገለው።

፲፩፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

<u>አርኬ ፡</u>

ሰላም ፡ ለእለእስክንድሮስ ፡ እምኍልቈ ፡ ጳጳሳት ፡ አሐዱ ። ድኅረ ፡ አመንደቦ ፡ ብዙኀ ለጸባሕተ ፡ ግብር ፡ ክበዱ ። በጸሎት ፡ ወጾም ፡ አስተፋጠና ፡ ለንግዱ ። ህየንተ ፡ መስቀል ፡ ሶበ ፡ አዘዘ ፡ ንጉሠ ፡ ተንባላት፡በእበዱ። ስመ፡ሐሳዊ፡ነቢይ፡ከመ፡ይጽሐፍ፡በእዱ።

፲፪፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት ፡ ፴ወ፰ ፡

፲፫፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ መንኰሰ ፡ ውስተ ፩ ፡ ደብር፡ ዘሀገረ ፡ መርዩጥ ፡ ወስሙ ፡ ለው እቱ፡ ደብር ፡ ጠንቡራ ፡ ወኮነ ፡ ረድአ ፡ ለአሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ አረጋዊ ፡ ፍጹም ፡ ወውእቱ ፡ ርእየ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ረድኡ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይሠየም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወነገሮሙ ፡ ለአኃው ፡ ዘንተ።

፲፬፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኮነ ፡ ጽሙደ፡ ወመስተጋድለ ፡ ወአርአያሁኒ ፡ ሠናይ ፡ ወይለብስ ፡ ዲበ ፡ ሥጋሁ ፡ ሠቀ ፡ ጸጉር፡ ወበ ላዕሌሁ ፡ ልብሰ ፡ ኀዊን ፡ ወኮነ ፡ ፍጹመ ፡ በትሕትናሁ ፡ ወበየውሀቱ ። ወበፈቃደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ተኀርየ ፡ ወተሠይመ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወዐ ቀበ፡ መርዔቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሠናይ ፡ ዕቅ በት ፡ ወኮነ ፡ ያነብብ ፡ ሎሙ ፡ መጻሕፍተ፡ ወይሜህሮሙ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ወፈድፋ ደሰ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ወበዓለት ።

፲፭፤ ወመዋዕለ ፡ ሢመቱ ፡ ኮነ ፡ ዛህነ፡ ወሰላመ ፡ ወነበረት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ በሰላም ፡ ወነ በረ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡

፲፪፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ቴዎድሮስ ፡ አረፈ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አርባ ፡ አምስተኛ ፡ ነው ።

፲፫፤ ይህም ፡ አባት ፡ መርዩጥ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ በአንድ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ መነኰሰ ፡ የዚያም ፡ ገዳም ፡ ስም ፡ ጠንቡራ ፡ ነው፡ ለአንድ ፡ ፍጹም ፡ ጻድቅ ፡ የሆነ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ሆነ ። እርሱም ፡ ልጁ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ እንደሚሾም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይቶ ፡ ይህንን ፡ ለመነኰሳቱ ፡ ነገራቸው።

፲፬፤ ይህም ፡ አባት ፡ ቴዎድሮስ ፡ በገድል ፡ የተጠ መደ ፡ ሆነ ፡ መልኩም ፡ የሚያምር ፡ ነው ፡ በሰውነቱም ፡ ላይ ፡ ከውስጥ ፡ ማቅ ፡ በመልበስ ፡ በላዩ ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ መንቈር፡ ይለብስ ፡ ነበር ፡ በቅንነቱና ፡ በት ሕትናው ፡ ፍጹም ፡ ሆነ ። በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ፈቃድ ፡ ተመርጦ ፡ በእስክን ድርያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ፡ የክርስቶስንም፡ መንጋዎች ፡ በበጎ ፡ አጠ ባበቅ ፡ ጠበቀ ፡ ሁልጊዜ ፡ መጻሕፍትን፡ በማንበብ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡ ይል ቁንም ፡ በሰንበትና ፡ በበዓላት ፡ ቀን ።

፲፭፤ የሹመቱም ፡ ዘመን ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ ነበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በሰላም ፡ ኖረች ፡ በወንጌላዊ ፡ ማርቆስ ፡ ወንበርም ፡ ላይ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲ወ፩ዓመተ ፡ ወመንፈቀ ፡ ዓመት ፡ ወአ
ዕረፈ ፡ በሰላም ።
፲፮፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስ
ሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ ከኖረ ፡
በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ።
፲፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

አርኬ ፡

ሰላም ፡ እብል ፡ ለቴዎድሮስ ፡ ምኩር ። በልብሰ ፡ ኀፂን ፡ ክቡድ ፡ ወበሠቀ ፡ ጸጕር ። አመ ፡ ውእቱ ፡ ረድኡ ፡ ለመልእክተ ፡ ቃሉ ፡ ክቡር ። እምኀበ ፡ አቡሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ በከመ ፡ ወጽአ ፡ ነገር ። በመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ አብ ፡ ዶለዎ ፡ ነቢር ።

፲፯፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡
ለቅዱሳን ፡ አብራቅያ ፡ ወአባዲር ፡ ወአባር
ያኖስ ፡ ወአብዱልማስ ፡ ወገዳማዊ ፡ ዘናዘዞ ፡
ለዕብሎይ ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስ
ሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ።

፲፯፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ የአብራቅያ ፡
የአባዲር ፡ የአባርያኖስ ፡ የአብዱልማስ ፡
ዕብሎይን ፡ ያረጋጋ ፡ የገዳማዊውም ፡ የዕረ
ፍታቸው ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ። በረከታ
ቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብ
ሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፡ አሜን ።

አርኬ ፡

ሰላም ፡ እብል ፡ ለገዳማዊ ፡ ብሒት ። ዘኢርእየ ፡ እምሰብእ ፡ መጠነ ፡ ሰብዓ ፡ ዓመት ። ከመ ፡ አዘዞ ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ። ድኅረ ፡ ወሀባ ፡ ኑዛዜ ፡ ለነፍስ ፡ ዕብሎይ ፡ ኃጥእት ። ዘአዕረፈ ፡ ዮም ፡ በሠሉስ ፡ ዕለት ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፰ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡
ኮነ ፡ በአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እምድኅረ ፡ ፵
መዋዕል ፡ እምልደቱ ፡ ክቡር ።
፪፡ እስመ ፡ ዮሴፍ ፡ ጻድቅ ፡ ዘኮነ ፡ ላእከ ፡ ለዝንቱ ፡
ምሥጢር ፡ ወእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡
ማርያም ፡ ወላዲቱ ፡ መጽኡ ፡ ከመ ፡ ይፈጽሙ ፡
ሕገ ፡ ዘሠርዓ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ላዕለ ፡
ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ያዕርጉ ፡ መሥዋዕተ ፡
ወስምዖን ፡ ካህን ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ተወክፎ ፡
ለሕፃን ፡ ወፆሮ ።

፫፡ ወኮነ ፡ ሶበ ፡ ነግሠ ፡ በጥሊሞስ ፡ ዘይሰመይ ፡
መዋዔ ፡ በዓመት ፡ ፶፻ ወ ፪፻ እምፍጥረተ ፡
አቡነ ፡ አዳም ፡ ወኮኑ ፡ ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡
ታሕተ ፡ ሥልጣኑ ፡ ወፈነወ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ወኀረየ ፡ ዕደወ ፡ ፸ እማእምራኒሆሙ ፡
ወእምሊቃውንቲሆሙ ፡ ወረበናቲሆሙ ፡ ወአ
ብጽሐሙ ፡ ኀቤሁ ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይተ

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ስም
ንት ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ከከበረ ፡ ልደቱ ፡ ከአርባ ፡ ቀኖች ፡
በኋላ ፡ ወደ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የገባበት ፡ ሆነ ።
፪፡ ለዚህ ፡ ምሥጢር ፡ አገልጋይ ፡ የሆነ ፡ ጻድቁ ፡
ዮሴፍና ፡ የወለደችው ፡ እመቤታችን ፡
ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የክብር ፡
ባለቤት ፡ እርሱ ፡ በእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
የሠራውን ፡ ሕግ ፡ ይፈጽሙ ዘንድ ፡ መሥዋ
ዕትም ፡ ሊአቀርቡ ፡ መጡ ። ጻድቅ ፡ ሰው ፡
ስምዖን ፡ ካህንም ፡ ሕፃኑን ፡ ተቀብሎ ፡
አቀፈው ።
፫፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ አባታችን ፡ አዳም ፡ ከተፈጠረ ፡
በአምስት ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡
አሸናፊ ፡ የተባለ ፡ በጥሊሞስ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡
የአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡
ነበሩ ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ልኮ ፡ ከሊቃውን
ቶቻቸው ፡ ከአዋቂዎች ፡ መምህራኖቻቸው ፡
ሰብዓ ፡ ሰዎችን ፡ መርጦ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወሰዳቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ርጕሙ ፡ መጻሕፍተ ፡ ሕግ ፡ እምልሳነ ፡ ዕብራ ይስጢ ፡ ኀበ ፡ ልሳነ ፡ ጽርዕ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ሀለዎ ፡ ይፍልስ ፡ እምአይሁድ ፡ ወይኩን ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ።

፱፡ ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ይፍልጥዎሙ ፡ በበ፪ቱ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ፸ወ፪ ወአስተዳለወ ፡ ፴፮ ወ፮ተ ፡ ሐይመተ ፡ ወአንበሮሙ ፡ በህየ ፡ በበ፪ቱ ፡ ወረሰየ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ዐቀብተ ፡ ከመ ፡ ኢይትራከቡ ፡ ወኢይሰነአዉ ፡ ወኢይወልጡ ፡ ቃለ ፡ ሕግ ፡ ዘይጽሕፉ ። እስመ ፡ እሙንቱ ፡ እሙራን ፡ በጕህሉት ።

፲፡ ወበጽሐ ፡ ለዝንቱ ፡ ስምዖን ፡ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ከመ ፡ ይተርጕም ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ ናሁ ፡ ድንግል ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡ ወልደ ፡ ወትሰምዮ ፡ ስሞ ፡ ዐማኑኤል ፡ ወፈርሀ ፡ ስምዖን ፡ ከመ ፡ ይጽሐፍ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ እስመ ፡ ሐለየ ፡ ከመ ፡ ይሣለቅ ፡ ላዕሌሁ ፡ ንጉሥ ፡ ወይብሎ ፡ እፎ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፡ ወኢይትዌከፎ ፡ ቃሎ ፡ ወለሊሁኒ ፡ ናፈቀ ፡ በዝንቱ ፡ ነገር ፡ ወይቤ ፡ እፎ ፡ ይትከሃል ።

፲፩፡ ወእንዘ ፡ ይሔሊ ፡ ዘንተ ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሁ ፡ ድቃስ ፡ ወኖመ ፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎ ፡ ኢትጥዕም ፡ ሞተ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ትሬእዮ ፡ ለዘናፈቀ ፡ ዘይትወለድ ፡ እምድንግል ፡ ወእስከ ፡ ትፀውሮ ፡ በእደዊከ ፡ ወተሐቅፎ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ሐይወ ፡ ፫፻ተ ዓመተ ፡ እስከ ፡ ተወልደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአብእዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ። ወሶበ ፡ ተወክፎ ፡ ስምዖን ፡ ለሕፃን ፡ እግዚእነ ፡ ተከሥታ ፡ አዕይንቲሁ ፡ እለ ፡ ዖራ ፡ ወተሐደሰ ፡ ኵለንታሁ ፡ እስመ ፡ ነገሮ ፡ መንፈስቅዱስ ፡ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ዘኮንከ ፡ ትጸንሖ ።

፲፪፡ ወባረኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይቤ ፡ ሠዐሮ ፡ ለገብርከ ፡ በሰላም ፡ እስመ ፡ ነበርኩ ፡ እሡረ ፡ በእንቲአከ ፡ ውስተ ፡ ሕይወተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ወናሁ ፡ መፃእከ ፡ ወርኢኩከ ፡ ወሠዓረኒ ፡ ከመ ፡ እሑር ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ። እስመ ፡ ርእያ ፡ አዕይንትየ ፡ አድኅ

የአሪትንም ፡ መጻሕፍት ፡ ከዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ወደ ፡ ጽርዕ ፡ ቋንቋ ፡ ይተረጕሙ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ። ይህም ፡ የሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ከአይሁድ ፡ ሕጉና ፡ ሥርዓቱ ፡ እንደሚፈልስና ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ላሉ ፡ ለክርስቲያን ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አለውና ።

፱፡ ዳግመኛም ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ እያደረጉ ፡ እንዲለዩአቸው ፡ አዘዘ ፡ እነርሱ ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ስለሆኑ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ድንኳን ፡ አዘጋጅቶ ፡ በዚያ ፡ ሁለት ፡ ሁለቱን ፡ አኖራቸው ፡ ተገናኝተው ፡ በመስማማት ፡ የሚጽፉትን ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡ እንዳይለውጡ ፡ በላያቸው ፡ ጠባቂዎችን ፡ አኖረ ። እነርሱ ፡ በተንኰል ፡ ሥራ ፡ የታወቁ ፡ ናቸውና ።

፲፡ ለዚህም ፡ ለስሞዖን ፡ ይተረጕም ፡ ዘንድ ፡ የነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ መጽሐፍ ፡ ደረሰውና ፡ እነሆ ፡ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ። ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ትወልዳለች ፡ ስሙንም ፡ ዐማኑኤል ፡ ትለዋለች ፡ ከሚለው ደረሰ ። ይህንንም ፡ ቃል ፡ ይጽፍ ፡ ዘንድ ፡ ፈራ ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ንጉሥ ፡ እንደሚዘብትበት ፡ ቃሉንም ፡ እንደማይቀበለው ፡ አሰቧልና ፡ እርሱ ፡ ራሱም ፡ እንዴት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ ብሎ ተጠራጠረ ።

፲፩፡ ይህንንም ፡ ሲያስብ ፡ እንቅልፍ ፡ መጣበትና ፡ አንቀላፋ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ተገልጦ ፡ የተጠራጠርከውን ፡ ከድንግል ፡ የሚወለደውን ፡ እስከምታየውና ፡ እስከምትታቀፈው ፡ ሞትን ፡ አትቀምስም ፡ አለው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከተወለደና ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እስከ ፡ አስገቡት ፡ ድረስ ፡ ስሞዖን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ ሕፃኑን ፡ ጌታችንንም ፡ በታቀፈው ፡ ጊዜ ፡ ታውረው ፡ የነበሩ ፡ ዓይነቹ ፡ ተገለጡ ፡ ሁለመናውም ፡ ሐዲስ ፡ ሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የምትጠብቀው ፡ የነበረ ፡ ሕፃን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነግሮታልና ።

፲፪፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነው ። እንዲህም ፡ አለ ፡ ባርያህን ፡ በሰላም ፡ አሰናብተው ፡ በአንተ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ በኃላፊው ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ ታሥሬ ፡ ኑሬአለሁና ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ መጥተህ ፡ አየሁህ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሕይወት ፡ እሔድ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብተኝ ፡ ዓይኖቼ ፡ ትድግናህን ፡ አይተዋልና ። በወገኖችህ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኖተከ ፡ ዘአስተዳሎከ ፡ ቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብከ፡ከመ፡ትክሥት፡ብርሃነ፡ለአሕዛብ፡ ወክብረ፡ለሕዝብከ፡እስራኤል።

፰፡ ወእምዝ ፡ ይቤላ ፡ ለእሙ ፡ እግዝእትነ ፡ ድንግል፡ማርያም፡ዝንቱ፡ወልድኪ፡ንቡር፡ ለድቀቶሙ ፡ ወለተንሥኦቶሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እምውስተ፡እስራኤል፡ወለትእምርት፡በዘይትዋቀሱ።

፱፡ ወአጠየቃ ፡ ካዕበ ፡ እምሕማም ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ ልባ ፡ ወይቤላ ፡ ለኪሰ ፡ ይበውእ ፡ ውስተ ፡ ልብኪ ፡ ኵናተ ፡ ኑፋቄ ። ወእምዝ ፡ አዕረፈ፡በሰላም።

፲፡ ወሀለወት ፡ በህየ ፡ ሐና ፡ ነቢዩት ፡ ወለተ ፡ ፋኑኤል፡ዘዘከራ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ወይእቲ፡ ተነበየት፡በእንቲአሁ፡ወኮነት፡ትሴብሖ፡ለእግዚአብሔር፡ ወዜነወቶሙ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ መድኀን ፡ ዘያድኅኖሙ ፡ እምግብርናተ ፡ ሰይጣን፡ወሎቱ፡ስብሐት፡ለእግዚእነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ምስለ፡አቡሁ፡ ኄር ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መስተሣህል ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ያዘጋጀኸውን ፡ ለአሕዛብ ፡ብርሃንን፡ ለወገኖችህ ፡ እስራኤልም፡ ክብርን ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ።

፰፡እመቤታችንን፡እናቱ፡ድንግል፡ማርያምንም፡ እንዲህ ፡ አላት ፡ ይህ ፡ ልጅሽ ፡ ከእስራኤል ፡ ውስጥ፡ለብዙዎች፡ለመውደቃቸውና፡ለመነሣታቸው ፡ በሚፈረድባቸውም ፡ ገንዘብ ፡ ለምልክት፡የተዘጋጀ፡ነው።

፱፡ዳግመኛው፡በመከራው፡ጊዜ፡በልቧ፡የሚያድርባትን፡ኀዘን፡አስረዳት፡እንዲህም፡አላት፡ በአንቺ፡ግን፡በልብሽ፡የሚከፋፍል፡ፍላፃ ይገባል፡ከዚህም፡በኋላ፡በሰላም፡አረፈ።

፲፡በዚያም፡የከበረ፡ወንጌል፡ያወሳት፡የፋኑኤል፡ ልጅ ፡ ነቢዩት ፡ ሐና ፡ ነበረች ፡ እርሷም ፡ ስለርሱ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረች ፡ እግዚአብሔርን፡ እያመሰገነች ፡ እርሱ ፡ ከሰይጣን ፡ ባርነት ፡ የሚያድናቸው ፡ መድኃኒት ፡ እንደሆነ፡ነገረቻቸው፡ለጌታችንና፡ለመድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከቸር፡አባቱና፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ከሆነ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለበአትከ ፡ በፀዊረ ፡ ርግብ ፡ መሐና ። ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቅድስት ፡ ከመ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡ መኰንነ፡ ሲና ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈጻሜ ፡ አምሳል ፡ ወዜና። ተወክፈከ ፡ ስምዖን ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ ለማርያም፡እምሕፅና።ወኂሩተከ፡አእኰተት፡ሐና።

ሰላም፡እብል፡እንዘ፡እዌድሶ፡ወእንዕዶ። መዝሙረ፡ማኅሌት፡በአስተዋድዶ፡ክብረ።ስምዖን፡ ነቢይ፡ለክብረ፡ሱራፌል፡ዘይፈደፍዶ።እስመ፡ሐቀፈ፡መለኮተ፡ ወገሠሠ፡ነዶ።እኤምኆ፡ ሕፅኖ፡ወእስዕም፡እዶ።

ነገረ፡ትንቢት፡እሙን፡ሶበ፡ናፈቀ፡ወተከዘ።እስከ፡ለአምላክ፡ይሬኢ፡ስነ፡መሢሑ፡ሐዋዘ። ስምዖን፡ዘኮነ፡በማዕሠረ፡ሕይወት፡እኁዘ።ዮም፡በሰላም፡ኀበ፡ምውታን፡ግዕዘ።ከመ፡እግዚኡ፡በሰላም፡ አዘዘ።

፲፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈት ፡ ሐና ፡ ነቢዩት ፡ ወለተ ፡ ፋኑኤል ፡ እምነገደ፡ አሴር ፡ ወለይእቲ፡ ኀለፈ ፡ መዋሊሃ ፡ ወምስለ ፡ ምታሰ፡ ነበረት ፡ ሰብዓተ ፡ ክረምተ ፡ እምድኅረ፡ነበረት፡በድንግልና።

፲፪፡ ወኮነት ፡ መዓስብተ ፡ ሰማንያ ፡ ወአርባዕተ ፡ ክረምተ ፡ ወኢትወጽእ ፡ እምኵራብ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ትትቀነይ ፡ በጾም፡ወበጸሎት።

፲፫፡ወሶበ፡አብእዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ውስተ፡ ቤተ፡መቅደስ፡በ፹ ዕለት፡እምድኅረ፡ተወ

፲፩፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ከአሴር ፡ ወገን ፡ የሆነች ፡ የፋኑኤል ፡ ልጅ ፡ ነቢዩት ፡ ሐና ፡ አረፈች ፡ የእርሷም፡ዘመኗ፡አልፎ፡ነበር፡በድንግልና፡ ከኖረች፡በኋላ፡ከባሏ፡ጋር፡ሰባት፡ዓመት፡ ኖረች።

፲፪፡ሰማንያ፡አራት፡ዓመት፡ፈት፡ሁና፡ኖረች፡ በጾምና፡ በጸሎትም ፡ እያገለገለች ፡ ቀንም ፡ ሌትም፡ከምኵራብ፡አትወጣም፡ነበር።

፲፫፡ ጌታችንን ፡ ኢየሱስን ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ በአርባ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በአስ

www.ethiopianorthodox.org

ልደ ፡ ሶቢሃ ፡ ተንሥአት ፡ ወገነየት ፡ ወአእ
ኰተቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወነገረት ፡ በእን
ቲአሁ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይሴፈዉ ፡ መድ
ኃኒተ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈት ፡
በሰላም ።

ገቡት ፡ ጊዜ ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ ተነሥታ ፡
አመነች ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነችው ፡
የኢየሩሳሌምን ፡ ድኅነት ፡ ተስፋ ፡ ለሚያ
ደርጉ ፡ ሁሉ ፡ ስለርሱ ፡ ነገረች ። ከዚህም ፡
በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈች ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለሐና ፡ ዘወሀበቶ ፡ አኰቴተ ። ለዘገብረ ፡ ወልድ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ዕርገተ ። እምዡራብ ፡ እንታክቲ ፡
እንዘ ፡ ኢትወጽእ ፡ ምንተ ። ነበረት ፡ አዝማነ ፡ሰማንያ ፡ ወአርባዕተ ። ድኅረ ፡ ምስለ ፡ ምታ ፡ ነበረት ፡ ሰብዓተ ።

፲፬፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈት ፡ ቅድስት ፡ አመተ ፡
ክርስቶስ ፡ እግዝእት ፡ ወ፪ቲ ፡ አማቲሃ ፡ ወዛቲ ፡
ቅድስት ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡
ወባቲ ፡ ምት ፡ እመሳፍንተ ፡ ንጉሥ ፡ ወሞተ ፡
በመዋዕለ ፡ ውርዙቱ ፡ ወኅደጋ ፡ ዕቤርተ ፡
እንዘ ፡ መዋዕሊሃ ፡ ፲ወ፪ቱ ።

፲፭፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ፈቀደ ፡
፩ብእሲ ፡ እምዐበይተ ፡ መንግሥት ፡ ይን
ሥኣ ፡ በኃይል ፡ ወአመክንየት ፡ ሎቱ ፡
ወትቤሎ ፡ ብየ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ጽኑዕ ፡ ጽንሐኒ ፡
እስከ ፡ አሐዩ ፡ ወእምዝ ፡ ዘረወት ፡ ኵሎ ፡
ንዋያ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወአግዓዘት ፡
አግብርቲሃ ፡ ወአእማቲሃ ፡ ወነሥአት ፡ ምስ
ሌሃ ፡ ፪ተ ፡ እምአእማቲሃ ፡ ወወጽአት ፡
በሌሊት ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይሬእያ ፡ ወቦአት ፡
ውስተ ፡ ጸላዕት ፡ ዘመትሕተ ፡ ወግር ፡ ዕሙቅ ፡
ወነበረት ፡ በህየ ፡ ፲ወ፩ዓመተ ፡ ወለለዕለት ፡
ያመጽኡ ፡ ላቲ ፡ አዕዋፍ ፡ እምፍሬያተ ፡
ዕፀው ፡ ወትሴሰይ ፡ ምስለ ፡ አእማቲሃ ፡

፲፮፤ ወእምዝ ፡ በመዋዕለ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡
ይቤ ፡ አሐዱ ፡ እምከታብያን ፡ ሖርኩ ፡
መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ከመ ፡ አስተጋብእ ፡
ጸባሕተ ፡ ወበጸሕኩ ፡ ውስተ ፡ ፩ደብር ፡ ወተቀ
በሉኒ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወመነኰሳት ፡ ወተአ
ማኅነ ፡ በበይናቲነ ፡ ወነበርነ ፡ ወሀለዉ ፡ ህየ ፡
አዕዋም ፡ ዘቦ ፡ ዘዚአሆሙ ፡ ፍሬያት ፡
ወርኢኩ ፡ አዕዋፈ ፡ እንዘ ፡ ይመትሩ ፡ አዕ
ጹቀ ፡ ምስለ ፡ ፍሬሆሙ ፡ ወይሠርሩ ፡ ፍጡነ ፡
ወኢይበልዑ ፡ ለሊሆሙ ።

፲፯፤ ወርእይየ ፡ አነ ፡ አንከርኩ ፡ ወእቤሎሙ ፡ ለመነ
ኰሳት ፡ ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ግብር ፡ ወይቤሉኒ ፡
እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ዘንተ ፡ ናሁ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ዓመት ፡

፲፬፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የከበረች ፡ እመቤት ፡ አመተ ፡
ክርስቶስ ፡ አረፈች ፡ ሁለቱም ፡ አገልጋዮቿ ።
ይችም ፡ ቅድስት ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ አገር ፡
ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ናት ፡ ከንጉሥ ፡ መሳፍን
ቶችም ፡ ባል ፡ ነበራት ፡ እርሱም ፡ በጐልማ
ሳነቱ ፡ ሙቶ ፡ ዕድሜዋ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡
ዓመት ፡ ሲሆናት ፡ ፈቶ ፡ አረጋት ።

፲፭፤ ከጥቂትም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከመንግሥት ፡
ታላላቆች ፡ ከሆኑት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
በኃይል ፡ ወስዶ ፡ ሊአገባት ፡ ፈለገ ፡ እርሷም ፡
ጽኑ ፡ ደዌ ፡ አለብኝ ፡ እስከምድን ፡ ጠብቀኝ ፡
አለችውና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገንዘቧን ፡ ሁሉ ፡
ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ በተነች ፡ ወንዶ
ችና ፡ ሴቶች ፡ ባሮቿን ፡ ነጻ ፡ አወጣች ፡ ሁለት ፡
ሴቶች ፡ ባሮቿንም ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ ይዛ ፡
ማንም ፡ ሳያያት ፡ በሌሊት ፡ ወጣች ፡ ከኰ
ረብታ ፡ በታች ፡ ጥልቅ ፡ ከሆነ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡
ወዳለ ፡ ዋሻ ፡ ገብታ ፡ በዚያ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ ኖረች ፡ በየዕለቱም ፡ ከዕፀዋት ፡ ፍሬ ፡
አዕዋፍ ፡ እያመጡላት ፡ ከአገልጋዮቿ ፡ ጋር ፡
ትመገባለች ።

፲፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡
ዘመን ፡ ከጸሐፊዎች ፡ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡
ግብር ፡ እሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡
አቅጣጫ ፡ ሔድኩ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ገዳምም ፡
ደረስኩ ፡ መነኰሳቱና ፡ አበ ፡ ምኔቱም ፡ ተቀበ
ሉኝ ፡ እርስበርሳችንም ፡ እጅ ፡ ተነሣሥተን ፡
ተቀመጥን ፡ ከዚያ ፡ በየአይነቱ ፡ ፍሬ ፡ ያላ
ቸው ፡ ዛፎች ፡ አሉ ፡ አዕዋፍም ፡ ቅርንጫፉን ፡
ከፍሬው ፡ ጋር ፡ እየቀረጡ ፡ ይበራሉ ፡ እነርሱ ፡
ራሳቸው ፡ አይበሉም ።

፲፯፤ እኔም ፡ አይቼ ፡ አደነቅሁ ፡ መነኰሳቱንም ፡
ይህ ፡ ሥራ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አልኳቸው ፡ እነር
ሱም ፡ እንዲህ ፡ ሲያደርጉ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኢነአምር፡ዘይከውን፡ወእቤሎሙ፡ሊተሰ፡ ይመስለኒ፡ዘያበጽሑ፡እሉ፡አዕዋፍ፡ለመነ ኰሳት፡እለ፡ውስተ፡አድበር።

፲፰፡ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡ እትናገር ፡ መጽአ ፡ ቋዕ ፡ ወመተረ፡አዕጹቀ፡ምስለ፡ፍሬ፡ወሠረረ፡ ወተለውክዎ ፡ ምስለ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ናእምር ፡ ግብሮ ፡ ወርኢነ ፡ ኀበ ፡ ይበውእ ፡ ወበጺሐነ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ወገርነ ፡ ዕብነ ፡ ወሰማዕነ ፡ ቃለ ፡ ዘይብል ፡ ለእመ ፡ ኮንክሙ ፡ ክርስቲያነ ፡ ኢትቅትሉነ ፡ ወን ቤሎሙ፡እምአይቴ፡አንትሙ፡ወይቤላነ፡ ለእመ፡ፈቀድክሙ፡ትርአዩ፡ኪያነ፡ገሩ፡ ለነ፡ ሠለስተ ፡ አልባሰ ፡ እስመ ፡ ንሕነ ፡ ዕሩቃት ፡ ወወገርነ ፡ ሎን ፡ አልባሰ ፡ ወወረድነ፡ ኀቤሆን ፡ በፍኖት ፡ ጽዕቅት ፡ ወሶበ፡በጻሕነ፡ተቀበላነ፡ወተአማኀነ፡በበ ይናቲነ ፡ ወነበረት ፡ አሐቲ ፡ ምስሌነ ፡ ወክልኤቲ፡ቆማ፡ቅድሜሃ፡ወይቤላ፡አበ፡ ምኔት፡አ፡እምየ፡ወእግዝእትየ፡እምአይቴ፡ አንቲ ፡ ወእፎ ፡ ጸአትኪ ፡ ዝየ ፡ ወነገረቶ ፡ እምጥንቱ፡እስከ፡ተፍጻሜቱ፡ኵሎ፡ግብራ፡ ወይቤላ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ለእመ ፡ ትፈቅዲ ፡ ናምጽእ ፡ ለክን ፡ ሲሳየ ፡ እምደብር ፡ ወን ሳተፍ፡ ምስሌክን ፡ ወይእቲ ፡ ትቤሎ ፡ አ ፡ አቡየ፡አዝዝ፡ለነ፡ከመ፡ያምጽእ፡ቀሲስ፡ ቍርባነ፡ወይመጥወነ፡ሥጋሁ፡ወደሞ፡ለክ ርስቶስ፡እምአመ፡መጻእነ፡ዝየ፡ኢነሣእነ።

፲፱፡ ወአዘዘ ፡ ሎን ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ቀሲሰ ፡ ወመጠዎን፡ቍርባነ፡ወበሳኒታ ፡ ጸለየት ፡ ጸሎተ ፡ ነዋኀ ፡ እመተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአዕ ረፈት ፡ ወእእማቲሃኒ ፡ አእረፋ ፡ እንዘ ፡ ይታለዋ ፡ ወገነዝዎን ፡ በዝማሬ ፡ ወበማ ኅሌት፡ወቀበርዎን፡በክብር።

፳፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቶን ፡ ወበረከቶን ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዓመት፡ነው፡የሚሆነውን፡ግን፡አናውቅም፡ አሉኝ፡እኔስ፡በተራራ፡ውስጥ፡ለሚኖሩ፡ መነኰሳት ፡ የሚወስዱ ፡ ይመስለኛል ፡ አልኳቸው።

፲፰፡ ይህንንም ፡ ስናገር ፡ ቍራ ፡ መጥቶ ፡ ቅርን ጫፍን፡ቆርጦ፡ከፍሬው፡ጋር፡ይዞ፡በረረ፡ ሥራውን፡አውቅ፡ዘንድ፡ከአበ፡ምኔቱ፡ጋር ተከተልኩት፡የሚገባበትንም፡አየን፡ወደ ዚያም፡ቦታ፡ደርሰን፡ደንጋይ፡ጣልን፡ክርስ ቲያኖች፡ከሆናችሁ፡አትግደሉን፡የሚል፡ ቃልን፡ሰማን፡እናንተ፡ከወዴት፡ናችሁ፡ አልናቸው፡እኛን፡ለማየት፡ከፈለጋችሁ፡ ራቁታችንን፡ስለሆን፡ሦስት፡ልብሶችን፡ ጣሉልን፡አሉን፡እኛም፡ልብሶችን፡ጣልንላ ቸውና ፡ ወደርሳቸው ፡ ጭንቅ ፡ በሆነች ፡ መንገድ፡ወረድን፡በደረስንም፡ጊዜ፡ተቀ በሉን፡እርስበርሳችንም፡እጅ፡ተነሣሥተን፡ አንዲቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ተቀመጠች፡ሁለቱ፡ ግን፡በፊቷ፡ቆሙ።አበ፡ምኔቱም፡እናቴና፡ እመቤቴ፡ሆይ፡ከወዴት፡ነሽ፡ወደዚህስ፡ አወጣጥሽ፡እንዴት፡ነው፡አላት፡እርሷም፡ ሥራዋን ፡ ሁሉ ፡ ከመጀመሪያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው፡ነገረችው፡አበ፡ምኔቱም፡የም ትፈቅጂ፡ከሆነ፡ከገዳም፡ምግብ፡እናምጣላ ችሁና ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ እን መገብ፡አላት።እርሷም፡ወደዚህ፡ከመጣን፡ ቅዱስ፡ቍርባንን፡አልተቀበልንምና፡የክር ስቶስን፡ሥጋና፡ደም፡አምጥቶ፡እንዲአቀ ብለን፡ቄስን፡እዘዝልን፡አለችው።

፲፱፡ አበ፡ምኔቱም፡ቄስን፡አዘዘላቸውና፡አቈረ ባቸው፡በማግሥቱም፡አመተ፡ክርስቶስ፡ ረድም፡ጸሎትን፡ጸለየችና፡አረፈች፡አገልጋ ዮቿም፡ተከታትለው፡አረፉ፡በዝማሬና፡ በማኅሌት፡ገንዘው፡በክብር፡ቀበሩአቸው።

፳፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎታቸው ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እ‌ብል፡ለሠላስ፡አንስት።ምንዳቤ፡ገዳም፡ዘፆራ፡እንዘ፡ዕሩቃት።እምድኅረ፡ነሥአ፡ቍርባነ፡ እምእደ፡ካህናት።አዕረፋ፡ዮም፡በበአሐቲ፡ትልወት።አሐቲ፡እግዝእት፡ወክልኤቲ፡አእማት።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ኤልያስ ፡ ዘገዳመ ፡ ሲሐት ፡ አረጋዊ ፡ ዐቢይ ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ።

፳፪፤ ወሶበ ፡ ለአከ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቅ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ ሲሐት ፡ እንዘ ፡ ይስእሎሙ ፡ ከመ ፡ ይፈንዉ ፡ ሎቱ ፡ ኀቤሁ ፡ መነኮሰ ፡ አረጋዌ ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ከመ ፡ ይናዝዞ ፡ ፈነዉ ፡ ሎቱ ፡ አረጋዌ ፡ ኤልያስሃ ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ጽሒፎሙ ፡ መጽሐፈ ፡ በእንቲአሁ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ፈነውነ ፡ ለከ ፡ አ ፡ ንጉሥ ፡ ብእሴ ፡ ጻድቀ ፡ ዘይሰመይ ፡ ኤልያስ ፡ ወውእቱ ፡ አምሳለ ፡ ኤልያስ ፡ በምግባሩ ።

፳፫፤ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ለአኩ ፡ መነኮሳት ፡ ኀቤየ ፡ በእንቲአከ ፡ ከመ በገድልከ ፡ ትመስል ፡ ኤልያስሃ ፡ ነቢየ ፡ ወይቤሎ ፡ አረጋዊ ፡ በትሕትና ፡ ወየውሀት ፡ አ ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቅ ፡ ስረይ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ይትዓወቅ ፡ እምግዕዙ ፡ ወገድሉ ፡ ለኤልያስ ፡ እንበይነ ፡ ጽድቁ ፡ ያመጽኡ ፡ ሎቱ ቋዓት ፡ ሲሳዮ ፡ ወሊተሰ ፡ ለእመ ፡ አነብር ፡ ሲሳይየ ፡ ውስተ ፡ ፀሐይ ፡ ይመጽእ ፡ ቋዕ ፡ ወይነሥእ ፡ ወየሐውር ፡ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ አንከረ ፡ እምጣዕመ ፡ ቃሉ ።

፳፬፤ ወካዕበ ፡ ይቤሎ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ በይነ ፡ ምንት ፡ ኢወሀበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ ወይቤሎ ፡ አረጋዊ ፡ እስመ ፡ ይመጽእ ፡ መዋዕል ፡ ዘይከውን ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ኑፋቄ ፡ ሃይማኖት ፡ በእንተዝ ፡ ኢወሀበከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ ከመ ፡ ኢይደመር ፡ ምስለ ፡ ንፉቃን ። ወፈቀደ ፡ ንጉሥ ፡ የሀቦ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢተመጠወ ፡ ወተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ኢጥዕመ ፡ እክለ ፡ እስከ ፡ ገብአ ፡ ውስተ ፡ በአቱ ፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ።

፳፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፳፩፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በትሩፋቱ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ታላቅ ፡ አረጋዊ ፡ የገዳመ ፡ ሲሐቱ ፡ ኤልያስ ፡ አረፈ ።

፳፪፤ የሚያረጋጋው ፡ በትሩፋቱ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ አረጋዊ ፡ መነኰሴ ፡ እንዲልኩለት ፡ በመለመን ፡ ጻድቁ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ወደ ፡ ገዳመ ፡ ሲሐት ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ በትሩፋቱ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ኤልያስን ፡ ላኩለት ፡ ስለርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጻፉ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እነሆ ፡ በሥራው ፡ ኤልያስን ፡ የሚመስል ፡ ኤልያስ ፡ የሚባል ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ልከንልሃል ።

፳፫፤ ወደ ፡ ንጉሥም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ አንተ ፡ በገድልህ ፡ ነቢይ ፡ ኤልያስን ፡ እንደምትመስል ፡ መነኰሳቱ ፡ ስለአንተ ፡ ወደእኔ ፡ ልከዋል ፡ አረጋዊውም ፡ በየውሀትና ፡ በትሕትና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ጻድቅ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በጠባዩና ፡ በሥራው ፡ ይታወቃል ፡ የኤልያስም ፡ ገድሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ደግነቱ ፡ ምግቡን ፡ ቍራዎች ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ምግቤን ፡ በፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ባሰጣው ፡ ቍራ ፡ ይዞት ፡ ይሔዳል ፡ ንጉሡም ፡ ሰምቶ ፡ ከቃሉ ፡ ጣዕም ፡ የተነሣ ፡ አደነቀ ።

፳፬፤ ዳግመኛም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አልሰጠኝም ፡ አለው ፡ አረጋዊውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚከፋፈልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፡ ከመናፍቃን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንዳይሆን ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅን ፡ አልሰጠህም ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብን ፡ ሊሰጠው ፡ ወደደ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አልተቀበለም ። ወደ ፡ በአቱም ፡ እስከተመለሰ ፡ ድረስ ፡ እህል ፡ እንዳልቀመሰ ፡ ስለርሱ ፡ ተነገረ ፡ በሰላምም ፡ አረፈ ።

፳፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለኤልያስ ፡ ዘተወደሰ ፡ ወተንዕደ ። ሶበ ፡ ለንጉሥ ፡ ይቤሎ ፡ ረኪበ ፡ ዘርዕ ፡ ዘፈቀደ ። በላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ እምእለ ፡ ይገብሩ ፡ ካህደ ። እስመ ፡ ይከውን ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ኑፋቄ ፡ ሃይማኖት ፡ ገሀደ ። ወበእንተዝ ፡ ኢሠምረ ፡ ከመ ፡ ትለድ ፡ ወልደ ።

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አሜ፡ ፲፱ ለየካቲት፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ ዐቢይ፡ አባ፡ በርሱማ፡ ሶርያዊ፡ አበ፡ መነኰሳት፡ ዘብሔረ፡ ሶርያ።

፪፤ ወለዝንቱ፡ ቅዱስ፡ አበዊሁ፡ እምሰብአ፡ ሀገረ፡ ሳሚሳጥ፡ ወተነበየ፡ ላዕሌሁ፡ ፩ ብእሲ፡ ዘጾማዕት፡ ወይቤሎ፡ ለአቡሁ፡ እምቅድመ፡ ልደቱ፡ እስመ፡ ሀሎ፡ ዘይወጽእ፡ እምኔከ፡ ፍሬ፡ ጥዑም፡ ወይሰማዕ፡ ዜና፡ ትሩፋቱ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ሀገረ፡ ሶርያ፡ ወአጠየቆ፡ ዘይከውን፡ እምኔሁ።

፫፤ ወሶበ፡ ተወልደ፡ ወልሕቀ፡ ወበጽሐ፡ ውስተ፡ አእምሮ፡ እግዚአብሔር፡ ጐየ፡ እምአበዊሁ፡ ወበጽሐ፡ ኀበ፡ ፈለገ፡ ኤፍራጥስ፡ ወነበረ፡ ህየ፡ ኀበ፡ ፩ ብእሲ፡ ዘስሙ፡ አብርሃም፡ ውእቱኒ፡ ሰደዶ፡ እምውእቱ፡ ደብር፡ በእንተ፡ ፍርሀተ፡ አበዊሁ፡ ወውእቱ፡ ሖረ፡ ወኀደረ፡ ውስተ፡ ኰኵሕ፡ ወተጋደለ፡ በህየ፡ ገድለ፡ ዐቢየ፡ ወሶበ፡ ተሰምዐ፡ ዜናሁ፡ ውስተ፡ ኵሎን፡ በሐውርት፡ ወተጋብኡ፡ ኀቤሁ፡ ብዙኃን፡ አርድእት፡ ወማየ፡ ውእቱሰ፡ መካን፡ ዘይነብር፡ ህየ፡ መሪር፡ ጥቀ፡ ወሶበ፡ ጸለየ፡ ላዕሌሁ፡ ተወለጠ፡ ወኮነ፡ ጥዑመ።

፬፤ ወገብረ፡ እግዚአብሔር፡ ዲበ፡ እደዊሁ፡ ተአምራተ፡ ወመንክራተ፡ ወእምኔሆሙ፡ በአሐቲ፡ ጊዜ፡ ኮነ፡ ርኁቀ፡ እምበአቱ፡ ምስለ፡ አርድእቲሁ፡ ወቀርበ፡ ዕርበተ፡ ፀሐይ፡ ወሰአሎ፡ ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ አሚሃ፡ ዐቀመ፡ ሎቱ፡ ፀሐየ፡ እስከ፡ በጽሐ፡ ኀበ፡ በአቱ።

፭፤ ወበካልዕ፡ ጊዜ፡ እስመ፡ ሀለወት፡ ሀገር፡ እንተ፡ ስማ፡ ረዓም፡ ወሰብአ፡ ዚአሃ፡ ከሀድያን፡ ወተከልአ፡ ዝናም፡ ላዕሌሆሙ፡ ወሶበ፡ ተመንደቡ፡ መጽኡ፡ ኀበ፡ ቅዱስ፡ አባ፡ በርሱማ፡ ወሰአልዎ፡ ውእቱኒ፡ ገሠጾሙ፡ በእንተ፡ ዐሊዎቶሙ፡ ወይቤሎሙ፡ ለእመ፡ ተመየጥክሙ፡ እምዕልወትክሙ፡ ወአመንክሙ፡ በእግዚአብሔር፡ ውእቱ፡ ያዘንም፡ ለክሙ፡ ብዙኀ፡ ዝናመ። ወይቤልዎ፡ አሆ፡ ነአምን፡ ቦቱ፡ ውእተ፡

፩፤ አንድ፡ አምላክ፡ በሆነ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ የካቲት፡ ዘጠኝ፡ በዚች፡ ቀን፡ የከበረ፡ በሶርያ፡ አገር፡ ላሉ፡ መነኰሳት፡ አባት፡ የሆነ፡ ታላቁ፡ አባ፡ በርሱማ፡ አረፈ።

፪፤ የዚህም፡ ቅዱስ፡ ወላጆቹ፡ ሳሚሳጥ፡ ከሚባል፡ አገር፡ ሰዎች፡ ውስጥ፡ ናቸው፡ አንድ፡ በዋሻ፡ ውስጥ፡ የሚኖር፡ ሰው፡ በእርሱ፡ ላይ፡ ትንቢትን፡ ተናገረ፡ ከመወለዱ፡ አስቀድሞ፡ ለአባቱ፡ እንዲህ፡ አለው፡ የትሩፋቱ፡ ዜና፡ በሶርያ፡ ሀገር፡ ሁሉ፡ የሚሰማ፡ ጣዕም፡ ያለው፡ ፍሬ፡ ከአንተ፡ ይወጣል፡ ከእርሱ፡ የሚሆነውንም፡ አስረዳው።

፫፤ ተወልዶም፡ አድጎ፡ እግዚአብሔርን፡ ወደ፡ ማወቅ፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ ከወላጆቹ፡ ሸሽቶ፡ ወደ፡ ኤፍራጥስ፡ ወንዝ፡ ደርሶ፡ በዚያ፡ ስሙ፡ አብርሃም፡ ከሚባል፡ ሰው፡ ዘንድ፡ ተቀመጠ፡ እርሱም፡ ወላጆቹን፡ ስለፈራ፡ ኪዚያ፡ ገዳም፡ ሰደደውና፡ ሒዶ፡ በአለት፡ ውስጥ፡ ኖረ፡ በዚያም፡ ታላቅ፡ ተጋድሎን፡ ተጋደለ፡ ወሬውም፡ በሶርያ፡ አገሮች፡ ሁሉ፡ በተሰማ፡ ጊዜ፡ ብዙዎች፡ ደቀመዛሙርት፡ ወደርሱ፡ ተሰበሰቡ፡ የዚያ፡ ቦታ፡ ውኃ፡ ግን፡ እጅግ፡ መራራ፡ ነበር፡ በላዩ፡ በጸለየ፡ ጊዜ፡ ተለውጦ፡ ጣፋጭ፡ ሆነ።

፬፤ እግዚአብሔርም፡ በእጆቹ፡ ድንቆች፡ ተአማራቶችን፡ አደረገ፡ ከእርሳቸውም፡ በአንዲት፡ ጊዜ፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ጋር፡ ከበአቱ፡ ርቆ፡ ሳለ፡ የፀሐይ፡ መግቢያ፡ ሰዓት፡ ተቃረበ፡ የክብር፡ ባለቤት፡ ጌታችንን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ለመነው፡ ወደ፡ በአቱም፡ እስቲደርስ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ፀሐይን፡ አቆመለት።

፭፤ በሌላ፡ ጊዜም፡ እንዲህ፡ ሆነ፡ ረዓም፡ የምትባል፡ አገር፡ ነበረች፡ ሰዎቿም፡ ከሀዲዎች፡ ናቸው፡ በላያቸውም፡ ዝናብ፡ ተከለከለ፡ በተጨነቁም፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ከበረ፡ አባ፡ በርሱማ፡ መጥተው፡ ለመኑት፡ እርሱም፡ ገሠጻቸው፡ እንዲህም፡ አላቸው፡ ከክህደታችሁ፡ ተመልሳችሁ፡ በእግዚአብሔር፡ ብታምኑ፡ እርሱ፡ ብዙ፡ ዝናብን፡ ያዘንብላችኋል፡ እነርሱም፡ እናምንበታለን፡ አሉት። በዚያን፡ ጊዜ፡ ጌታችንን፡ ለመነውና፡ ብዙ፡ ዝናብ፡ ዘነበ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ፡ ሰአሎ፡ ለእግዚእነ፡ ወዘንመ፡ ሎሙ ፡ ዝናም ፡ ብዙኀ፡ ወአምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር፡በእግዚእነ፡
፮፥ ወከማሁ ፡ ሀለወት ፡ ካልዕት ፡ ሀገር ፡ ወሰብአ ፡ ዚአሃ ፡ ከሀድያን ፡ ለእሉኒ፡ ገሠጾሙ ፡ ወመሀሮሙ ፡ ወሜጦሙ ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአንሀለ፡ አብያተ ፡ ጣዖታቲሆሙ።
፯፥ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አስተዳለወ ፡ ለርእሱ፡ መካነ፡ ወኮነ ፡ ቅውመ ፡ ህየ፡ ዘእንበለ፡ ነቢር፡ ፵ ወ፬ተ ፡ ዓመተ ፡ ወሶበ ፡ ይደክም ፡ እምትጋህ፡ ያሰምክ ፡ ዲበ ፡ አረፍተ ፡ ናሕስ ፡ ወይዴቅስ፡ወይጸውም፡በበሱባኤ።
፰፥ ወኮነ ፡ ቅዱስ ፡ አባ፡ ስምዖን ፡ ዘዓምድ ፡ ይፈቅድ፡ ይርአዮ ፡ ወፈነወ፡ ኀቤሁ ፡ እስመ ፡ ሰምዐ ፡ ዜና ፡ ትሩፋቲሁ ፡ ወቅድስናሁ ፡ እምነ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ውእቱኒ፡ ሖረ ፡ ኀበ፡ አባ፡ስምዖን፡ወተባረኩ፡በበይናቲሆሙ።

፱፥ ወእምዝ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ደብሩ ፡ ወሰበከ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ሶርያ ፡ ወአምኑ ፡ በእደዊሁ ፡ ብዙኃን፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ተአምራተ ፡ በቅድሜሆሙ።
፲፥ ወሖረ ፡ ካዕበ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘይንእስ ፡ ወአጽንዖ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወወሀቦ፡ ንጉሥ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢነሥአ፡ ምንተኒ ። ወጸሐፈ ፡ ንጉሥ፡ከመ፡ይኩን፡ሎቱ፡ሥልጣን፡ላዕለ፡ ኵሎሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘብሔረ፡ አንጾኪያ፡ወወሀቦ፡ሕልቀቶ።
፲፩፥ ወሶበ፡ተጋብኡ፡በሀገረ፡ኤፌሶን፡፪፻ኤጲስቆጶሳት ፡ በእንተ ፡ ንስጥሮስ ፡ ከሀዲ፡ ሀሎ፡ ምስሌሆሙ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ወአውገዙ፡ ለንስጡር፡ ምስሌሆሙ ፡ ወዓዲ ፡ ጸሐፈ፡ ንጉሥ ፡ ክታበ፡ ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎሙ ፡ መኳንንት ፡ ወመሳፍንት ፡ ወሥዩማን፡ ዘብሔረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወኮነ፡ ውእቱ፡ዘይጽሕፍ፡ወየኀትም፡በህልቀቱ፡ ለንጉሥ ፡ ወይፌኑ ፡ ለኵሎን ፡ አህጉር ፡ ዘይኤዝዝ፡ከመ፡ይግበሩ፡ምግባረ፡ሠናይ፡ ወይጽንዑ፡በሃይማኖት፡ርትዕት።

ላቸው ፡ የሀገር፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ በጌታችን ፡ አመኑ።

፮፥ እንዲሁም ፡ ሰዎቿ ፡ ከሀድያን ፡ የሆኑ ፡ ሌላ ፡ ሀገር ፡ ነበረች ፡ እነርሱንም ፡ ገሥጾ ፡ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ወደ፡ ማወቅ ፡ መለሳቸው ፡ የጣዖቶቻቸውንም ፡ ቤቶች ፡ አፈረሰ።
፯፥ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ለራሱ ፡ ቦታ ፡ አዘጋጅቶ ፡ በዚያ፡ ሳይቀመጥ ፡ ሃምሣ ፡ አራት፡ ዓመት ፡ ቁሞ ፡ ኖረ ፡ ከመትጋት ፡ የተነሣ፡ ሲደክመው፡ ከናሱ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ያሸልባል፡በየሰባት፡ቀንም፡ይጾማል፡
፰፥ የከበረ ፡ አባ ፡ ስሞዖን ፡ ዘዓምድ ፡ ሊያየው ፡ ወዶ ፡ ወደርሱ ፡ ላከ፡ የትሩፋቱንና ፡ የቅድስናውን ፡ ዜና ፡ ከብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ እርሱም ፡ ወደ፡ አባ ፡ ስምዖን ፡ መጥቶ፡ እርስበርሳቸው ፡ በረከትን ፡ ተቀባበሉ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ተመለሰ።
፱፥ በሶርያ፡አገርም፡አስተማረ፡በፊታቸው፡ተአምራትን ፡ በአደረገ ፡ ጊዜ፡ በትምህርቱ ፡ ብዙዎች፡አመኑ።

፲፥ ዳግመኛም ፡ ወደ፡ ታናሹ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ንጉሥ፡ሒዶ፡በቀናች፡ሃይማኖት፡አጸናው፡ ንጉሡም ፡ ብዙ፡ ገንዘብን፡ ሰጠው ፡ እርሱ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አልወሰደም ፡ በአንጾኪያም ፡ አገር ፡ በኤጲስቆጶሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን፡ እንዲኖረው ፡ ንጉሥ፡ ጻፈለትና ፡ ኀቲም፡ቀለበቱን፡ሰጠው።
፲፩፥ በከሀዲው ፡ ንስጥሮስ ፡ ምክንያት ፡ ሁለት ፡ መቶ፡ኤጲስቆጶሳት፡በኤፌሶን፡ከተማ፡በተሰበሰቡ፡ጊዜ፡ከእሳቸው፡ጋር፡ይህ፡ቅዱስ፡ አለ ። ከእርሳቸውም ፡ ጋር ፡ ንስጡርን ፡ አወገዘው ፡ ዳግመኛም ፡ በአንጾኪያ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ መኳንንት ፡ መሳፍንት ፡ሹማምንት ፡ ሁሉም ፡ ይታዘዙለት ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤን ፡ ጻፈለት ፡ እርሱም ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ በሃይማኖት ፡ እንዲጸኑ ፡ የሚያዝዝ ፡ ደብዳቤ ፡ በመጻፍ ፡ በንጉሥ ፡ ኀቲም፡ ቀለበት ፡ እያተመ፡ ለሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚልክ፡ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወጸልእዎ ፡ እኩያን ፡ ሰብእ ፡ ወአስተዋ
ደይዎ፡ኀበ፡ንጉሥ፡ወይቤልዎ፡ናሁ፡አባ፡
በርሱማ፡ኮነ፡ከመ፡ሰብአ፡ዓለም፡ይበልዕ፡
ወይሰቲ ፡ ወይለብስ ፡ አልባሰ ፡ ሠናያነ ፡
ወፈነወ፡ንጉሥ፡እምዐርካኒሁ፡፩ደ፡ከመ፡
ይጠይቅ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ ፡ አባ፡
በርሱማ። ወሶበ፡በጽሐ፡ዐርኩ፡ለንጉሥ፡
ኀበ፡አባ፡በርሱማ፡ኢረከበ፡ምንተኒ፡እም
ዘተነግረ፡በላዕሌሁ፡ወእምዝ፡አብጽሖ፡
ኀበ፡ንጉሥ፡ንጉሥኒ፡ኢረከበ፡ውሉጠ፡
ነገረ፡እምግብሩ፡መንፈዊ፡ዘኮነ፡የአምር፡
ቀዲሙ፡ወአክበሮ፡ንጉሥ፡ክብረ፡ዐቢየ፡
ወሜጦ፡ኀበ፡መካኑ።

፲፫፤ ወሶበ፡አስተጋብአ፡ማኅበረ፡ጉባኤ፡ዘኬል
ቄዶን ፡ ንጉሥ ፡ መርቅያን ፡ ዐላዊ ፡ አም
ከርዎ ፡ መማክርቲሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ ፡
ኢያምጽአ ፡ ለአባ ፡ በርሱማ ፡ እስመ ፡
እሙንቱ ፡ የአምሩ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡
ኢየኀፍር፡ ወኢያደሉ፡ለገጽ፡ወከመ፡ኢይ
ትዋሥአሙ፡ወኢያስተኀፍሮሙ።

፲፬፤ ወሶበ፡ተፈጸመ፡ዝንቱ፡ጉባኤ፡ዘፈለጥዎ፡
ለ፩ዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወረሰይዎ ፡ ፪ተ ፡
ጠይባዓተ ፡ ተቃረኖሙ ፡ ብፁዕ ፡ አባ ፡
በርሱማ ፡ ወሠዓረ፡ ቃላቲሆሙ ፡ ወአው
ገዞሙ ፡ ወረገሞሙ ፡ ወእሉ፡ ጸሐፉ ፡ ኀበ ፡
ንጉሥ ፡ ወአስተዋደይዎ፡ ወፈነወ ፡ ንጉ
ሥኒ፡ወአብጽሖ፡ኀቤሁ፡ባሕቱ፡ኢክህለ፡
ተቃውሞቶ ፡ በእንተ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ፡ ዘኀዱር ፡ ላዕሌሁ ። ወረገማ፡
ለንግሥት ፡ በእንተ ፡ ዘገብረት ፡ እኩየ ፡
ላዕለ፡ ቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ መስተጋድል ፡
ወሐረ፡ ውስተ፡ መካኑ ፡ ወኢነበረት፡
ዘእንበለ፡ ኀዳጥ ፡ መዋዕል ፡ አላ ፡ ሞተት ፡
በእኩይ፡ሞት።

፲፭፤ ወእምዝ ፡ ኮኑ ፡ ዐላውያን ፡ ዘይትቃረንዎ ፡
ወይጽሕፉ፡ውስተ፡ኵሎን፡አህጉር፡ከመ፡
ኢይትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ መሃይምናን ፡ እሙ
ንቱሰ፡ኢተወክፍዎሙ፡ወኢኀደጉ፡ተአ
ዝዞተ፡ሎቱ።

፲፮፤ ወተሰነዐው ፡ ዓዲ ፡ ፪ ፻ ዕደው፡ ዐላውያን ፡
ምስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዓላውያን ፡

፲፪፤ ክፉዎች ፡ ሰዎችም ፡ ጠሉት ፡ በንጉሥም ፡
ዘንድ ፡ ነገር፡ ሠሩበት ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፡
እነሆ ፡ አባ ፡ በርሱማ ፡ እንደ ፡ ዓለም፡ ሰው፡
ሁኖ ፡ ይበላል፡ ይጠጣል ፡ መልካም ፡ ልብ
ስንም ፡ ይለብሳል ፡ ንጉሥም፡ ስለ አባ ፡
በርሱማ ፡ የተነገረውን ፡ ያረጋግጥ ፡ ዘንድ፡
ከባለሟሎቹ ፡ አንዱን ፡ ላከ። የንጉሡም ፡
ባለሟል፡ ወደ፡ አባ፡ በርሱማ፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡
በእርሱ ፡ ላይ ፡ ከተነገረው ፡ ምንም ፡ ምን፡
ያገኘው ፡ የለም፡ ከዚህም፡ በኋላ ፡ ወደ፡
ንጉሥ፡ ወሰደው፡ ንጉሥም ፡ ቀድሞ ፡ ከሚያ
ውቀው ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ሥራው ፡ ልውጥ ፡
ሁኖ ፡ ያገኘው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ንጉሡም ፡
ታላቅ፡ ክብርን፡ አከበረው፡ ወደ፡ ቦታውም፡
መለሰው።

፲፫፤ መናፍቁ ፡ ንጉሥ ፡ መርቅያንም ፡ የኬልቄ
ዶንን፡ ጉባኤ፡ በሰበሰበ፡ ጊዜ፡ የንጉሥ፡ አማ
ካሪዎች ፡ አባ ፡ በርሱማን፡ እንዳያስመጣ ፡
ንጉሡን ፡ መከሩት ፡ እንደማይፈራና ፡ እንደ
ማያፍር ፡ ለሰው ፡ ፊትም ፡ እንደማያዳላ ፡
ተከራክሮ ፡ ረትቶ ፡ እንደሚያሳፍራቸውም ፡
ስለሚያውቁ ፡ ነው።

፲፬፤ አንዱን ፡ ክርስቶስን ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ የከፋፈ
ሉበት ፡ ይህ ፡ ጉባኤ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡
የከበረ፡ አባ ፡ በርሱማ ፡ ተጣላቸው ፡ ነቀ
ፋቸው ፡ ቃላቸውንም ፡ በመሻር ፡ አወገ
ዛቸው፡ እነርሱም፡ ወደ፡ ንጉሥ፡ ወንጅለው፡
በጽሑፍ፡ ከሰሱት፡ ንጉሡም፡ ልኮ፡ ወደርሱ፡
አስቀረበው፡ ግን፡ በላዩ፡ ስለ፡ አደረ፡ መንፈስ፡
ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ሊቃወመው ፡ አልቻለም ፡
በሊቁ፡ ቅዱስ፡ ዲዮስቆሮስ፡ ላይ፡ ስለ፡ አደረ
ገችው ፡ ክፋት ፡ ንግሥቲቱን ፡ ረገማት ፡
ከጥቂት፡ ቀንም፡ በቀር፡ አልኖረችም፡ በክፉ፡
አሟሟትም፡ ሞተች።

፲፭፤ ከዚህም፡ በኋላ፡ መናፍቃን፡ የሚቃወሙት፡
ሆኑ ፡ ምእመናን ፡ እንዳይታዘዙለት ፡ ወደ ፡
ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ ጽፈው ፡ የሚልኩ ፡ ሆኑ ፡
እነርሱ ፡ ግን ፡ አልተቀበሏቸውም ፡ ለእርሱ ፡
መታዘዛቸውንም፡ አልተዉም።

፲፮፤ ዳግመኛም፡ በጐዳና፡ ሽምቀው፡ ይገድሉት፡
ዘንድ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ መናፍቃን ፡ ሰዎች ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይጽንሕዎ ፡ በፍኖት ፡ ወይቅትልዎ ፡ ወለአኩ፡ኀቤሁ፡ከመ፡ይምጻእ፡ወይሑር፡ ምስሌሆሙ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ኀቡረ። ወሶበ ፡ መጽአ ፡ ወአንሶሰወ ፡ ምስሌሆሙ፡ነሥኡ፡አዕባነ፡ወወገርዎ፡ ወኮኑ፡አዕባኒሆሙ፡ዘይትመየጡ፡ዲበ፡ ርእሶሙ፡ወጐዩ፡እምኔሁ፡በፍርሀት።

፲፯፣ ወሶበ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያውጽኦ፡ እመዋቅሕተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ፈነወ፡መልአኮ፡ወይቤሎ፡እምድኅረ፡፬ቱ፡ መ ዓልት፡ ትፈልስ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ። ወሶቤሃ ፡ ፈነወ፡ ረድኦ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡ እለ፡የዐውድዎ፡ከመ፡ይናዝዞሙ፡ለመሃይ ምናን፡ወእንዘ፡የዐውድ፡ረድእ፡በጽሐ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ሀለወት ፡ ርእሱ ፡ ለቅዱስ፡ዮሐንስ፡መጥምቅ፡ወተአምኃ፡ ለርእሰ ፡ ዮሐንስ ፡ ቅድስት ፡ ወበከየ፡ ወሰአለ፡ በብካይ ፡ በእንተ ፡ መርቅያን ፡ ንጉሥ፡ዓላዊ፡ወወጽአ፡ ቃል፡እምርእሰ፡ ዮሐንስ፡መጥምቅ፡ዘይብል፡ኢትፍራህ፡ እስመ፡ ውእቱ፡መርቅያን፡ሞተ፡እስመ፡ ሰከየ፡አባ፡በርሱማ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ ወቅዱስ፡አባ፡በርሱማ፡ባረኮ፡ ለረድኡ፡ ወአዕረፈ፡በሰላም፡ወአስተርአየ፡ዓምደ፡ ብርሃን፡ኀበ፡አንቀጸ፡በአቱ፡ዘይበጽሕ፡ እምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይ ። ወርእይዎ ፡ ኵሎሙ ፡ መሃይምናን ፡ እምርኁቅ ፡ ወመጽኡ፡ኀቤሁ፡ወረከብዎ፡በዘአዕረፈ፡ ወተባረኩ፡እምሥጋሁ፡ወበከዩ፡ላዕሌሁ፡ በእንተ ፡ ተፈልጠቶሙ ፡ እምኔሁ ፡ ወገነዝዎ፡በከመ፡ ይደሉ፡ በዝማሬ፡ወበማ ኅሌት፡ወአንበርዎ፡ውስተ፡መቃብር።

፲፰፣ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፱፣ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማተ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ ሶርያዊ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁ፡ ሶርያውያን፡ ወእሙንቱ፡ ነጋ ድያን፡እለ፡የኀድሩ፡ውስተ፡ሀገረ፡እስክን ድርያ፡ወእምዝ፡ኮኑ፡ዘየኀድሩ፡በሀገረ፡ እስሙናይን።

ከመናፍቃን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ጋር ፡ ተስማ ምተው፡ወደ፡እርሳቸው፡እንዲመጣና፡በአ ንድነት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ሚሔዱ ፡ ሁነው ፡ ላኩበት ፡ መጥቶም ፡ አብሮ፡ በተጓዘ ፡ ጊዜ ፡ ደንጊየዎችን ፡ አንሥተው፡ጣሉበት፡ደንጊያዎቻቸውም፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ የሚመለሱ ፡ ሆኑ ፡ በፍር ሃትም፡ከእርሱ፡ሸሹ።

፲፯፣ እግዚአብሔርም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እሥረ ኛነት ፡ ሊአወጣው ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ መል አኩን፡ወደርሱ፡ልኮ፡ከአራት፡ቀን፡በኋላ፡ ከዓለም፡እንደሚፈልስ፡ነገረው፡በዚያንም፡ ጊዜ፡በዙሪያው፡ወዳሉ፡አገሮች፡ ምእመ ናንን፡ያጽናናቸው፡ዘንድ፡ረድኡን፡ላከው፡ እርሱም ፡ ሲዞር ፡ የመጥመቁ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ፡ ራስ ፡ ወደምትኖርበት ፡ ቦታ ፡ ደረሰና፡የከበረች፡የቅዱስ፡ዮሐንስን፡ራስ፡ እጅ፡ነሣት፡ስለ፡ከሀዲው፡ስለ፡ንጉሥ፡ መርቅያን፡በማልቀስ፡ለመነ ። እንዲህ ፡ የሚልም፡ ቃል፡ከመጥምቁ፡ዮሐንስ፡ራስ፡ ወጣ፡ አባ፡በርሱማ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ ስለ፡ ከሰሰው ፡ ያ ፡ መርቅያን ፡ ሙቷልና ፡ አትፍራ ። የከበረ፡አባ፡በርሱማ፡ረድኡን፡ ባረከውና፡በሰላም፡አረፈ።ከበአቱም፡ደጃፍ፡ ከምድር፡እስከ፡ሰማይ፡የሚደርስ፡የብርሃን፡ ምሰሶ፡ተተክሎ፡ታየ። ምእመናንም፡ሁሉ፡ ከሩቅ፡አይተው፡ወደርሱ፡መጡ፡አርፎም፡ አገኙት። ከሥጋውም ፡ ተባረኩ ፡ በላዩም ፡ አለቀሱ ፡ ከእርሱም ፡ ስለመለየታቸው ፡ እጅግ፡አዘኑ፡እንደሚገባም፡እየዘመሩና፡ እያመሰገኑ፡ገንዘው፡በመቃብር፡አኖሩት።

፲፰፣ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

፲፱፣ በዚችም፡ዕለት፡የከበረ፡ሶሪያዊ፡ጳውሎስ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወላጆቹ፡የሶርያ፡ሰዎችና፡በእስክንድርያ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ ነጋዴዎች ፡ ናቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በእስሙናይን ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩ፡ሆኑ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፤ ወሶበ ፡ አዕረፉ ፡ አበዊሁ ፡ ኀደጉ ፡ ሎቱ ፡ ብዙኀ፡ ንዋየ ፡ ወእምዝ ፡ ሰምዐ ፡ ከመ፡ ነገሥታት፡ወመኳንንት፡ዐላውያን፡ይኄንንዎሙ፡ለመሃይምናን፡እለ፡የአምኑ፡በክርስቶስ፡ ወይቀትልዎሙ፡ወተንሥአ፡ሶቤሃ፡ ወዘረወ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን። ወእምዝ ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ፡ ይምርሖ ፡ ፍኖተ ፡ ዘሠምረ፡ ወፈነወ፡ እግዚእነ ፡ መልአኮ፡ ሱርያልሃ ፡ ኀቤሁ ፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ፡ ዘይበጽሖ ፡ ኵነኔ ፡ በእንተ ፡ ስሙ፡ ለክርስቶስ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት፡ ወይቤሎ፡ ናሁ ፡ አዘዘኒ፡እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ አሀሉ ፡ ምስሌከ ፡ ወአጽንዕከ፡ ወኢትፍራህ።

፳፩፤ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ወሖረ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እንዴናው ፡ ወተአመነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በቅድመ፡ መኰንን፡ ወአዘዘ ፡ መኰንን ፡ ያዕርቅዎ ፡ አልባሲሁ ፡ ወይቅሥፍዎ ፡ በአስዋጥ ፡ ወገብሩ ፡ ቦቱ ፡ ዘንተ ፡ ወእምዝ፡ ገብሩ ፡ መኃትወ ፡ ውስተ ፡ ገበዋቲሁ ፡ ወኢለከፈቶ፡እሳት፡ግሙራ።ወአምጽአ፡ሎቱ፡ መኰንን ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ፡ ከመ ፡ ይስግድ ፡ ለጣዖት ፡ ወይቤሎ፡ ብፁዕ፡ ጳውሎስ ፡ ሶበ ፡ ሞቱ ፡ አበውየ፡ ኀደጉ ፡ ሊተ ፡ ፲ ወ ፺ተ ፡ መካልየ ፡ ወርቅ ፡ ወአነ፡ መነንክዎ ፡ ወዘረውክዎ ፡ ለነዳያን ፡ በእንተ ፡ ፍቅሩ ፡ለክርስቶስ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡ እፎ፡ እትመየጥ፡ ኀበ፡ንዋይከ፡ምኑን።

፳፪፤ ወሰሚዖ ፡ መኰንን ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ያርስኑ ፡ ኀፃውንተ፡በእሳት፡ወይደይዎሙ፡በአፉሁ፡ ወዕዘኒሁ ፡ ወገብሩ ፡ ቦቱ ፡ ዘንተ ፡ ወወረደ ፡ መልአክ ፡ ሱርያል ፡ ገሠሦ ፡ ወአሕየዎ ፡ ወካዕበ ፡ ሰደዱ ፡ ላዕሌሁ ፡ አክይስተ ፡ ወኢለከፍዎ ፡ ወመተሩ ፡ ልሳኖ ፡ ወአሕየዎ ፡ እግዚእነ።

፳፫፤ ወሶበ ፡ ሖረ ፡ መኰንን ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ነሥአ ፡ ምስሌሁ ፡ ወአስተርአዮ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በውስተ፡ ሐመር ፡ ወናዘዞ ፡ ወአጽንዖ ። ወሀለዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ዐርክ ፡ ዘስሙ ፡ ኤሲ ፡ ወቴ

፳፤ ወላጆቹም ፡ ሲሞቱ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ተዉለት፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከሀድያን ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡በክርስቶስ፡ የሚያምኑ ፡ ምእመናንን ፡ እንደሚያሠቃዩአቸውና ፡ እንደሚገድሏቸው ፡ ሰማ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ በተነ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የወደደውን ፡ መንገድ፡ ይመራው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ጸለየ፡ ጌታችንም ፡ መልአኩን ፡ ሱርያልን ፡ ላከ ፡ እርሱም፡ በክብር፡ ባለቤት ፡ክርስቶስ፡ ስም፡ የሚደርስበትን ፡ ሥቃይ ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ፡ እነሆ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እንድኖር ፡ እንዳጸናህም፡እግዚአብሔር፡ አዞኛልና ፡ አትፍራ፡ አለው።

፳፩፤ በዚያንም፡ጊዜ፡ተነሥቶ፡ወደ፡እንዴናው፡ ከተማ ፡ ሔደ ፡ በመኰንኑም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታመነ ፡ መኰንኑም ፡ ልብሱን ፡ አራቁተው ፡ ይገርፉት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ይህንንም ፡ አደረጉበት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በጐኖቹ ፡ ውስጥ ፡ መብራቶችን ፡ አስገብተው ፡ ለበለቡት ፡ እሳት ፡ ግን ፡ አልነካችውም፡መኰንኑም፡ለጣዖት፡እንዲሰግድ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አመጣለት ፡ የተመሰገነ ፡ ጳውሎስም ፡ ወላጆቼ ፡ ሲሞቱ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት፡ የወርቅ ፡ መክሊት ፡ ትተውልኝ ፡ ነበር። ስለ ፡ ክብር ፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስ ፡ ፍቅር፡ ትቼ ፡ ለድኆች ፡ መጸወትኩት ፡ ወደዚህ ፡ ወደተናቀ ፡ ገንዘብህ ፡ እንዴት ፡ እመለሳለሁ፡አለው።

፳፪፤ መኰንኑም ፡ ሰምቶ ፡ ብረቶችን ፡ በእሳት ፡ አግለው፡በአፉና፡በጆሮዎቹ፡እንዲጨምሩ፡ አዘዘ ፡ ይህንንም ፡ አደረጉበት ፡ ሱርያል ፡ መልአክም ፡ ወርዶ ፡ ዳሠሠውና ፡ አዳነው ፡ ሁለተኛም ፡ እባቦችን ፡ በላዩ ፡ ሰደዱ ፡ አልነኩትም ፡ ምላሱንም ፡ ቆረጡ ፡ ጌታችንም ፡ አዳነው።

፳፫፤ መኰንኑም ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ከተማ ፡ በሚሔድ ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወሰደው ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም፡ በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ ተገለጠለትና ፡ አጽናናው፡የዚህም፡ቅዱስ፡ኤሲ፡የሚባል፡

ክላ፡እኅቱ፡ወነገሮ፡እግዚእነ፡ከመ፡ሥጋሁ፡
ይከውን፡ምስለ፡ሥጋሆሙ፡ወነፍሱ፡ምስለ፡
ነፍሶሙ፡ወሀለዉ፡አሜሃ፡እሉ፡ቅዱሳን፡
ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡በሀገረ፡እስክንድርያ፡
ወሶበ፡በጽሐ፡ኀቢሆሙ፡ቅዱስ፡ጳውሎስ፡
ተአምኁ፡በበይናቲሆሙ፡ተፈሥሐት፡ነፍ
ሶሙ፡በተራክቦቶሙ፡ወሰብሕዎ፡ለእግዚአ
ብሔር።

፳፬፤ ወጊዜ፡ተመይጦቱ፡ለመኰንን፡ሀገረ፡
እንዴናው፡መተሩ፡ርእሶ፡ለቅዱስ፡ጳው
ሎስ፡ ወወረዉ፡ሥጋሁ፡ውስተ፡ሐይቀ፡
ባሕር፡ወነሥአ፡አክሊለ፡ስምዕ፡በመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ወነሥኡ፡መሃይምናን፡
ሥጋሁ፡በኅቡእ፡ወገነዝዎ፡በአልባስ፡
ሠናያት፡ወኀብእዎ፡በኀቢሆሙ፡ወተከ
ሥቱ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡እምኔሁ።

፳፭፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡
ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ወዳጅ፡ኢለው፡እኅቱ፡ቴክላም።ጌታችንም፡
ሥጋው፡ከሥጋቸው፡ነፍሱ፡ከነፍሳቸው፡
ጋር፡እንደሚሆን፡ነገረው፡ያን፡ጊዜ፡እሊህ፡
ቅዱሳን፡በእስክንድርያ፡ከተማ፡በእሥር፡
ቤት፡ነበሩ፡የከበረ፡ጳውሎስም፡ወደር
ሳቸው፡በደረሰ፡ጊዜ፡እርስበርሳቸው፡
ተሳሳሙ፡በመገናኘታቸውም፡ነፍሳቸው፡
ደስ፡ብሏት፡እግዚአብሔርን፡አመሰገኑት።

፳፬፤ መኰንኑም፡ወደ፡እንዴናው፡ከተማ፡
በሚመለስ፡ጊዜ፡የቅዱስ፡ጳውሎስን፡ራስ፡
ቆርጠው፡ሥጋውን፡ከጥልቅ፡ባሕር፡
ወረወሩ፡የሰማዕትነትንም፡አክሊል፡በመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ፡ምእመናንም፡
ሥጋውን፡በሥውር፡ወስደው፡በአማሩ፡
ልብሶች፡ገነዙት፡በእነርሱም፡ዘንድ፡
አኖሩት፡ከእርሱም፡ድንቆች፡ተአምራቶች፡
ተገለጡ።

፳፭፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛ
ንም፡በጸሎቱ፡ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡
ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለጳውሎስ፡ቅሡፈ፡ዘባን፡በተጠብጥቦ።ወበመኃትው፡ነድ፡ውዑየ፡ገቦ።ሱርያል፡መልአክ፡
እንዘ፡ይሜግቦ።በድሮ፡ፈጺሞ፡ወሃይማኖቶ፡ዐቂቦ።ዘምስለ፡ኤሲ፡ወቴክላ፡ተወፈየ፡ዐስቦ።

፳፮፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሩ፡ለቅዱስ፡ጴጥሮስ፡
ሰማዕት፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ወስብ
ሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩
አምላክ፡አመ፡፲ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡
ሰማዕተ፡ቅዱስ፡ያዕቆብ፡ወልደ፡እልፍዮስ፡
ሐዋርያ፡፩እም፲ወ፪ቱ፡ሐዋርያት።

፪፤ ወዝንቱ፡ሐዋርያ፡እምድኅረ፡ሰበከ፡ውስተ፡
አህጉር፡ብዙኃት፡ተመይጠ፡ኀበ፡ኢየሩ
ሳሌም፡ወቦአ፡ምኵራበ፡ወሰበከ፡ገሀደ፡
ሃይማኖተ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሎቱ፡ስብሐት፡መሠጥዎ፡አይሁድ፡ወረሰዩ፡
ደሞ፡ላዕለ፡ርእሶሙ፡ወአብጽሕዎ፡ኀበ፡ቀላ
ውዴዎስ፡ንጉሥ፡ዘኮነ፡ህየንቴሁ፡ለንጉሠ፡
ሮም፡ወአስተዋደይዎ፡ለቅዱስ፡ሐዋርያ፡
ያዕቆብ፡ወይቤልዎ፡እስመ፡ዝንቱ፡ብእሲ፡
ይሰብክ፡ለነ፡ካልአ፡ንጉሠ፡ዘእንበለ፡ቄሣር፡

፳፮፤ በዚችም፡ቀን፡የከበረ፡ሰማዕት፡ጴጥሮስ፡
መታሰቢያው፡ነው፡ለእግዚአብሔርም፡
ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

* * *

፩፤ አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ዐሥር፡
በዚች፡ቀን፡ከዐሥራ፡ሁለቱ፡ሐዋርያት፡
አንዱ፡የዕልፍዮስ፡ልጅ፡የከበረ፡ሐዋርያ፡
ያዕቆብ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፪፤ ይህም፡ሐዋርያ፡በብዙ፡ሀገሮች፡ውስጥ፡
ከሰበከ፡በኋላ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ተመለሰ፡
ወደ፡ምኵራብም፡ገብቶ፡የክብር፡ባለቤት፡
የጌታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ሃይማኖት፡
በግልጥ፡አስተማረ።አይሁድም፡ደሙ፡
በእኛ፡ላይ፡ይሁን፡ብለው፡ከሕዝብ፡መካ
ከል፡ነጥቀው፡ወሰዱት፡ለሮም፡ንጉሥ፡
እንደራሴ፡ለንጉሥ፡ቀላውዴዎስም፡አቀረ
ቡትና፡ይህ፡ሰው፡ስለ፡ቄሣር፡ሳይሆን፡ስለ፡
ሌላ፡ንጉሥ፡ይሰብካል፡ብለው፡ወነጀሉት፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሰሚያ ፡ ንጉሥ ፡ አዘዘ ፡ ይገርዎ ፡ በአዕባን ፡ አይሁድኒ ፡ አስተፋጠኑ ፡ ወወገርዎ ፡ ወመጠው፡ ነፍሶ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወነሥኡ ፡ ሥጋሁ ፡ መሃይምናን ፡ ወገነዝዎ ፡ ወቀበርዎ።

፫፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ለሐዋርያ፡ያዕቆብ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ንጉሡም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በደንጊያ ፡ እንዲወግሩት፡አዘዘ፡አይሁድም፡ፈጥነው፡ወገሩት፡ነፍሱንም ፡ በጌታችን ፡ እጅ ፡ ሰጠ ፡ ምእመናንም፡ሥጋውን፡ወስደው፡ገንዘው፡ቀበሩት።

፫፤ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በሐዋርያ ፡ ያዕቆብ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለያዕቆብ፡ ሐዋርያሁ፡ወሰማዕቱ።ለክርስቶስ፡ ዘኮነ፡በውስተ፡ዓለም፡አስተርእዮቱ።ፈጺሞ፡ምንዳቤ፡እንተ፡ተውህበት፡ሎቱ። ሶበ፡በጽሐ፡ዕድሜሁ፡ወተዳደቀ፡ዕለቱ። በውግረተ፡ዕብን፡ኮነ፡ለያዕቆብ፡ሞቱ።

፩፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡ዮስጦስ፡ወልደ፡ኑማርያኖስ፡ንጉሥ።

፪፤ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡እንዘ፡ሀሎ፡ውስተ፡ጸብእ፡ተወስበት፡እኅቱ፡ለዲዮቅልጥያኖስ፡ከሀዲ፡ወረሰየቶ፡ንጉሠ፡ወሶበ፡ገብአ፡እምጸብእ፡ረከቦ፡ለዲዮቅልጥያኖስ፡በዘክህዶ፡ለክርስቶስ፡ንጉሠ፡ስብሐት፡ወኀዘነ፡ጥቀ።

፫፤ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ተጋብኡ ፡ ኀቤሁ፡ወይቤልዎ፡ንሕነ፡ንቀትሎ፡ለዲዮቅልጥያኖስ፡ወአንተ፡እግዚእነ፡ትነብር፡ዲበ፡መንበረ፡መንግሥትከ፡ውእቱሰ፡ኢፈቀደ፡ዘንተ፡ወከልአሙ፡ከመ፡ኢይቅትልዎ፡እስመ፡ኀረየ፡መንግሥተ፡ሰማያዊተ፡እምነ፡መንግሥት፡ምድራዊት።

፬፤ወእምዝ፡ቀርበ፡ኀበ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ንጉሥ፡ወተአመነ፡በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወይቤሎ፡ንጉሥ፡መኑ፡አገበረከ፡ኦ፡እግዚእየ፡ዮስጦስ፡ከመ፡ትግበር፡ ዘንተ፡እስመ፡ንጉሥ፡ፈርሀ፡ፈድፋደ፡እምኔሁ፡ወይቤሎ፡ቅዱስ፡ዮስጦስ፡ሕያው፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ስብሐት፡ለእመ፡ኢጸሐፍከ፡ስምዕየ፡ወእመ፡አኮ፡አነ፡አነሥኦሙ፡ለሕዝብየ፡ላዕሌከ፡ወያወጽኡከ፡እመንግሥትከ። ወፈርሀ፡ሶቤሃ፡ወአዘዘ፡ከመ፡ይሰድዎ፡ኀበ፡ብሔረ፡ግብጽ፡ምስለ ፡ ታውክልያ ፡ ብእሲቱ ፡ ወአቦሊ ፡ ወልዱ ፡ ወአዘዞ ፡ ለመኰንነ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ፡ከመ፡ይኊጠሙ፡ብዙኀ፡ወኢያኀዝን፡ልቦሙ፡ዮጊ፡ለእመ፡ይትመየጥ፡ልቦሙ፡

፩፤ በዚችም፡ዕለት፡የንጉሥ፡ኑማርያኖስ፡ልጅ፡የከበረ፡ዮስጦስ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፪፤ ይህም፡ቅዱስ፡በጦር፡ሜዳ፡እያለ፡እኅቱ፡ከሀዲ፡ዲዮቅልጥያኖስን፡አግብታ፡ንጉሥም፡አደረገችው፡ከጦርነትም፡በተመለሰ፡ጊዜ፡የክብር፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስን ፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡ክዶ፡አገኘውና፡እጅግ፡አዘነ።

፫፤የሀገሩም፡ሰዎች፡በአዩት፡ጊዜ፡ወደርሱ፡ተሰብስበው፡ዲዮቅልጥያኖስን፡እኛ፡እንገድለዋለን፡አንተም፡ጌታችን፡በመንግሥትህ፡ዙፋን፡ላይ፡ትቀመጣለህ፡አሉት፡እርሱ፡ግን፡ ይህን፡ስለአልፈለገ፡እንዳይገድሉት፡ከለከላቸው ፡ ከምድራዊት ፡ መንግሥት ፡ ሰማያዊት፡መንግሥትን፡መርጧልና።

፬፤ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡ንጉሥ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ቀርቦ፡በክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ታመነ፡ንጉሡም፡ፈርቶታልና፡ጌታዬ፡ዮስጦስ፡ሆይ፡ይህን፡ታደርግ፡ዘንድ፡ያስገደደህ ፡ ማነው ፡ አለው ፡ የከበረ ፡ ዮስጦስም፡ በምስክርነቴ፡ደሜን፡እንዳፈስ፡ካልጻፍክ፡ሕዝቡን፡በአንተ፡ላይ፡አስነሥቼ፡ከመንግሥትህ፡እንደማስወጣህ፡የክብር፡ባለቤት፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሕያው፡ነው፡ብሎ፡ማለ። በዚያንም፡ጊዜ፡ንጉሡ፡ፈርቶ፡ከሚስቱ፡ከታውክልያ፡ከልጁ፡ከአቦሊ፡ጋር፡ወደ፡ግብጽ፡አገር፡እንዲወስዱአቸው፡አዘዘ፡የእስክንድርያንም፡ገዥ፡አብዝቶ፡እንዲሸነግላቸው፡ምናልባት፡ልባቸው፡ቢመለስ፡እንዳያሳዝናቸውም፡አለዚያ፡እያንዳንዱን፡እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

ወእመ፡አኮ፡ይፍልጠሙ፡ለለ፩ዱ።

፰፤ ወሶበ፡በጽሑ፡ብሔረ፡ግብጽ፡ወምስሌሆሙ፡ አግብርት፡ወመጽሐፈ፡መልእክቱ፡ለንጉሥ፡ ወሶበ ፡ ርእዮሙ ፡ መኰንነ ፡ ሀገረ ፡ እስክን ድርያ ፡ ፈርሀ ፡ ፈድፋደ ፡ ወአኀዘ ፡ ይኂጦ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮስጦስ ። ወይቤሎ ፡ ኢትግበር ፡ ዘንተ፡እግዚእየ፡እስመ፡ይኄይሰከ፡ክብርከ፡ ወይቤሎ፡ቅዱስ፡ዮስጦስ፡ኢታብዝኀ፡ነገረ፡ ወፈርሀ ፡ መኰንን ፡ ወፈነዎ ፡ ኀበ ፡ ላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ ለዮስጦስ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እንጼናው ፡ ወለወልዱ፡አቦሊ፡ኀበ፡ሀገረ፡ብስጣ፡ወለታ ውክልያ፡ብእሲቱ፡ኀበ፡ሀገረ፡፶፡ወወሀቦሙ፡ ፩ደ፡ ፩ደ ፡ ገብረ ፡ ዘይትለአኮሙ ፡ እምአግብ ርቲሁ፡ወበሀገረ፡እንጼናው፡መተርዎ፡ርእሶ፡ ለቅዱስ፡ዮስጦስ፡እምድኅረ፡ኰነንዎ፡ብዙኀ፡ ወነሥአ፡አክሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማ ያት፡ወኮኑ፡እምሥጋሁ፡ተአምራት፡ወመን ክራት፡ወፈውስ፡ዐቢይ፡ለድውያን።

፱፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ለሰማዕት፡ወበረከቶሙ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ለያያቸው፡አዘዘው።

፰፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገርም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ከእር ሳቸው ፡ ጋር ፡ የንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ አገልጋ ዮችም ፡ አሉ ፡ የእስክንድርያም ፡ ገዥ ፡ በአያ ቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ፡ ሊሸነግለውም ፡ ጀምሮ፡ ቅዱስ ፡ ዮስጦስን ፡ ጌታዬ ፡ እንዲህ ፡ አታድርግ ፡ ክብርህ ፡ ይሻልሃል ፡ አለው ፡ የከበረ ፡ ዮስጦስም ፡ ነገር ፡ አታብዛ ፡ አለው ፡ መኰንኑም ፡ ፈርቶ ፡ ቅዱስ ፡ ዮስጦስን ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ወደ ፡ እንጼናው ፡ ከተማ ፡ ሰደደው ፡ ልጁ ፡ አቦሊን ፡ ወደ ፡ ሀገረ ፡ ብስጣ ፡ ሚስቱ ፡ ታውክልያን ፡ ወደ ፡ ሀገረ ፡ ፶ ፡ ላካቸው፡ከአገልጋዮቹም፡የሚአገለግሏቸው፡ አንዳንድ፡ሰጣቸው፡የከበረ፡ዮስጦስንም፡በእ ንጼናው ፡ ከተማ ፡ ብዙ ፡ ከአሠቃዩት ፡ በኋላ ፡ ራሱን፡ቆረጡት፡የሰማዕትነት፡አክሊልንም፡ ተቀበለ ፡ ከሥጋውም ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶች፡ ተገለጡ፡ለበሽተኞችም፡ታላቅ፡ፈውስ፡ሆነ።

፱፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም በሰማዕታት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከታቸውም፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ዕፍረተ፡ስሙ፡ጽዑጠ።እምብዝኀ፡ገድሉ፡እንዘ፡እነግር፡ኀዳጠ።ዐሠረ፡ክርስቶስ፡ ይትሉ፡ሶበ፡ዮስጦሳ፡ተፈልጠ።መንገለ፡ወልዱ፡ወብእሲቱ፡ገጾ፡ኢሜጠ።ወአፍቅሮ፡ዘመድ፡ካዕበ፡ በልቡ፡ኤሦጠ።

፲፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡ጽሙድ፡ መስተጋድል ፡ ወማእምር ፡ መምህረ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም፡አባ፡ኤስድሮስ፡ዘእምሀገረ፡ፈርማ።

፲፩፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮኑ ፡ አበዊሁ ፡ ብዑላነ ፡ ወክቡራነ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ምስር ፡ ወኮኑ አዝማደ፡ለአባ፡ቴዎድሮስ፡ወአባ፡ቄርሎስ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወአልቦሙ ፡ ውሉድ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ወመሀ ርዎ፡ኵሎ፡ትምህርተ፡መንፈሳዊተ፡ወኵሎ፡ መጻሕፍተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወዐቀቦሙ፡ ወአጽንዖሙ፡ገሀደ፡ወካዕበ፡ተምህረ፡ትም ህርተ ፡ ዮናናውያን ፡ ወሑረተ ፡ ከዋክብት ፡ ወዑደቶሙ ፡ ዓለመ ፡ ወተለዓለ ፡ ላዕለ ፡ ብዙኃን ፡ በአእምሮቱ ፡ ወበጥበቡ ፡ ወኮነ ፡ ጽሙደ ፡ ወመስተጋድለ ፡ ወትጉሀ ፡ ወት ሑተ።

፲፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በገድል ፡ የተጠመደ ፡ ምሁር ፡ የሆነ ፡ የዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ መምህር ፡ አባ ፡ ኤስድሮስ፡ፈርማ፡ከሚባል፡አገር፡አረፈ።

፲፩፤ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወላጆቹ ፡ በምስር ፡ አገር ፡ የከበሩ ፡ ባለጸጎች ፡ ናቸው ፡ ለእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትም ፡ አባ ፡ ቴዎድሮስና ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ ዘመዶች ፡ ናቸው ፡ ከእርሱም ፡ በቀር፡ ልጅ ፡ የላቸውም ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህ ርትን፡ሁሉ፡የቤተ፡ክርስቲያንንም፡መጻሕ ፍት ፡ ሁሉ ፡ አስተማሩት ፡ ግልጽ ፡ አድርጎ ፡ አጠናቸው ፡ ጠበቃቸውም ፡ ዳግመኛም ፡ የዮ ናናውያንን፡የፍልስፍና፡ትምህርት፡የከዋክ ብትን፡አካሔድና፡ዓለምን፡መዞራቸውን፡ ተማረ፡በእውቀቱና፡በጥበቡም፡ከብዙዎች፡ ከፍ፡ከፍ፡አለ፡በገድልም፡የተጠመደ፡ትሑ ትና፡የሚተጋ፡ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወሶበ፡ሰምዑ፡በእንቲአሁ፡ሰብአ፡አህጉር፡ ተማከሩ ፡ ወተሰነዓዉ ፡ ከመ ፡ ይሢምዎ ፡ ምስለ፡ኤጲስቆጶሳት፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ላዕለ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወወጽአ ፡ ወጕየ ፡ በሌሊት ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ፈርማ ፡ ወመንኰሰ፡በህየ፡ወእምህየኒ፡ፈለሰ፡ኀበ፡ ንስቲት ፡ በዓት ፡ ወነበረ ፡ ውስቴታ ፡ ባሕ ቲቶ፡ብዙኀ፡ዓመታተ፡ወደረሰ፡ድርሳናተ፡ ወተግሣጻተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ፡ነገሥት፡ወመኳንንት፡ወተርጐመ፡ መጽሐፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብሉያተ ፡ ወሐዲሳተ።

፲፫፤ወኍልቆሙ፡ለመጻሕፍቲሁ፡፹ወ፹፪እሉኒ፡ ድርሳናት ፡ ወተግሣጻት ፡ ወተስእሎታት ፡ ወተሰጥዎ ፡ ወመልእክታት ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፡ ወኀበ ፡ መሃይ ምናን፡እስመ፡ውእቱ፡ኮነ፡ዘይጐሥዖሙ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በከመ ፡ ይጐሥዑ ፡ አፍላጋት፡ማያተ።

፲፬፤ወሶበ፡ፈጸመ፡ዘንተ፡ምግባረ፡ኄረ፡ወሐረ፡ ሐረተ ፡ ሠናየ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ርሥእና ፡ ሠናይ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአዕረፈ፡በሰላም።

፲፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፪፤ በሀገሮችም ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ስለርሱ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና፡ይሾሙት፡ዘንድ፡ተማከረው፡ከኤ ጲስቆጶሳቱ፡ጋር፡ተስማሙ። በሌሊትም፡ ወጥቶ ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ፈርማ ፡ ገዳም ፡ ደርሶ ፡ በዚያ ፡ መነኰሰ ፡ ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አንዲት፡አነስተኛ፡ዋሻ፡ገብቶ፡ብቻውን፡ በውስጧ፡ብዙ፡ዘመናት፡ኖረ፡ብዙ፡ድርሳ ናትንና ፡ ተግሣጻትንም ፡ ደረሰ ፡ ከእርሳ ቸውም፡ስለ፡ነገሥታትና፡ስለ፡መኳንንት፡ የደረሳቸው፡አሉ፡የቤተ፡ክርስቲያንን፡መጻ ሕፍቶችን፡ብሉያትና፡ሐዲሳትን፡ተረጐመ።

፲፫፤ የመጻሕፍቶቹም ፡ ቊጥራቸው ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ነው ፡ እሊህም ፡ ድርሳናት ተግሣጻት ፡ ጥያቄዎችና ፡ መልሶች ፡ ወደ ፡ ሊቃነ፡ጳጳሳትና፡ኤጲስቆጶሳት፡የተላኩ፡ መልእክቶች ፡ ናቸው ፡ ወደ ፡ ምእመናንም ፡ ወንዞች፡ውኃዎችን፡እንደሚያፈልቁ፡እርሱ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚያፈልቃቸው ፡ ሆኗ ልና።

፲፬፤ ይህንንም ፡ በጎ ፡ ሥራውን ፡ ሲፈጽም ፡ መል ካም፡ጉዞውንም፡አከናውኖ፡ወደ፡በጎ፡ሽም ግልና፡ደርሶ፡እግዚአብሔርንም፡ አገልግሎ፡ በሰላም፡አረፈ።

፲፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ሰላም፡ለኤስድሮስ፡እብሎ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ ዘጐሥዐ፡መጻሕፍተ፡ጥበብ፡ኵሎ። ፈለሰ፡ ዮም ፡ እምድኅረ ፡ ፈጸመ ፡ ገድሎ ። ወሰላም ፡ ካዕበ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ፊሎ ። ዘንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ በመጥባሕት ፡ ቀተሎ።

፲፮፤ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡አባ፡ፊሎ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ፋርስ ፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አዘዞ፡ንጉሠ፡ፋርስ፡ከመ፡ይሡዕ፡ለእሳት፡ ወይስግድ ፡ ለፀሐይ ፡ ወሶበ ፡ አበዮ ፡ ኰነኖ ፡ ኵነኔ፡ ዐቢየ ፡ ወመተረ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ። ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

፲፯፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኒቆላዎስ፡ወስምዖን፡ወበረከቶሙ፡ተሀሉ፡

፲፮፤ በዚች ፡ ቀን ፡ የፋርስ ፡ ሀገር ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ አባ ፊሎ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ። ይህንንም ፡ ቅዱስ ፡ ለእሳት ፡ እንዲሠዋ ፡ ለፀሐይም ፡ እን ዲሰግድ ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ አዘዘው ፡ እምቢ ፡ በአለውም ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ሥቃይን ፡ አሠቃ ይቶ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጠው ፡ በመን ግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሰማዕትነትን ፡ አክሊል፡ ተቀበለ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ለእ ግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ይገባል፡አሜን።

፲፯፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የከበሩ ፡ የኒቆላዎስና ፡ የስ ምዖን ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ ለእግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡ አመ፡፲ወ፩ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡ ኮነ፡ሰማዕተ፡አብ፡ቅዱስ፡በላትያኖስ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ዘሮሜ።

፪፤ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ጠቢብ፡ወማእምር፡ወመስተ ጋድል ፡ ገድለ ፡ ዐቢየ ፡ ወተሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ወነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበረ፡ጴጥሮስ፡፲ወ፪ተ፡ዓመተ፡በሰላም፡ እንዘ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ሃይማኖተ ፡ ርትዕተ ፡ ወሶበ ፡ ተንሥአ ፡ ላዕለ ፡ ቀላው ዴዎስ፡ንጉሥ፡መኰንን፡ፊልጶስ፡ወቀተሎ፡ ለንጉሥ ፡ ወነግሠ ፡ ህየንቴሁ ፡ ወአምጽአ ፡ ምንዳቤ፡ዐቢየ፡ላዕለ፡መሃይምናን፡ወብዙ ኃን፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡በእደዊሁ፡ለዝንቱ፡ንጉሥ፡ ዳኬዎስ።

፫፤ ወበመዋዕሊሁ፡ጕዩ፡፯ቱ፡ደቂቅ፡እለ፡ኖሙ፡ ውስተ፡በዓት፡፫፻ተ፡ወ፸ወ፪ተ፡ዓመተ፡ወው እቱ፡ሐነፀ፡ምኵራብ፡በሀገረ፡ኤፌሶን፡ወአን በረ፡ውስቴቱ፡ጣዖታተ፡ወአገበሮሙ፡ለኵ ሎሙ፡ሰብእ፡ይሡዑ፡ለጣዖታት፡ወለእለሂ፡ ኢሦዑ፡ለጣዖታት፡ቀተሎሙ።

፬፤ ወሶበ፡ሰምዐ፡ንጉሥ፡ከመ፡ዝንቱ፡ቅዱስ፡በላ ትያኖስ፡ይትቃረን፡አምልኮ፡ጣዖታት፡ወይ ሜህሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ይጽንዑ ፡ በሃይ ማኖተ ፡ክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡ ፈነወ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ይሡዕ ፡ ለጣዖ ታቲሁ፡ ውእቱሰ ፡ ኢሰምዐ ፡ ቃሎ ፡ አላ ፡ ተሣ ለቀ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወረገመ ፡ አማልክቲሁ ፡ ወተ ምዐ፡ንጉሥ፡ወኰነኖ፡ኵነኔ፡ጽኑዐ፡መጠነ፡ አሐቲ፡ዓመት፡ወሶበ፡ደክመ፡እምኰንኖቱ፡ መተረ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፭፤ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐ ረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓ ለመ፡ዓለም፡አሜን።

ሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡አባት ፡ በላትያኖስ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ።

፪፤ ይህም፡ቅዱስ፡ብልህና፡አዋቂ፡የሆነ፡ታላቅ፡ ተጋድሎን ፡ የሚጋደል ፡ ነው ፡ በሮሜ ፡ ሀገርም፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሹሞ ፡ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት፡ በሰላም፡ኖረ፡ሕዝቡን፡የቀናች፡ሃይ ማኖትን፡እያስተማራቸው፡ሳለ፡መኰንኑ፡ ፊልጶስ ፡ በንጉሥ ፡ ቀላውዴዎስ ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ በገደለው ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ነገሠ፡በምእመናንም፡ላይ፡ታላቅ፡መከራን፡ አመጣ ፡ በዚህ ፡ በንጉሥ ፡ ዳኬዎስ ፡ እጅ ፡ ብዙዎች፡በሰማዕትነት፡ሞቱ።

፫፤ በዘመኑም ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ ከእርሱ ፡ ሸሹ ፡ ሦስት፡መቶ፡ሰባ፡ሁለት፡ዓመት፡ተኝተው፡ ነቁ፡እርሱም፡በኤፌሶን፡ከተማ፡መስጊድ፡ ሠርቶ ፡ በውስጡ ፡ ጣዖታትን ፡ አኖረ ፡ ሰዎ ችን ፡ ሁሉ ፡ ለጣዖታት ፡ እንዲሠዉ ፡ አስገደ ዳቸው ፡ ለጣዖታት ፡ ያልሠዉትንም ፡ ገደላ ቸው።

፬፤ ይህ ፡ የከበረ ፡ በላትያኖስም ፡ የጣዖታት ፡ አምልኮን ፡ እንደሚቃወም ፡ ሕዝቡም ፡ በክ ብር ፡ ባለቤት ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚያስተምር ፡ ንጉሥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ አገር ፡ ልኮ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ከተማ ፡ አስመጣውና ፡ ለጣዖታት ፡ እንዲሠዋ ፡ ለመነው ። እርሱ ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ አልሰማም ፡ ተሣለቀበት ፡ አማልክቶቹንም ፡ ረገመ ፡ እንጂ ፡ ንጉሡም ፡ ተቆጣ ፡ አንዲት ፡ ዓመት ፡ ያህልም ፡ ጽኑዕ ፡ ሥቃይን ፡ አሠቃ የው፡ማሠቃየቱንም፡በሰለቸ፡ጊዜ፡በሰይፍ፡ ራሱን ፡ ቆረጠው ፡ የምስክርነት ፡ አክሊ ልንም፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ።

፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለበላትያኖስ፡በመንበረ፡ጴጥሮስ፡ዘተሠይመ። አመ፡ጸአለ፡ጣዖቶ፡ወአማልክቲሁ፡ረገመ። በኑኀ፡ዓመት፡ነጺሮ፡እንዘ፡ይትዔገሥ፡ሕማመ። እምኰንኖቱ፡ሶበ፡ዳኬዎስ፡ደክመ፡በአፈ፡መጥባሕት፡ክሣዶ፡ገዘመ።

፳፯፥ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አባ ፡ አውሎግ ፡ አንበሳዊ ፡ መስተጋድል ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁ ፡ እምሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ ወፍጹማን ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ወብዑላን ፡ በወርቅ ፡ ወብሩር።

፳፰፥ ወመሀርዎ ፡ ለወልዶሙ ፡ ኵሎ ፡ ትምህርተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ አዕረፉ ፡ አበዊሁ ፡ ወኀደጉ ፡ሎቱ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ።

፳፱፥ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ተዘከረ ፡ አውሎግ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘይቤ ፡ ሢጥ ፡ ዘብከ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወፁር ፡ መስቀለ ፡ ሞትከ ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ፡ ወበጊዜሃ ፡ ዘረወ ፡ ኵሎ፡ንዋዮ፡ለነዳያን፡ወለምስኪናን፡ወሖረ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ አውሎጊን ፡ ውእቱኒ ፡ ተወክፎ ፡ በፍሥሓ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ እምቅድመ ፡ ይምጻእ ፡ ኀቤሁ ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዘይቤሎ ፡ ናሁ ፡ ወሬዛ ፡ ይመጽእ ፡ ኀቤከ ፡ ተወከፎ ፡ ወደምሮ ፡ ምስለ ፡ አኃው ፡ እለ፡ ይትለአኩ፡ወነበረ፡እንዘ፡ያሜክሮ፡መጠነ፡ ፫ዓመት፡ወሶበ፡ርእየ፡ቅድስናሁ፡ፍጹመ፡ አልበሶ፡አልባሰ፡ምንኵስና፡ወአስኬማ፡ዘመላእክት።

፴፥ ወነበረ፡በፃማ፡ብዙኀ፡እንዘ፡ይጸውም፡እምሰንበት፡እስከ፡ሰንበት፡ወመብልዑኒ፡ኅብስት፡ ወዔው፡ወይጼሊ፡፲፪ተ፡ጸሎታተ፡ዘምስለ፡ ሰጊድ፡መዓልተ፡ወሌሊተ፡ወኢይነውም፡ ወነበረ፡በዝንቱ፡ገድል፡፵፡ዓመተ።

፴፩፥ ወእምዝ ፡ አስተብቍዖ ፡ ለመምህሩ ፡ አባ ፡ አውሎጊን፡ከመ፡ይፈንዎ፡ወሖረ፡ውስተ፡ ገዳም፡ወቦአ፡ውስተ፡ንስቲት፡በዓት፡ወነበረ፡ በህየ፡ እንዘ፡ይትጋደል፡፶ዓመተ፡ወወሀቦ፡ እግዚአብሔር ፡ ፪ተ ፡ አናብስተ ፡ ዘይትለአክዎ፡ ለኵሉ ፡ መፍቅዱ ፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ሐመ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለአናብስት ፡ እፈቱ ፡ እስተይ ፡ ማየ ፡ ምውቀ ። ወሖረ ፡ ፩ አንበሳ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ወረከበ ፡ ኖላዌ ፡ ወአብጽሖ ፡

፳፯፥ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ተጋዳዩ ፡ ባለ ፡ አንበሳው፡ አውሎግ፡ አረፈ፡ የዚህ፡ ቅዱስ፡ ወላጆች፡ ከሀገረ ፡ ንጽቢን ፡ የሆኑ ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ፍጹማን፡ በወርቅና ፡ በብርም ፡ የበለጸጉ ፡ ናቸው።

፳፰፥ ለልጃቸውም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት፡ ሁሉ፡ አስተማሩት፡ ከጥቂት፡ ቀኖች፡ በኋላ፡ ወላጆቹ፡ ብዙ፡ ገንዘብን፡ ትተውለት፡ ሞቱ።

፳፱፥ በአንዲትም፡ ዕለት፡ አውሎግ፡ ያለህን፡ ገንዘብህን ፡ ሁሉ ፡ ሽጠህ ፡ ለድኆች ፡ ስጥተህ፡ መከራ ፡ መስቀልህን ፡ ተሸክመህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ የሚለውን ፡ የከበረ ፡ የወንጌልን ፡ ቃል፡ አሰበና ፡ ወዲያውኑ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለድኆችና፡ለችግረኞች፡በትኖ፡ወደ፡አባ፡ አውሎጊን ፡ ሔደ ፡ እርሱም ፡ በደስታ ፡ ተቀበለው። ስለ፡ርሱ፡እንዲህ፡የሚለውን፡ ራእይ ፡ አይቶ ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡ ወዳንተ ፡ ጐልማሳ፡ይመጣል፡ተቀበለውና፡ከሚያገለግሉ፡መነኰሳት፡ጋር፡ቀላቅለው፡እየፈተነውም፡ሦስት፡ዓመት፡ያህል፡ኖረ፡ፍጹም፡ የሆነ፡ቅድስናውንም፡በአየ፡ጊዜ፡የምንኵስናን ፡ ልብስ ፡ የመላእክትንም ፡ አስኬማ ፡ አለበሰው።

፴፥ ከሰንበትም፡እስከ፡ሰንበት፡እየጾመ፡በብዙ፡ ተጋድሎ፡ኖረ፡ምግቡም፡እንጀራና፡ጨው፡ ነበረ፡በቀንና፡በሌሊትም፡ሰባት፡መቶ፡ጊዜ፡ አቡነ፡ዘበሰማያትን፡ከስግደት፡ጋር፡ይጸልያል፡በዚህም፡ተጋድሎ፡አርባ፡ዓመት፡ኖረ።

፴፩፥ ከዚህም፡በኋላ፡ያሰናብተው፡ዘንድ፡መምህሩ፡ አባ፡አውሎጊንን፡ማለደውና፡ወደ፡በረሀ፡ ሔደ ፡ ከአንዲት ፡ ታናሽ ፡ ዋሻ ፡ ውስጥም ፡ ገብቶ፡እየተጋደለ፡ኃምሳ፡ዓመት፡ኖረ። ለፍላጎቱም፡የሚያገለግሉት፡ሁለት፡አንበሶችን፡ እግዚአብሔር፡ሰጠው፡በአንዲትም፡ዕለት፡ ታመመ፡አንበሶቹንም፡እጠጣ፡ዘንድ፡የሞቀ፡ ውኃ፡እሻለሁ፡አላቸው። አንዱ፡አንበሳም፡ ወደተራራ፡ሒዶ፡እረኛ፡አግኝቶ፡ወደ፡አባ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኀበ፡አባ፡አውሎግ፡ወሶበ፡ርእዮ፡ሰገደ፡ሎቱ፡
ወይቤሎ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ ምንተ ፡ ትፈቅድ ፡
ውእቱኒ፡ይቤሎ፡እፈቅድ፡ታስትየኒ፡ማየ፡
ምውቀ ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡ ይቤሎ ፡
ወእምዝ ፡ ሜጠ ፡ አንበሳ ፡ ኀበ ፡ መካኑ ፡
ለኖላዊ።

፲፭፡ ወውእቱ፡ኖላዊ፡ነገረ፡ለኵሉ፡ሰብእ፡እንዘ፡
ይብል፡ረከብኩ፡ብእሴ፡ጻድቀ፡ዘኢይከውን፡
ዓለም፡መጠነ፡ሰኰና፡እግሩ፡ወሰሚያሙ፡
ዜናሁ ፡ ተጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ኀቤሁ ፡
ወአምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ኵሎ ፡ ድውያነ ፡ ወፈወ
ሶሙ።

፲፮፡ ወበውእቱ፡መዋዕል፡ፈቀደ፡መምህሩ፡አባ፡
አውሎጊን ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ሀገረ ፡ ፋርስ ፡
ይሚጠሙ፡ለመምለክያነ፡ጣዖት፡ውስተ፡
ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወፈቀደ፡ካዕበ፡ይንሥእ፡
ለወልዱ ፡ አውሎግ ፡ ምስሌሁ ፡ ወይፈኑ ፡
ላእከ። ወእምቅድመ ፡ ይብጻሕ ፡ ላእክ ፡
አለበዎ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ለአንበሳ፡ወነሥአ፡
ዐጽፎ፡ወወንጌሎ፡ወፆረ፡ወአመሮ፡ለአባ፡
አውሎግ ፡ ሐዊረ ፡ ውእቱኒ ፡ ተንሥአ ፡
ወተለዎ፡ ለአንበሳ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ማር ፡
አውሎጊን፡ውእቱኒ፡ተቀበሎ፡በፍሥሐ።

፲፯፡ ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡ ፈለገ ፡
ጤግሮስ፡ወተከፍለ፡ሎሙ፡ማይ፡ወዐደዉ፡
ወበጺሖሙ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ መሀርዎሙ ፡
ወሜጥዎሙ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡
ወአጥመቅዎሙ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ።

፲፰፡ ወበአሐቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡ሶበ፡ርኀቡ፡እሉ፡
ቅዱሳን ፡ አዘዞሙ ፡ ለአናብስት ፡ አባ ፡ አው
ሎግ፡ ይኅሥሡ፡ሎሙ፡ሲሳየ፡ወሐዊሮሙ፡
ረከቡ፡ብእሴ፡አረጋዌ፡ጽዒኖ፡ኀብስተ፡ዲበ፡
አድግ፡ሕፃንኒ፡ሀሎ፡ምስለ፡ኀብስት።ወአብ
ጽሕዎ፡ለአድግ፡ኀበ፡ቅዱሳን፡ወእምድንጋፄ፡
ሞተ፡ሕፃን፡ወጸለዩ፡ቅዱሳን፡ላዕለ፡ሕፃን፡
ወተንሥአ፡ሕያዎ፡ወተሴሰዩ፡ቅዱሳን፡ወአ
ናብስት፡ሜጥዎ፡ለአድግ፡ምስለ፡ኀብስት፡
ወምስለ፡ሕፃን፡ኀበ፡አረጋዊ።

፲፱፡ ወእምዝ፡ተመይጠ፡አባ፡አውሎግ፡ኀበ፡
በዓቱ ፡ ወደወየ ፡ ንስቲተ ፡ ወአዕረፈ ፡ ወተ
ቀብረ ፡ በዐቢይ ፡ ክብር ፡ ወነበሩ ፡ እሉ ፡

አውሎግ፡አመጣው፡በአየውም፡ጊዜ፡ሰገደ
ለትና፡አባቴ፡ሆይ፡ምን፡ትሻለህ፡አለው፡
እርሱም ፡ የሞቀ ፡ ውኃ ፡ ታጠጣኝ ፡ ዘንድ ፡
እሻለሁ ፡ አለው ፡ እንዳለውም ፡ አደረገለት ፡
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አንበሳው ፡ እረኛውን ፡
ወደቦታው፡መለሰው።

፲፭፡ ያም፡እረኛ፡ለእግሩ፡ተረከዝ፡ዓለሙ፡ሁሉ፡
መጠኑ፡የማይሆን፡ጻድቅ፡ሰውን፡አገኘሁ፡
ብሎ፡ለሰው፡ሁሉ፡ተናገረ፡በሰሙ፡ጊዜም፡
ሰዎች፡ሁሉ፡ወደርሱ፡ተሰበሰቡ፡በሽተኞ
ችንም፡ሁሉ፡አመጡለትና፡ፈወሳቸው።

፲፮፡ በዚያ ፡ ወራትም ፡ መምህሩ ፡ አባ ፡ አው
ሎጊን ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልኩ ፡ የፋርስ ፡
ሰዎችን ፡ ወደ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ለመ
መለስ፡ ወደ፡ፋርስ፡ሀገር፡ሊሔድ፡ፈለገ፡
ዳግመኛም፡ልጁ፡አውሎግን፡ከእርሱ፡ጋር፡
ሊወስደው፡ወደርሱ፡መልእክተኛ፡ሊልክ፡
ሽቶ፡ሳለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡አንበሳውን፡አስ
ገነዘበውና፡አጽፉንና፡ወንጌሉን፡አንሥቶ፡
ተሸከመ።አባ፡አውሎግንም፡ጉዞን፡አመለ
ከተው፡ተንሥቶም፡አንበሳውን፡ተከትሎ፡
ወደ፡መምህር፡አውሎጊን፡ደረሰ፡እርሱም፡
በደስታ፡ተቀበለው።

፲፯፡ ሲጓዙም ፡ ከጤግሮስ ፡ ወንዝ ፡ ደረሱ ፡
ውኃውም ፡ ተከፍሎላቸው ፡ ተሻገሩ ፡ ወደ ፡
ሀገሩም ፡ ውስጥ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አስተማሩ
አቸው ፡ ወደ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ መለሷ
ቸውና፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡
ስም፡አጠመቋቸው።

፲፰፡ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ደግሞ ፡ ቅዱሳን ፡ በተ
ራቡ ፡ ጊዜ ፡ምግባቸውን ፡ ይፈልጉላቸው፡
ዘንድ ፡ አባ ፡ አውሎግ ፡ አንበሶችን ፡ አዘዘ ፡
ሒደውም ፡ እንጀራ ፡ በአህያ ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡
የሚጓዝ ፡ ሽማግሌ ፡ አገኙ ፡ ሕፃንም ፡ ከእን
ጀራው ፡ ጋር ፡ አለ ። አህያውንም ፡ ወደ ፡
ቅዱሳን፡ አመጡት ፡ ከድንጋጤም ፡ የተነሣ ፡
ብላቴናው ፡ ሞተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ጸለየው ፡
ሕፃኑ ፡ ድኖ ፡ ተነሣ ፡ ቅዱሳንም ፡ ተመገቡ ፡
አንበሶችም ፡ አህያውን ፡ ከእንጀራውና ፡
ከሕፃኑ፡ጋር፡ወደ፡ሽማግሌው፡መለሱት።

፲፱፡ ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡አውሎግ፡ወደ፡በዓቱ፡
ተመለሰና፡ጥቂት፡ታሞ፡አረፈ፡በታላቅ፡
ክብርም ፡ ተቀበረ ፡ እነዚያ ፡ አንበሶችም ፡

www.ethiopianorthodox.org

አናብስት፡እንዘ፡የዐቅቡ፡መቃብሮ፡፲ወ፪ተ፡ ዓመተ፡ወእምዝ፡አተዉ፡ውስተ፡ገዳም።

፲፮፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐ ረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

መቃብሩን ፡ እየጠበቁ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት፡ ኖሩ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ገቡ።

፲፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለአንበሳዊ፡አውሎግ።ለአውሎጊን፡ዓዲ፡መምህረ፡ሕግ።እንዘ፡ይሰምዑ፡ቃሎ፡ወይ ትኤዘዙ ፡ በደርግ ። አምጽኡ ፡ አናብስት ፡ ሲሳየ ፡ ርኁባን ፡ አዕሩግ ። ዘምስለ ፡ ሕፃን ፡ ኅብስተ ፡ ጽዑነ ፡ በአድግ።

፲፯፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ አብርሃም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወመቃቢስ ፡ መነ ኰስ፡ ወኮንቲ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስ ሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፲፯፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የከበሩ ፡የኤጲስቆጶስ ፡ አብ ርሃም፡የመነኰስ፡መቃቢስና፡የኮንቲ፡መታ ሰቢያቸው፡ነው፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ ትኑር፡ ለእግዚአብሔርም ፡ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

፲፰፡ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አባ፡በትራ፡ረድኡ፡ ለአባ ፡ ስልዋኖስ ፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አመ ፡ ኮነ፡ ንቡረ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ፡ ዘደብረ ፡ ሲና ፡ ኮነ፡ ዘየዐቅብ ፡ ቅርኀምተ ፡ ወበጊዜ፡ ድራር፡ ይሁብ፡ለሥጋሁ፡መፍቅዶ።

፲፰፡በዚችም፡ቀን፡የአባ፡ስልዋኖስ፡ረድእ፡አባ፡ በትራ፡አረፈ፡ይህም፡ቅዱስ፡በደብረ፡ሲና፡ ካለች ፡ በዓቱ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ትርኀምትን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ፡ በራትም ፡ ጊዜ፡ ለሥጋው ፡ የሚያሻውን፡ይመገባል።

፲፱፡ ወሶበ ፡ ረሰይዎ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ፈርኑ፡አድከመ፡ነፍሶ፡ፈድፋደ፡በአብዝኆ፡ ትርኀምት፡ወይቤልዎ፡አርዳኢሁ፡አ፡አቡነ፡ ሶበ ፡ ነበርከ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ በበአትከ ፡ ኢኮንከ ፡ ትትኄረም ፡ ከመዝ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ውእቱ፡አብ፡አሜሃ፡ነበርኩ፡ውስተ፡ንዴት፡ በገዳም ፡ ከመ ፡ ኢይድወይ ፡ ሥጋየ ፡ ገበርኩ ፡ ይእዜሰ ፡ ሀሎኩ ፡ ማዕከለ ፡ ማኅበር ፡ ወብየ ፡ መፍቅድ ፡ ብዙኀ ፡ ባሕቱ ፡ ይኄይስ ፡ ከመ ፡ አግርር፡ሥጋየ፡ወእቅንዮ፡ወከመዝ፡እንዘ፡ ይትጋደል፡ነበረ፡ወእምዝ፡አዕረፈ፡በሰላም።

፲፱፡ፈርኑ፡በሚባል፡ትገር፡ላይ፡ኤጲስቆጶስ፡በአደ ረጉት ፡ ጊዜ ፡ ትርኀምትን ፡ በማብዛት ፡ ሰውነቱን ፡ እጅግ ፡ አደከመ ፡ ደቀ ፡ መዛሙ ርቱም ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ በገዳም ፡ በበአትህ ፡ በነበርክ ፡ ጊዜ ፡ ትርኀምትን ፡ እንዲህ ፡ አላበ ዛህም ፡ ነበር ፡ አሉት ፡ ይህም ፡ አባት ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በገዳም ፡ በችግር ፡ ውስጥ ፡ ነበርኩ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከብዙዎች ፡ መካከል ፡ በአን ድነት ፡ አለሁ ፡ የምሻውም ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ አለኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሥጋዬን ፡ ቀጥቼ ፡ ብገዛው ፡ ይሻላል ፡ እንዲህም ፡ እየተጋደለ ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፳፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፡ ለእግዚአብሔርም ፡ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በጸሎቱ፡ይማረን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለበትራ፡ረድአ፡ስልዋኖስ፡ወምእኑ።ኤጲስቆጶሰ፡ዘኮነ፡በሀገረ፡ፈርኑ።ከመ፡እንግር፡ጽድቆ፡ ወኂሩቶ፡እዜኑ።ለአፉየ፡ወለልሳንየ፡በመጠኑ።ዘይረድአኒ፡መንፈስ፡ይፌኑ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ተዝካረ፡በዓሉ፡ለመልአክ፡ክቡር፡ሚካኤል፡ሊቀ፡መላእክት።

ሁለት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የከበረ ፡ መልአክ ፡ ሚካኤል ፡ የበዓሉ ፡ መታሰቢያ፡ነው።

፪፤ እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ፈነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚካኤል ፡ ክቡር ፡ ኀበ ፡ ሶምሶን ፡ ረዓይታዊ ፡ ወረድአ ፡ እስከ ፡ ቀተሎሙ ፡ ወሞዖሙ ፡ ለሰብአ፡ፍልስጥዔም፡ሶበ፡ተንሥኡ፡ላዕሌሁ፡ ይቅትልዎ ፡ ወወሀቦ ፡ ኃይለ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወቀተለ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፲ተ ፡ ፻ተ ፡ ዕደወ ፡ በመንሰከ ፡ አድግ ። ወሶበ ፡ ጸምዐ ፡ ወቀርበ ፡ ለመዊት፡አስተርአየ፡ሎቱ፡ሊቀ፡መላእክት፡ ሚካኤል፡ወአጽንዖ፡ወአውኀዘ፡ሎቱ ፡እግዚአብሔር ፡ማየ ፡ እምዐፅመ ፡ መንሰከ ፡ አድግ ፡ ስትየ፡ወድኅነ።

፪፤ በዚች ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ ሚካኤልን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ረዓይታዊ ፡ ወደ ፡ ሶምሶን ፡ ላከው፡ የፍልስጤም ፡ ሰዎች ፡ ሊገድሉት ፡ በጠላትነት፡በተነሡበት፡ጊዜ፡ድል፡እስከ፡አደረጋቸውና፡ እስከ ፡ ገደላቸው ፡ ድረስ ፡ ረዳው ፡ ኃይልንም ፡ ሰጥቶ ፡ በአህያ ፡ መንጋጋ ፡ ከእርሳቸው ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰዎችን ፡ ገደለ ። ተጠምቶም ፡ ለሞት ፡ በተቃረበ ፡ ጊዜ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ሚካኤል፡ ተገለጠለትና ፡ አጸናው ፡ እግዚአብሔር ፡ከአህያ ፡ መንጋጋ ፡ አጥንት፡ውኃን፡አፈለቀለትና፡ጠጥቶ፡ዳነ።

፫፤ ወዓዲ ፡ ተሰነዓዉ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወአዖሩ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወላፀዩ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ወሞቅሕዎ፡ወእምዝ፡ሶበ፡አስተዳለዉ፡በዓለ፡ለአማልክቲሆሙ ፡ ወሰድዎ ፡ ለሶምሶን ፡ ቤተ ፡ ጣዖቶሙ፡ወሀለዉ፡በህየ፡ሰብእ፡ጉብአነ፡መጠነ፡ ፴፻ወአስተርአየ፡ቅዱስ፡ሚካኤል፡ወመልአ፡ ኃይለ፡ወመልሐሙ፡ለአዕማደ፡ውእቱ፡ቤት፡ ወወድቀ፡ወቀተሎሙ፡ለኵሎሙ፡ምስሌሁ።

፫፤ ዳግመኛም ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ ዐይኖቹን፡አሳወሩ፡የራሱንም፡ጠጕር፡ላጩ፡ አሠሩትም ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለጣዖቶቻቸው ፡ በዓልን፡በአዘጋጁ፡ጊዜ፡ሶምሶንን፡ወደ፡ጣዖቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ወሰዱት ፡ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ሽህ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ፡ የከበረ፡ ሚካኤልም ፡ተገለጠለትና ፡ ኃይልን ፡ መላው ፡ የዚያንም ፡ ቤት ፡ ምሰሶዎች ፡ ነቀላቸው ፡ ቤቱም ፡ በላያቸው ፡ ወድቆ ፡ ከእርሱ፡ ጋር፡ ሁሉንም፡ ገደላቸው።

፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በትንብልናሁ፡ለመልአክ፡ክቡር፡ሚካኤል፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፬፤ ለእግዚአብሔርም ፡ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በከበረ ፡ መልአክ ፡ ሚካኤል ፡ አማልጅነት ፡ ይማረን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ሠናይተከ ፡ ተአዛዜ ። ለትፍሥሕተ ፡ ሰብእ ፡ ወለኑዛዜ ። ሚካኤል ፡ኢይበል ፡ አድኅኖተከ፡ ማእዜ።ረሲ፡ደኅሪትየ፡እምግብረ፡ኃጢአት፡አግዓዜ።እንተ፡ተቀነይኩ፡የአክል፡እምይእዜ።

፭፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ መስተጋድል ፡ አባ ፡ ገላስዮስ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁ ፡ መሃይምናን ፡ ፈራህያነ ፡ እግዚአብሔር፡ወወሀርዎ፡ኵሎ፡ጥበበ፡ወትምህርተ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ወተሠይመ፡ዲያቆነ።

፭፤ በዚችም፡ቀን፡ተጋዳይ፡የሆነ፡የከበረ፡አባት፡ አባ፡ገላስዮስ፡አረፈ፡የዚህ፡ቅዱስ፡ወላጆቹ፡ እግዚአብሔርን ፥ የሚፈሩ ፡ ምእመናን ፡ ናቸው፡ ጥበብንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት፡አስተማሩትና፡ዲቁና፡ተሾመ።

፮፤ ወመነነ ፡ ዘንተ ፡ ዓለመ ፡ እምንእሱ ፡ ወፆረ ፡ ዐርዐቶ፡ ለክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ተጋደለ፡ ገድለ ፡ ዐቢየ ፡ በምንኵስና ፡ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ወይጸውም፡ወይሰግድ፡በትጋህ፡ወኀረዮ፡እግዚአብሔር ፡ ወተሠይመ ፡ ቀሲሰ ፡ ላዕለ ፡

፮፤ ከታናሽነቱም ፡ ጀምሮ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቆ ፡ ተወ፡የክብር፡ባለቤት፡የሆነ፡ የክርስቶስንም፡ ቀንበር ፡ በመሸከም ፡ በምንኵስና ፡ ሁኖ ፡ በትጋት፡እየጾመ፡እየጸለየና፡እየሰገደ፡ታላቅ፡ ተጋድሎን ፡ ተጋደለ ፡ እግዚአብሔርም ፡መርጦት ፡ በአስቈጥስ ፡ ገዳም ፡ ባሉ ፡ መነኰሳት ፡

መነኰሳተ፡ገዳመ፡አስቄጥስ።

፳፯፤ ወሶበ፡እንዘ፡ይፌጽም፡ተጋድሎቶ፡ወተጸምዶቶ፡ አስተርአዮ፡መልአከ፡እግዚአብሔር፡በከመ፡ አስተርአዮ፡ለአባ፡ጳኵሚስ፡ወአዘዞ፡ከመ፡ያስ ተጋብእ፡መነኰሳተ፡ወይምሀሮሙ፡ፈሪሀ፡እግ ዚአብሔር፡ወፍኖተ፡ምንኵስና፡ወሶቤሃ፡አስ ተጋብአሙ ፡ ለብዙኃን ፡ መነኰሳት ፡ ወሠ ርዐ፡ሎሙ፡ሱታፌ፡መንፈሳዌ፡ወኢኮነ፡በማዕ ከሎሙ፡ከመ፡ሊቅ፡አላ፡ከመ፡ገብር፡ዘይንእስ፡ እምኔሆሙ።

፳፰፤ ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ መናኒ ፡ ኵሎ ፡ ጥሪተ ፡ ዝንቱ፡ ዓለም ፡ ወኮነ ፡ የዋሀ ፡ ወኄረ ፡ ጥቀ ፡ ወአጽሐፈ፡ አሐደ ፡ መጽሐፈ ፡ ዐቢየ ፡ ዘተጋብአ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ወአውጽአ፡ዐስበ፡ጽሕፈቱ፡፲ወ፰ተ፡ዲናረ፡ ወርቅ፡ወአንበሮ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ላዕለ ፡ አትሮንስ ፡ ከመ ፡ ያንብብዎ ፡ መነ ኰሳት፡ሶበ፡ይፈቅዱ፡እምኔሁ፡ይትፈወሱ።

፳፱፤ ወሶበ፡ቦአ፡፩ብእሲ፡ፈላሲ፡ከመ፡የሐውጾ፡ ለአረጋዊ፡አባ፡ገላስዮስ፡ወርእዮ፡ለውእቱ፡ መጽሐፍ ፡ ወአደሞ ፡ ወሰረቆ ፡ ወወጽአ ፡ እምህየ፡በጽሚት፡ወበጺሖ፡ውስተ፡ሀገር፡ ፈቀደ፡ይሢጦ። ወይቤሎ፡አሐዱ፡ብእሲ፡ ሚ፡መጠን፡ሤጡ፡ውእቱኒ፡ይቤሎ፡ሀበኒ፡ ፲ወ፯ተ፡ዲናረ፡ወርቅ፡ወይቤሎ፡ውእቱ፡ ዘይሣየጦ ፡ አነ ፡ እሁበከ ፡ ዘትቤ ፡ ባሕቱ ፡ ተዓገሠኒ፡እስከ፡አርእዮ፡ለዐርክየ፡ወወሀቦ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ ውእቱሰ ፡ ብእሲ ፡ ዘይሣየጦ፡ወሰዶ፡ኀበ፡ገላስዮስ፡ወአርአዮ፡ ወይቤሎ፡ነጽር፡ሊተ፡መጽሐፈ፡ለእመ፡ኮነ፡ ሠናየ፡እሣየጦ። ወይቤሎ፡አባ፡ገላስዮስ፡ለዘ አምጽአ፡ብእሲ፡ሚ፡መጠነ፡ኃሠሠ፡እም ኔከ፡ወይቤ፡፲ወ፯ተ፡ዲናረ፡ወርቅ፡ወአ ውሥአ፡ቅዱስ፡ገላስዮስ፡ተሣየጦ፡እስመ፡ ውእቱ፡ሠናይ፡ወቀሊል፡ሤጡ።

፴፤ ወሶበ፡ተመይጠ፡ኀበ፡ሰራቂ፡ኀብአ፡ዘነገሮ፡ አባ፡ገላስዮስ፡ወይቤሎ፡አርአይክዎ፡ለአባ፡ ገላስዮስ፡ወውእቱ፡ይቤለኒ፡ሤጡ፡ብዙኅ፡ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ሰራቂ ፡ ኢተናገረከኑ ፡ ካልአ ፡ ነገረ ፡ ውእቱ ፡ አረጋዊ ፡ ወይቤሎ ፡ አልቦ፡ወይቤሎ፡ሰራቂ፡ኢይሠይጦ፡እምዝ። ወሖረ፡ኀበ፡አባ፡ገላስዮስ፡ወወድቀ፡ታሕተ፡

ላይ፡ቅስና፡ተሾመ።

፳፯፤ ተጋድሎውንና፡አገልግሎቱን፡እየፈጸመ፡ሳለ፡ ለአባ ፡ ጳኵሚስ ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ የእግዚአ ብሔር፡መልአክ፡ተገለጠለትና፡መነኰሳትን፡ ሰብስቦ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምንኵስ ናንም፡ሕግ፡ያስተምራቸው፡ዘንድ፡አዘዘው፡ በዚያንም፡ጊዜ፡ብዙዎች፡መነኰሳትን፡ሰበ ሰበ፡መንፈሳዊ፡የሆነ፡የአንድነት፡ማኅበራዊ፡ ኑሮንም ፡ ሠራላቸው፡እርሱ፡በመካከላቸው ፡ እንደ፡መምህር፡አልሆነም፡ከእርሳቸው፡እን ደሚያንስ፡አገልጋይ፡እንጂ።

፳፰፤ ይህም ፡ አባት ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ጥሪት ፡ ሁሉ ፡ ንቆ፡የተወ፡ሆነ፡እጅግም፡የዋህና፡ቸር፡ሆነ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ መጻሕፍቶችም ፡ የተሰ በሰበ፡አንድ፡ታላቅ፡መጽሐፍን፡አጻፈ፡ለማጻ ፊያውም ፡ ዋጋ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ የወርቅ ፡ ዲናር፡አወጣ፡ከርሱ፡ሊጠቀሙ፡በሚፈልጉ፡ ጊዜ፡መነኰሳቱ፡እንዲያነቡት፡በቤተ፡ክርስ ቲያን፡ውስጥ፡በአትሮንስ፡ላይ፡አኖረው።

፳፱፤ አንድ ፡ መጻተኛ ፡ ሰውም ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ገላስዮስን፡ሊጎበኝ፡በገባ፡ጊዜ፡ያንን፡መጽ ሐፍ፡አየውና፡አማረው፡በጭልታም፡ከዚያ፡ ሰርቆት፡ወጣ፡ወደ፡ከተማ፡ውስጥም፡በገባ፡ ጊዜ ፡ ሊሸጠው ፡ ወደደ ፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ ዋጋው፡ምን፡ያህል፡ነው፡አለው፡እርሱም፡ ዐሥራ፡ሰባት፡የወርቅ፡ዲናር፡ስጠኝ፡አለው። ያ፡የሚገዛውም፡ሰው፡ያልከውን፡እሰጥሃለሁ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለወዳጄ ፡ እስካሳየው ፡ ታገሠኝ ፡ አለው፡ያሳየውም፡ዘንድ፡ሰጠው፡የሚገዛው፡ ሰው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ገላስዮስ ፡ ወሰደውና ፡ ተመልከትልኝ፡መልካም፡ከሆነ፡እገዛዋለሁ፡ አለው ፡ አባ ፡ ገላስዮስም፡ ያመጣውን ፡ ሰው ፡ ከአንተ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ፈለገ ፡ አለው ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ አለው ፡ ቅዱስ ፡ ገላስ ዮስም፡መጽሐፉ፡መልካም፡ነው፡ዋጋውም፡ ቀላል፡ነው፡ግዛው፡ብሎ፡መለሰለት።

፴፤ ወደ፡ሌባውም፡በተመለሰ፡ጊዜ፡አባ፡ገላስዮስ፡ የነገረውን ፡ ሠውሮ ፡ ለአባ ፡ ገላስዮስ ፡ አሳየ ሁት ፡ እርሱም ፡ ዋጋው ፡ በዝቷል ፡ አለኝ ፡ አለው፡ሌባውም፡ያ፡ሽማግሌ፡ሌላ፡የተናገ ረህ ፡ ነገር ፡ የለምን ፡ አለው ፡ አዎን ፡ የለም ፡ አለው ። ሌባውም ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ አልሸ ጠውም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ገላስዮስ ፡ ሒዶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እገሪሁ ፡ ወሰአሎ ፡ ወይቤሎ ፡ ስረይ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ ሰይጣን ፡ አስሐተኒ ፡ ወንሣእ ፡ መጽሐፊከ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ ገላስዮስ ፡ አንሰ፡ ኢይፈቅድ ፡ እንሣእ ፡ ሰራቂኒ ፡ ሰአሎ ፡ ብዙኀ፡ እንዘ ፡ ይበኪ ፡ ወይሰግድ ፡ ቅድሜሁ፡ ወበብዙኀ ፡ ፃማ ፡ ነሥአ ፡ እምኔሁ ፡ መጽሐፎ ፡ ወአልቦ ፡ ዘአእመረ ፡ መኑሂ ። ወወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ ወገብረ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ።

፲፩፤ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ አምጽኡ ፡ ዓሣ ፡ ኀበ፡ ደብር፡ ለመነኮሳት ፡ ወአብሰሎ ፡ በዓለ ፡ ጸብሕ ፡ ወአንበሮ ፡ ውስተ ፡ በአት ፡ ወረሰዮ ፡ ለ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ከመ ፡ ይዕቀቦ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ግብሩ ፡ ወበልዐ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ እምውእቱ ፡ ዓሣ ። ወሶበ ፡ ተመይጠ ፡ በዓለ ፡ ጸብሕ ፡ ረከቦ ፡ በዘተበልዐ ፡ ወተምዐ ፡ ላዕለ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤሎ ፡ እፎ ፡ ደፈርከ ፡ ከመ ፡ ትብላዕ ፡ እምቅድመ ፡ ይባርኩ ፡ አበው ፡ አረጋውያን ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ልቡ ፡ መንፈሰ ፡ ቍጥዓ ፡ ወረገዖ ፡ ለሕፃን ፡ ወበጊዜሃ ፡ሞተ ። ወርእዮ ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ደንገፀ ፡ ወፈርሀ ፡ ዐቢየ ፡ ፍርሀተ ፡ ወሖረ ፡ ወነገሮ ፡ ለአባ ፡ ገላስዮስ ፡ ዘኮነ ፡ ኵሎ ፡ ወይቤሎ ፡ ውእቱኒ ፡ ሰዶ ፡ ቅድመ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወአስከቦ ፡ ውእቱኒ ፡ ገብረ ፡ በከመ ፡ አዘዞ ።

፲፪፤ ወጊዜ ፡ ፍና ፡ ሠርክ ፡ ተጋብኡ ፡ አረጋውያን ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጸለዩ ፡ ጸሎተ ፡ ሠርክ ፡ ወፈጺሞሙ ፡ ወጽኡ ፡ ወሶበ ፡ ወጽአ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ገላስዮስ ፡ ተንሥአ ፡ ሕፃን ፡ ዘሞተ ፡ ወተለዎ ፡ በድኅሬሁ ፡ ወኢያእመረ ፡ መኑሂ ፡ እመነኮሳት ፡ ውእቱኒ ፡ አዘዞ ፡ ለበዓለ ጸብሕ ፡ ኢይንግር ፡ ለመኑሂ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ።

፲፫፤ ወፈጺሞ ፡ አባ ፡ ገላስዮስ ፡ ብፁዕ ፡ ኵሎ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ወገድሎ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኀዲጎ ፡ ዘንተ ፡ ተዝካረ ፡ ሠናየ ፡ ወበጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ፍልሰቱ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ።

፲፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወድቆ፡ ለመነው ፡ ሰይጣን ፡ አስቶኛልና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ መጽሐፍህንም ፡ ውሰድ ፡ አለው ፡ የነበረ ፡ ገላስዮስም ፡ እኔ ፡ መጽሐፉን ፡ መውሰድ ፡ አልሻም ፡ አለው ። ሌባ ውም ፡ በፊቱ ፡ እያለቀሰና ፡ እየሰገደ ፡ ብዙ ፡ ለመነው ፡ በብዙ ፡ ድካምም ፡ መጽሐፉን ፡ ተቀበለው ፡ ማንም ፡ ያወቀ ፡ የለም ። እግዚአብሔርም ፡ ትንቢት ፡ የመናገርን ፡ ሀብት ፡ ሰጥቶት ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አደረገ ።

፲፩፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ለገዳሙ ፡ መነኮሳት ፡ ዓሣ ፡ አመጡ ፡ ባለ ፡ ወጡ ፡ ዓሣውን ፡ አብስሎ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አኑሮ ፡ አንዱን፡ ብላቴና ፡ ጠባቂ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ሔደ ፡ ብላቴናውም ፡ ከዚያ ፡ ዓሣ፡ በላ ። ባለ፡ ወጡ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ተበልቶ ፡ አገኘውና፡ በብላቴናው ፡ ላይ ፡ ተቆጥቶ ፡ አረጋውያን ፡ አባቶች ፡ ሳይባርኩት ፡ እንዴት ፡ ደፍረህ ፡ በላህ ፡ አለው ፡ የቍጣ ፡ መንፈስም ፡ በልቡ ፡ አደረና ፡ ብላቴናውን፡ ረገጠው ፡ ወዲያውኑ ፡ ሞተ ፡ እንደሞተም ፡ አይቶ ፡ ደነገጠ ፡ ታላቅ ፡ፍርሀትንም ፡ ፈራ ፡ ሒዶ ፡ ለአባ ፡ ገላስዮስ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ፡ እርሱም ፡ ወስደህ ፡ ከቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ፊት ፡ አስተኛው ፡ አለው ፡ ሰውየውም ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ።

፲፪፤ ወደ ፡ ማታ ፡ ጊዜም ፡ አረጋውያን ፡ መነኮሳት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ተሰብስበው ፡ የማታውን ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ወጡ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ገላስዮስም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የሞተው ፡ ብላቴና ፡ ተነሥቶ ፡ በኋላው ፡ ተከተለው ፡ ከመነኮሳትም ፡ ማንም ፡ አላወቀም ፡ እርሱም ፡ የገደለውን ፡ ባለ ፡ ወጥ ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገር ፡ አዘዘው ።

፲፫፤ የተመሰገነ ፡ አባ ፡ ገላስዮስም ፡ ያማረ ፡ ትሩፋቱንና ፡ ተጋድሎውን ፡ ፈጽሞ ፡ አድርሶ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አገልግሎ ፡ ይህንንም ፡ በጎ ፡ መታሰቢያ ፡ ትቶ ፡ ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡ የሚለይበት ፡ ሲደርስ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ።

፲፬፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ ለገላስዮስ፤ ለሐውዘ፡ ዓለም፡ ዘገደፎ። ምንዳቤ፡ ገዳም፡ በተሳትፎ። መንፈሶ፡ አኒኖ፡ ወትዕግሥቶ፡ አዝሊፎ። ለብእሲ፡ ሰራቂ፡ ኢተሀበለ፡ ይዝልፎ። እንዘ፡ በእዴሁ፡ እኁዘ፡ ይሬኢ፡ መጽሐፎ።

፲፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካራ ፡ ለዶርቃስ ፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

* * *

፩፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አመ፡ ፲ወ፫ ለየካቲት፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነ፡ ሰማዕተ፡ ቅዱስ፡ ሰርግዮስ፡ ዘእምሀገረ፡ አትሪብ ፡ አቡሁኒ ፡ ወእሙ ፡ ወአኃዊሁ ፡ ምስሌሁ፡ወብዙኃን፡ሰብእ፡ካልአን።

፪፡ ወለዝንቱ፡ ቅዱስ፡ ሰርግዮስ፡ አቡሁ፡ ወእሙ፡ ኄራን፡ ወስመ፡ አቡሁ፡ ቴዎድሮስ፡ ወስማ፡ ለእሙ፡ ማርያም፡ ወሶበ፡ ኮነ፡ መዋዕሊሁ፡ ፳ ዓመተ፡ ሐለየ፡ በልቡ፡ ከመ፡ ይሙት፡ በእንተ፡ ስሙ፡ ለክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ ወበጽሐ፡ ኀበ፡ ቆጽርያኖስ፡ መኰንን፡ ወተአመነ፡ በእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት። ወአዘዘ፡ መኰንን፡ ከመ፡ ይኰንንዎ፡ ኵነኔ፡ ጽኑዐ ፡ ወይሞቅሕዎ ፡ ወእግዚእነ ፡ አዘዘ ፡ ከመ፡ ይምሥጥዋ፡ ለነፍሱ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ ወያርእይዋ፡ ማኅደሪሆሙ፡ ለቅዱሳን፡ ሰማዕት ፡ ወርእያ ፡ ተናዘዘት ፡ ወእምሕማሙኒ፡ ፈወሶ።

፫፡ ወሰምዑ፡ ተጋድሎቶ፡ ቀሲስ፡ ዘስሙ፡ አባ፡ መጹን፡ ወክልኤቱ፡ ዲያቆናት፡ ወተንሥኡ፡ ሶቤሃ ፡ ወበጽሑ ፡ ኀበ ፡ መኰንነ ፡ ሀገረ ፡ አትሪብ፡ ወተአመኑ፡ በእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአዘዘ ፡ ይቅሥፍዎሙ ፡ ዐቢየ፡ መቅሠፍተ፡ ወገብሩ፡ ቦሙ፡ ከማሁ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ይኔጽርዎሙ ፡ ወየዓውድዎሙ፡ ወየኀዝኑ፡ በእንተ፡ ቀሲስ፡ ወለእለ፡ ምስሌሁ፡ ቀሲስሰ፡ ሚጠ፡ ገጾ፡ ኀቤሆሙ፡ ወገሠጾሙ ፡ ወመሀሮሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ከመ፡ ጽንዑ፡ ውስተ፡ ሃይማኖት፡ ርትዕት፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት። ወእምዝ፡ ጸለየ፡ ላዕለ፡ ማይ፡ ወነዝሀ ላዕሌሆሙ፡ ወሶቤሃ፡ ነሥኡ፡ ጸጋ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ እስመ፡ ወረደ፡ ላዕሌሆሙ፡ ወተአመኑ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወመተርዎሙ ፡ አርእስቲሆሙ ፡

፲፰፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የዶርቃስ ፡ መታሰቢያዋ ፡ ነው ፡ ለእግዚአብሔርም ምስጋና ፡ ይገባል ፡ አሜን።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት፡ በዚች፡ ቀን፡ የከበረ፡ ሰርግዮስ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ ወንድሞቹም ፡ ከእርሱ፡ ጋር፡ ሌሎችም፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ሞቱ።

፪፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ሰርግዮስ ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ ደጎች ፡ ናቸው ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ቴዎድሮስ ፡ የእናቱ፡ ስም፡ ማርያም፡ ነው፡ ዕድሜውም፡ ሃያ፡ ዓመት፡ ሲሆነው፡ በክብር፡ ባለቤት፡ ክርስቶስ፡ ስም ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ አሰበ ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ ቆጽርያኖስም ፡ ቀርቦ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ስም ፡ ታመነ ፡ መኰንኑም ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይን ፡ ያሠቃዩት ፡ ዘንድ ፡ ያሥሩትም ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ጌታችንም፡ ነፍሱን፡ ወደ፡ ሰማይ፡ አምጥቀው፡ የቅዱሳን ፡ ሰማዕታትን ፡ መኖሪያ ፡ ያሳዩዋት ፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ አይታም፡ ተጽናናች፡ ከሥቃይ፡ ከሕማሙም፡ ፈወሰው።

፫፡ ቀሲስ ፡ አባ ፡ መጹንና ፡ ሁለት ፡ ዲያቆናትም ፡ ተጋድሎውን፡ ሰሙ፡ ያን፡ ጊዜም፡ ተነሥተው፡ ወደ፡ አትሪብ፡ አገረ፡ ገዥ፡ ቀርበው፡ በክብር፡ ባለቤት፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ታመኑ፡ የጸና፡ ግርፋትንም ፡ ይገርፏአቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ እንዲሁም፡ አደረጉባቸው። ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ በዙሪያቸው ፡ ሁነው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር ፡ ስለ ፡ ቄሱና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ስላሉትም ፡ አዘኑ ፡ ቄሱ ፡ ግን ፡ ፊቱን ፡ ወደርሳቸው ፡ መልሶ ፡ ገሠጻቸው ፡ አስተማራቸውም ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በቀናች፡ ሃይማኖት፡ እንዲህ፡ ጽኑ፡ አላቸው፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ በውኃ፡ ላይ፡ ጸልዮ፡ በላያቸው፡ ረጨ፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ በላያቸው ፡ ወርዶአልና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ፡ ተቀብለው፡ በክብር፡ ባለቤት፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ታመኑ፡ ራሶቻቸውንም፡

www.ethiopianorthodox.org

በሰይፍ ፡ ወነሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ፡ሰማያት።

በሰይፍ ፡ ቆረጧቸው ፡ የሰማዕትነት ፡ አክሊልንም፡በመንግሥት፡ሰማያት፡ተቀበሉ።

፬፡ ወእምዝ፡አዘዘ፡መኰንን፡ይደይዎ፡ለቀሲስ፡ውስተ፡ምንዳደ፡ብለኔ፡ወአድኃኖ፡እግዚአብሔር፡እምእሳት፡ወአስተርአዮ፡መልአከ፡እግዚአብሔር፡ወአጠየቆ፡ከመ፡ይከውን፡ሰማዕተ፡ሠለስተ፡ጊዜ፡በእንተ፡ስሙ፡ለክርስቶስ፡ንጉሥ፡ስብሐት፡ወአውጽኦ፡እምእቶነ እሳት።ወፈነዎ፡መኰንን፡ኀበ፡ሀገረ፡እስክንድርያ ፡ ወፈጸመ ፡ ገድሎ ፡ በህየ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቄሱን ፡ ከውሽባ ፡ ቤት ፡ ማንደጃ ፡ ውስጥ ፡ ይጨምሩት ፡ ዘንድ፡ መኰንኑ፡አዘዘ፡እግዚአብሔርም፡ከእሳት፡አዳነው። ከእግዚአብሔርም፡የታዘዘ፡መልአክ፡ተገለጠለትና፡እርሱ፡ስለ፡ክብር፡ባለቤት፡ክርስቶስ፡ስም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ምስክር ፡ እንደሚሆን ፡ አስረዳው ፡ ከእሳት ፡ ማንደጃው ፡ ውስጥም ፡ አወጣው ። መኰንኑም ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሀገር ፡ ላከው ፡ ተጋድሎውንና ፡ ምስክርነቱን ፡ በዚያ ፡ ፈጸመ ፡ የምስክርነቱን ፡ አክሊልንም ፡ በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ።

፭፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ቆጽርያኖስ ፡ ያብጽሕዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሰርግዮስ ፡ ወኰነኖ ፡ ኵነኔ ፡ ዐቢየ ፡ ወአምጽኡ ፡ መንኰራኵራተ ፡ ዘብርት ፡ አኬድዎ ፡ ውስቴቶን ፡ ወኮና ፡ መለያልያቲሁ ፡ ፬ተ ፡ ክፍለ ፡ ወተመትረ ፡ ኵሉ ፡ ሥጋሁ ፡ ወእግዚእነ ፡ አሕየዎ ፡ ወአንሥኦ ፡ ጥዑየ፡ዘእንበለ፡ሙስና።

፭፡ ከዚህም፡በኋላ፡መኰንኑ፡ቆጽርያኖስ፡የከበረ፡ሰርግዮስን፡ ያቀርቡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ታላቅ ፡ ሥቃይንም ፡ አሠቃየው ፡ የነሐስ ፡ መንኰራኵሮችንም ፡ አምጥተው፡ ከውስጣቸው ፡ አስገብተው፡አበራዩት፡ሕዋሳቱም፡አራት፡ክፍል፡ሁኖ፡ሥጋው፡ሁሉ፡ተቆራረጠ፡ጌታችንም፡አድኖ፡ያለ፡ጉዳት፡በጤና፡አስነሣው።

፮፡ ወዓዲ፡አምጽኡ፡ጣዖተ፡ከመ፡ይስግድ፡ሎቱ፡ቅዱስሰ ፡ ሶበ ፡ ረገጾ ፡ ለጣዖት ፡ ወድቀ ፡ ወተቀጥቀጠ ፡ ወርእዮ ፡ ቆጽርያኖስ ፡ መኰንን ፡ አምነ፡ በእግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ስብሐት ፡ ወይቤ ፡ ለእመ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ እምክህለ፡ያድኅን፡ርእሶ።

፮፡ዳግመኛም፡እንዲሰግድለት፡ጣዖትን፡አመጡ፡ቅዱሱ፡ግን፡ሲረግጠው፡ወድቆ፡ተቀጥቅጦ፡ደቀቀ ፡ መኰንን ፡ ቆጽርያኖስም ፡ አይቶ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመነ፡አምላክ፡ቢሆን፡ራሱን፡ማዳን፡በቻለ፡ነበር፡አለ።

፯፡ ወእምድኅረዝ ፡ ኃሠሦ ፡ ለቅዱስ ፡ ሰርግዮስ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ዘስሙ ፡ አውህዮስ ፡ ወአኀዞ ፡ ወአዘዘ ፡ ይዝሐቁ ፡ ማዕሶ ፡ ወይመዝምዝዎ ፡ በብሂእ ፡ ወዔው ፡ ድሙር ፡ ወእግዚእነሰ ፡ ያጸንዖ፡ወያጌይሎ፡ላዕለ፡ኵነኔያት።

፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ፡ ስሙ ፡ አውህዮስ ፡ የሚባል ፡ የከበረ ፡ ሰርግዮስን ፡ ፈልጎ፡ያዘው፡ቆዳውንም፡ገፈው፡በተቀላቀለ፡ኮምጣጤና፡ጨው፡ቍስሉን፡ያሹት፡ዘንድ፡አዘዘ፡ጌታችን፡ግን፡በሥቃዮች፡ላይ፡ያጸናው፡ና፡ያበረታው፡ነበር።

፰፡ ወሰሚያን ፡ እሙ ፡ ወእኅቱ ፡ በጽሓ ፡ ኀቤሁ ፡ ወሶበ፡ርእያሁ፡በከየ፡ላዕሌሁ፡ወእምብዝኀ፡ኀዘን፡መጠወት፡ነፍሳ፡እኅቱ፡ወጸለየ፡ቅዱስ ሰርግዮስ፡ኀበ፡እግዚእነ፡በእንተ፡እኅቱ፡ወተንሥአት፡እሞት፡ሕያውታ።

፰፡እናቱና፡እኅቱም፡ሰምተው፡ወደርሱ፡መጡ፡በአዩትም ፡ ጊዜ ፡ በላዩ ፡ አለቀሱ ፡ ከኀዘንም ፡ ብዛት፡እኅቱ፡ነፍሷን፡አሳለፈች፡የከበረ፡ሰርግዮስም ፡ ስለ ፡ እኅቱ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ጸለየ ፡ ከሞትም፡ድና፡በሕይወት፡ተነሣች።

፱፡አሚሃ፡መጽአ፡ኀቤሁ፡ቅዱስ፡ዮልዮስ፡ዘሀገረ አቅፋሐስ ፡ ዘይጽሕፍ ፡ ገድሎሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ወጠየቀ ፡ እምኔሁ ፡ ኵሎ ፡ ገድሎ ፡ ወተካየዶ፡ከመ፡ውእቱ፡የሐሊ፡ለሥጋሁ።

፱፡ያን፡ጊዜ፡የሰማዕታትን፡ገድል፡የሚጽፍ፡የአቅፋሐስ ፡ ሀገር ፡ ሰው ፡ የከበረ ፡ ዮልዮስ ፡ መጣ ፡ ገድሉንም፡ሁሉ፡ከእርሱ፡ተረዳ፡ለሥጋውም፡እንደሚአስብ፡ቃል፡ገባለት።

፲፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ አውህዮስ ፡ ይኰንንዎ ፡ ለቅዱስ፡ ሰርግዮስ፡በመንኰራኵር፡ወይደዩ፡መኃትወ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ዕዘኒሁ ፡ ወይም

፲፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የከበረ ፡ ሰርግዮስን ፡ በመንኰራኵር፡ውስጥ፡ያሠቃዩት፡ዘንድ፡በጆሮዎቹ፡የእሳት፡መብራቶችን፡እንዲጨምሩ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልሑ፡ አጽፋረ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወይስ
ቅሉ ፡ ዕብነ ፡ ክቡደ፡ በክሣዱ ፡ ወያስክብዎ ፡
ዲበ፡ዐራተ፡ኃዊን፡ወያንድዱ፡እሳተ፡በመት
ሕቴሁ ፡ ወገብሩ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ወእግ
ዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ያጸንዖ ፡ ወያነሥኦ ፡ ጥዑየ ፡
ዘእንበለ፡ሙስና።

፲፩፡ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ ሊቀ ፡ ሠራዊት ፡ አውህዮስ ፡
እምኰንኖቱ ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡
በሰይፍ ፡ ወሰሚዖ ፡ ቅዱስ ፡ ሰርግዮስ ፡
ተፈሥሐ፡ፈድፋደ፡ወለአከ፡ኀበ፡አቡሁ፡
ወእሙ ፡ ወአኃዊሁ ፡ ወበጽሑ ፡ ኵሎሙ ፡
አዝማዲሁ ፡ ወሰብአ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ይር
አይዎ ፡ ወረከብዎ ፡ እንዘ ፡ ይስሕብዎ ፡ ኀበ ፡
ይመትሩ፡ክሣዶ፡ወውስተ፡አፉሁ፡ልጓም፡
ወረገምዎ፡ለመኰንን፡ወለጣዖታቲሁ፡ርኵ
ሳን ። ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይምትሩ ፡ ክሣውዲ
ሆሙ፡ለኵሎሙ፡ምስለ፡ቅዱስ፡ሰርግዮስ፡
ወነሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡
ሰማያት።

፲፪፡ ወኮነ ፡ እምውስተ ፡ ሕዝብ ፡ ፩ዱ ፡ ሕፃን ፡
ንኡስ ፡ ወከሠተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዕይን
ቲሁ ፡ ወርእየ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡
ሰማዕት ፡ እንዘ ፡ ያዐርግዎን ፡ መላእክት ፡
ውስተ፡ሰማያት። ወጸርሐ፡በቃል፡ልዑል፡
እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ተሣሃለኒ ፡ ወፈርሁ ፡ አቡሁ ፡
ወእሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስማዕ ፡ መኰንን ፡ ወኢ
ያጥፍኦሙ፡በእንቲአሁ፡ወኮኑ፡ዘይፈፅሙ፡
አፉሁ፡ ውእቱሰ፡ ኢኀደገ፡ ከመዝ ፡ ብሂለ፡
እስከ፡ሰከቡ፡ ላዕሌሁ፡ወእስከ፡ወጠወ፡ነፍሶ፡
ወነሥአ፡አክሊለ፡ስምዕ፡ምስሌሆሙ፡ለሰ
ማዕታት።

፲፫፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ለሰማዕት፡ወበረከቶሙ፡
ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

የእጆቹንና፡የእግሮቹን፡ጥፍሮች፡እንዲነቅሉ፡
በአንገቱም ፡ ከባድ ፡ ደንጊያ ፡ አንጠልጥለው ፡
ከብረት ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ አስተኝተው ፡ ከበታቹ ፡
እሳትን ፡ እንዲያነዱ ፡ አውህዮስ ፡ አዘዘ ፡ እንዳዘ
ዘውም ፡ አደረጉበት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስም ፡ ያጸ
ናውና፡ያለ፡ጥፋት፡በጤና፡ያስነሣው፡ነበር።

፲፩፡የሠራዊት ፡ አለቃ ፡ አውህዮስም ፡ ማሠቃየቱን
በደከመ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆርጡ ፡
ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ የከበረ ፡ ሰርግዮስም ፡ ሰምቶ ፡
እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ወደ ፡ አባቱና ፡ ወደ ፡
እናቱ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቹም ፡ ላከ ፡ ዘመዶቹ ፡
ሁሉም ፡ የእርሱ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎችም ፡ መጡ ፡ በአ
ፉም፡ልጓም፡ለጕመው፡ቾብቾቦውን፡ወደሚ
ቆርጡበት ፡ ሲስቡት ፡ አገኙትና ፡ መኰንኑን ፡
የረከሱ ፡ ጣዖታቱንም ፡ ረገሙ ፡ መኰንኑም ፡
ከከበረ ፡ ሰርግዮስ ፡ ጋር ፡ ሁሉንም ፡ ቾብቾቧ
ቸውን ፡ እንዲቆርጡ ፡ አዘዘ ፡ በመንግሥተ ፡
ሰማያትም ፡ የሰማዕትነት ፡ እክሊልን ፡ ተቀ
በሉ።

፲፪፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ከሕዝቡ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡
ታናሽ፡ሕፃን፡እግዚአብሔር፡ዐይኖቹን፡ገል
ጦለት ፡ የቅዱሳን ፡ ሰማዕታትን ፡ ነፍሶቻቸ
ውን፡ መላእክት ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ ሲያወ
ጧቸው ፡ አይቶ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ እያለ ፡ በከፍተኛ ፡ ቃል ፡
ጮኸ ፡ እናትና ፡ አባቱም፡ መኰንኑ ፡ ሰምቶ ፡
ስለርሱ ፡ እንዳያጠፋቸው ፡ አፉን ፡ የሚዘጉ ፡
ሆኑ ፡ እርሱ ፡ ግን፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ መጮኹን ፡
አልተወም፡በላዩ፡እስከ፡ተኙበትና፡ነፍሱን፡
እስከ፡አሳለፈ፡ድረስ፡ከሰማዕታትመ፡ጋር፡
የምስክርነት፡አክሊልን፡ተቀበለ።

፲፫፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸ
ውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለመስተጋድል፡ሰርግዮስ።ምሉሐ፡አጽፋር፡በመጥባሕት፡ወዝሉቀ፡ማዕስ።ለማኅበ
ራኒሁ፡ሰላም፡ሰማዕታተ፡ክርስቶስ።ምስለ፡ዲያቆናት፡ክልኤቱ፡ወምስለ፡መጁን፡ቀሲስ።ዘአስተርአይዎ፡
በስብሐት፡ለሕፃን፡ንኡስ።

፲፬፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡
ጢሞቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክን

፲፬፡በዚችም፡ዕለት፡የከበረ፡አባት፡የእስክንድርያ፡
አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጢሞቴዎስ ፡ አረፈ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡
ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፻ወ፲፪ቱ።

፲፭፡ ለዝንቱሰ ፡ አብ ፡ በጽሐ ፡ ምንዳቤ ፡ ብዙኅ ፡
በእንተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወኮነ፡እስመ፡
አባ ፡ ሳዊሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡
በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ በውእቱ ፡
መዋዕል ፡ ወውእቱ ፡ የዓውድ ፡ እምሀገር ፡
ለሀገር ፡ ወእምደብር ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡
ወእመካን፡ውስተ፡መካን፡እንዘ፡ያጸንዖሙ፡
ለመሃይምናን ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡
ጢሞቴዎስ።

፲፮፡ ወበመዋዕሊሁ፡ለዝንቱ፡አብ፡ጢሞቴዎስ፡
አስተርአዩ ፡ በብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ሰብእ ፡
እኩያን፡ዘእምሀገረ፡ቍስጥንጥንያ፡ወእሉ፡
እለ፡የአምኑ፡በግዕዘ፡ለአውጣኪ፡ርኩስ፡
ዘይሬሲ፡ተዋሕዶቶ፡ለክርስቶስ፡ከመ፡ምት
ሐት ፡ ወይክህድ ፡ ሕማሞ ፡ ወትንሣኤሁ፡
ለመድኃኒነ ፡ ወአውገዞሙ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡
ወሰደዶሙ፡እምብሔረ፡ግብጽ።

፲፯፡ ወበመዋዕሊሁ፡ካዕበ፡አዕረፈ፡አንስጣስዮስ፡
ንጉሥ፡መሃይምን፡ወነግሠ፡ህየንቴሁ፡ዮስ
ጣትያኖስ፡ዐላዊ፡ኬልቄዶናዊ። ወውእቱ፡
ሤሞ፡ለሊናርዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ህየንቴሁ፡
ለአባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፈቂዶ ፡ ይሚጦሙ ፡
ለኵሎሙ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ውስተ ፡
ሃይማኖት ፡ ዘማኅበረ ፡ ኬልቄዶን ፡ ወአስተ
ጋብአ ፡ ማኅበረ ፡ በሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡
ወአብጽሐ፡ለአባ፡ሳዊሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ዘአንጾኪያ፡ምስለ፡ኤጲስቆጶሳቲሁ፡ ወአገ
በሮሙ ፡ ከመ ፡ ይእመኑ ፡ በሃይማኖቱ ፡
ሙስንት፡ዘኬልቄዶን፡እሙንቱሰ፡ኢተወ
ክፍዎ፡ወኢሰምዑ፡ትእዛዞ፡ወበእንተዝ፡
አብጽሐ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ምንደቤ ፡ ዐቢየ ፡
ወላዕለ፡ኵሎሙ፡ርቱዓነ፡ሃይማኖት።

፲፰፡ ወነበረ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ዲበ ፡
መንበረ ፡ ሢመቱ ፡ ፲ወ፯ተ ፡ ዓመተ ፡
ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ወስብሐት፡ ለእግ
ዚአብሔር፡አሜን።

እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሠላሰ ፡
ሁለተኛ፡ነው።

፲፭፡ ይህንንም ፡ አባት ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡
ብዙ ፡ መከራና ፡ ችግር ፡ ደርሶበታል ፡ እንዲ
ህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ሳዊሮስ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገር ፡
መጣ ፡ እርሱም ፡ ከዚህ ፡ አባት ፡ ጢሞቴዎስ ፡
ጋር ፡ ምእመናንን ፡ እያጽናና ፡ ከሀገር ፡ ወደ ፡
ሀገር፡ከገዳም፡ወደ፡ገዳም፡ከቦታ፡ወደ፡ቦታ፡
የሚዘዋወር፡ሆነ።

፲፮፡ በዚህም፡አባት፡ጢሞቴዎስ፡ዘመን፡ከቍስ
ጥንጥንያ ፡ የመጡ ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡
በግብጽ፡አገር፡ተገለጡ፡እነርሱም፡ የክርስ
ቶስን ፡ ተዋሕዶ ፡ ምትሐት ፡ በሚያደርግ ፡
መከራውንና ፡ ትንሣኤውንም ፡ በሚ
ክድ ፡ በረከሰ ፡ በአውጣኪ ፡ ትምህርት ፡
የሚያምኑ፡ናቸው፡ይህም፡አባት፡አውግዞ፡
ከግብጽ፡አገር፡አሳደዳቸው።

፲፯፡ዳግመኛም፡በዘመኑ፡ምእመን፡ንጉሥ፡አንስ
ጣስዮስ ፡ አረፈና ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ኬልቄ
ዶናዊ ፡ መናፍቅ ፡ ዮስጣትያኖስ ፡ ነገሠ ፡
እርሱም፡በአባ፡ጢሞቴዎስ፡ፈንታ፡ሊናር
ዮስን ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሾመው ፡ ሃይማኖ
ታቸው ፡ የቀና ፡ ምእመናንን ፡ ሁሉ ፡ በኬል
ቄዶን፡ጉባኤ፡ወደተወሰነ፡ሃይማኖት፡ሊመ
ልሳቸው ፡ ወዶ ፡ በቀስጥንጥንያ ፡ ጉባኤ ፡
ሰብስቦ፡የአንጾኪያውን፡ሊቀ፡ጳጳስት፡አባ፡
ሳዊሮስን ፡ ከኤጲስቆጶሳቶቹ ፡ ጋር ፡
አስመጣው ። በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በተወ
ሰነች ፡ በተበላሸች ፡ ሃይማኖቱ ፡ ያምኑ ፡
ዘንድ፡አስገደዳቸው፡እነርሱ፡ግን፡አልተቀ
በሉትም፡ትእዛዙንም፡አልሰሙም፡ስለዚ
ህም ፡ ሃይማኖታቸው ፡ በቀና ፡ ምእመናን ፡
ሁሉ፡ታላቅ፡መከራ፡አደረሰባቸው።

፲፰፡ ይህም ፡ አባት ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በመንበረ ፡
ሢመቱ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኑሮ ፡
በሰላም ፡ አረፈ ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ለዘላለም ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ·ምስ
ጋና፡ይገባል፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ጢሞቴዎስሃ፡ ሰባኬ።ወሊቀ፡ጳጳሳት፡ዝኬ።ዘበመዋዕሊሁ፡ተውህበ፡ለመሃይምናን፡ ቡራኬ። ወውዕዩ፡በነደ፡ ቃሉ፡ከመ፡ አገዳ፡ ሐምል፡ ወመሎኬ።እለ፡ ተአመኑ፡ በትምህርቱ፡ ለዕልው፡ አውጣኬ።

፲፱፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ስምዑ ፡ ለቴዎድሮ(ስ)፡ ወልደ ፡ ፋሲለደስ ፡ ወአባ ፡ ክፍላ ፡ ወአባ ፡ ኀብስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ አሜን

፳፤ ወበዛቲ፡ዕለት፧ተዝካረ፡ስምዑ፡ወዕርፍቱ፡ ለብፁዕ፡አውሳብዮስ፡ ካልዕ፡ሠናየ፡ዝክር፡ ወጥዑመ፡ዜና፡ወልዱ፡ለመስፍነ፡ሶርያ።

፳፩፤ ወሎቱ፡ሀለወቶ፡እኅት፡ምልእተ፡መንፈስ ቅዱስ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ አውሎፊያ ፡ ወለዝንቱ፡ ቅዱስ ፡ ሐፀንዎ ፡ በተግሣጽ ፡ ወበጥበብ፡ወሶበ፡ልሕቀ፡ሐፀዩ፡ሎቱ፡ወለተ፡ ንጉሠ፡ሮም፡ላሕይተ፡ጥቀ፡ወአዕተዉ፡ ሎቱ፡በክብር፡ብዙኅ፡ወአስተዋሰብዎ።

፳፪፤ወበይእቲ፡ዕለት፡ቦአ፡ኀበ፡እኅቱ፡ወይቤላ፡ አምክርኒ ፡ እስመ ፡ ሕሊናየ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ዘንተ ፡ ሰብሳበ ፡ አላ ፡ ይጽሕቅ ፡ ከመ ፡ ይመንን፡ዓለመ፡ወትቤሎ፡እኅቱ፡ምንት፡ ይበቍዓከ፡ጣዕመ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ኃላፊ፡ ይኄይሰከ፡ነቢር፡በድንግልና፡ከመ፡ድሜጥሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት።

፳፫፤ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ምሴተ ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ ሀለወት ፡ መርዓት፡ወአኀዛ፡ክሣዳ፡ወሰዓማ፡ወይቤላ፡ ኦሆ ፡ በልኒ ፡ ሠናየ ፡ ነገረ ፡ እንግርኪ ፡ ወትቤሎ፡በል፡ተናገር፡ወይቤላ፡አእምሪ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወኵሉ ፡ ፍትወቱ ፡ የኀልፍ ፡ ወስንኪ ፡ ወላሕይኪኒ ፡ ይማስን ፡ ወአልቦ ፡ ዘይበቍዓነ ፡ ዘእንበለ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወይእዜኒ ፡ ይኄይሰነ ፡ ንዕቀብ ፡ ድንግልናነ ፡ እምናርኵስ ፡ ምኵራበ፡ ሥጋነ ፡ ወይእቲ ፡ ትቤሎ ፡ ኦ ፡ እኁየ፡ አነኒ፡ ኢይፈቅድ፡ አውስቦ፡ ይኩን፡ በከመ፡ትቤ።ወተሰነዓዉ፡በዝንቱ፡ምክር። ወወጠኑ፡ገቢረ፡ጽድቅ፡፪ሆሙ፡ኅቡረ፡ እንዘ፡ ይጼልዩ፡ ወይጸውሙ፡ ወለለኵላ፡ ሌሊት ፡ ይቀውሙ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡

፲፱፤ በዚችም፡ዕለት፡ለፋሲለደስ፡ልጅ፡ለቴዎድሮስ ፡ የምስክርነቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ የአባ፡ክፍላ፡የአባ፡ኀብስም፡በረከታቸው፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና፡ይገባል።

፳፤ በዚችም፡ዕለት፡ መልካም፡ስም፡አጠራርና፡ ጣፋጭ፡ዜና፡ያለው፡ለሶርያ፡መስፍን፡ልጁ፡ የሆነ ፡ ለተመሰገነ ፡ ለሁለተኛው ፡ አውሳብዮስ፡ የምስክርነቱና፡የዕረፍቱ፡መታሰቢያ፡ ነው።

፳፩፤ ለርሱም ፡መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የተመላች ፡ ስሟ፡አውሎፊያ፡የሚባል፡እኅት፡አለችው፡ ይህንንም ፡ ቅዱስ ፡ በተግሣጽና፡ ጥበብን ፡ በማስተማር ፡ አሳድጉት ፡ በአደገም፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ያላትን፡ የሮሜውን ፡ ንጉሥ፡ልጅ፡በብዙ፡ክብር፡አጋቡት።

፳፪፤በዚያችም፡ዕለት፡ወደ፡እኅቱ፡ገብቶ፡እስቲ፡ ምከሪኝ፡ልቤ፡ይህን፡ጋብቻ፡አይሻውም፡ ዓለምን ፡ ንቆ ፡ መተውን፡ እንጂ ፡ አላት ፡ እኅቱም፡የዚህ፡የኃላፊው፡ዓለም፡ጣዕም፡ ምን፡ይጠቅምሃል፡እንደ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ ድሜጥሮስ፡በድንግልና፡መኖር፡ይሻልሃል፡ አለችው።

፳፫፤ ምሽትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሙሽሪት ፡ ወዳለችበት ፡ ገብቶ ፡ አንገቷን ፡ ያዝ ፡ አድርጎ ፡ ሳማት፡እኅቴ፡መልካም፡ነገርን፡እነግርሽ፡ ዘንድ፡እሺ፡በይኝ፡አላት፡በል፡ተናገር፡ አለችው ፡ እርሱም ፡ ዕወቂ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ፍላጎቱም፡ሁሉ፡ኃላፊ፡እንደሆነ፡ያንቺም፡ ደም ፡ ግባትሽና ፡ ላሕይሽ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ከጽድቅ፡ሥራ፡ብቻ፡በቀር፡የሚጠቅመን፡ የለም፡አሁንም፡ሥጋችንን፡ከምናሳድፍ፡ ድንግልናችንን ፡ ጠብቀን ፡ መኖር ፡ ይሻለናል፡ አላት ። እርሷም ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እኔም፡ጋብቻን፡አልሻም፡እንዳልክ፡ይሁን፡ አለችው ። በዚህም ፡ ምክር፡ ተስማምተው ፡ ሁለቱም፡ በአንድነት፡ የጽድቅን ፡ ሥራ ፡ በመጀመር ፡ እየጸለዩ ፡ እየጾሙ ፡ በየሌሊቱ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይበይቱ፡ወየሐውሩ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡እንተ፡ስማ፡አትራ፡ወይሰግዱ፡በበ፬
፻ጊዜ፡ወመዝሙረ፡ዳዊት፡ወወንጌለ፡
ዮሐንስ፡ያነብቡ፡ወትረ፡ወኢይጥዕሙ፡
እክለ፡ዘእንበለ፡ይትመጠዉ፡ቍርባነ።

፳፬፡ ወበአሐቲ፡ዕለት፡ርእየቶ፡ብእሲቱ፡
ለንጉሠ፡ሶርያ፡ወፈተወቶ፡ጥቀ፡ወአዘዘት፡
፪ተ፡እምአግብርቲሃ፡ይምጽእዎ፡ለአውሳ
ብዮስ፡ኀቤሃ፡ወነጸፈት፡ዘርቤታተ፡ወአ
ልባሰ፡ደርከኖ፡ላዕለ፡ዓራታ፡ወተሠር
ገወት፡ውስተ፡ክሣዳ፡ቃማ፡ዘወርቅ፡
ወትቤሎ፡ለአውሳብዮስ፡ነዓ፡ንበር፡ዝየ፡
እንግርከ፡ዘሀሎ፡ውስተ፡ልብየ፡ውእቱኒ፡
ይቤላ፡አንሰ፡ኢይነብር፡ምስለ፡ብእሲተ፡
ንጉሥ፡እንዘ፡ሀሎኩ፡ቀዊምየ፡ንግርኒ፡
ወትቤሎ፡ይእቲ፡እምብዝኀ፡አፍቅሮትየ፡
ኪያከ፡ያንቀለቅል፡ሥጋየ፡ወይትመሰዉ፡
ኵለንታየ፡ወነዓ፡ስክብ፡ምስሌየ፡ወይቤላ፡
ኢይሰክብ፡ምስሌኪ፡በዘኢኮነ፡ድልወትየ፡
ወበዘኢኮነ፡ትእዛዝ፡እምእግዚአብሔር፡
ከመዝ።ወሶበ፡ፈቀደት፡ተአኀዞ፡አምሠጣ፡
ወሮጸ፡ወሖረ፡ወቦአ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡ወይእቲ፡ከልሐት፡በዐቢይ፡ቃል፡
ወበጽሑ፡አግብርቲሃ።ወይቤልዋ፡ምንተ፡
ኮንኪ፡አ፡እግዝእትነ፡ወይእቲ፡ትቤሎሙ፡
ዝንቱ፡መሠርይ፡አውሳብዮስ፡ቦአ፡ኀቤየ፡
ወተናገረኒ፡ነገረ፡ዘኢይደሉ፡ወሶበ፡
አበይክዎ፡እስመ፡ሠረየኒ፡አኀዘኒ፡ጻዕር፡
ወነቀልቃል።

፳፭፡ ወእምዝ፡አዘዘት፡፲ወ፩ተ፡ረበናተ፡ከመ፡
ያውጽእዎ፡እምቤተ፡ክርስቲያን፡ወያም
ጽእዎ፡ወሶበ፡አብጽሕዎ፡ኀቤሃ፡አዘዘት፡
ይዝብጥዎ፡በአብትረ፡ኀፂን፡ወይእሥሩ፡
እደዊሁ፡ወእገሪሁ፡ወይስቅልዎ፡ዲበ፡፬ቱ፡
ዕፀው፡አፍአ፡ሀገር፡ወፈነወት፡አሐተ፡እም
አእማቲሃ፡ወትቤሎ፡ይእቲ፡አሆ፡በላ፡ለእግ
ዝእትየ፡ከመ፡ታውርድከ፡እምስቅለትከ፡
ወኢሰምዐ፡ቃላ፡ለዘማ።

ከባሕር፡ውስጥ፡ቁመው፡ያድራሉ፡አትራ፡
ወደምትባልም፡ቤተ፡ክርስቲያን፡እየሔዱ፡
አራት፡ሺህ፡ጊዜ፡ይሰግዳሉ፡የዳዊትን፡
መዝሙርና፡የዮሐንስን፡ወንጌል፡ያነባሉ፡
ሥጋውንና፡ደሙን፡ሳይቀበሉ፡ሁል፡ጊዜ፡
እህልን፡አይቀምሱም

፳፬፡ በአንዲትም፡ዕለት፡የሶርያ፡ንጉሥ፡ሚስት፡
አውሳብዮስን፡አይታው፡እጅግ፡ወደደ
ችው፡ከባሮቿም፡ሁለቱን፡ልካ፡ወደርሷ፡
አስመጣችው፡በዐልጋዋም፡ላይ፡ምንጣ
ፎችን፡አንጥፋ፡ብጫ፡ሐር፡ልብስ፡
አለበሰች፡በአንገቷም፡የወርቅ፡ማርዳ፡
በማድረግ፡አጌጠች፡አውሳብዮስንም፡
በልቤ፡ያለውን፡እነግርህ፡ዘንድ፡ና፡ከዚህ፡
ተቀመጥ፡አለችው። እርሱም፡ከንጉሥ፡
ሚስት፡ጋር፡አልቀመጥም፡እንደቆምኩ፡
ንገሪኝ፡አላት፡እርሷም፡አንተን፡
ከመውደዴ፡ብዛት፡የተነሣ፡ሰውነቴ፡
ይናወጣል፡ሁለመናዬም፡ይቀልጣልና፡ና፡
ከእኔ፡ጋር፡ተኛ፡አለችው፡እርሱም፡
ከንጉሥ፡ሚስት፡ጋር፡መተኛት፡የሚገባኝ፡
ሳይሆን፡የእግዚአብሔርም፡ትእዛዝ፡
እንዲህ፡አልሆነምና፡ከአንቺ፡ጋር፡
አልተኛም፡አላት። ልትይዘውም፡
በወደደች፡ጊዜ፡አመለጣትና፡ሩጦ፡ሒዶ፡
ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ገባ፡እርሷም፡
በታላቅ፡ድምፅ፡ጮኸች፡ባሮቿም፡
ደርሰው፡እመቤታችን፡ሆይ፡ምን፡ሆንሽ፡
አሏት። እርሷም፡ይህ፡ሥራየኛ፡አውሳ
ብዮስ፡ወደኔ፡ገብቶ፡የማይገባ፡ነገርን፡
ተናገረኝ፡አይሆንም፡ባልሁትም፡ጊዜ፡
ሥራይን፡ስላደረገብኝ፡መንቀጥቀጥና፡
ጻዕር፡ያዘኝ፡አለቻቸው።

፳፭፡ ከዚህም፡በኋላ፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡
አውጥተው፡ያመጡት፡ዘንድ፡ዐሥራ፡
አራት፡መምህራንን፡አዘዘች፡ወደርሷም፡
ባደረሱት፡ጊዜ፡በብረት፡ዘንጎች፡ይደበ
ድቡት፡ዘንድ፡እጆቹንና፡እግሮቹንም፡
አሥረው፡ከከተማ፡ውጭ፡በአራት፡
ዕንጨቶች፡ላይ፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡አዘዘች፡
ከባሮቿም፡አንዲቷን፡ልካ፡እርሷም፡ከተሰ
ቀልክበት፡እንድታወርድህ፡ለእመቤቴ፡
ያለችህን፡እሺ፡በላት፡አለችው፡እርሱም፡
የአመንዝራን፡ቃል፡አልሰማም፡አላት።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፤ ወሶቤሃ፡ወጠነ፡ጸልዮ፡ወይቤ፡ኦ፡እግዚኦ፡
እግዚአብሔር፡አምላከ፡አብርሃም፡ይስሐቅ
ወያዕቆብ፡ዘአድኃንኮሙ፡ለአበዊነ፡እም
ኵሉ፡ምንዳቤሆሙ፡አድኅነኒ፡ሊተ፡ለገብ
ርከ፡አውሳብዮስ፡ወዘአድኃንኮ፡ለዳንኤል፡
እምአፈ፡አናብስት፡ወለሶስና፡እምእደ፡
ረበናት፡አድኅነኒ፡ሊተ፡እምእደ፡ዐማፂት፡
ወገፋዒት፡እስመ፡አልብየ፡ረዳኢ፡ዘእን
በሌከ።

፳፰፤ ወእምዝ፡ካዕበ፡አዘዘት፡ከመ፡ይህንቁ፡
ክሣዶ፡በሐብል፡ወይንድፍዎ፡በ፻ወ፷፡
አኅፃ፡ወሶበ፡ገብሩ፡ቦቱ፡ዘንተ፡አዘዞሙ፡
እግዚእነ፡ለሊቃነ፡መላእክት፡ሚካኤል፡
ወገብርኤል፡ወእሉ፡መልሑ፡አኅፃ፡
እምአባሉ፡ወኮነ፡ጥዑየ፡ዘእንበለ፡ሙስና።

፳፱፤ ወሶበ፡አተወ፡ንጉሥ፡እምኀበ፡ሖረ፡
ተሰአለ፡ወይቤ፡ምንተ፡አበሳሁ፡ለአውሳ
ብዮስ፡ዘመጠውኪዮ፡ለስቅለት፡ወሞት፡
ወትቤሎ፡ብእሲቱ፡ለንጉሥ፡አንሰ፡
አኀፍር፡ነጊሮተከ፡ወእፈርህ፡እምኔከ።
ወይቤላ፡ንጉሥ፡በሊ፡ንግርኒ፡ወኢትፍርሂ፡
እምኔየ፡ወትቤሎ፡እስመ፡ውእቱ፡ብእሲ፡
መሠርይ፡ቦአ፡ኀቤየ፡እንዘ፡እነብር፡
ባሕቲትየ፡ወሰአለኒ፡ግብረ፡ዘኢይደሉ፡
ተናግሮቶ፡ወሶበ፡አበይክዎ፡አሕመመኒ፡
በሥራዩ።

፴፤ ወአዘዘ፡ንጉሥ፡ያውርድዎ፡ለአውሳብዮስ፡
እምስቅለት፡ወያብጽሕዎ፡ኀቤሁ፡ወይ
ቤሎ፡ንጉሥ፡ለአውሳብዮስ፡ለምንት፡
ሐለይከ፡እኩየ፡ግብረ፡ላዕለ፡ብእሲትየ፡
አውሥአ፡አውሳብዮስ፡ወይቤሎ፡ኦ፡
እግዚእየ፡ይመስለከኑ፡እሙነ፡ዝንቱ፡ነገር፡
ወንጉሥ፡ሐተቶሙ፡ለአግብርቲሁ፡ወይ
ቤሎሙ፡እሙንኑ፡ዝንቱ፡ነገር፡ዘእሰምዕ፡
ወእሙንቱ፡ይቤልዎ፡ኦ፡እግዚእነ፡ንጉሥ፡
ንሕነሰ፡ሶበ፡ሰማዕነ፡ክላሀ፡ወበጻሕነ፡
ውስተ፡ጽርሕ፡ረከብናሃ፡ለእግዝእትነ፡
ንግሥት፡እንዘ፡ትኬልሀ፡ወሶበ፡ንቤላ፡
ምንተ፡ኮንኪ፡ነገረተነ፡ከመዝ።

፴፩፤ ወሶበ፡ሰምዐ፡ዘንተ፡ጥህረ፡ከመ፡አንበሳ፡
ወአዘዘ፡ይምትሩ፡ክሣዶ፡በሰይፍ፡ወይግ
ምድዎ፡ሥጋሁ፡ከመ፡ሥጋ፡ላሕም፡

፳፯፤ በዚያንም፡ጊዜ፡መጸለይ፡ጀመረና፡እንዲህ፡
አለ፡አቤቱ፡የአብርሃም፡የይስሐቅና፡
የያዕቆብ፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡ሆይ፡አባ
ቶቻችንን፡ከመከራቸው፡ሁሉ፡ያዳን
ካቸው፡አንተ፡ነህና፡እኔን፡ባርያህን፡አውሳ
ብዮስን፡አድነኝ፡ዳንኤልንም፡ከአንበሶች፡
አፍ፡ሶስናን፡ከረበናት፡እጅ፡ያዳንህ፡አንተ፡
ነህና፡ያላንተ፡ረዳት፡የለኝምና፡ከዐመፀኛ
ዩቱና፡ከግፈኛዩቱ፡ሴት፡እጅ፡አድነኝ።

፳፰፤ ከዚህም፡በኋላ፡ዳግመኛ፡አንገቱን፡
በገመድ፡አንቀው፡በመቶ፡ስሳ፡ፍላፃዎች፡
ይነድፉት፡ዘንድ፡አዘዘች፡ይህንንም፡በአደ
ረጉበት፡ጊዜ፡የመላእክት፡አለቆች፡ሚካኤ
ልንና፡ገብርኤልን፡ጌታችን፡አዘዛቸው፡
እነርሱም፡ከሰውነቱ፡ውስጥ፡ፍላፃዎችን፡
አወጡ፡ያለ፡ጉዳትም፡ጤነኛ፡ሆነ።

፳፱፤ ንጉሥም፡ከሔደበት፡በገባ፡ጊዜ፡ለስቅ
ላትና፡ለሞት፡አሳልፈሽ፡የሰጠሽው፡የአው
ስብዮስ፡በደሉ፡ምንድን፡ነው፡ብሎ፡
ጠየቃት፡የንጉሡም፡ሚስት፡ላንተ፡
መናገርን፡አፍራለሁ፡አንተንም፡እፈ
ራለሁ፡አለችው፡አትፍሪኝ፡በዪ፡ንገሪኝ፡
አላት፡እርሷም፡ብቻዬን፡ተቀምጬ፡
ሳለሁ፡ይህ፡ሥራየኛ፡ሰው፡ወደ፡እኔ፡ገብቶ፡
ሊናገሩት፡የማይገባ፡ሥራ፡ለመነኝ፡በከለከ
ልኩትም፡ጊዜ፡በሥራዩ፡አሳመመኝ፡
አለችው።

፴፤ ንጉሡም፡አውሳብዮስን፡ከተሰቀለበት፡
አውርደው፡ወደርሱ፡ያቀርቡት፡ዘንድ፡
አዘዘ፡ሲቀርብም፡ንጉሡ፡አውሳብዮስን፡
በሚስቴ፡ላይ፡ክፉ፡መሥራትን፡ለምን፡
አሰብክ፡አለው፡አውሳብዮስም፡ይህ፡ነገር፡
እውነት፡ይመስልሃልን፡ብሎ፡መለሰለት፡
ንጉሥም፡ይህ፡የምሰማው፡ነገር፡እውነት፡
ነውን፡በማለት፡ባሮቹን፡መረመራቸው።
እነርሱም፡ጌታችን፡ንጉሥ፡ሆይ፡እኛ፡ግን፡
ጩኸት፡ሰምተን፡ወደ፡አደራሹ፡በደረስን፡
ጊዜ፡ንግሥት፡እመቤታችንን፡እየጮኸች፡
አገኘናት፡ምን፡ሆንሽ፡በአልናትም፡ጊዜ፡
ይህንኑ፡ነገረችን፡አሉት።

፴፩፤ ይህንንም፡በሰማ፡ጊዜ፡እንደ፡አንበሳ፡ጮኸ፡
ቸብቸቦውንም፡በሰይፍ፡እንዲቈርጡ፡
ሥጋውንም፡እንደ፡ላም፡ሥጋ፡ቈራርጠው፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይደይዎ፡ውስተ፡መቅጹት፡ምስለ፡ፒሳ፡ ወይኀትሙ፡አፉሁ፡ወያብስልዎ፡በእሳት። ወመጽኡ፡ሶቤሃ፡ሊቃነ፡መላእክት፡ሚካ ኤል፡ወገብርኤል፡ወአውጽእዎ፡እምውስተ፡ መቅጹት፡ወአንሥእዎ፡እሞት፡ሕያዎ።

፴፩፡ ወእምድኅረ፡ተንሥአ፡ረከብዎ፡እንዘ፡ ያንሶሱ፡ውስተ፡ሀገር፡ወነገርዎ፡ለንጉሥ፡ ከመ፡ሕያው፡ውእቱ፡ወአዘዘ፡ያምጽእዎ፡ ወይደዩ፡፬ተ፡ጋጋተ፡ውስተ፡አባላቲሁ፡ ፩ደ፡ውስተ፡ክሣዱ፡ወ፩ደ፡ውስተ፡ገቦሁ፡ ወ፩ደ፡ውስተ፡ሐቌሁ፡ወ፩ደ፡ውስተ፡ ብርኩ፡ወይእሥሩ፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ፡ ወይደይዎ፡ውስተ፡እሳት፡ወመጽኡ፡ቅዱ ሳን፡ሚካኤል፡ወገብርኤል፡ወአቍረሩ፡ እሳተ፡ወመሠጦ፡ዑራኤል፡ሊቀ፡ መላእክት፡ወአዕረጎ፡ውስተ፡ሰማይ፡ ወነበረ፡በህየ፡፲ወ፬ተ፡ዓመተ፡ወእምዝ፡ ተመይጠ፡ወወረደ፡ውስተ፡ምድር፡ወነበረ፡ ፵ዓ፡መተ፡እንዘ፡ይሰብክ፡ሃይማኖተ፡ ወንጌል፡ወአምኑ፡በእዴሁ፡፷፡፻ወ፺፻፡ አረሚ፡ወወሀቦ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ኪዳነ፡ ለዘይጼውዕ፡ስሞ፡ወይገብር፡ተዝካሮ፡ እስከ፡ሳብዕ፡ትውልድ።

ከአደሮ፡ማር፡ጋር፡ከምንቸት፡ውስጥ፡ ጨምረው፡አፉን፡ዘግተው፡በእሳት፡ ያበስሉት፡ዘንድ፡አዘዘ፡በዚያንም፡ጊዜ፡የመ ላእክት፡አለቆች፡ሚካኤልና፡ገብርኤል፡ መጡ፡ከምንቸትም፡ውስጥ፡አውጥተው፡ ከሞት፡አድነው፡አስነሡት።

፴፩፡ ከተነሣም፡በኋላ፡በሀገር፡ውስጥ፡ሲጓዝ፡ ሰዎች፡አገኙት፡ሕያው፡እንደሆነም፡ ለንጉሥ፡ነገሩት፡ንጉሥም፡እንዲአመ ጡትና፡አራት፡ዛንጅሮችን፡በአካላቶቹ፡ ውስጥ፡እንዲአስገቡ፡አንዱን፡በአንገቱ፡ ውስጥ፡አንዱን፡በወገቡ፡አንዱን፡በጐኑ፡ አንዱን፡በጉልበቱ፡ውስጥ፡አስገብተው፡ እጅና፡እግሩንም፡አሥረው፡ከእሳት፡ ውስጥ፡ይጨምሩት፡ዘንድ፡አዘዘ፡የከበሩ፡ ሚካኤልና፡ገብርኤል፡መጥተው፡እሳቱን፡ አቀዘቀዙ፡የመላእክት፡አለቃ፡ዑራኤልም፡ ነጥቆ፡ወደ፡ሰማይ፡አሳረገውና፡በዚያ፡ ዐሥራ፡አራት፡ዓመት፡ኖረ። ከዚያም፡ በኋላ፡ወደ፡ምድር፡ተመልሶ፡ወርዶ፡የወን ጌልን፡ሃይማኖት፡እያስተማረ፡አርባ፡ ዓመት፡ኖረ፡በእርሱ፡ትምህርትም፡ሰማ ንያ፡አምስት፡ሺህ፡አረማውያን፡አመኑ፡ ጌታችን፡ኢየሱስም፡ስሙን፡ለሚጠራ፡ መታሰቢያውንም፡ለሚያደርግ፡እስከ፡ ሰባት፡ትውልድ፡ሊምርለት፡ቃል፡ኪዳን፡ ሰጠው።

፴፪፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነ፡ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፪፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛ ንም፡በጸሎቱ፡ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለአውሳብዮስ፡በውዴተ፡ብእሲት፡ዘተመከረ። ሶበ፡ትእዛዛ፡ኢሰምዐ፡ወፈቃዳ፡ኢገብረ። አመ፡ውስተ፡እሳት፡አብእዎ፡በጋጋ፡ኀፂን፡እሡረ። በእደ፡ዑራኤል፡ዐሪጎ፡እስከነ፡ይትመየጥ፡ምድረ። ካዕበተ፡ሱባዔ፡ዓመተ፡በሰማይ፡ነበረ።

፴፫፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካረ፡ልደቱ፡ለፊቅጦር፡ ሰማዕት፡ወልደ፡ኅርማኖስ፡ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአ ብሔር፡አሜን።

፴፫፡ በዚችም፡ዕለት፡የኅርማኖስ፡ልጅ፡የሰማ ዕት፡ፊቅጦር፡የልደቱ፡መታሰቢያ፡ነው። በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለልደትከ ፡ ከመ ፡ ጽጌ ፡ ደንጎላ ፡ ዘቈላ ። ለሦከ ፡ ኃጢአት ፡ በማዕከላ ። ፊቅጦር ፡ ፀሐይ ፡ ዘትረውጽ፡ በሠረገላ ። ኢያስጥም ፡ ሕይወትየ ፡ ለቊረ ፡ ኃጢአት ፡ ማዕበላ ። ሐመረ ፡ ንግደትየ ፡ አጥዒ ፡ በሞትከ፡ተድላ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፬ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኊልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፸ወ፭ቱ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ እምሀገረ ፡ ፍዩም ፡ ወተሠይመ ፡ ቀሲሰ ፡ ባቲ ፡ ወእምዝ ፡ ፈለሰ ፡ እምህየ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ቅዱስ ፡ ፊቅጦር ፡ ሰማዕት ፡ ዘአፍአ ፡ ሀገረ ፡ ምስር ፡ ኀበ ፡ ዐዘቅተ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወነበረ ፡ ውስቴቱ ፡ ብዙኀ ፡ አዝማነ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል ፡ ተጋድሎ ፡ ዐቢየ።

፫፤ ወሶበ ፡ ተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ወአእምሮቱ ፡ ወቅድስናሁ ፡ አኀዝዎ ፡ ወሤምዎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ ወዐቀበ ፡ መርዔቶ ፡ በሠናይ ፡ ተዐቅቦ ፡ ወሠርዐ ፡ ቀኖና ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ለካህናት ፡ ሶበ ፡ ይትለአኩ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጊዜ ፡ ቊርባን ፡ ወጸሎት ። ወነበረ ፡ በሢመቱ ፡ ፯ ዓመተ ፡ ወ፱ተ ፡ አውራኀ ፡ ወ፳ወ፯ተ ፡ መዓልተ ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም።

፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፭፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ መምህሮሙ ፡ ለርቱዓነ ፡ ሃይማኖት።

፮፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አዝማዲሁ ፡ እምብሔረ ፡ ሮሜ ፡ አቡሁኒ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘስሙ ፡ ሳዊሮስ ፡ ወውእቱ ፡ በጽሐ ፡ ምስለ ፡ አበው ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ፪ቱ ፡ ፻ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ሶበ ፡ ኮነ ጉባኤ ፡ በእንተ ፡ ንስጥሮስ ፡ ወርእየ ፡ ራእየ ፡ ዘይቤሎ ፡ እስመ ፡ ዘይትወለድ ፡ ወልድከ ፡ ውእቱ ፡ ያቀውም ፡ ርትዕተ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወይሰመይ ፡ ስሙ ፡ ሳዊሮስሃ ፡ ከመ ፡ ስምከ።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ቄርሎስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሰባ ፡ አምስተኛ ፡ ነው።

፪፤ ይህም ፡ አባት ፡ ፍዩም ፡ ከምትባል ፡ ሀገር ፡ ነው ፡ በእርሷም ፡ ቅስና ፡ ተሹሞ ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ለቆ ፡ ከምስር ፡ ከተማ ፡ ውጭ ፡ ወደ ፡ ሆነች ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ የጕድጓድ ፡ ውኃ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ፊቅጦር ፡ ገዳም ፡ ደረሰ ፡ በውስጡም ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን ፡ እየተጋደለ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ኖረ።

፫፤ የዕውቀቱና ፡ የቅድስናው ፡ ዜና ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ውዴታው ፡ ይዘው ፡ በእስክንድርያ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሾሙት ፡ መንጋውንም ፡ በበጎ ፡ አጠባበቅ ፡ ጠበቀ ፡ በቊርባንና ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ሊሠሩት ፡ የሚገባቸውን ፡ ለካህናት ፡ ሥርዓትን ፡ ሠራ ። በሹመቱም ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከሃያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ኑሮ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፬፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

፭፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ለቀና ፡ ምእመናን ፡ መምህራቸው ፡ የሆነ ፡ የአንጾኪያ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ሳዊሮስ ፡ አረፈ።

፮፤ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ዘመዶቹ ፡ ከሮሜ ፡ ሀገር ፡ ናቸው ፡ አባቱም ፡ ስሙ ፡ ሳዊሮስ ፡ የሚባል ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ስለ ፡ ንስጥሮስ ፡ በኤፌሶን ፡ ከተማ ፡ ጉባኤ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ አባቶች ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ጋር ፡ መጣ ፡ በዚያም ፡ እንዲህ ፡ የሚለውን ፡ ራእይ ፡ አየ ፡ ከአንተ ፡ የሚወለድ ፡ ልጅህ ፡ ስሙም ፡ እንደ ፡ ስምህ ፡ ሳዊሮስ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ እርሱ ፡ የቀናች ፡ ሃይማኖትን ፡ ያጸናታል።

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወሶበ፡አዕረፈ፡ውእቱ፡ኤጲስቆጶስ፡ሰመይዎ፡
ለወልዱ፡ሳዊሮስሃ፡ወተምህረ፡ኵሎ፡ጥበበ፡
ዘአፍኣ፡ቤተ፡ክርስቲያን።

፰፤ ወእንዘ፡ይወጽእ፡እመምህሩ፡ሖረ፡ኀበ፡፩
መካን፡ተራከቦ፡ብእሲ፡ጻድቅ፡ዘጾማዕት፡
ዘረሰየ፡ርእሶ፡ሙቁሐ፡ወይቤሎ፡ሠናይ፡
ምጽአትከ፡አ፡ሳዊሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአን
ጾኪያ፡መምህሮሙ፡ለርቱዓነ፡ሃይማኖት፡
ወተፈሥሐ፡ቦቱ፡ወአንከረ፡ሳዊሮስ፡ሶበ፡
ጸውዖ፡በስሙ፡እንዘ፡ኢየአምሮ፡ግሙራ፡
ወተናግሮቱ፡ዘይከውን፡ሎቱ፡እምቅድመ፡
ይኩን።

፱፤ ወእምዝ፡ልሕቀ፡ሳዊሮስ፡በገቢረ፡ትሩፋት፡
ወተሰምዐ፡ዜናሁ፡ወዝክሩ፡ሠናይ፡ወመን
ኰሰ፡በደብረ፡አባ፡ሮማኖስ፡ወተጋደለ፡
ገድለ፡ዐቢየ፡ወተጸምደ፡ፈድፋደ፡ለምግባረ፡
ጽድቅ፡ወተሰምዐ፡ዜናሁ፡በኵሉ፡በከመ፡
ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ኢትክል፡ተከብቶ፡
ሀገር፡እንተ፡ተሐንፀት፡መልዕልተ፡ደብር።

፲፤ ወሶበ፡አዕረፈ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ፡
ተሰነዓዉ፡ኤጲስቆጶሳት፡ማእምራን፡ከመ፡
ይሢምዎ፡ለዝንቱ፡ቅዱስ፡ሳዊሮስ፡ነሥእዎ፡
ዘእንበለ፡ፈቃዱ፡ወሤምዎ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ላዕለ፡ሀገረ፡አንጾኪያ፡ወበርሀት፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡በሢመቱ፡ዘውስተ፡ኵሉ፡አጽናፈ፡
ዓለም፡እስመ፡ነገሩ፡ሶበ፡ይበጽሕ፡ኀበ፡
ዐላውያን፡ዘውስተ፡ኵሎን፡አህጕር፡ወይበ
ትክ፡ሥርዎሙ፡ከመ፡ሰይፍ፡በሊሕ፡ዘ፪
አፉሁ።

፲፩፤ ወእምድኅረ፡ኅዳጥ፡መዋዕል፡ሞተ፡ንጉሥ፡
ምእመን፡ወነግሠ፡ህየንቴሁ፡ዐላዊ፡ዘስሙ፡
ዮስጥያኖስ፡ወብእሲቱሰ፡ንግሥት፡ርትዕተ፡
ሃይማኖት፡ወስማ፡ቴዎድራ፡ወኮነ፡ንጉሥ፡
ዘያፈርሆ፡ለዝንቱ፡ቅዱስ፡ሳዊሮስ፡ከመ፡
ያብኦ፡ውስተ፡ሃይማኖቱ፡ርኵስት፡ዘኬል
ቄዶን፡ውእቱሰ፡ኢይፈርሆ፡ለንጉሥ፡ዐላዊ፡
ወኢይትኤዘዝ፡ሎቱ፡ወተቈጥዐ፡ላዕሌሁ፡
ፈድፋደ፡እስመ፡መሰሎ፡ዘይፈርህ፡ቍጥ
ዓሁ፡ወእምዝ፡መከረ፡ንጉሥ፡ያቅትሎ፡
በኅቡእ፡ለቅዱስ፡አባ፡ሳዊሮስ፡ወአእሚራ፡
ንግሥት፡አምከረቶ፡ለሊቀ፡ጳጳሳት፡ከመ፡
ይጕየይ፡እምገጸ፡ንጉሥ፡ዝንቱኒ፡ወጽአ፡

፯፤ ይህም፡ኤጲስቆጶስ፡በአረፈ፡ጊዜ፡ልጁን፡
ሳዊሮስ፡ብለው፡ጠሩት፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡
ውጭ፡የሆነውን፡ጥበብን፡ሁሉ፡ተማረ።

፰፤ ከመምህሩም፡ወጥቶ፡ወደ፡አንድ፡ቦታ፡
ሲጓዝ፡በዋሻ፡ራሱን፡እሥረኛ፡አድርጎ፡
የሚኖር፡ጻድቅ፡ሰው፡ተገናኘው፡በእርሱም፡
ደስ፡ብሎት፡የአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ሃይማ
ኖታቸው፡ለቀና፡ምእመናን፡መምህራቸው፡
የሆንክ፡ሳዊሮስ፡ሆይ፡መምጣትህ፡መልካም፡
ነው፡አለው፡ሳዊሮስም፡ከቶ፡ሳያውቀው፡
በስሙ፡በጠራው፡ጊዜ፡የሚደረግለትንም፡
ከመሆኑ፡አስቀድሞ፡በመናገሩ፡አደነቀ።

፱፤ ከዚህም፡በኋላ፡ሳዊሮስ፡ትሩፋት፡በመሥራት፡
አደገ፡መልካም፡ስም፡አጠራሩና፡ዜናው፡
ተሰማ፡በአባ፡ሮማኖስም፡ገዳም፡መንኵሶ፡
ታላቅ፡ተጋድሎን፡ተጋደለ፡ለትሩፋትም፡
ሥራ፡እጅግ፡የተጠመደ፡ሆነ፡የከበረ፡
ወንጌል፡በተራራ፡ላይ፡የተሠራች፡መንደር፡
መሠወር፡አትችልም፡እንዳለ፡ዜናው፡በሁሉ፡
ዘንድ፡ተሰማ።

፲፤ የአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳትም፡በአረፈ፡ጊዜ፡
አዋቂዎች፡ኤጲስቆጶሳት፡ይህን፡የከበረ፡
ሳዊሮስን፡ይሾሙት፡ዘንድ፡ተስማምተው፡
ያለ፡ውዴታው፡ወስደው፡በአንጾኪያ፡ሀገር፡
ላይ፡ሊቀ፡ጵጵስና፡ሾሙት፡በሹመቱም፡
እስከ፡ዓለም፡ዳርቻ፡ያለች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ብርሃን፡ሆነላት፡በሀገሮች፡ሁሉ፡ወዳሉ፡
መናፍቃን፡ከሀድያን፡ትምህርቱ፡በሚደርስ፡
ጊዜ፡ሁለት፡አፍ፡እንዳለው፡ስለታም፡ሰይፍ፡
ሥራቸውን፡ይበጥሳልና።

፲፩፤ ከጥቂት፡ቀኖችም፡በኋላ፡አማኒው፡ንጉሥ፡
ሙቶ፡በርሱ፡ፈንታ፡ስሙ፡ዮስጥያኖስ፡
የሚባል፡መናፍቅ፡ነገሠ፡ንግሥቲቱ፡
ሚስቱ፡ግን፡ሃይማኖቷ፡የቀና፡ነው፡
ስሟም፡ቴዎድራ፡ይባላል።ንጉሡም፡የኬል
ቄዶን፡ወደሆነች፡ወደረከሰች፡ሃይማኖቱ፡
ይህን፡የከበረ፡አባት፡ያስገባው፡ዘንድ፡ያስ
ፈራራው፡ነበር፡እርሱ፡ግን፡ፈርቶ፡አይታዘ
ዝለትም፡ቍጣውንም፡የሚፈራ፡መስሎት፡
በእርሱ፡ላይ፡አብዝቶ፡ተቆጣ፡ቍጣውንም፡
ባልፈራ፡ጊዜ፡በሥውር፡ሊያስገድለው፡
መከረ፡ንግሥቲቱም፡አውቃ፡ከንጉሡ፡ፊት፡
ይሸሽ፡ዘንድ፡ሊቀ፡ጳጳሳቱን፡መከረችው፡

www.ethiopianorthodox.org

በኀቡእ፡ወተግኅሠ፡እስመ፡ኢፈቀደ፡እግዚአ ብሔር ፡ ሞቶ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ አላ ፡ ዐቀቦ ፡ በእንተ፡በቍዔተ፡መሃይምናን።

፲፪፡ ወኮነ ፡ ዘየዐውድ ፡ ውስተ ፡ አዕፃዳት ፡ ወአድ ባራት ፡ በአምሳለ ፡ ፩ መነኰስ ፡ ወያጸን ዖሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ እንዘ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ስካ ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ ምእመን ፡ ኄር ፡ ዘስሙ ፡ ዶርታኦስ ፡ ወይገብር ፡ እግዚእነ ፡ በእደዊሁ ፡ ተአም ራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወይሜ ህሮሙ፡ለኵሎሙ፡ከመ፡ይጽንዑ፡ውስተ፡ ሃይማኖት፡ርትዕት፡እስከ፡አዕረፈ፡በሀገረ፡ ስካ። ወእምዝ ፡ አፍለሱ ፡ ሥጋሁ ፡ ኀበ ፡ ደብረ፡ዝጋግ።

፲፫፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከያኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እርሱም፡በሥውር፡ወጥቶ፡ገለል፡አለ፡እግ ዚአብሔር፡የዚህን፡አባት፡ሞት፡አልፈቀ ደምና፡ስለ፡ምእመናንም፡ጥቅም፡ጠበቀው።

፲፪፡ በአንድ ፡ ተራ ፡ መነኰሴ ፡ አምሳል ፡ ሁኖ ፡ በቦታዎችና ፡ በገዳማት ፡ የሚዘዋወርና ፡ ምእ መናንን ፡ የሚያጠናክራቸው ፡ ሆነ ፡ ስካ ፡ በሚባል ፡ አገርም ፡ ስሙ ፡ ዶርታኦስ ፡ ከሚባል ፡ ደግ ፡ ምእመን ፡ ባለ ፡ ጸጋ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ጌታችን ፡ በእጆቹ ፡ ብዙ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ አደረገ ፡ ስካ ፡ በተባለ ፡ ሀገርም ፡ እስከ ፡ አረፈ ፡ ድረስ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ንም ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡ ከዚህም፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዝጋግ ፡ ገዳም ፡ አፈለሱት።

፲፫፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡ እኛ ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ሰላም ፡ ለሳዊሮስ ፡ አንበሳ ። አገዳ ፡ ዐላውያን ፡ ዘይሰብር ፡ ወዘመናፍቃን ፡ ቴክሳ ። እስመ ፡ በትምህርቱ፡ አንጽሓ ፡ ወበሃይማኖቱ ፡ ቀደሳ ። ከመ ፡ ኢይቅረባ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከኒሳ ። በዕብነ ፡ ቃሉ ፡ እንዘ፡ ይዌግር ፡ እንስሳ ።

፲፬፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክን ድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፶።

፲፭፡ ወዝንቱ፡ አብ ፡ ተሠይመ ፡ በ፲ወ፯ቱ ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ ፡ ለንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ ዘስሙ ፡ እል መቱዝ ፡ ወውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ እኑሁ ፡ ለመኰንን፡ ወልደ ፡ ኀሮን ፡ ረሺድ ፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ተሐደሱ ፡ አድባራተ ፡ አስቄጥስ ፡ ወተመይጡ ፡ መነኮሳት ፡ ኀቤሆሙ ።

፲፮፡ ወሀሎ ፡ ፩ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ መቃርስ ፡ እምሀ ገረ ፡ አፎን ፡ ወመጽአ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ያዕቆብ ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ይምጻእ ፡ ኀበ ፡ ቤቱ ፡ ወይባርክ ፡ ሎቱ ፡ ውእቱኒ ፡ ሖረ፡ ምስሌሁ ፡ ወወልዱሰ ፡ ዘሐመ ፡ ሞተ ፡ ሶቤሃ፡ ወነሥአ ፡ አቡሁ ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ወሰአሎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተሣሃለኒ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ እስመ ፡ አልብየ ፡ ወልድ ፡ ዘእን በሌሁ ፡ ወውእቱ ፡ ናሁ ፡ ሞተ፡ ወእስእለከ ፡

፲፬፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ አባ ፡ ያዕ ቆብ ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኃምሳኛ ፡ ነው።

፲፭፡ ይህም ፡ አባት ፡ እልመቱዝ ፡ የተባለ ፡ የግ ብጽ ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ሰባት፡ ዓመት ፡ ተሾመ ፡ እርሱም ፡ ለመኰንኑ ፡ ለወ ልደ ፡ ኀሮን ፡ ረሺድ ፡ ወንድም ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ አባት ፡ ዘመን ፡ የአስቄጥስ ፡ ገዳማት ፡ ታድሰው ፡ መነኮሳቱ ፡ ወደሳቸው ፡ ተመለሱ።

፲፮፡ አፎን ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ስሙ ፡ መቃርስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ወደዚህ ፡ አባት ፡ ወደ፡ ያዕቆብ ፡ መጥቶ ፡ ወደቤቱ ፡ በመሔድ ፡ ቤቱን ፡ ይባርክለት ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፡ እር ሱም ፡ አብሮት ፡ ሔደ ፡ ታሞ ፡ የነበረ ፡ ልጁም ፡ ሞተ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ያዕቆብም ፡ አቅርቦ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ልጅ ፡ የለኝምና ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ራራልኝ ፡ እርሱም ፡ እነሆ ፡ ሞተ ፡ ስለርሱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ታስተብቍዖ ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአሁ ።

፲፯፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ኢትፍራህ ፡ በከመ፡ አሚኖትከ ፡ ይኩንከ ፡ ወነሥአ ፡ እምአቡሁ ፡ ወሐቀፎ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡ ወጸለየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአተቦ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወሰአለ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአሁ ፡ ወተወ ክፈ ፡ እግዚእነ ፡ ስእለቶ፡ ወገብአት ፡ ነፍሱ ፡ ለሕፃን ፡ ወከሠተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወሐይወ ፡ እሞት ፡ ወይቤሎ ፡ ለአቡሁ ፡ ንሣእ ፡ ወል ደከ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ምውተ ፡ አላ ፡ ኮነ ፡ ንውመ።

፲፰፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ አቡሁ ፡ ለሕፃን ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ ፈድፋደ ፡ ፈርሀ ፡ ወወሀቦ ፡ መን ፈቀ ፡ ንዋዩ ፡ ለምጽዋት ፡ ውእቱኒ ፡ ፈነወ ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሐነፀ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ጸወነ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይበጽሑ ፡ ኀቤሃ ፡ እምነ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማ ኖት ።

፲፱፡ ወዲዮናስዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ምስር ፡ ተራከበ ፡ ምስለ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ወነበረ ፡ ኀቤሁ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ ወተመይጠ ፡ ብሔሮ ።

፳፡ ወነበረ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ያዕቆብ ፡ ዲበ ፡ መን በረ፡ ሢመቱ ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ ወ፰ተ ፡ አው ራኀ ፡ ወ፲ተ ፡ ዕለተ ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም። ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ አሜን ።

ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትማልድ ፡ ዘንድ ፡ እለመንሃለሁ ፡ አለው።

፲፯፡ አባ ፡ ያዕቆብም ፡ እንደ ፡ እምነትህ ፡ ይሁን ልህ ፡ አትፍራ ፡ አለው ፡ ሕፃኑንም ፡ ከአባቱ ፡ ተቀብሎ ፡ ታቀፈውና ፡ በላዩ ፡ ጸለየ ፡ በመ ስቀል ፡ ምልክትም ፡ አማተበበት ፡ ስለር ሱም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመነ ፡ ጌታ ችንም ፡ ልመናውን ፡ ተቀበለው የሕፃኑ ፡ ነፍስ ፡ ተመልሳ ፡ ዐይኖቹን ፡ ገለጠ፡ ከሞ ትም ፡ ድኖ ፡ ተነሣ ፡ አባቱንም ፡ ልጅህን ፡ ውሰድ ፡ የሞተ ፡ አይደለም ፡ ያንቀላፋ ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለው።

፲፰፡ የሕፃኑም ፡ አባት ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡ ሥራ በአየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ፡ የገንዘቡንም ፡ እኩሌታ ፡ ለምጽዋት ፡ ብሎ ፡ ሰጠው ፡ እር ሱም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልኮ ፡ ሃይማኖ ታቸው ፡ ለቀና ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ወደርሷ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ መጠጊያ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሠራበት ።

፲፱፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮናስዮስም ፡ ወደ ፡ ምስር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከአባ ፡ ያዕቆብ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ተመለሰ።

፳፡ ይህም ፡ አባት ፡ ያዕቆብ ፡ በሹመቱ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ከስምንት ፡ ወር ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ ኑሮ፡ በሰላም ፡ አረፈ ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለያዕቆብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱሱ ። ዘአድባረ ፡ ገዳም ፡ ኵሉ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ተሐደሱ ። እስከ ፡ አቡሁ ፡ ገነየ ፡ ለብዕለ ፡ ጸጋሁ ፡ ወዕበየ ፡ ሞገሱ። በግሠተ ፡ እዴ ፡ ወበጽላሎታ ፡ ለርእሱ ። ውስተ ፡ በድን፡ ሕፃን ፡ ገብአት ፡ ዘወጽአት ፡ መንፈሱ ።

፳፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ዳርዮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ወአኩዳራስ ፡ ወሊድና፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፰ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡

፳፩፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱሳን ፡ ዳርዮስ ፡ የጳውሎስ ፡ የአኩደራስና ፡ የሊድና ፡ መታሰ ቢያቸው ፡ ነው ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ፡ አሜን።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ዐቢይ ፡ ነቢይ ፡ ወጻድቅ ፡ ዘካርያስ ፡ ፩ ፡ እም ፲ ፡ ወ፪ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ።

፬፡ ወውእቱ ፡ እምነገደ ፡ ሌዊ ፡ ወስመ ፡ አቡሁ ፡ በራክዩ ፡ ወወለዶ ፡ በምድረ ፡ ገለዓድ ፡ ወተዜወወ ፡ አመ ፡ ፍልሰተ ፡ ባቢሎን ፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ በህየ ፡ ተነበየ ፡ ትንቢተ ፡ መለኮታዊተ ፡ ዘወረደት ፡ ላዕሌሁ ፡ ወተናገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልሳኑ ፡ ቃላተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወበቋዕያተ ፡ ወተነበየ ፡ ለኢዮሴዴቅ ፡ ወይቤሎ ፡ ትወልድ ፡ ወልደ ፡ ወይከውን ፡ ካህኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እምድኅረ ፡ ሚጠት ፡ ተገብረ ፡ ባቲ ፡ ከማሁ ።

፭፡ ወተነበየ ፡ ለሰላትያል ፡ ወባረኮ ፡ ወይቤሎ ፡ ትወልድ ፡ ወልደ ፡ ወትሰምዮ ፡ ስሞ ፡ ዘሩባቤልሃ ፡ ወውእቱ ፡ የሐንፅ ፡ መቅደሰ ፡ በኢየሩሳሌም ። ወተነበየ ፡ ዓዲ ፡ ለንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ወከሠተ ፡ ሎቱ ፡ ትእምርተ ፡ መዊዕ ።

፮፡ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዘ ፡ ይጼዓን ፡ ዲበ ፡ ዕድግት ፡ ወዲበ ፡ ዕዋለ ፡ ዐድግ ።

፯፡ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ፴ ብሩር ፡ ዘነሥአ ፡ ይሁዳ ፡ በእንተ ፡ አግብኦቱ ፡ ክርስቶስሃ ፡ መድኃኒነ። ወበእንተ ፡ ዝርወቶሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ በሌሊተ ፡ ዓርብ ፡ ዕለተ ፡ ስቅለቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ወበእንተ ፡ ጽልመተ ፡ ፀሐይ ፡ በጊዜ ፡ ቀትር ፡ ወበእንተ ፡ ኀዘኖሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ይቤ ፡ ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይርአይዎ ፡ ለዘወግዕዎ ፡ ወይትመየጡ ፡ ውስተ ፡ ላህ ፡ ወይላህውዎ ፡ ከመ ፡ ዘያፈቅርዎ ፡ ወየሐምሞሙ ፡ ሕማመ ፡ ከመ ፡ ዘለበኵር ፡ ወሶበ ፡ ተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ትንቢቱ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወተቀብረ ፡ ውስተ ፡ መቃብረ ፡ ነቢያት ።

፰፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ፡ ታላቅ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነቢይ ፡ ዘካርያስ ፡ አረፈ።

፬፡ እርሱም ፡ ከሌዊ ፡ ነገድ ፡ ነው ፡ የአባቱም ፡ ስም ፡ በራክዩ ፡ ነው ፡ በገለዓድም ፡ ወለደው ፡ በባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ ጊዜ ፡ ተማረከ ፡ ከዚያ ፡ ሳለም ፡ በላዩ ፡ የወረደለትን ፡ መለኮታዊ ፡ ትንቢትን ፡ ተናገረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በእርሱ ፡ አንደበት ፡ ጠቃሚዎች ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ቃሎችን ፡ ተናገረ ። ለኢዮሴዴቅም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ትንቢትን ፡ ተናገረ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ካህን ፡ ሁኖ ፡ የሚያገለግል ፡ ልጅን ፡ ትወልዳለህ ፡ ከሚጠትም ፡ በኋላ ፡ እንደቃሉ ፡ ሆነ።

፭፡ ለሰላትያልም ፡ ትንቢት ፡ ተናገረለት ፡ ባረከውም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳለህ ፡ ስሙንም ፡ ዘሩባቤል ፡ ትለዋለህ ፡ እርሱም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መቅደስን ፡ ይሠራል፡ አለው ፡ ዳግመኛም ፡ ለፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ተናገረ ፡ የድል ፡ ምልክትንም ፡ ገለጠለት።

፮፡ ጌታችን ፡ በውርንጫዪቱና ፡ በታላቂቱ ፡ አህያ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስለ ፡ መምጣቱ ፡ ተናገረ።

፯፡ ይሁዳም ፡ መድኃኒታችንን ፡ ክርስቶስን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠቱ ፡ ስለ ፡ ተቀበለው ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ። መድኃኒታችንም ፡ በሚሰቀልበት፡ ዐርብ ፡ ሌሊት ፡ ስለ፡ ሐዋርያት ፡ መበተን ፡ ተናገረ። በቀትር ፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ፀሐይ ፡ መጨለም ፡ ተናገረ። ስለ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኀዘንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የወጉትን ፡ ያዩት ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ፡ ወደ ፡ ኀዘንም ፡ ይመለሳሉ ፡ እንደሚወዱትም ፡ ያለቅሱለታል ፡ ሰው ፡ ለበኵር፡ ልጁ ፡ እንደሚያዝን ፡ ጽኑ ፡ ኀዘንን ፡ ያዝናሉ። የትንቢቱም ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በሰላም፡ አረፈ፡ በነቢያት ፡ መቃብርም ፡ ተቀበረ።

፰፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለዘካርያስ ፡ ዘኮነ ፡ ልሁለ ፡ ቃል። በወርኀ ፡ ከሲል ። ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ ዘሐዋርያት፡ መድበል ። አምሳለ ፡ ተቅዋም ፡ ዘመኃትዊሃ ፡ ጽዱል ። ማዕከለ ፡ ክልኤ ፡ አዕፁቅ ፡ ርኢክዋ ፡ ይብል ።

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ቅዳቤሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ዘሰማዕታት፡ ፴ሐራ ፡ ሰማይ በሀገረ ፡ ስብስ ጥያ ።

፰፤ ወእይቲ ፡ ቀዳሚት ፡ ዘተሐንፀት ፡ በስሞሙ ፡ ወቀደሳ ፡ አብ ፡ ዐቢይ ፡ ባስልዮስ ፡ ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ወገብረ ፡ ሎሙ፡ በዓለ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወስብሐት ፡ ለእግ ዚአብሔር ፡ አሜን ።

፯፤ በዚህችም ፡ ዕለት ፡ ስብስጥያ ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ የሰማዕታት ፡ አርባ ፡ ሐራ ፡ ሰማይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ተከበረች።

፰፤ ይችም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስማቸው ፡ አስቀድማ ፡ ተሠራች ፡ ታላቁ ፡ አባት ፡ ባስ ልዮስም ፡ አከበራት ፡ ስለርሳቸውም ፡ ድርሳ ናትን ፡ ደረሰ ፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በዓልን ፡ አደረገላቸው። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስ ጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለቅዳሴ ፡ ቤትክሙ ፡ ዮም ። በሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ባስልዮስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ አድያም ። ሐራ ፡ ሰማይ ፡ አርብዓ ፡ ክቡራነ ፡ ስም። እምግብርናትየ ፡ ተሣየጡኒ ፡ በደም። አመ ፡ ውሉዳ ፡ ኢታድኅን ፡ እም ።

፱፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ጽሙድ ፡ ወመስተ ጋድል ፡ አባ ፡ በፍኑትዮስ ።

፲፤ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ መንኰሰ ፡ እምንእሱ ፡ ወተጋደለ ፡ ተጋድሎ ፡ ዐቢየ ፡ እንዘ ፡ ይተግህ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወበሰጊድ ።

፲፩፤ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ምግባረ ፡ ምንኵስና ፡ ሠናየ ፡ አዘዞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ከመ ፡ ይባእ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ ርኁቀ ፡ እምአድባ ራተ ፡ መነኰሳት ፡ ወየሐውጾሙ ፡ ለገዳማ ውያን ፡ ቅዱሳን ፡ ወይጽሐፍ ፡ ገድሎሙ ፡ በእንተ ፡ በቀኖዔት ፡ ለእለ ፡ ያነብብዋ ።

፲፪፤ ወሶቤሃ ፡ ደነነ ፡ ለትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቦአ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ ወዔለ ፡ ማዕከለ ፡ በድው ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘየዓይል ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወረከቦሙ ፡ ለገዳማውያን ፡ ብዙኃን፡ ወጠየቀ ፡ ዜናሆሙ ፡ ወጸሐፈ ፡ ገድሎሙ ፡ ወቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወቅ ዱስ ፡ አቡናፍር ፡ ገዳማውያን ።

፲፫፤ ወበጽሐ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ በፍኑትዮስ ፡ ምንዳቤ ፡ እምረኃብ ፡ በበዊአቱ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ እስመ ፡ ነበረ ፡ ፫ተ ፡ ዕለተ ፡ ዘእን በለ ፡ ሲሳይ ፡ ወእምዝ ፡ ርኅበ ፡ ወቀርበ ፡ ለመዊት፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ወመዝመዘ ፡ ኵሎ ፡ ሥጋሁ ፡ ወአ ፉሁ፡ ወነበረ ፡ ፲ተ ፡ ወ፯ተ ፡ መዓልተ ፡ ዘእን በለ ፡ ሲሳይ።

፱፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በገድል ፡ ተጠምዶ ፡ የኖረ ፡ አባ ፡ በፍኑትዮስ ፡ አረፈ።

፲፤ ይህም ፡ አባት ፡ ከታናሽነቱ ፡ መንኵሶ ፡ በጾም፡ በጸሎት ፡ በስግደትም ፡ እየተጋ ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን ፡ ተጋደለ።

፲፩፤ ያማረ ፡ የምንኵስናውን ፡ ሥራ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ መነኰሳት ፡ ከሚኖሩበት ፡ ገዳማት ፡ ርቆ ፡ ወደሚገኝ ፡ በረሀ ፡ ውስጥ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ የከበሩ ፡ ገዳማውያንንም ፡ ይጐበ ኛቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሚያነቧት ፡ ጥቅም ፡ ትሆን፡ ዘንድ ፡ ገድላቸውንም ፡ እንዲጽፍ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘው።

፲፪፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ራሱን ፡ ዝንበል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ በረሀ ፡ ገባ ፡ በመንደር ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ሚዞር ፡ ሰው ፡ በዱር ፡ መካከል ፡ ዞረ ። ከገዳ ማውያንም ፡ ብዙዎችን ፡ አገኛቸውና ፡ ዜና ቸውን ፡ ተረድቶ ፡ ገድላቸውን ፡ ጻፈ ፡ ከው ስጣቸውም ፡ የከበሩ ፡ ገዳማውያን ፡ ጢሞቴ ዎስና ፡ አቡናፍር ፡ አሉ።

፲፫፤ ይህንንም ፡ አባት ፡ በፍኑትዮስን ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ በረሀ ፡ በመግባቱ ፡ ከረኃብ ፡ የተነሣ ፡ ሥቃይ ፡ ደርሶበታል ፡ ያለምግብ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አድሮአልና ። ከዚህም ፡ በኋላ፡ ተርቦ ፡ ለሞት ፡ ተቃረበ ፡ ከእግዚአብሔ ርም፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ተገለጸለትና ፡ ሰው ነቱን ፡ ሁሉ ፡ አፉንም ፡ ዳሠሠው ፡ ያለ፡ ምግብም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ኖረ።

፲፬፡ ወካዕበ ፡ ተናገረ ፡ መንክራተ ፡ እምንብረቶሙ ፡ ለገዳማውያን ፡ መጠነ ፡ ፰ ፡ ወ፸ዓ ፡ ዓመት ፡ ወዘይፈደፍድ ፡ እምኔሁ ፡ እንዘ ፡ ኢይሬእዩ ፡ ብእሴ ፡ ግሙራ ፡ በመጠነ ፡ ዝንቱ ፡ መዋዕል ። ወተናገረ ፡ በእንተ ፡ ዘይበጽሖሙ ፡ ምንዳቤ ፡ አመ ፡ በአቶሙ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ እመናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ ወእምአራዊት ፡ ግሩማን ፡ በእንተ ፡ ጸቢአቶሙ ፡ ኪያሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ ይገርሩ ፡ ሎሙ ፡ በትዕግሥቶሙ ፡ አራዊትኒ ፡ ይትለአክዎሙ ፡ ከመ ፡ አግብርት ፡ ወተናገረ ፡ ካዕበ ፡ በእንተ ፡ ተመጥዎተ፡ ቍርባን ፡ እስመ ፡ መላእክት ፡ ያመጽኡ ፡ ሎሙ ፡ ወይሜጥውዎሙ ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሞ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይሁብዎሙ ፡ እምፍሬያተ ፡ ገነት ።

፲፭፡ ወደለዎ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ወይኩን ፡ ስምዐ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ መንክራት ፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ።

፲፮፡ ለስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፲፬፡ ዳግመኛም ፡ ከቶ ፡ ሰው ፡ ሳያዩ ፡ ስድሳና ፡ ሰባ ፡ ዓመት፡ ከዚያም ፡ የሚበዛ ፡ የሚያስደንቅ ፡ የገዳማውያንን ፡ ኑሮአቸውን ፡ ተናገረ ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ በረሀ ፡ በሚገቡ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱን ፡ ስለሚዋጓቸው ፡ ከርኩሳን ፡ መናፍስትና ፡ ከሚያስፈሩ ፡ አራዊት ፡ ስ፡ሚደርስባቸውም ፡ ፈተና ፡ ተናገረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በትዕግሥታቸው ፡ የሚገዙላቸው ፡ ይሆናሉ ፡ አራዊትም ፡ እንደ ፡ ባሮች ፡ ያገለግሏቸዋል ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባንንም ፡ እንዴት ፡ እንደሚቀበሉ ፡ ደግሞ ፡ ተናገረ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ የመድኃኒታችንን፡ ክርስቶስን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ መላእክት ፡ አምጥተው ፡ ያቀብሏቸዋልና ፡ ከገነትም ፡ ፍራፍሬዎችን ፡ ይሰጧቸዋል።

፲፭፡ ለዚህም ፡ አባት ፡ ስለ ፡ እሊህ ፡ ድንቆች ፡ ሥራዎች ፡ አይቶ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ የተገባው ፡ ሆነ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፲፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለበፍኑትዮስ ፡ ከመ ፡ ነገረ ፡ ወይቤ ። ሡነኔ ፡ ሀካያን ፡ ነጺሮ ፡ ወፍዳ ፡ ኃጥአን ፡ ሶቤ ። እንዘ ፡ ከመ ፡ ያፍ ፡ የዓይል ፡ አውግረ ፡ ስሂን ፡ ወአድባረ ፡ ከርቤ። ተዓገሠ ፡ መከራ ፡ ሐቅል ፡ ወዘገዳማት ፡ ምንዳቤ ። ማርቆስ ፡ ሎቱ ፡ እስከነ ፡ ኮነ ፡ ሀቤ ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፮ ፡ ለየካቲት ፡ በዛቲ ዕለት ፡ ኮነት ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ እሙ፡ ለዮሐንስ ፡ ወጥምቅ ።

፪፡ ወዛቲ ፡ ቅድስት ፡ እምሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወስማ ፡ ለእማ ፡ ሶፍያ ፡ ወለቱ ፡ ለማጣት ፡ እምቤተ ፡ አሮን ፡ ዘእምነገደ ፡ ሌዊ ፡ ወኮነት፡ በዘመድ ፡ ወለተ ፡ እኅተ ፡ እማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ። እስመ ፡ ማጣት ፡ ወለደ ፡ ሠላሰ ፡ አዋልደ ፡ ወስማ ፡ ለእተ ፡ ትልሕቅ ፡ ማርያም ፡ ወይእቲ ፡ ወለደታ ፡ ለሰሎሜ ፡ እንተ ፡ ተልዕከታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ አመ ፡ ስደታ ፡ ብሔረ ፡ ግብጽ ። ወካልዕታ ፡ ሶፍያ ፡ ወይእቲ ፡ እማ ፡

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የመጥምቁ ፡ ዮሐ /ስ፡ እናት ፡ የከበረች ፡ ኤልሳቤጥ ፡ አረፈች።

፪፡ ይህች ፡ ቅድስት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የሆነች ፡ የእናቱዋ ፡ ስም ፡ ሶፍያ ፡ ነው ፡ እርሷም ፡ ከሌዊ ፡ ነገድ ፡ ከአሮን ፡ ወገን ፡ ለሆነ ፡ ለማጣት ፡ ልጁ ፡ ናት ፡ በዝምድና ፡ አምላክን ፡ ለወለደች ፡ ላእመቤታችን ፡ ለቅድስት፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የእናቷ ፡ እኅት ፡ ልጅ ፡ ናት። ማጣት ፡ ሦስት ፡ ልጆችን ፡ ወለዷልና ፡ የታላቂቱም ፡ ስም ፡ ማርያም ፡ ነው ፡ እርሷም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በተሰደደች ፡ ጊዜ ፡ እመቤታችንን ፡ ያገለገለች ፡ ሰሎሜን ፡ ወለ

ለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ወለእንተ ፡ ትንእስ ፡ ስማ ፡ ሐና ፡ ወይእቲ ፡ ወለደታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወኮና፡ ሰሎሜ ፡ ወኤልሳቤጥ ፡ ወእግዝእትነ፡ ማርያም ፡ አዋልደ ፡ አኃት ።

፫፡ ወለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ አውሰባ ፡ ዘካርያስ ፡ ካህን ፡እስመ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ጻድቃን ፡ ወኄራን ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በኵሉ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ።

፬፡ ወኤልሳቤጥኒ ፡ በእንተ ፡ ከዊኖታ ፡ መካነ ፡ ኮኑ፡ ዘይስእሉ ፡ ወያስተበቍዑ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሶበ ፡ ልሕቁ ፡ ውኅለፈ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብርኤልሃ ፡ መልአኮ ፡ ኀበ ፡ ዘካርያስ ፡ ወዜነዎ ፡ ከመ ፡ ተሰምዐ ፡ ስእለቶሙ ፡ ወአጠየቆ ፡ በእንተ ፡ ልደቱ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወይከውን ፡ እምኔሆሙ።

፭፡ ወእምዝ ፡ ፀንሰቶ ፡ ዛቲ ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ፡ ወወለደቶ ፡ ለዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ወተአተተ ፡ ዝንጓጔሃ ፡ እምሰብእ ፡ ወተፈሥሐት ፡ ጥቀ።

፮፡ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ ዕጓል ፡ በውስተ ፡ ከርሣ ፡ ሶበ ፡ ተአምኃታ ፡ እግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ከልሐት ፡ ወትቤ ፡ ቡርክት ፡ አንቲ ፡ እምአንስት ፡ ወቡሩክ ፡ ፍሬ ፡ ከርሥኪ ፡ ምንትኑ ፡ አነ ፡ ከመ ፡ ትምጽኢ ፡ ኀቤየ ፡ እሙ ፡ ለእግዚእየ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ሶበ ፡ ሰማዕኩ ፡ ቃለኪ ፡ እንዘ ፡ ትትአምኅኒ ፡ አንፈርዐፀ ፡ ዕጓል ፡ በውስተ ፡ ከርሥየ ፡ በፍሥሐ።

፯፡ ወእምዝ ፡ ርእየቶ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወተአመነት ፡ በመለኮቱ ፡ ወተፈሥሐት ፡ በድኅነቶሙ ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ፡ ወፈጺማ ፡ መዋዕሊሃ፡ አዕረፈት ፡ በውስተ ፡ ገዳም።

፰፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎታ ፡ ለኤልሳቤጥ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ደቻት ፡ ሁለተኛዋም፡ ሶፍያ ፡ ናት ፡ እርሷም ፡ የዚች ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ እናቷ ፡ ናት ፡ የታናሺቱም ፡ ስም ፡ ሐና ፡ ነው። እርሷም ፡ የከበረች ፡ ድንግል ፡ እመቤታችንን ፡ ማርያምን ፡ ወለደቻት። ሰሎሜ፡ ኤልሳቤጥ ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ የእኅትማማች ፡ ልጆች ፡ ናቸው።

፫፡ ይችንም ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ካህኑ ፡ ዘካርያስ ፡ አገባት ፡ የከበረ ፡ ወንጌልም ፡ ስለ ርሳቸው ፡ ተናግሯልና ፡ እነርሱ ፡ ሁለቱም ፡ ያለ ፡ ነውር ፡ ያለ ፡ ነቀፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ዕውነተኞች ፡ ደጎች ፡ ሆኑ።

፬፡ ኤልሳቤጥም ፡ መካን ፡ ስለሆነች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚለምኑና ፡ የሚማልዱ ፡ ሆኑ ፡ አርጅተውም ፡ የመውለጃቸው ፡ ዘመን ፡ በአለፈ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአኩን ፡ ገብርኤልን ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ ልኮ ፡ ጸሎታቸው ፡ ልመናቸው ፡ እንደ ፡ ተሰማ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ መወለድና ፡ ከእርሱ ፡ ስለሚሆነው ፡ አስረዳው።

፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይቺ፤ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ መጥምቁን ፡ ዮሐንስን ፡ ፀንሳ ፡ ወለደችው ፡ ከሰዎችም ፡ የሚደርስባት ፡ ሽሙጥ ፡ ተወግዶ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላት።

፮፡ ሕፃኑም ፡ በማሕፀኗ ፡ እያለ ፡ እመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሰላምታ ፡ በሰጠቻት ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ጮኸች ፡ ከሴቶች ፡ ተለይተሽ ፡ አንቺ ፡ የተባረክሽ ፡ ነሽ ፡ የማኅፀንሽም ፡ ፍሬ ፡ ቡሩክ ፡ ነው። የጌታዬ ፡ እናት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመጪ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ምንድን ፡ ነኝ ፡ እነሆ ፡ እንደዬት ፡ ነሽ ፡ ስትይኝ ፡ የሰላምታሽን ፡ ድምፅ ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ በማሕፀኔ ፡ ውስጥ ፡ በደስታ ፡ ዘለለ።

፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታችንን ፡ አየችው ፡ በአምላክነቱም ፡ አመነች ፡ የሚያምኑበትም ፡ በመዳናቸው ፡ ደስ ፡ አላት ፡ ዕድሜዋንም ፡ በፈጸመች ፡ ጊዜ ፡ በበረሀ ፡ ውስጥ ፡ ሳለች ፡ አረፈች።

፰፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በኤልሳቤጥ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቷም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለኤልሳቤጥ ፡ እንተ ፡ ወደሳ ፡ ወአልዓላ። ሉቃስ ፡ ወንጌለ ፡ ሶበ ፡ ጸሐፈ ፡ ለታኦፊላ። ሀገረ ፡ ይሁዳ ፡ አሜሃ ፡ ሶበ ፡ በጽሐት ፡ እምገሊላ። ተንሥየ ፡ በውስተ ፡ ከርሣ ፡ ወአንፈርዓፀ ፡ ዕጓላ። ለማርያም ፡ ድንግል ፡ ሶበ ፡ ሰምዓት ፡ ቃላ።

፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ይገብሩ ፡ በዓለ ፡ ኵሎሙ ፡ ዘመደ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ።

፲፡ እስመ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ነሥአት ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ እምኀበ ፡ ወልዳ ፡ ፍቁር ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት ፡ ለዘይገብር ፡ ተዝካራ ፡ ወይጼውዕ ፡ ስማ ፡ ወለዘይሁብ ፡ ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ እስከ ፡ ማይ ፡ ቈሪር።

፲፩፡ ወዛቲ ፡ ቅድስት ፡ እግዝእትነ ፡ እምድኅረ ፡ ዐርገ ፡ ወልዳ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ነሢኦ ፡ ሥጋሃ ፡ ንጹሐ ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ፡ ፈጺሞ ፡ ኵሎ ፡ ሕገ ፡ ትስብእት ፡ ዘእንበለ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ወሠሊጦ ፡ ሕማማተ ፡ መስቀል ፡ በሥምረቱ ፡ ዘገብሮ ፡ በእንቲ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወኀደጋ ፡ ለእሙ ማርያም ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ዮሐንስ ፡ ረድኡ ፡ በከመ ፡ አማሕፀና ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ነዋ ፡ ወልድኪ ፡ ወለውእቱኒ ፡ ይቤሎ ፡ ነያ ፡ እምከ።

፲፪፡ ወእምአሜሃ ፡ ነበረት ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም፡ እንዘ ፡ ተሐውር ፡ ከመ ፡ ትጸሊ ፡ ኀበ ፡ መቃብረ ፡ ወልዳ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዓት ፡ ዘውእቱ ፡ ጎልጎታ።

፲፫፡ ወሶበ ፡ ርእይዋ ፡ አይሁድ ፡ ተመልኡ ፡ መዓተ ፡ ወቅንአተ ፡ ወፈቀዱ ፡ ይገርዋ ፡ በአዕባን ፡ ወሠወራ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአዕይንቲሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ ተማከሩ ፡ ወሜሙ፡ ዐቀብተ ፡ ኀበ ፡ መቃብር ፡ ከመ ፡ ኢትብጻሕ ፡ ዳግመ ፡ ወኢትጸሊ ፡ በህየ ፡ ይእቲሰ ፡ ኢያጽርዓት ፡ ሐዊረ ፡ ለለዕለቱ ፡ ዐቀብትኒ ፡ ኢይሬእይዋ ፡ እስመ ፡ ሠወራ ፡ መንጦላዕተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለወልዳ ፡ ወይመጽኡ ፡ መላእክት ፡ ከመ ፡ ይትለአክዋ ፡ ወእግዚእነሂ ፡ ይሔ

፱፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የክርስቲያን ወገኖች ፡ ሁሉም ፡ አምላክን ፡ ለወለደች ፡ ለእመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በዓልን ፡ ያደርጋሉ።

፲፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ መታሰቢያዋን ፡ ለሚያደርግ ፡ ስሟን ፡ ለሚጠራ ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች፡ እስከ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ውኃ ፡ ለሚሰጥ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ከሆነ ፡ ከተወደደ ፡ ልጅዋ ፡ ከጌታችንና ፡ ከመድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የምሕረት ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ተቀብላለችና።

፲፩፡ ይህችም ፡ የከበረች ፡ እመቤታችን ፡ ልጅዋ ፡ ንጹሕ ፡ ሥጋዋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ከብቻዋ ፡ ኃጢአት ፡ በቀር ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለእኛ ፡ መዳን ፡ ወዶ ፡ የደረገውን፡ መከራ ፡ ተቀብሎ ፡ ሙቶ ፡ ተነሥቶ ፡ ከዐረገና ፡ በአባቱ ፡ ዕሪና ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ እርሷን ፡ እናቱን ፡ ማርያምን ፡ በደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘንድ ፡ ትቷት ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡ ልጅሽ ፡ እርሱንም ፡ እነሆዋት ፡ እናትህ ፡ ብሎ ፡ አደራ ፡ እንዳስጠበቀው።

፲፪፡ ከዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ጀምራ ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ትጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ፡ ወደ ፡ ልጅዋ ፡ መቃብር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ስትሔድ ፡ ኖረች ፡ ይኸውም ፡ ጎልጎታ ፡ ነው።

፲፫፡ አይሁድም ፡ በአዩዋት ፡ ጊዜ ፡ ቊጣንና ፡ ቅናትን ፡ ተመልተው ፡ በደንጊያ ፡ ሊወግሩዋት ፡ ወደዱ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከዓይናቸው ፡ ሠወራት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ መጥታ ፡ በዚያ ፡ እንዳትጸልይ ፡ ተማክረው ፡ ከመቃብሩ ፡ ዘንድ ፡ ጠባቂዎችን ፡ አኖሩ ፡ እርሷ ፡ ግን ፡ በየዕለቱ ፡ መሔድን ፡ አላቋረጠችም ፡ ጠባቆችም ፡ አያይዋትም ፡ የልጅዋ ፡ የጌትነቱ ፡ መጋረጃ፡ ሠውርዋታልና ፡ መላእክትም ፡ መጥተው ፡ ያገለግ

www.ethiopianorthodox.org

ውፃ ፡ ዘልፈ፡ ወይፌጽም ፡ ላቲ ፡ ኵሎ ፡ ዘኃሠ
ሠት።
፲፬፡ ወእምዝ ፡ አዕረግዋ ፡ መላእክት ፡ ውስተ ፡
ሰማያት ፡ ወአርአይዋ ፡ መካነ ፡ ማኅደሮሙ፡
ለጻድቃን ፡ ወአብጽሕዋ ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡
አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወተቀ
በልዋ ፡ ኵሎሙ ፡ አበው ፡ እለ ፡ አዕረፉ ፡
እምአዳም ፡ እስከኔሁ ፡ ወሰገዱ ፡ ላቲ ፡ እንዘ፡
ይብሉ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘፈ
ጠረ፡ ለነ ፡ ኪያኪ ፡ ሥጋ ፡ እምሥጋነ ፡ ወዐ
ፅመ ፡ እምዐፅምነ ፡ ወብኪ ፡ እስመ ፡ ረከ
ብነ ፡ መድኃኒተ ፡ ወኮንክነ ፡ መርሶ ፡ ሕይ
ወት ፡ እሙስና ፡ በተሠግዎቱ ፡ ለወልደ ፡
አምላክ ፡ እምኔኪ።
፲፭፡ ወእምህየ ፡ አብጽሕዋ ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ስብ
ሐቲሁ፡ለፍቁር፡ ወልዳ፡ኀበ፡ተተክሉ፡መን
ጠዋልዕ ፡ ዘነደ ፡ እሳት ፡ ይምነ ፡ ወጽግመ ፡
ወአኃዛ፡እግዚእነ፡እዴሃ፡ወአብአ፡ውሳጤ፡
መንጦላዕት ፡ ወአዕረጋ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡
ስብሐቲሁ፡ ወአንበራ፡ ምስሌሁ፡ ወዜነዋ፡
ኵሎ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ዘዐይን ፡ ኢርእየ፡
ወዕዝን፡ ኢሰምዐ ፡ ወውስተ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡
ዘኢተሐለየ፡ዘአስተደለወ፡ላቲ።
፲፮፡ ወእምታሕተ፡መንበረ፡ስብሐቲሁ፡ርእየቶ፡
ለዳዊት ፡አቡሃ፡ንጉሠ፡እስራኤል፡ምስለ፡
ኵሎሙ ፡ ማኅበረ ፡ ነቢያት ፡ ወመላእክት ፡
ወነፍሳተ ፡ ጻድቃን ፡ ከቢቦሙ ፡ ከመ ፡ አረ
ፍት፡ይዜምር፡በመሰንቆ፡ወይብል፡ስምዒ፡
ወለትየ ፡ ወርእዪ ፡ ወአጽምዒ ፡ ዕዝነኪ ፡
ርስዒ ፡ ሕዝበኪ ፡ ወቤተ ፡ አቡኪ ፡ እስመ ፡
ፈተወ ፡ ንጉሥ ፡ ስነኪ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡
እግዚእኪ።
፲፯፡ ወእምህየ፡ካዕበ፡ወሰድዋ፡መላእክት፡ከመ፡
ያርእይዋ፡መካነ፡ኵነኔ፡ወአብጽሕዋ፡ኀበ፡
ሀሎ፡ጸናፌ፡ጽልመት፡ዘድልው፡ለሰይጣን፡
ወለሠራዊቱ፡ ወለኵሎሙ፡ እለ ፡ የሐውሩ፡
በፍናዊሁ ። ወትቤ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡
ወይ ፡ ሊተ ፡ መኑ ፡ እምዜነዎሙ ፡ ለውሉደ ፡
ሰብእ ፡ ከመ ፡ ኢይምጽኡ ፡ ዝየ ፡ ወይቤላ ፡
መልአክ ፡ ኢትፍርሂ ፡ አ ፡ እግዝእትየ ፡
ቡርክት ፡ ማርያም ፡እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡
ምስሌኪ ፡ ለኪሂ ፡ ወለእለ ፡ እምድኅሬኪ ፡

ሏታል ፡ ጌታችንም ፡ ዘወትር ፡ ይጐበኛታል ፡
የምትሻውንም ፡ ይፈጽምላት ፡ ነበር።
፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መላእክት ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡
አሳረጓትና ፡ የጻድቃንን ፡ ማደሪያዎች ፡ አሳዩ
ዋት ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ያዕቆብም ፡ ወዳ
ሉበት ፡ አደረሱዋት ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡
እስከዚያ ፡ ዕለት ፡ በአካለ፡ ነፍስ ፡ ያሉ ፡
አባቶች ፡ ሁሉ ፡ አንቺን ፡ ከሥጋችን ፡
ሥጋን ፡ ከዐፅማችን ፡ ዐፅምን ፡ ለፈጠረልን ፡
ለእግዚአብሔር ፡ምስጋና ፡ ይሁን ፡ የአምላክ ፡
ልጅ ፡ ከአንቺ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ በአንቺ ፡
ድኅነትን ፡ አግኝተናልና ፡ ከጥፋትም ፡ የሕይ
ወት ፡ ወደብ ፡ ሁነሽልናልና ፡ እያሉ ፡ ሰገ
ዱላት።
፲፭፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ተወደደ፡ ልጅዋ ፡የእሳት ፡
መጋረጃ ፡ ወደተተከለበት ፡ ወደ ፡ ጌትነቱ
ዙፋን ፡ አደረሱዋት ፡ ጌታችንም፡ እጅዋን ፡
ይዞ፡ወደ፡ውስጠኛው፡መጋረጃ፡አስገብቶ፡
ከጌትነቱ፡ዙፋን፡ላይ፡አውጥቶ፡ከእርሱ፡
ጋር፡አስቀመጣት፡ያዘጋጀላትንም፡ዐይን፡
ያለየው፡ጆሮ፡ያልሰማው፡በሰው፡ልቡና፡
ያልታሰበ፡ተድላ፡ደስታን፡ሁሉ፡ነገራት።
፲፮፡ ከጌትነቱ ፡ ዙፋንም ፡ በታች ፡ የእስራኤል ፡
ንጉሥ ፡ አባቷ ፡ ዳዊትን ፡የነቢያትና ፡ የመላ
እክት ፡ ማኅበር ፡ እንደግድግዳ ፡ ከበውት ፡
በመሰንቆ፡ሲያመሰግን፡አየችው፡እንዲህም፡
ይላል፡ልጄ፡ስሚ፡በጆሮሽም፡አድምጪ፡ወገ
ንሽን ፡ የአባትሽንም ፡ ወገን፡ ርሺ ፡ ንጉሥ ፡
ደም፡ግባትሽን፡ወዷልና፡እርሱም፡ጌታሽ፡
ነውና።
፲፯፡ ዳግመኛም ፡ የሥቃይን ፡ ቦታ ፡ ያሳዩዋት ፡
ዘንድ፡ መላእክት፡ ከዚያ፡ ወሰዱዋት፡ ለሰይ
ጣንና ፡ ለሠራዊቱ ፡ በእርሱ ፡ ጐዳና ፡
ለሚጓዙ፡ ሁሉ ፡ ወደተዘጋጀ ፡ ወደጨ
ለማው፡ ዳርቻ ፡ አደረሷት ። እመቤታችን ፡
ማርያምም ፡ ወዮልኝ ፡ ወደዚህ ፡ እንዳ
ይመጡ፡ ለሰው፡ ልጆች፡ ማን ፡ በነገራቸው፡
አለች ፡ መልአኩም ፡ እመቤቴ ፡ ቡርክት ፡
ማርያም ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንቺ ፡
ጋር፡ ይኖራልና ፡ ለአንቺም ፡ ከአንቺ ፡
በኋላም፡ በቃል ፡ ኪዳንሽ ፡ ለሚታመኑ ፡
አትፍሪ ፡ አላት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወእምዝ፡ሜጥዋ፡ኀበ፡መካና።
፲፰፡ ወእምአሜሃ፡ነበረት፡እግዝእትነ፡ማርያም፡
ድንግል ፡ እንዘ ፡ ተኀዝን ፡ ጥቀ ፡ በእንተ ፡
ኃጥኣን፡ወበከመ፡ዛቲ፡ዕለት፡እመ፡፲ወ፰ለ
የካቲት ፡ ቆመት ፡ መካነ ፡ ጎልጎታ ፡ ወሰ
አለት፡ ኀበ ፡ ወልዳ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ አም
ሕለከ፡ኦ፡ወልድየ፡በእግዚአብሔር፡አቡከ፡
ወበክርስቶስ ፡ ስምከ ፡ ወበጰራቅሊጦስ ፡
መንፈስ፡ቅዱስ፡ዘህልው፡ምስሌከ፡ወአም
ሕለከ ፡ በከርሥየ ፡ ዘፆረተከ ፡ ፱ አውራኀ ፡
ወ፫ተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ኵሎን ፡ ዓለማት ፡
ኢይክሉ ፡ ፀዊሮተከ ፡ ወአምሕለከ ፡ ኦ ፡
ወልድየ ፡ በጸአትከ ፡ እምኔየ ፡ ወበልደትከ፡
ዘእንበለ ፡ ድካም ፡ ወሕማም ፡ ወበአጥባ
እትየ፡ እለ ፡ ሐፀናከ ፡ ወበከናፍርየ ፡ እለ ፡
ሰዓማከ፡ወበአእዳውየ፡እለ፡ሐቀፉከ፡ወበአ
እጋርየ ፡ እለ ፡ አንሶሰዋ ፡ ምስሌከ ፡
አምሕልከ፡በጎል፡ዘሰከብከ፡ውስቴቱ፡ወበ
አጽርቅት ፡ ዘተጠብለልከ ፡ ቦቱ ፡ ኦ ፡ ወል
ድየ፡ ወፍቁርየ ፡ እስእል፡ ወአስተበቍዕ ፡
ኀቤከ ፡ ከመ ፡ ትስማዕ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ፡
ወትምጻእ ፡ ኀቤየ ፡ ወትፌጽም ፡ ኵሎ ፡
ዘውስተ፡ልብየ።
፲፱፡ ወሶቤ፡ትቤ፡ከመዝ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡
ድንግል ፡ ማርያም ፡ እሙ ፡ ለብርሃን ፡ ናሁ ፡
ወረደ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ወምስሌሁ ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ፡
መላእክት፡እንዘ፡የዐውድዎ፡ወይሴብሕዎ።
ወይቤላ፡ምንተ፡እግበር፡ለኪ፡
እምየ ፡ ወአውሥአቶ ፡ እግዝእትነ ፡ ወት
ቤሎ፡ ለፍቁር ፡ ወልዳ ፡ ኦ ፡ ወልድየ ፡ ወፍ
ቁርየ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ተስፋየ ፡
ወጸወንየ፡ወብከ፡ጸናዕኩ፡በውስተ፡ከርሠ፡
እምየ ፡ ወበውስተ ፡ ማሕፀን ፡ አንተ ፡ ከደ
ንከኒ፡ወአንተ፡ዝክርየ፡በኵሉ፡ጊዜ።

፳፡ ወይእዜኒ ፡ ስምዓኒ ፡ ጸሎትየ ፡ ወስእለትየ ፡
ወአፅምዕ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ፡ አነ ፡ እምከ ፡ ወአነ ፡
አመትከ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ተዝካርየ ፡
ወየሐንፁ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስምየ ፡
አው ፡ ዘያለብስ ፡ ዕሩቀ ፡ ወዘያጸግብ ፡ ርኁበ ፡
ወዘያሰቲ ፡ ጽሙዐ ፡ ወዘይሔውጽ ፡ ድውየ ፡
ወይናዝዝ ፡ ኀዙነ ፡ ወያስተፌሥሕ ፡ ትኩዘ ፡
አው፡ዘይጽሕፍ፡ውዳሴየ፡ወይሰሚ፡ውሉዶ፡

ቦታዋ፡መለሷት።
፲፰፡ ከዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ጀምራ ፡ እመቤታችን ፡
ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስለ ፡ ኃጥአን ፡ እጅግ ፡
እያዘነች፡ኖረች፡እንደ፡ዛሬዪቱም፡የካቲት፡
ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ በጎልጎታ ፡ ቦታ ፡
ቁማ፡ ወደ ፡ ልጅዋ ፡ እንዲህ ፡ ብላ፡ ለመነች።
ልጄ ፡ ሆይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አባትህ ፡ በክር
ስቶስ ፡ ስምህ ፡ ከአንተ ፡ ጋርም ፡ ህልው ፡
በሆነ፡ አጽናኝ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አማፅን
ሃለሁ፡ ዓለም፡ ሁሉ፡ ሊሸከምህ፡ የማይችል፡
ሲሆን፡ዘጠኝ፡ወር፡ከአምስት፡ቀን፡በተሸከ
መችህ፡ማሕፀኔ፡አማፅንሃለሁ፡ልጄ፡ሆይ፡
ያለ ፡ ሕማም ፡ ያለ ፡ ድካም ፡ ከእኔ ፡ በመው
ጣትህ ፡ በመወለድህ ፡ በአሳደጉህ ፡ ጡቶቼ ፡
በሳሙህ ፡ ከንፈሮቼ ፡ በአቀፉህ ፡ እጆቼ ፡
ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በተመላለሱ ፡ እግሮቼ ፡ አማፅ
ንሃለሁ። በውስጡ፡በተኛህበት፡በረት፡በተ
ጠቀለልክበት ፡ ጨርቅ ፡ አማፅንሃለሁ ፡
የምወድህ፡ልጄ፡ሆይ፡በልቡናዬ፡ያለውን፡
ሁሉ፡ትፈጽም፡ዘንድ፡የልመናዬን፡ቃል፡
ሰምተህ፡ወደእኔ፡ትመጣ፡ዘንድ፡ወዳንተ፡
ፈጽሜ፡እማልድሃለሁ።

፲፱፡ የብርሃን ፡ እናቱ ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ ማርያምም፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ በጸ
ለየች፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ጌታችንና ፡ መድኃኒ
ታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወረደ ፡
ከእርሱም፡ጋር፡አእላፋት፡መላእክት፡አሉ፡
በዙሪያውም ፡ ሁነው ፡ ያመሰግኑታል ።
እርሱም፡እናቴ፡ማርያም፡ሆይ፡ምን፡ላድር
ግልሽ፡አላት፡እመቤታችንም፡ለተወዳጅ፡
ልጅዋ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ፡ ልጄ ፡
ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ጌታዬና ፡ ፈጣሪዬ ፡ አለኝ
ታዬና፡ መጠጊያዬ ፡ በእናቴ ፡ ማሕፀንም ፡
ሳለሁ፡በአንተ፡ጸናሁ፡አንተም፡ጠበቅኸኝ፡
ሁልጊዜም፡ስም፡አጠራሬ፡አንተ፡ነህ።
፳፡ አሁንም ፡ ጸሎቴንና ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፡
ቃሌንም፡አድምጥ፡እኔ፡እናትህ፡እኔም፡አገል
ጋይህ ፡ የምለምንህ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ መታሰቢ
ያዬን፡ ለሚያደርጉ ፡ በስሜ ፡ አብያተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ለሚሠሩ ፡ ወይም ፡ የተራቆተውን ፡
ለሚያለብሱ፡የተራበውን፡ለሚያጠግቡ፡የተ
ጠማውንም ፡ ለሚያጠጡ ፡ የታመመውን፡
ለሚጐበኙ ፡ ያዘነውን ፡ ለሚያረጋጉ ፡ የተከዘ

www.ethiopianorthodox.org

በስምየ፡ወዘኀለየ፡ማኅሌተ፡በዕለተ፡በዓልየ፡ ዕስዮ ፡ እግዚኦ ፡ ዘዐይን ፡ ኢርእየ ፡ ወዕዝን ፡ ኢሰምዐ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢተሐለየ ፡ ወለኵሉ ፡ ዘይትአመን ፡ በአስተብቍዖትየ ፡ ረስዮ፡እግዚኦ፡ግዑዘ፡እምሲኦል፡ተዘኪረከ፡ ረኃበ ፡ ወጽምዐ ፡ ወኵሎ ፡ ዐጸባ ፡ ዘበጽሐኪ ፡ ምስሌከ ፡ ወይቤላ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይኩንኪ ፡ በከመ ፡ ትቤሊ ፡ መሐልኩ ፡ ለኪ ፡ በርእስየ ፡ ከመ ፡ ኢይኄሱ ፡ ኪዳንየ፡ዘወሀብኩኪ።

፳፩፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ውንም ፡ ደስ ፡ ለሚያሰኙ ፡ ወይም ፡ ምስጋናዬን፡ ለሚጽፉ ፡ ልጆቼንም ፡ በስሜ ፡ ለሚሰይም፡በበዓሌም፡ቀን፡በማኅሌት፡ለሚያመሰግን፡አቤቱ፡ዐይን፡ያላየውን፡ጆሮ፡ያልሰማውን ፡ በሰውም ፡ ልቡና ፡ ያልታሰበውን ፡ በጎ፡ዋጋ፡ስጣቸው፡በአማላጅነቴም፡የሚታመነውን፡ሁሉ፡ከሲኦል፡ነጻ፡አድርገው፡ከአንተ ፡ ጋር ፡ የደረሰብኝን ፡ ረኃቡንና ፡ ጥማቱን ፡ መከራውን፡ሁሉ፡አስብ፡አለችው። ጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ እንደልሽው ፡ ይሁንልሽ፡የሰጠሁሽም፡ቃል፡ኪዳን፡እንዳይታበል፡በራሴ፡ማልኩልሽ፡አላት።

፳፩፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በእመቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም፡ በጸሎቷ ፡ ይማረን ፡ በረከቷም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለኪ፡መጽሐፈ፡ሕግ፡ወኪዳን። አምሳለ፡ጽሌ፡ዘዕብን። ለእለ፡ጸውዑ፡ስመኪ፡ውስተ፡ገጸ፡ኵሉ፡መካን። ርኅርኀተ፡ልብ፡ለኃጥአን፡ርኅርኀተ፡ልብ፡ለግፉዓን። ርኅርኀተ፡ልብ፡ለኵሉ፡ማርያም፡አማን።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፲ወ፯ ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡ ኮነ፡ሰማዕተ፡ሚናስ፡መነኰስ፡እምሀገረ፡ አክሚም፡ዘላዕላይ፡ግብጽ።

፪፤ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡አበዊሁ፡ክርስቲያን፡እለ፡ ይትጌበሩ፡ምድረ። ወውእቱ፡መነነ፡ዓለመ፡ ወመንኰሰ ፡ በውስተ ፡ ፩ ደብር ፡ ዘሀገረ ፡ አክሚም፡ወነበረ፡ብዙኀ፡መዋዕለ፡እንዘ፡ ይጸውም፡በበ፪ቱ፡መዓልት፡ወኢይጸመድ፡ ለሲሳይ፡ወለስታይ፡ወእምህየ፡ፈለሰ፡ኀበ፡ ሀገረ፡እስሙናይን፡ወነበረ፡ውስተ፡፩ደብር፡ ፲ወ፯ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይጸመድ ፡ ወይት ጋደል ፡ ወኢይወጽእ ፡ እምኖኅተ ፡ ውእቱ ፡ ደብር።

፫፤ ወሶበ ፡ ነግሡ ፡ ተንባላት ፡ በብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ሰምዑ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይብሉ፡አልቦ፡ወልድ፡ለእግዚአብሔር፡እምነ፡ ባሕርዩ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ዘሠረፀ፡እምኔሁ፡ ዘህልው፡ምስሌሁ፡ለዓለም፡ኀዘነ፡ፈድፋደ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ከአክሚም፡መንደር፡መነኰስ፡ሚናስ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፪፤ የዚህም፡ቅዱስ፡ወላጆቹ፡ምድርን፡የሚያርሱ፡ ክርስቲያን ፡ ገበሬዎች ፡ ናቸው ፡ እርሱም ፡ ይህን፡ዓለም፡ንቆ፡ትቶ፡በሀገረ፡አክሚም፡ በሚገኝ ፡ በአንድ ፡ ገዳም ፡ መነኰሰ ፡ ለመብልና ፡ ለመጠጥ ፡ ሳይገዛ ፡ በየሁለት ፡ ቀን፡እየጾመ፡ብዙ፡ቀኖችን፡ኖረ፡ከዚያም፡ ወጥቶ፡ ወደ፡ እስሙናይን ፡ ሀገር ፡ ሒዶ ፡ በአንድ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ እያገለገለና፡ እየተ ጋደለ ፡ ከገዳሙ ፡ ደጃፍ ፡ ሳይወጣ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት፡ዓመት፡ኖረ።

፫፤ እስላሞችም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ህልው ፡ የሆነ ፡ ከባሕርዩ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ የሚሠርፅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የለውም ፡ እንደሚሉ ፡ ሰማ ፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በእንተዝ ፡ ነገር ፡ ወተባረከ ፡ እምኀበ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወወጽአ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እስሙ ናይን ፡ ወቆመ ፡ ቅድመ ፡ መኰንን፡ ዘሠራዊተ ፡ ተንባላት ። ወይቤሎ ፡ እሙንቱ ፡ አንትሙ ፡ ትብሉ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ወልድ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ እምጠባይዑ ፡ ወይቤሎ ፡ መኰንን ፡ እወ ፡ ወንሕነ ፡ ናርኅቅ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ እምእግዚ አብሔር ፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትእመኑ ፡ ዘእንበለ ፡ ወልድ ፡ በኢተ ራክቦ፡ ዘርዕ ፡ አላ ፡ ዘእምባሕርዩ ፡ ተወልደ ። ወይቤ ፡ መኰንን ፡ ዝንቱ፡ ክህደት ፡ ውእቱ ፡ በሕገ ፡ ዚአነ ፡ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ አእምር፡ አ ፡ መኰንን ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘየአምን ፡ በወልድ ፡ ቦ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ወዘሰ ፡ ኢያምን ፡ በወልድ ፡ ኢይሬእያ ፡ ለሕይወት ፡ አላ ፡ ይወርድ ፡ መዓተ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ላዕሌሁ።

፬፤ ወበእንተዝ ፡ ተምዐ ፡ መኰንን ፡ ዐቢየ ፡ መዓተ ፡ ወአዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወይ ግምዱ፡ ሥጋሁ ፡ በበግማድ ፡ ወይደይዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወነሥኡ ፡ መሐይምናን ፡ ሥጋሁ ፡ ወገነዝዎ ፡ ሠናየ ፡ ግንዘተ ፡ ወቀበርዎ፡ ወገብሩ ፡ ተዝካሮ።

፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

አዘነ። ከአበ ፡ ምኔቱም ፡ ቡራኬ ፡ ተቀበለ ፡ ወደ፡ እስሙናይን ፡ ከተማ ፡ ወጥቶ ፡ ሔደ ፡ የእስ ላሞች ፡ ሠራዊት፡ አለቃ ፡ በሆነ ፡ በመኰንኑ ፡ ፊት ፡ ቁሞ ፡ እንዲህ ፡ አለው ። እናንተ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ከባሕርዩ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ እንደ ሌለው ፡ አድርጋችሁ ፡ የምትናገሩ ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ መኰንኑም ፡ አዎን ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ ማለትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እናርቃለን ፡ አለ። አባ ፡ ሚናስም ፡ ያለ ፡ ልጅ ፡ ልታምኑ ፡ አይገባም፡ እርሱም ፡ ያለ ፡ ዘር ፡ ያለ ፡ ሩካቤ ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ ከባሕርዩ ፡ ተወለደ ፡ እንጂ ፡ አለው። መኰንኑም ፡ ልጅ ፡ አለው ፡ ማለት ፡ በሕጋችን ፡ ክህደት ፡ ነው ፡ አለ ፡ አባ ፡ ሚናስም፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ መኰንን ፡ ሆይ ፡ እወቅ ፡ የከበረ ፡ ወንጌል ፡ በወልድ ፡ ያመነ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ በወልድ፡ ያላመነ ፡ ሕይወትን ፡ አያይም ፡ የእግ ዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በላዩ ፡ ይወርዳል ፡ እንጂ ፡ ብሏልና።

፬፤ ስለዚህም ፡ መኰንኑ ፡ እጅግ ፡ ተቆጣ ፡ ራሱንም ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቆርጡ ፡ ሥጋውንም ፡ በየቍር ጥራጭ ፡ ቆራርጠው ፡ ከባሕር ፡ እንዲጥሉት ፡ አዘዘ ፡ ምእመናንም ፡ ሥጋውን ፡ ወስደው ፡ በበጎ ፡ አገናነዝ ፡ ገንዘው ፡ ቀበሩት ፡ መታሰቢያ ውንም ፡ አደረጉ።

፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረ ከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለሚናስ ፡ ፍጹም ። ዘሀገረ ፡ አክሚም ። ሶበ ፡ ይብል ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ። ተንባላት ፡ በበግማድ ፡ ገመድዎ ፡ ዮም ። ወወረውዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ መሥጥም።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፰ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ተአማኒ ፡ አባ ፡ መላ ልዮስ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾያ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ማእምር ፡ ወለባዊ ፡ ወተ ሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ፡ በመዋዕለ ፡ መንግሥቱ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ ዘይንእስ ፡ ወእምአመ ፡ ተሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፴ ዕለተ ፡ ነበረ ፡ ወእምዝ ፡ አውገዞሙ፡ ለሕዝበ ፡ አርዮስ ፡ ወሰደዶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ታማኝ ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ መላልዮስ ፡ አረፈ።

፪፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ አዋቂና ፡ አስተዋይ ፡ ነበረ ፡ በታናሹ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ ዘመነ ፡ መን ግሥት ፡ በአንጾኪያ ፡ ሀገር ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ። ከተሾመም ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ኖረ ፡

www.ethiopianorthodox.org

እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ ሰደዶ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እመንበረ ፡ ሢመቱ ፡ እስመ ፡ ንጉሥ ፡ አርዮሳዊ፡ውእቱ።

፫፡ ወተጋብኡ፡ልሒቃነ፡ሀገረ፡አንጾኪያ፡ወኤጲስቆጶሳት፡ወካህናት፡ወጸሐፉ፡ወለአኩ፡ኀበ፡ንጉሥ ፡ በእንተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዘ ፡ ይስእልዎ፡ከመ፡ይሚጦ፡ሎሙ፡ወተወክፈ፡ስእለቶሙ ፡ ወሜጦ ፡ ወሶበ ፡ ገብአ ፡ ዝንቱ ፡ አብ፡ኢኀደገ፡አውግዞቶሙ፡ለአርዮሳውያን፡ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ በቃሎሙ ፡ ወይከሥት፡ስሕተቶሙ፡ወጽርፈቶሙ።ወከመ፡ተወልደ፡ ወልድ፡እምባሕርየ፡አብ፡ወዕሩይ፡በመለኮቱ፡ኮነ፡ዘይሰብክ፡ለኵሉ።

፬፡ ወተንሥኡ ፡ ዓዲ ፡ ሕዝበ ፡ አርዮስ ፡ ወጸሐፉ ፡ ኀበ፡ንጉሥ፡እንዘ፡ያስተዋድይዎ፡ለዝንቱ፡አብ፡መላልዮስ፡እስከ፡ሜጡ፡ልቦ፡ለንጉሥ፡ወፈነወ ፡ ዳግመ ፡ ወሰደዶ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ዘይርኅቅ፡እምቀዳሚ።

፭፡ ወሶበ፡በጽሐ፡ኀበ፡ሰደድዎ፡ሀገረ፡ኮነ፡ከመ፡ዘይነብር፡ምስለ፡ሕዝቡ፡እንዘ፡ይፌኑ፡መልእክታቲሁ፡ኀቤሆሙ፡ወይተረጐም፡ሎሙ፡እመጻሕፍት፡ዘኮነ፡እምኔሆሙ፡ኀቡአ፡ወይበጽሕ ፡ ለኵሉ ፡ መርዔቱ ፡ እለ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ፡ወይኤዝዞሙ፡ለኤጲስቆጶሳት፡ወለቀሳውስት፡ማእምራን፡ከመ፡ይስብኩ፡ በሥላሴ፡ቅድስት ፡ ሃይማኖተ ፡ ርትዕተ ፡ ዘአበዊነ ፡ ፫፻፲ወ፰ ፡ ወከመዝ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ስደት ፡ ብዙኀ፡ዓመታተ፡እስከ፡አዕረፈ።

፮፡ ወወደሶ፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡ወደረሰ፡ሎቱ፡ድርሳናተ ፡ ውዳሴ ፡ ወከሠተ ፡ ሎቱ ፡ ክብሮ ፡ ወግርማሁ ፡ ወአይድዐ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሐጽጽ ፡ እምሐዋርያት ፡ ቅዱሳን ፡ በእንተ ፡ ዘበጽሐ ፡ ምንዳቤ ፡ ብዙኅ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት፡ርትዕት።

፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ከዚህም፡በኋላ፡አርዮሳውያንን፡አወገዛቸው፡በአንጾኪያም ፡ ካለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉንም ፡ አሳደዳቸው ። ንጉሡም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ፡ ከመንበረ ፡ ሢመቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱን፡አሳደደው፡እርሱ፡ንጉሡ፡አርዮሳዊ፡ነውና።

፫፡ የአንጾኪያ፡ አገርም ፡ ታላላቆችና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ካህናቱም ፡ ተሰበሰቡ ፡ ስለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ይመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ ላኩ ፡ ንጉሡም ፡ ልመናቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ መለሰላቸው ። ይህም ፡ አባት፡በተመለሰ፡ጊዜ፡አርዮሳውያንን፡ወደ፡ማውገዙ ፡ ተመለሰ ፡ በቃላቸው ፡ የሚያምኑትንም ፡ ስሕተታቸውንና ፡ ስድባቸውን ፡ ግልጽ ፡ እያደረገ ፡ ወልድ ፡ ከአብ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ፡ ተወለደ ፡ በመለኮቱም ፡ ትክክል ፡ እንደሆነ፡ለሁሉ፡የሚሰብክ፡የሚያስተምር፡ሆነ።

፬፡ ዳግመኛም፡አርዮሳውያን፡ተነሡ፡የንጉሡን፡ልብ፡ወደእሳቸው፡እስከ፡መለሱት፡ድረስ፡ይህን፡አባት፡እየወነጀሉ፡ወደ፡ንጉሥ፡ጻፉ፡ዳግመኛም፡ ልኮ ፡ ከፊተኛው፡ ወደሚርቅ ፡ አገር፡አሳደደው።

፭፡ ወደተሰደደበትም፡አገር፡በደረሰ፡ጊዜ፡መልእክቶቹን ፡ ጽፎ ፡ በመላክ ፡ ከወገኖቹ ፡ ጋር ፡ እንዳለ ፡ ሆነ ፡ ከእርሳቸውም ፡ ሥውር ፡ የሆነውን፡የመጻሕፍትን፡ቃል፡ይተረጕምላቸው፡ነበር፡በአንጾኪያ፡ላሉ፡መንጋዎቹም፡ይደርሳቸዋል ፡ አዋቂዎች ፡ የሆኑ ፡ ኤጲስቆጶሳትንና፡ቀሳውስትን፡ ልዩ ፡ በሆነች፡ ሦስትነት ፡ ሦስት፡መቶ፡ዐሥራ፡ስምንቱ፡አባቶቻችን፡ያስተማሩዋት፡የቀናች፡ሃይማኖትን፡እንዲአስተምሩ ፡ ያዛቸዋል ፡ እንዲህም ፡ እያደረገ ፡ እስከ፡ዐረፈባት፡ቀን፡ድረስ፡በተሰደደበት፡ብዙ፡ዘመናት፡ኖረ።

፮፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅም ፡ አመስግኖታል ፡ የምስጋና ፡ ድርሰቶችንም ፡ ደረሰለት ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ክብሩና ፡ ግርማው ፡ ከከበሩ ፡ ሐዋርያት፡ክብር፡እንደማይጎድል፡ተናገረ።

፯፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

አርኬ

ሰላም፡ለመላልዮስ፡ዘእሙን፡ነገሩ።አርዮሳውያን፡ሕዝብ፡እለ፡አውጽእዎ፡እማኅደሩ።አፈ፡ወርቅ፡ዮሐንስ፡ በከመ፡ወደሶ፡በዕለተ፡ተዝካሩ።እንበይነ፡ስደቱ፡ወእንበይነ፡ብዙኅ፡ኀሣሩ።እምሐዋርያት፡ይቤ፡ ኢየሐጽጽ፡ክብሩ።

፳፰፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሩ፡ለያዕቆብ፡ሐዋርያ፡
እኁሁ፡ለእግዚእነ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስ
ሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩፡
አምላክ፡አመ፡፲ወ፱፡ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡
ኮነ፡ፍልሰተ፡ሥጋሁ፡ለአባ፡መርትያኖስ፡
መነኰስ፡መስተጋድል፡እምሀገረ፡አቴና፡
ኀበ፡አንጾኪያ።
፪፤ ውእቱኬ፡እምድኅረ፡በጽሐ፡መከራ፡እምነ፡
ብእሲት፡ዘማ፡ሶበ፡ፈቀደት፡ትሒጦ፡
ወታውድቆ፡ውስተ፡ኃጢአት፡ውእቱሰ፡
ሰሐባ፡ወአብኣ፡ውስተ፡ንስሓ፡እስከ፡ኮነት፡
መነኮሳዪተ፡ወተጸምደት፡በገድል።
፫፤ ወእምዝ፡ኀደገ፡ላቲ፡ማኀደሮ፡ወኮነ፡ዘየ
ዓውድ፡እምሀገር፡ለሀገር፡ወበጺሖ፡ሀገረ፡
አቴና፡ነበረ፡ህየ፡ኀዳጠ፡መዋዕለ፡ወሐመ፡
ንስቲተ፡ወአዕረፈ፡በሰላም፡በከመ፡ጽሑፍ፡
ዜናሁ፡አመ፡፳ወ፩ለወርኀ፡ግንቦት።
፬፤ ወሶበ፡ተሠይመ፡ብፁዕ፡ቴዎድሮስ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ለሀገረ፡አንጾኪያ፡በመዋዕሊሁ፡ለን
ጉሠ፡ፋርስ፡ከሐዲ፡ፈነወ፡ዝንቱ፡አብ፡
ሊቃናተ፡ካህናት፡ወመሃይምናነ፡ወአፈለሱ፡
ሥጋሁ፡እምአቴና፡ወአብጽሕዎ፡ሀገረ፡አን
ጾኪያ፡ ወተቀበልዎ፡ በማኅሌት፡ ወበመ
ዝሙር፡ወተአምኆ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወአን
በሮ፡በሣፁን፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ወገብረ፡ሎቱ፡በዓለ፡በዛቲ፡ዕለት።

፭፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፰፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የጌታችን ፡ ወንድም ፡
የሐዋርያ ፡ ያዕቆብ ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡
በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብ
ሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

* * *

፩፤ አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡በመን
ፈስ፡ቅዱስ፡ ስም፡ የካቲት ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡
በዚች ፡ ዕለት ፡ የተጋዳይ ፡ መነኰስ ፡ የአባ፡
መርትያኖስ፡ ሥጋው፡ ከአቴና፡ አገር፡ ወደ፡
አንጾኪያ፡የፈለሰበት፡ሆነ።
፪፤ እርሱም ፡ ሽንግላ ፡ በኃጢአት ፡ ልትጥለው ፡
በወደደች ፡ ጊዜ ፡ ከአመንዝራ ፡ ሴት ፡ ከተ
ፈተነ፡ በኋላ፡እርሱ፡ግን፡መንኵሳ፡በገድል፡
እስከ፡ተጸመደች፡ድረስ፡ስቦ፡ወደ፡ንስሓ፡
መልሷታል።
፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መኖሪያውን ፡ ትቶላት ፡
ከሀገር፡ ወደ፡ ሀገር፡ የሚዞር፡ ሆነ፡ ከአቴና፡
አገርም፡ ደርሶ፡ በዚያ፡ ጥቂት፡ ቀን፡ ኖረ፡
ጥቂትም፡ታመመና፡በሰላም፡አረፈ፡ዜናው፡
በግንቦት፡በሃያ፡አንድ፡ቀን፡እንደ፡ተጻፈ።
፬፤ የከበረ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ለአንጾኪያ ፡ ሀገር ፡
በከሀዲው ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ሊቀ ፡
ጵጵስና ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አባት ፡ የካህ
ናት ፡ አለቆችንና ፡ ምእመናንን ፡ ልኮ ፡ ሥጋ
ውን ፡ ከአቴና ፡ አፍልሰው ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡
ከተማ ፡ አመጡት ፡ በምስጋናም ፡ እየዘመሩ ፡
አክብረው ፡ ተቀበሉት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡
ተሳለመው፡በሣጥንም፡አድርጐ፡በቤተ፡ክር
ስቲያን፡ውስጥ፡አኖረው። በዚችም፡ዕለት፡
በዓልን፡አደረገለት።
፭፤ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በጸሎቱ፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡
ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

አርኬ

ሰላም፡ ለፍልሰተ፡ሥጋከ፡ኀበ፡አንጾኪያ፡እምአቴና። በእደ፡ቴዎድሮስ፡አብ፡ዘሥርግው፡ በጵጵስና፡መርትያኖስ፡ተወከፍ፡ዘመሥዋዕተ፡ቃል፡ጼና።በከናፍረ፡ልብ፡ወበአፈ፡ኅቡእ፡ሕሊና።ሶበ፡ ለሥጋከ፡እኤምኅ፡ሣፁና።

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ፳ሁ ፡ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱሳን ፡ ባስልዮስ ፡ ወቴዎዶስዮስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ በሀገረ ፡ እስክንድርያ ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን ። | ፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሃያ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የከበሩ ፡ ባስልዮስ ፡ ቴዎዶስዮስና ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን ። |

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ እብል ፡ ለባስልዮስ ፡ ብፁዕ ። ወቴዎዶስዮስ ፡ ካልዕ ። ወጢሞቴዎስ ፡ ሣልስ ፡ ቅኑታነ ፡ ኃይል ፡ ወጽንዕ ። ውስተ ፡ ቤተ ፡ መርዓ ፡ አምሳለ ፡ እሡራን ፡ ሰብእ ። ዘተጸዋዕክሙ ፡ ኅቡረ ፡ ለስምዕ ።

| | |
|---|---|
| ፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፳ወ፩ዱ ። | ፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጴጥሮስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሃያ ፡ አንደኛ ፡ ነው ። |
| ፫፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ በጽሐ ፡ ምንዳቤ ፡ ብዙኅ ፡ እምኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ ዐላዊ ፡ ወእምሕዝበ ፡ አርዮስ ፡ ክሀዲ ፡ አመ ፡ ነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱ ፡ እምድኅረ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ። | ፫፡ ይህንንም ፡ ቅዱስ ፡ ከሐዋርያዊ ፡ አትናቴዎስ ፡ በኋላ ፡ በሹመቱ ፡ ወንበር ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሥ ፡ ዳርዮስና ፡ ከከሀዲ ፡ አርዮስ ፡ ወገኖች ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ደርሶበታል ። |
| ፬፡ ወሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ ይቅትልዎ ፡ ጐየ ፡ ወተኀብአ ፡ መጠነ ፡ ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ወአርዮሳውያን ፡ አንበሩ ፡ ህየንቴሁ ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ብእሴ ፡ ዐላዌ ፡ ዘስሙ ፡ ሉቅዮስ ፡ ወነበረ ፡ ፪ተ ፡ ዓመተ ። ወእምዝ ፡ ተንሥኡ ፡ ኵሎሙ ፡ መሃይምናን ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወሰደድዎ ፡ ለሉቅዮስ ፡ አርዮሳዊ ፡ ወሜጥዎ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀበ ፡ መንበሩ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይትቃረኖሙ ፡ ለአርዮሳውያን ፡ ወያወግዞሙ ፡ ወይሰድዶሙ ፡ ፯ተ ፡ ዓመተ ። ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ እምፃማ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ። | ፬፡ ሊገድሉትም ፡ በፈለጉ ፡ ጊዜ ፡ ሸሽቶ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ተሠወረ ፡ አርዮሳውያንም ፡ ሉቅዮስ ፡ የተባለ ፡ ከሀዲውን ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ፈንታ ፡ በወንበሩ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ ምእመናን ፡ ሁሉም ፡ ተነሥተው ፡ አርዮሳዊ ፡ ሉቅዮስን ፡ አሳደዱትና ፡ ይህን ፡ አባት ፡ ጴጥሮስን ፡ ወደ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱ ፡ መለሱት ፡ አርዮሳውያንንም ፡ በመጣለት ፡ እያወገዛቸውና ፡ እያሳደዳቸው ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካም ፡ አርፎ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ዕረፍት ፡ ሔደ ። |
| ፭፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ። | ፭፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ። |

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለጴጥሮስ ፡ በመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ዘነበረ ። እምነ ፡ አትናቴዎስ ፡ ድኅረ ። አመ ፡ አርዮሳውያን ፡ ለወልድ ። እንዘ ፡ ይሰምይዎ ፡ ፍጡረ ። በመዋዕሊሁ ፡ ተዓጊሦ ፡ ምንዳቤ ፡ ወፃዕረ ። ውስተ ፡ ዘለዓለም ፡ ዕረፍት ፡ ፈለሰ ፡ ወሖረ ።

| | |
|---|---|
| ፮፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ ፊልሞን ፡ መዓንዝር ፡ ዘኮነ ፡ ያስተዛውዖ ፡ ለአርያኖስ ፡ መኰንን ። | ፮፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ መኰንን ፡ አርያኖስን ፡ የሚያጫውተው ፡ አዝማሪው ፡ ፊልሞን ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ። |

፯፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ጸውዖ ፡ አርያኖስ ፡ ለአስ
ቃሎን፡ አናጉንስጢስ ፡ ወይቤሎ ፡ ሡዕ ፡
ለአጽሎን፡ወሖረ፡አስቃሎን፡ኀበ፡ፊልሞን፡
ወይቤሎ፡አነ፡እሁበከ፡፬ተ፡ዲናረ፡ወርቅ፡
ለእመ ፡ ትሠውዕ ፡ ህየንቴየ ፡ ወይቤሎ ፡ ፊል
ሞን፡ሀበኒ፡ልብሰከ፡ተገልቢብየ፡እሠውዕ፡
ህየንቴከ።

፰፤ ወሶበ፡ቦአ፡እእመርዎ፡ወይቤልዎ፡ምንተ፡
ኮንከ፡ወይቤሎሙ፡ፊልሞን፡አንሰ፡ክርስ
ቲያን፡ምእመን፡በክርስቶስ፡ወይቤሎ፡አር
ያኖስ፡ሡዕ፡ለአማልክት፡ከመ፡ትሕየው፡
ወይቤሎ፡ፊልሞን፡አልቦ፡ሕይወት፡ዘእን
በለ፡መዊት፡በስመ፡ክርስቶስ። ወይቤሎ፡
አርያኖስ፡አነ፡እቀትለከ፡ፍጡነ፡ዘእንበለ፡
ትንሣእ፡ጥምቀተ፡ወተኀንጽእ፡ዘተሰፎከ፡
ወሰሚዖ፡ፊልሞን፡ጸለየ፡ኀበ፡እግዚአብ
ሔር፡ከመ፡ይክፍሎ፡ጥምቀተ፡ክርስትና፡
ወሶቤሃ፡መጽአ፡ደመና፡ብሩህ፡እምሰማይ፡
ወአጥመቆ።

፱፤ወአዘዘ፡አርያኖስ፡፫ተ፡ሐራ፡ከመ፡ይጽፍዕዎ፡
እመ፡የኀፍር፡ወይትመየጥ፡ወይቤ፡ፊልሞን፡
አንሰ፡ኢየኀፍር፡ለእመ፡ጸፍዑኒ፡ዘየአኪ፡
እምዝ፡እስመ፡እሬኢ፡ከመ፡መላእክተ፡እግ
ዚአብሔር፡ይትፌሥሑ፡በእንቲአየ።

፲፤ ወአዘዘ፡ካዕበ፡አርያኖስ፡ከመ፡ይስቅልዎ፡
ዲበ፡አልጌን፡ወይንድፍዎ፡በአሕፃ፡ወባ
ሕቱ፡አልቦ፡ዘለከፎ፡ወነገርዎ፡ለአርያኖስ፡
ከመ፡አልቦ፡ዘለከፎ፡ወአዘዘ፡ካዕበ፡ከመ፡
ይንድፍዎ፡እንዘ፡ውእቱ፡ይቀውም፡ወተመ
ይጠት፡አሐቲ፡ሐፅ፡ውስተ፡ዓይኑ፡ለአር
ያኖስ፡ወአየረቶ፡ውእተ፡ጊዜ፡አዘዘ፡ያው
ርድዎ ፡ እምስቅለት ፡ ወይምትሩ ፡ ርእሶ ፡
ምስለ፡አስቃሎን፡አናጉንስጢስ፡ወፈጸሙ፡
ስምዖሙ፡ወነሥኡ፡አክሊለ፡ስምዕ።

፲፩፤ወሶበ፡ተመንደበ፡መኰንን፡በሕማመ፡ሐፅ፡
አምከርዎ፡ሰብእ፡ከመ፡ይንሣእ፡እምደመ፡
ቅዱሳን፡ወይደይ፡ውስተ፡ዐይኑ፡ወሶበ፡
ገብረ፡ዘንተ፡ሐይወ፡ወአምነ፡በእግዚእነ፡
ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወፈትሖሙ፡
ለኵሎሙ፡ሙቁሐን፡ወኮነ፡ውእቱ፡ሰማ
ዕተ፡በእደ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡አመ፡፰ለ
መጋቢት፡ወበረከቶሙ፡ለሰማዕታት፡ተሀሉ፡

፯፤ በአንዲትም፡ዕለት፡አርያኖስ፡አናጉንስጢስ፡
አስቃሎንን፡ጠርቶ፡ለአጵሎን፡ሠዋ፡አለው፡
አስቃሎንም፡ወደ፡ፊልሞን፡ሒዶ፡በእኔ፡
ፈንታ፡ብትሠዋ፡አራት፡የወርቅ፡ዲናር፡እስ
ጥሃለሁ፡አለው፡ፊልሞንም፡ልብስህን፡ስጠ
ኝና፡ተሸፋፍኜ፡በአንተ፡ፈንታ፡እሠዋለሁ፡
አለው።

፰፤ በገባም ፡ ጊዜ ፡ አውቀውት ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡
አሉት፡ፊልሞንም፡በክርስቶስ፡የማምን፡ክር
ስቲያን ፡ ነኝ ፡ አላቸው፡ አርያኖስም ፡
በሕይወት፡እንድትኖር፡ለአማልክት፡ሰዋ፡
አለው ፡ ፊልሞንም፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡
ከመሞት፡በቀር፡ሕይወት፡የለም፡አለው።
አርያኖስም፡ጥምቀትን፡ሳታገኝ፡ፈጥኜ፡እገ
ድልሃለሁ ፡ ተስፋህን ፡ ታጣለህ ፡ አለው ፡
ፊልሞንም፡ሰምቶ፡የክርስትና፡ጥምቀትን፡
ያድለው፡ዘንድ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ጸለየ፡
በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከሰማይ ፡ ብሩህ ፡ ደመና ፡
መጥቶ፡አጠመቀው።

፱፤ አርያኖስም፡አፍሮ፡ቢመለስ፡ብሎ፡ሦስት፡
ወታደሮች፡እንዲጸፉት፡አዘዘ፡ፊልሞንም፡
የእግዚአብሔር፡መላእክት፡ስለ፡እኔ፡ደስ፡
ሲላቸው ፡ አያለሁና ፡ ከዚህ ፡ የከፋ ፡ ቢጸፉ
ኝም፡እኔ፡አልፍርም፡አለ።

፲፤አርያኖስም፡ባላ፡ባለው፡ግንድ፡ላይ፡ሰቅለው፡
በፍላፃዎች፡ይነድፉት፡ዘንድ፡አዘዘ፡ግን፡
ምንም፡የነካው፡የለም፡ፍላፃውም፡እንዳል
ነካው ፡ ለአርያኖስ ፡ ነገሩት ፡ ዳግመኛም ፡
እርሱ፡እንደ፡ቆመ፡ይነድፉት፡ዘንድ፡አዘዘ፡
አንዲቱም ፡ ፍላፃ ፡ ተመልሳ ፡ የአርያኖስን ፡
ዐይን፡ነድፋ፡ዐሳወረችው፡በዚያንም፡ጊዜ፡
ከተሰቀለበት፡አውርደው፡ከአናጉንስጢስ፡አስ
ቃሎን፡ጋር፡ራሱን፡እንዲቆርጡ፡አዘዘ፡ገድ
ላቸውንም ፡ ፈጽመው ፡ የሰማዕትነት ፡
አክሊልን፡ተቀበሉ።

፲፩፤ መኰንኑም፡በፍላፃው፡ሕመም፡በተሠቃየ፡
ጊዜ ፡ ከቅዱሳን ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ ከዐይኑ ፡
ውስጥ ፡ እንዲጨምር ፡ ሰዎች ፡ መከሩት ፡
ይህንንም፡ሲያደርግ፡ዳነ፡በክብር፡ባለቤት፡
በጌታችን ፡ ክርስቶስም ፡ አመነ ፡ እሥረኞ
ችንም ፡ ሁሉ ፡ ፈታቸው ፡ እርሱም ፡ መጋ
ቢት፡ስምንት፡ቀን፡በዲዮቅልጥያኖስ፡እጅ፡
በሰማዕትነት፡ሞተ። የሰማዕታትም፡በረከ

www.ethiopianorthodox.org

ምስሌነ፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

ታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለከ፡መዓንዝር፡ፊልሞን፡ዘፈጸምከ፡ገድለ፡ምስለ፡አስቃሎን።እንዘ፡ትብል፡ዘንተ፡ቅድመ፡መኰንን።አልቦ፡ሐይው፡በሠዊዕ፡ለጣዖት፡ምኑን።እንበለ፡መዊት፡በክርስቶስ፡መድኅን።

፲፱፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለቅዱሳን፡አባ፡ ገብረ ፡ መርዓዊ ፡ ዘአግዶ ፡ ወአባ ፡ ክፍለ ፡ ማርያም ፡ ዘድባጋ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን።

፲፱፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱሳን ፡ የአግዶ ፡ ገዳም ፡ አባ፡ ገብረ ፡ መርዓዊ ፡ የድባጋ ፡ ገዳም ፡ አባ ፡ ክፍለ ፡ማርያም፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም፡ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

እቄድሰከ፡አባ፡አልዒልየ፡ቃለ። ኀበ፡ዐውደ፡ክብር፡ዝክርከ፡ለለይትገበር፡በዓለ።ክፍለ፡ማርያም፡ስንከ፡እምገጸ፡ሰማይ፡ጸደለ።ክፍለ፡መንግሥትከ፡ተሀበኒ፡ክፍለ።እስመ፡በስምከ፡ስምየ፡ተብህለ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፩ ፡ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ተዝካረ፡በዓላ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ ድንግል፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ።

፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ሃያ፡አንድ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ አምላክን ፡ ለወለደች ፡ ለእመቤታችን ፡ ለቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የበዓልዋ፡መታሰቢያ፡ነው።

፪፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቷ ፡ ይማረን ፡ በረከቷም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለኪ ፡ ለብርሃነ ፡ ሕይወት ፡ መፆሩ። አምሳለ ፡ ተቅዋም ፡ ዘወርቅ ፡ ጠበብተ ፡ እሥራኤል ፡ ዘገብሩ። ማርያም ፡ ክብርት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በክብሩ። ረስዩ ፡ ፍና ፡ ትሕትና ፡ አእጋርየ ፡ ይሑሩ። ትዕቢትሰ፡ለአምላክ፡ፀሩ።

፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ጳጳሳት፡፺ወ፯ቱ።

፬፡ ወዝንቱ፡ አብ ፡ መንኰሰ፡እምንእሱ፡በገዳመ፡ አስቄጥስ፡ወተጋደለ፡ተጋድሎ፡ዐቢየ፡እንዘ፡ ይጸመድ ፡ በጾም ፡ ወጸሎት ፡ ወሰጊድ ፡ ወትጋህ ፡ ወቦ ፡ ውስቴቱ ፡ የውሃት ፡ ወትሕትና ፡ ወፍቅር።

፭፡ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ አሐዱ፡ አረጋዊ ፡ ዘስሙ ፡ መክሲሞስ ፡ ይቤሎ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ለምንት ፡ ትጕይይ ፡ እምሰብእ ፡

፫፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ አረፈ ፡ እርሱም፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኃምሳ ፡ ሰባተኛ ፡ ነው።

፬፡ ይህም ፡ አባት ፡ በታናሽነቱ ፡ በአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ መነኰሰ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ እየተጋ ፡ ፍጹም ፡ ተጋድሎን ፡ በመጋደል ፡ ተጠምዶ፡ኖረ፡በውስጡም፡ትሕትና፡ፍቅር፡ ቅንነት፡አለው።

፭፡ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ስሙ ፡ መክሲሞስ፡ ወደሚባል ፡ አረጋዊ ፡ ቤት ፡ ገባ ፡ እርሱም ፡ ልጄ ፡ ከሰው ፡ ለምን ፡ ትሸሻለህ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ በወን

www.ethiopianorthodox.org

አንተሰ፡ ሀለወከ፡ ትንበር፡ ማዕከለ፡ ዕደው፡ ወአንስት፡ ብዙኃት፡ ውእቱሰ፡ ኢለበወ፡ ትርጓሜ፡ ዝንቱ፡ ቃለ፡ አረጋዊ፡ ወኮነ፡ ወትረ፡ ዘይበኪ፡ ወይስእል፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ያድኅኖ፡ እመሥገርቱ፡ ለጸላኢ።

፮፡ ወሶበ፡ አዕረፈ፡ አባ፡ ሚካኤል፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘእምቅድሜሁ፡ አኀዝዎ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ወሤምዎ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘእንበለ፡ ፈቃዱ፡ በከመ፡ ተነበየ፡ ላዕሌሁ፡ አባ፡ መክሲሞስ፡ አረጋዊ፡ ወሶበ፡ ተሠይመ፡ ኢተሀየየ፡ ዘቀዳሚ፡ ተጋድሎቶ፡ ወተጸምዶቶ፡ እንዘ፡ ይነበር፡ ውስተ፡ ገዳመ፡ አስቄጥስ።

፯፡ ወሶበ፡ ያጌብርዎ፡ በእንተ፡ ግብሮን፡ ለአብያተ፡ ክርስቲያን፡ ከመ፡ ይሑር፡ ኀበ፡ ሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ወሀገረ፡ ምስር፡ የሐውር፡ ወፍጡነ፡ ይትመየጥ፡ ኀበ፡ ገዳመ፡ አስቄጥስ።

፰፡ ወውእቱ፡ ወሬዛ፡ በመዋዕሊሁ፡ ወፍትወት፡ እንስሳዊት፡ ትትሀወክ፡ በውስቴቱ፡ ውእቱሰ፡ ያበዝኅ፡ ጾመ፡ ወትጋሀ፡ ለጸሎት፡ ወሰጊድ፡ ወሶበ፡ ኢተክህሎ፡ ያግርራ፡ ተአመነ፡ ሎቱ፡ ለአሐዱ፡ አረጋዊ፡ ውእቱኒ፡ ይቤሎ፡ ኢትጠፍእ፡ ዛቲ፡ ፍትወት፡ እንስሳዊት፡ ዘእንበለ፡ ግብረ፡ ትሕትና፡ ዘምስለ፡ ጾም፡ ወጸሎት፡ ወሰጊድ፡ ወፈድፋደሰ፡ ትሕትና፡ እስመ፡ ውእቱ፡ መድኃኒተ፡ ዚአሃ።

፱፡ ወሶበ፡ ሰምዐ፡ ዘንተ፡ ገብረ፡ ሎቱ፡ ምስሐበ፡ እዳው፡ ዘኀፂን፡ ወይለብስ፡ ኀሱረ፡ ወኀፂረ፡ ወይትነሣእ፡ በሌሊት፡ ወየዐውድ፡ አብያተ፡ መነኰሳት፡ ወይኰስትር፡ ኵስሐተ፡ ወይፀውሮ፡ ወይወስዶ፡ ወይገድፎ፡ ርኁቀ፡ ወነበረ፡ እንዘ፡ ይገብር፡ ዘንተ፡ ግብረ፡ መጠነ፡ ፪ቱ፡ ዓመት፡ ወነጺሮ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕለ፡ ንጽሕናሁ፡ ወትሕትና፡ ልቡ፡ አእተተ፡ እምላዕሌሁ፡ ፍትወተ፡ ጠባይዕ።

፲፡ ወነበረ፡ ዝንቱ፡ አብ፡ እንዘ፡ ይጸመድ፡ ወይትጋደል፡ ወይጌሥጾሙ፡ ወይሜህሮሙ፡ ወያጸንዖሙ፡ ለመርዔቱ፡ ውስተ፡ ሃይማኖት፡ ርትዕት፡ ፲ተ፡ ወ፪ተ፡ ዓመተ። ወአዕረፈ፡ በሰላም።

፲፩፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለም፡ ዓለም፡ አሜን።

ዶችና፡ በብዙ፡ ሴቶች፡ መካከል፡ ትኖር፡ ዘንድ፡ አለህ፡ አለው፡ እርሱ፡ ግን፡ የሽማግሌውን፡ የቃሉን፡ ትርጓሜ፡ አላስተዋለም፡ ከጠላትም፡ ወጥመድ፡ ያድነው፡ ዘንድ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ በማልቀስ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚለምን፡ ሆነ።

፮፡ ከእርሱም፡ አስቀድሞ፡ የነበረ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አባ፡ ሚካኤል፡ በአረፈ፡ ጊዜ፡ ይህን፡ አባት፡ ይዘው፡ ያለ፡ ውዴታው፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አድርገው፡ ሾሙት፡ አረጋዊ፡ አባ፡ መክሲሞስ፡ ትንቢት፡ እንደ፡ ተናገረለት፡ በተሾመም፡ ጊዜ፡ በአስቄጥስ፡ ገዳም፡ ተቀምጦ፡ የቀድሞውን፡ ተጋድሎውንና፡ አገልግሎቱን፡ ቸለል፡ አላለም።

፯፡ ስለ፡ አብያተ፡ ክርስቲያንም፡ ጉዳይ፡ ወደ፡ እስክንድርያና፡ ወደ፡ ምስር፡ ይሔድ፡ ዘንድ፡ ግድ፡ በአሉት፡ ጊዜ፡ ይሔዳል፡ ፈጥኖም፡ ወደ፡ አስቄጥስ፡ ገዳም፡ ይመለሳል።

፰፡ እርሱም፡ በዕድሜው፡ ጐልማሳ፡ ስለሆነ፡ እንስሳዊት፡ ፍትወት፡ ትነሣሣበት፡ ነበር፡ እርሱም፡ ያጠፋት፡ ዘንድ፡ ለጾም፡ ለጸሎት፡ ለስግደትም፡ መትጋትን፡ ያበዛል፡ ሊያበርዳትም፡ ባልተቻለው፡ ጊዜ፡ ለአንድ፡ አረጋዊ፡ ተናዘዘለት፡ እርሱም፡ እንዲህ፡ አለው፡ ይህች፡ እንስሳዊት፡ ፍትወት፡ ከጾምና፡ ከጸሎት፡ ከስግደትም፡ ጋር፡ ያለ፡ ትሕትና፡ ሥራ፡ አትጠፋም፡ በበለጠ፡ ግን፡ ትሕትና፡ መድኃኒቷ፡ ነውና።

፱፡ ይህንንም፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ የጉድፍ፡ መጐተቻ፡ ከብረት፡ ሠራ፡ አጭር፡ የሆነ፡ የቆሸሸ፡ ልብስ፡ በመልበስ፡ በሌሊት፡ ተነሥቶ፡ የመነኰሳቱን፡ መንደር፡ እየዞረ፡ ቆሻሻውን፡ ጠርጎ፡ ተሸክሞ፡ ወስዶ፡ ከራቀ፡ ቦታ፡ ይጥለዋል። ይህንንም፡ ሥራ፡ እየሠራ፡ ሁለት፡ ዓመት፡ ያህል፡ ኖረ፡ እግዚአብሔርም፡ ንጽሕናውንና፡ የልቡን፡ ትሑትነት፡ ተመልክቶ፡ የባሕርይ፡ የሆነውን፡ ፍትወት፡ አራቀለት።

፲፡ ይህም፡ አባት፡ በገድል፡ እንደ፡ ተጠመደ፡ ሁኖ፡ መንጋዎቹ፡ በቀናች፡ ሃይማኖት፡ ይጸኑ፡ ዘንድ፡ እያስተማራቸውና፡ እየገሠጻቸው፡ እየመከራቸውም፡ ፲፪፡ ሁለት፡ ዓመት፡ ኑሮ፡ በሰላም፡ አረፈ።

፲፩፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በጸሎቱ፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ ለገብርኤል፡ እንበይነ፡ ጽድቁ፡ ወሃይማኖቱ። እንተ፡ ደለዎ፡ ይሠየም፡ ለአረጋዊ፡ በከመ፡
ትንቢቱ። በግብረ፡ ትሕትና፡ ወፍቅር፡ ከመ፡ ያድክም፡ ኃይለ፡ ፍትወቱ። ኰስተረ፡ አብያተ፡ ማይ፡
መጠነ፡ዓመታት፡ክልኤቱ።እንዘ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዓቢይ፡ወክቡር፡ውእቱ።

፲፪፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ አባ፡
ዘካርያስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡ስሐ፡ዝንቱኒ፡
አብ፡እምውሉደ፡ጸሐፍት፡አቡሁሰ፡ኀዲጎ፡
ጽሕፈተ፡ ተሠይመ፡ ቀሲሰ፡ ወስሙ፡ ዮሐ
ንስ።
፲፫፡ ወሶበ፡ ልሕቀ፡ ወልዱ፡ ዘካርያስ፡ ተምህረ፡
ትምህርታተ፡ወጽሕፈተ፡ወጥበበ፡ዘጽርእ፡
ወዘሮማውያን፡ ወዘሕገ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡
ወነሥአ፡ ሊቀ፡ ሐራሁ፡ ለንጉሥ፡ ወሤሞ፡
ጸሐፌ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ንጉሥ፡ ወኮነ፡ ሎቱ፡
ዐርከ፡ በጽሕፈቱ፡ ዘስሙ፡ አብጥልማዎስ፡
ዘኮነ፡ መኰንነ፡ ላዕለ፡ ሀገረ፡ ስሐ፡ ወእ
ሙንቱ፡ ተሰነዓዉ፡ ከመ፡ ይሑሩ፡ ኀበ፡
ገዳመ፡አስቄጥስ፡ወይኩኑ፡መነኰሳተ።

፲፬፡ ወበውእቱ፡ ጊዜ፡ በጽሐ፡ ኀቤሆሙ፡ ፩
መነኰስ፡እምደብረ፡አባ፡ዮሐንስ፡ዘገዳመ፡
አስቄጥስ፡ ወተሰነዓዉ፡ ከመ፡ ይሑሩ፡
ምስሌሁ፡ ወሰሚያሙ፡ መኳንንት፡ ዘንተ፡
ከልዕዎ፡ሐዊረ።
፲፭፡ ወእምድኅረ፡ኅዳጥ፡መዋዕል፡ርእዩ፡ራእየ፡
ዘከመ፡ ይቢሎሙ፡ ለምንት፡ ኢትፌጽሙ፡
ብፅዓተ፡ ዘበፃዕክሙ፡ ለእግዚአብሔር፡
ወተንሥኡ፡ ሶቤሃ፡ ወወጽኡ፡ በኅቡእ፡
እሙንቱሰ፡ ኢየአምሩ፡ ፍኖቶ፡ ወአስተር
አዮሙ፡ ፩ መነኰስ፡ ወመርሐሙ፡ ወአብ
ጽሖሙ፡ኀበ፡ደብረ፡አባ፡ዮሐንስ፡ዘገዳመ፡
አስቄጥስ። ወሶበ፡ ሰምዑ፡ መኳንንት፡
ሑረቶሙ፡ ተሰነዓዉ፡ ከመ፡ ይንሥኡ፡
መጽሐፈ፡ መልእክት፡ እምኀበ፡ ንጉሥ፡
ከመ፡ ይልአኩ፡ ወያውጽእዎሙ፡
እምደብር፡ ወዘረወ፡ ምክሮሙ፡ እግዚእነ
ሎቱ፡ስብሐት፡
፲፮፡ ወሶበ፡ መንኰሱ፡ ተጸምዱ፡ በተጋድሎ፡
ብዙኀ፡ ወፈድፋደሰ፡ አባ፡ ዘካርያስ፡
ወበውእቱ፡ መዋዕል፡ ኮኑ፡ አረጋውያን፡
አባ፡ አብርሃም፡ ወአባ፡ ገዐርጊ፡ ይመጽኡ፡
ኀቤሆሙ፡ወይናዝዝዎሙ፡ወያጸንዕዎሙ፡

፲፪፡ በዚችም፡ ቀን፡ የሀገረ፡ ስሐ፡ ኤጲስቆጶስ፡
የከበረ፡አባት፡አባ፡ዘካርያስ፡አረፈ፡ይህም፡
አባት፡የጸሐፊዎች፡ወገን፡ነው፡አባቱ፡ግን፡
ጸሐፊነቱን፡ ትቶ፡ ቅስና፡ ተሾመ፡ ስሙም፡
ዮሐንስ፡ነው።
፲፫፡ልጁ፡ዘካርያስም፡በአደገ፡ጊዜ፡ትምርቶችን፡
ሁሉ፡ ጽሕፈትንም፡ የጽርእና፡ የሮማው
ያንን፡ ጥበብ፡ የቤተ፡ ክርስቲያንንም፡ ሕግ
ተማረ፡ የንጉሥም፡ የጭፍራ፡ አለቃ፡
ወሰደውና፡ በንጉሡ፡ ቤት፡ ጸሐፊነት፡
ሾመው። በጽሕፈቱም፡ የሀገረ፡ ስሐ፡
መኰንን፡ የሆነው፡ ስሙ፡ አብጥልማዎስ፡
የሚባል፡ ወዳጅ፡ ሆነው፡ እነርሱም፡ ወደ፡
አስቄጥስ፡ ገዳም፡ ሒደው፡ ይመነኵሱ፡
ዘንድ፡ተስማሙ።
፲፬፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ ከአስቄጥስ፡ ገዳም፡ ከአባ፡
ዮሐንስ፡ደብር፡አንድ፡መነኰስ፡ወደነርሱ፡
መጣ፡ አብረውትም፡ ይሔዱ፡ ዘንድ፡
ተስማሙ፡ መኳንንቶችም፡ ይህን፡ በሰሙ፡
ጊዜ፡መሔድን፡ከለከሉዋቸው።

፲፭፡ከጥቂት፡ቀኖች፡በኋላም፡ለእግዚአብሔር፡
የተሰላችሁትን፡ ስለት፡ ለምን፡ አትፈ
ጽሙም፡ የሚላቸውን፡ ራእይ፡ አዩ፡
በዚያንም፡ ጊዜ፡ በሥውር፡ ወጡ፡ እነርሱ፡
ግን፡መንገዱን፡አያውቁትም፡ነበር፡አንድ፡
መነኰስም፡ ተገለጠላቸውና፡ ወደ፡ አስ
ቄጥስ፡ ወደ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ ገዳም፡ መርቶ፡
አደረሳቸው። መኳንንቱም፡ መሔዳቸውን፡
በሰሙ፡ ጊዜ፡ ከንጉሥ፡ ዘንድ፡ ደብዳቤ፡
ተቀብለው፡ በመላክ፡ ከገዳም፡ ሊአስወጡ
አቸው፡ ተስማሙ፡ የክብር፡ ባለቤት፡
ጌታችንም፡ምክራቸውን፡በተነ።

፲፮፡ በመነኰሱም፡ ጊዜ፡ በብዙ፡ ተጋድሎ፡ ተጠ
መዱ፡ ይልቁንም፡ አባ፡ ዘካርያስ፡ በዚያም፡
ወራት፡ አረጋውያን፡ አባ፡ አብርሃምና፡ አባ፡
ገዐርጊ፡ ነበሩ፡ ወደ፡ እርሳቸው፡ እየመጡ፡
በሥራቸው፡ ሁሉ፡ ያረጋጉዋቸውና፡ ያጸኑ

www.ethiopianorthodox.org

በኵሉ፡ምግባሮሙ።

፲፯፤ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ስሐ ፡ ተዘከርዎ፡ሕዝብ፡ለአባ፡ዘካርያስ፡ወጸሐፉ፡ መልእክተ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በእንተ ፡ አባ፡ዘካርያስ፡ከመ፡ይሚም፡ሎሙ፡ኪያሁ፡ እንዘ ፡ ይስእልዎ ፡ ወፈነወ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ኀበ፡ገዳመ፡አስቄጥስ፡ላእካነ፡ወአብጽሐ፡ ኀቤሁ ፡ ለአባ ፡ ዘካርያስ ፡ ወሤሞ ፡ ኤጲስ ቆጶሰ ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ስሐ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትኒ ፡ እንዘ፡ያነብር፡እደ፡ላዕሌሁ፡ርእየ፡ኃይለ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወተከለለ፡ገጹ፡በብርሃን።

፲፰፤ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱ ፡ ተቀበልዎ ፡ ሕዝቡ ፡ በፍሥሓ ፡ ዐቢይ ፡ በከመ፡ ተቀበልዎ ፡ ለመድኃኒነ ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ወእምዝ ፡ በርሀት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡በትምህርቱ፡ወበ ድርሳናቲሁ ፡ ወቃሉኒ ፡ ጥዑም ፡ ፈድፋደ ፡ ወምሉዕ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወነበረ ፡ ዲበ፡ መንበረ፡ ሢመቱ ፡ ፴ ዓመተ ፡ ወአ ሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት፤ ለእግዚአብሔር፡አሜን።

ዋቸው፡ነበር።

፲፯፤ የሀገረ ፡ ስሐ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ፡አባ፡ዘካርያስን፡አሰቡት፡እርሱንም ይሾምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ እየለመኑ፡ወደ፡ሊቀ፡ጳጳሳቱ፡የመልእክት፡ ደብዳቤ ፡ ጻፉ ። ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ፡ገዳም፡ልኮ፡አባ፡ዘካርያስን፡ወደ፡ እርሱ ፡ አስመጣው ፡ በሀገረ ፡ ስሐ ፡ ላይም ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ ሾመው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም፡ እጁን ፡ በላዩ ፡ በጫነ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔ ርን ፡ኃይል፡ አየ ፡ በላዩ ፡ ወርዷልና ፡ ፊቱም፡ በብርሃን፡ተጋረደ።

፲፰፤ ወደ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበሉት ፡ በዕለተ፡ ሆሣዕና ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ፡ መድ ኃኒታችንን ፤ እንደተቀበሉት ። ከዚህም ፡ በኋላ፡በትምህርቱና፡በድርሰቶቹ፡ቤተ፡ክር ስቲያን ፡ ብርሃን ፡ ሆነች ፡ ቃሉም ፡ እጅግ ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡ እርሱም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን፤ ጸጋ ፡ የተመላ ፡ ነው። በመንበረ ፡ ሢመቱም፡አርባ፡ዘመን፡ኖረ፡እግዚአብሔ ርንም ፡ አገልግሎ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ። በረ ከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዘካርያስ ፡ ለኃይለ ፡ ሰማይ ፡ ምሕዋጹ። በብርሃን ፡ ዐቢይ ፡ እንዘ ፡ ይኬልላ ፡ ለገጹ። እስከ ፡ ተፈሥሐት፡ ሀገረ ፡ ስሐ ፡ ወአባግዒሃ ፡ አንፈርዓፁ ። ለቴዎድሮስ ፡ ሰላም ፡ ወለጢሞቴስ ፡ ቢጹ። ዘማኅደ ረሆሙ፡በሰማይ፡ሐነፁ።

፲፱፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ አናሲሞስ ፡ ረድኡ ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ።

፳፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ገብረ ፡ ቀዳሚ ፡ ለ፩ ብእሲ፡ዘስሙ፡ፊልሞና፡እምሰብአ፡ሮሜ፡ ወዝንቱ ፡ ፊልሞና ፡ አምነ ፡ በእግዚእነ ፡ በእዴሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሶበ ፡ ሰበከ ፡ በሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ወእምዝ ፡ ነገደ ፡ ዝንቱ ፡ ፊልሞና ፡ እምሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ኀበ ፡ አስባንያ ፡ ወነሥአ ፡ ምስሌሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አናሲሞስ ፡ ገብሩ ፡ ሰይጣንሰ ፡ አስሐቶ ፡ ለአናሲሞስ ፡ ወአማሰነ ፡ ልቦ ፡ ወሰረቀ ፡ ንዋየ ፡ እግዚኡ ፡ ፊልሞና ፡ ወአእሚሮ ፡ ከመ ፡ እግዚኡ ፡

፲፱፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የሆነ ፡ ቅዱስ ፡ አናሲሞስ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፳፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ አስቀድሞ ፡ ከሮሜ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡ ፊልሞና ፡ ለሚባል ፡ ለሮሜ፡ሰው፡አገልጋይ፡ሆኖ፡ነበር፡ይህም፡ ፊልሞና ፡ በሮሜ ፡ በአስተማረ ፡ ጊዜ ፡ በቅዱስ፡ ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ በጌታችን ፡ አመነ ፡ ይህ፡ ፊልሞናም ፡ ከዚያ ፡ ከሮሜ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አስባንያ ፡ ሔደ ። ይህንንም ፡ አገ ልጋዩን ፡ አናሲሞስን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወሰደው ፡ ሰይጣን ፡ ግን ፡ አናሲሞስን ፡ አሳተው ፡ ልቡንም ፡ ለወጠውና ፡ የጌታውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰረቀ ፡ ጌታውም ፡ እንደሚቀጣው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይኰንኖ ፡ ጕየ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡
ወነበረ፡በህየ።

፳፩፤ ወበፈቃደ ፡ እግዚአብሔር፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወሰምዐ ፡
ትምህርቶ ፡ ወአምነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት። ወኮነ ፡ ረድአ ፡
ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወባሕቱ ፡ ኮነ ፡ ኀዘን ፡
ውስተ ፡ ልቡ፡ ለአናሲሞስ ፡ ወነገሮ ፡
ለሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡
ወይቤሎ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ኢትፍራህ ፡
ወኢይኅዝን ፡ ልብከ ፡ ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡
መልእክተ ፡ ኀበ ፡ ፊልሞና ፡ እግዚኡ ፡
ወይእቲ ፡ አሐቲ ፡ እመልእክታቲሁ ፡ በእ
ንተ፡ዝንቱ፡አናሲሞስ።

፳፪፤ ወይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ አነ ፡ አስተበቍዓከ ፡
በእንተ ፡ ወልድየ ፡ ዘወለድክዎ፡ በመዋቅ
ሕትየ ፡ ዘውእቱ ፡ አናሲሞስ። ዘቀዲሙሰ ፡
ኢበቍዓከ ፡ ይእዜሰ ፡ ለከሂ ፡ ወሊተሂ ፡
ባቍዐ፡ኮነ፡ጥቀ፡ወናሁ፡ፈነውክዎ፡ኀቤከ፡
ተወከፎ ፡ ከመ ፡ ወልድየ። ወእመኒ ፡ ቦ ፡
ዘአበሰ ፡ ለከ ፡ አው ፡ እመቦ ፡ ዘይፈድየከ ፡
ላዕሌየ፡ረሲ።

፳፫፤ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አናሲሞስ ፡
ኀበ፡ እግዚኡ ፡ ፊልሞና ፡ ተፈሥሐ ፡ በአሚ
ኖቱ ፡ ወንስሓሁ ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡
አዘዞ ፡ ሐዋርያ ፡ ወአፍቀሮ ፡ ፈድፋደ ፡
ወወሀቦ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢነሥአ ፡
ምንተኒ ፡ አላ ፡ ይቤሎ ፡ አንሰ ፡ ኮንኩ ፡ ባዕለ ፡
በክርስትና ። ወእምዝ ፡ አስተፋነዎ ፡ ወተመ
ይጠ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ወኮነ ፡ ዘይትለአኮ ፡
ለሐዋርያ፡ጳውሎስ፡እስከ፡ጊዜ፡ስምዑ።

፳፬፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ተሠይመ ፡ ካህነ ፡ ወወ
ደስዎ፡ ሐዋርያት ፡ ወዘከርዎ ፡ በቀኖናሆሙ ፡
ዘ፸ወ፰ቱ ፡ ዘ፹ወ፩ዱ ፡ ዘ፻ወ፫ቱ ፡ ዘ፻ወ፰ቱ ፡
ወይቤሉ፡ከመ፡ካህን፡ምእመን፡ውእቱ።

፳፭፤ ወእምድኅረ ፡ ስምዑ ፡ ለሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡
አኀዞ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ሊቀ ፡ ሐራሁ ፡
ለንጉሥ ፡ ወሰደዶ ፡ ኀበ ፡ አሐቲ ፡ ደሴት ፡

አውቆ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ተመልሶ፡
ሔደና፡በዚያ፡ተቀመጠ።

፳፩፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ ከበረ ፡
ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ሔደ ፡ ትምህርቱንም ፡
ሰምቶ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመነ ፡ ለቅዱስ ፡
ጳውሎስም ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ሆነ ። ነገር ፡
ግን፡ የጌታውን ፡ ገንዘብ ፡ በመስረቁ ፡ በአና
ሲሞስ ፡ ልብ ፡ ጽኑ ፡ ኀዘን ፡ አደረ ፡ ለሐዋርያ ፡
ጳውሎስም ፡ የሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ፡
ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ አትፍራ ፡ ልብህም ፡
አይዘን ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ ወደ ፡
ፊልሞናም ፡ መልእክትን ፡ጻፈለት ፡ ይቺም ፡
ስለ ፡ አናሲሞስ ፡ የጻፋት ፡ ከመልእክቶቹ ፡
አንዲቱ፡ናት።

፳፪፤ በመልእክቱም፡ እንዲህ፡ አለ፡ እኔ፡ በእሥ
ራቴ ፡ ጊዜ ፡ ስለወለድኩት ፡ ልጄ ፡ እማልድ
ሃለሁ ፡ ይኸውም ፡ አናሲሞስ ፡ ነው።
የቀድሞው ፡ ሥራው ፡ አልጠቀመህም ፡
ነበር፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ላንተም ፡ ለኔም ፡ እጅግ ፡
የሚጠቅም፡ሁኗል፡አሁንም፡ወዳንተ፡ልኬ
ዋለሁና ፡ ልጄ ፡ እንደመሆንህ ፡ ተቀበለው።
የበደለህ ፡ በደልም ፡ ቢኖር ፡ ወይም ፡ የሚከ
ፍልህ፡ቢኖር፡በኔ፡ላይ፡አድርገው።

፳፫፤ ይህ ፡ የከበረ ፡ አናሲሞስም ፡ ወደ ፡ ፊልሞና ፡
ወደ ፡ ጌታው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በማመኑና ፡
በመጸጸቱ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ሐዋርያው ፡ እንዳዘ
ዘውም ፡ አደረገለት ፡ እጅግም ፡ ወደደው ፡
ብዙ ፡ ገንዘብም ፡ ሰጠው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡
ምንም፡ ምን ፡ አልወሰደም ፡ እኔ ፡ በክርስትና ፡
ባለጸጋ ፡ ሁኜአለሁ ፡ አለ ፡ እንጂ ። ከዚህም ፡
በኋላ ፡ ሸኙትና ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ አገር ፡ ተመለሰ ፡
በሰማዕትነት ፡ እስከ ፡ ሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡
ሐዋርያ፡ጳውሎስን፡የሚያገለግለው፡ሆነ።

፳፬፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ካህን ፡ ሆኖ ፡ ተሾመ ፡ ሐዋር
ያትም ፡ በሥርዓት ፡ መጽሐፋቸው ፡
በአንቀጽ ፡ ሰባ ፡ ሰባት ፡ ሰማንያ ፡ አንድ ፡
በኃምሣ፡ ሦስትና፡ በኃምሳ፡ ሰባት፡ በምስ
ጋና ፡ አስታውሰውታል ፡ እንደ ፡ ታማኝ ፡
ካህንም፡ነው፡አሉ።

፳፭፤ ከሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ የምስክርነት ፡
ሞት፡በኋላ፡የንጉሥ፡ጭፍራ፡አለቃ፡ይህን፡
ቅዱስ፡ይዞ፡ወደ፡አንዲት፡ደሴት፡ሰደደው፡

www.ethiopianorthodox.org

ወነበረ ፡ ህየ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለሰብአ ፡ ይእቲ ፡ ደሴት ፡ ሃይማኖተ ፡ ወአጥመቆሙ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል ፡ በጽሐ ፡ ሊቀ ፡ ሐራሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ኀበ ፡ ይእቲ ፡ ደሴት ፡ ወረከቦ ፡ ለቅዱስ ፡ አናሲሞስ ፡ ሕያዎ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ሃይማኖተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአዘዘ ፡ ይቅሥፍዎ ፡ መቅሠፍተ ፡ ጽኑዓ ፡ ወይስብሩ ፡ አቍያጺሁ ፡ ወፈጸመ ፡ ስምዖ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ፡ሰምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፳፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

የዚያችን፡ደሴት፡ሰዎች፡ሃይማኖትን፡እያስተማራቸው፡ኖረ፡የክርስትና፡ጥምቀትንም፡አጠመቃቸው ። ከብዙ ፡ ቀኖችም ፡ በኋላ ፡ የንጉሥ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ፡ ወደዚያች ፡ ደረሰ፡የከበረ፡አናሲሞስንም፡ሕያው፡ሁኖ፡የክብር፡ባለቤት፡የጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን ፡ ሃይማኖት ፡ ለሰዎች ፡ ሲያስተምራቸው ፡ አገኘው ፡ ጽኑ ፡ ግርፋትንም ፡ ገርፈው፡ጭኖቹን፡እንዲሰብሩ፡አዘዘ፡ምስክርነቱንም ፡ ፈጸመ። የሰማዕትነት ፡ አክሊልንም፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ።

፳፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለአናሲሞስ፡ለጳውሎስ፡ረድኡ። በከመ፡ነሥአ፡መባሕተ፡እምፊልሞና፡ረድኡ። በሲኖዶሶሙ፡ዝክሮ፡እስከ፡ሐዋርያት፡ለክዐ። ሰብአ፡ደሴት፡በትምህርቱ፡እምድኅረ፡አምኑ፡ወጸንዑ። በተሰብሮ፡ቍየጽ፡ፈጸማ፡ለስምዑ።

፳፯፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለቅዱሳን፡አባ፡አካክዮስ፡ወአባ፡ገብርኤል፡ጳጳስ፡ዘሀገረ፡ኢትዮጵያ፡ወበረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ። ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

* * *

፳፯፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ለከበሩ ፡ አባ ፡ አካክዮስና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ጳጳስ ፡ ለአባ ፡ ገርርኤል ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ፡ አመ፡፳ወ፱ለየካቲት፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ተዝካረ፡ ዕረፍቱ፡ ለአባ፡ማሩና፡ ኤጲስቆጶስ፡ ወፍልሰተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰማዕት ፡ እለ ፡ብሔረ፡ ፋርስ፡ በመዋዕሊሁ፡ ለዲዮቅልጥያኖስ፡ዐላዊ።

፪፡ ወለማሩናሰ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በእንተ ፡ ብዙኅ ፡ መንክራቲሁ፡ወትሩፋቲሁ፡ወጽድቁ፡ፈነዎ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘየዐቢ ፡ አቡሆሙ ፡ ለአኖሬዎስ ፡ ወአርቃዴዎስ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ፡ ወምስሌሁ ፡ አምኃ ፡ በእንተ ፡ ፍቅር ፡ ዘማዕከሎሙ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሳቦር ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ አክበሮ ፡ ክብረ ፡ ዐቢየ ፡ ወአንበሮ ፡ ውስተ፡ጽርሐ፡መንግሥቱ።

፫፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ወለቱ ፡ ለንጉሥ ፡ ሐመት ፡ ወተጽዕነ ፡ ላዕሌሃ ፡ ጋኔን ፡ እኩይ፡ጸውዓ፡ቅዱስ፡አባ፡ማሩና፡ወአቀማ፡ቅድሜሁ፡ወጸለየ፡ላዕሌሃ፡ወወጽአ፡እምኔሃ፡

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ሃያ፡ሁለት፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ማሩና ፡ የዕረፍቱ፡መታሰቢያና፡በከሀዲ፡በዲዮቅልጥያኖስ ፡ ዘመን ፡ በፋርስ ፡ አገር ፡ ለተገደሉ ፡ ሰማዕታት፡ሥጋቸው፡የፈለሰበት፡ነው።

፪፡ ኤጲስቆጶስ፡ማሩናንም፡ስለ፡ድንቆች፡ተአምራቶቹ፡ስለ፡ትሩፋቱና፡ስለ፡ጽድቁ፡የአኖሬዎስና፡የአርቃዴዎስ፡አባት፡ታላቁ፡ቴዎዶስዮስ፡ንጉሥ፡ወደ፡ፋርስ፡ንጉሥ፡ላከው፡ ከእርሱም፡ጋር፡እጅ፡መንሻ፡በመካከላቸው፡ስለ፡አለው፡ፍቅር፡ተላከ። ወደ፡ሳቦር፡ወደ፡ፋርስ ፡ ንጉሥም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ክብርንም፡አከበረው፡በቤተ፡መንግሥቱም፡እልፍኝ፡ውስጥ፡አኖረው።

፫፡ ይህ ፡ ቅዱስም ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ጋኔን ፡ አድሮባት ፡ እንደታመመች ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡ አባ ፡ ማሩና ፡ ብላቴናዪቱን ፡ ጠርቶ ፡ በፊቱ ፡ አቁሞ ፡ በላይዋ ፡ ጸለየ ፡ ጋኔኑም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጋኔን፡ወሐይወት፡ወርእየ፡ከመ፡ተፈወሰት፡ ወለቱ፡ተፈሥሐ፡ንጉሥ፡ፈድፋደ፡ወወሰከ፡ አክብሮቶ፡ወአፍቅሮቶ፡ለአባ፡ማሩና።

፬፡ወእምዝ፡ኃሠሠ፡አባ፡ማሩና፡እምኀበ፡ንጉሥ፡ በእንተ ፡ አስተጋብኦተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን፡እለ፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡በብሔረ፡ፋርስ፡ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ያስተጋብኡ ፡ ሎቱ፡ ሥጋ ሆሙ፡ለሰማዕታት፡ወይሕንፁ፡ሎሙ፡ቤተ፡ ክርስቲያን፡ወያንብሩ፡ሥጋሆሙ፡ውስቴታ። ወይእቲ፡ተቀደሰት፡በዛቲ፡ዕለት፡ወሐነፁ፡ ካዕበ፡በውስተ፡ሀገር፡ዐባይ፡ቤተ፡ክርስቲ ያን፡ሠናይተ፡በስሙ፡ለቅዱስ፡አባ፡ማሩና፡ እንተ፡ይእቲ፡ምርቅና።

፭፡ወእምዝ፡ተመይጠ፡ዝንቱ፡አብ፡ኀበ፡ንጉሥ፡ ቴዎዶስዮስ፡ወነበረ፡ውስተ፡ሀገረ፡ሮሜ፡ ፪ተ፡ዓመተ፡ወአዕረፈ፡በዛቲ፡ዕለት፡ዘተቀ ደሰት፡ባቲ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘእሙንቱ፡ ሰማዕታት ፡ ወኮኑ ፡ ይገብሩ ፡ ሎቱ ፡ በዓለ ፡ ምስለ፡ቅዳሴሃ፡ለቤተ፡ክርስቲያን።

፮፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ከእርሷ፡ወጥቶ፡ዳነች፡ንጉሡም፡ልጁ፡እንደ ዳነች ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ የአባ ፡ ማሩናንም፡ፍቅርና፡አክብሮት፡ጨመረ።

፬፡ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡ማሩና፡በፋርስ፡ሀገር፡በሰ ማዕትነት ፡ ስለሞቱ ፡ የከበሩ ፡ ሰማዕታት ፡ ሥጋቸውን፡ስለ፡መሰብሰብ፡ከንጉሥ፡ዘንድ፡ ፈለገ፡ንጉሡም፡የሰማዕታትን፡ሥጋቸውን፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሠርተው ፡ በውስጧ ፡ ሥጋቸውን ፡ ያኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በዚች፡ዕለት፡ከበረች።ዳግመኛም፡በታላቋ፡ ከተማ፡ ውስጥ ፡ በከበረ ፡ አባ ፡ ማሩና ፡ ስም ፡ ያማረች፡ቤተ፡ክርስቲያንን፡ሠሩ፡እርሷም፡ ማረፊያ፡የተባለች፡ናት።

፭፡ከዚህም፡በኋላ፡ይህ፡አባት፡ወደ፡ንጉሥ፡ቴዎ ዶስዮስ ፡ ተመልሶ ፡ በሮሜ ፡ አገር ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ፡ የእነዚያ ፡ ሰማዕታት ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡በከረችበት፡በዚች፡ዕለት፡ አረፈ፡ከቤተ፡ክርስቲያኒቱም፡ክብር፡ጋር፡ በዓሉንና ፡ መታሰቢያውን ፡ የሚያከብሩለት ሆኑ።

፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረ ከቱም፡ከእኛ፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለማሩና፡ሠናየ፡ተልእኮ፡ቀሲስ።ወዓዲ፡ካዕበ፡ኤጲስቆጶስ።ቤተ፡ሰማዕታት፡ሐኒፆ፡በሀገረ፡ ፋርስ።በዕለተ፡ቀደሳ፡በስመ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ። ተጸውዐ፡ዮም፡ለመርዓ፡ሐዳስ።

፯፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለቅዱሳን፡አባ፡ ቡላ፡ወ፫ቱ፡፻ወ፹ ሰማዕታት፡ወበረከቶሙ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ አሜን።

***

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፳ወ፫ለየካቲት፡ በዛቲ፡ዕለት፡ ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡አውሳብዮስ፡ወልዱ፡ ለፋሲለደስ፡ብፁዕ።

፪፡ ወዝንቱ፡ብፁዕ፡ፋሲለደስ፡ሊቀ፡ሐራ፡ዘመን ግሥተ፡ሀገረ፡አንጾኪያ፡ወአቡሆሙ፡ለው ሉደ ፡ መንግሥት ፡ ውእቱኬ ፡ እንዘ ፡ሀሎ ፡ ውስተ፡ጸብእ፡ምስለ፡ሰብአ፡ፋርስ፡ሰምዐ፡ ከመ ፡ ክህዶ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ለእግዚእነ ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ስብሐት፡ወአምለከ፡ጣዖተ፡

፯፡በዚችም፡ዕለት፡የከበሩ፡የአባ፡ቡላና፡የሦስት፡ መቶ፡ ሰማንያ፡ ሰማዕታት፡ መታሰቢያቸው፡ ነው፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ትኑር፡ለእግዚአ ብሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

***

፩፡ አንድ ፡አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ሃያ፡ሦስት፡ በዚች፡ቀን፡የክቡር፡ፋሲለደስ፡ልጅ፡የከበረ፡ አውሳብዮስ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፪፡ ይህም ፡ የከበረ ፡ ፋሲለደስ ፡ ለአንጾኪያ ፡ መን ግሥት ፡ የሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ነው ፡ ለመን ግሥት ፡ ልጆችም ፡ አባታቸው ፡ ነው ፡ እርሱም፡ ከፋርስ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በጦርነት ፡ ውስጥ ፡ እያለ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችንን ፡ ክርስቶስን ፡ ክዶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኀዘነ ፡ ጥቀ ፡ ወፈነወ ፡ ኀበ፡ አውሳብዮስ ፡
ወልዱ ፡ ወነገሮ ፡ ዘንተ ፡ ወዓዲ ፡ ጸውዖሙ ፡
ለቅዱሳን ፡ አዝማዲሁ ፡ ሰብአ ፡ ቤተ፡ መን
ግሥት ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ዮስጦስ ፡ ወልደ ፡
ንጉሥ ፡ ወአባዲር ፡ ወገላውዴዎስ ፡ ወቴዎ
ድሮስ ፡ ወእለ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወነገሮሙ፡
በእንተ ፡ ንጉሥ ፡ ዐላዊ ፡ ወኀዘኑ ፡ ፈድፋደ ፡
ኵሎሙ።ወይቤሎሙ፡ካዕበ፡አንሰ፡እፈቅድ፡
ከመ ፡ እክዐው ፡ ደምየ ፡ በእንተ ፡ ስሙ፡ ለክር
ስቶስ ፡ አምላኪየ ፡ ወተሰነዓዉ ፡ ኵሎሙ ፡
በዝንቱ ፡ ምክር ፡ ሠናይ፡ ወተመሐሉ፡ በበይና
ቲሆሙ።
፫፤ ወመዊዖሙ ፡ ፀሮሙ ፡ ሶበ ፡ ገብኡ ፡ ሀገሮሙ ፡
ወጽአ ፡ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወተቀበ
ልዎሙ፡በፍሥሓ።

፬፤ ወእምዝ ፡ አምከሮ ፡ ለንጉሥ ፡ ህርማኖስ ፡
አቡሁ፡ ለቅዱስ፡ ፊቅጦር ፡ ከመ ፡ ያቅርብ ፡
ሎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ጣዖተ ፡ ወይስግዱ ፡ ሎቱ ፡
ወገብረ፡ንጉሥ፡በከመ፡አምከሮ፡ህርማኖስ።
ወሶቢሃ፡ጸውዖሙ፡ለቅዱሳን፡ወይቤሎሙ፡
አንትሙ፡ተአምሩ፡ከመ፡አነ፡አፈቅረክሙ፡
ፈድፋደ፡ወእፈቅድ፡እምኔክሙ፡ከመ፡ታስ
ተፍሥሑ ፡ ልብየ ፡ ወትስግዱ ፡ ለአጽሎን ።
ወሰሚዖሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ተምዑ ፡ ጥቀ ፡ ወአው
ሳብዮስ ፡ መልሐ ፡ ሰይፎ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ፡
ለንጉሥ ፡ ወጐየ ፡ ንጉሥ ፡ ወተኀብአ ፡ ወቀ
ተሎሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እምዐርካኒሁ ፡ ለንጉሥ ፡
ወሶበ ፡ አኮ ፡ ኢክልአሙ ፡ ፋሲለደስ ፡ ብፁዕ ፡
እምኢያትረፉ ፡ ሰብአ ፡ ምንተኒ ፡ ዘውስተ ፡
ቤተ፡ንጉሥ፡ወለሠራዊቱኒ።

፭፤ ወእምዝ፡ካዕበ፡አምከሮ፡ህርማኖስ፡ለንጉሥ፡
ከመ ፡ ይስድዶ ፡ ለአውሳብዮስ ፡ ብሔረ ፡
ግብጽ፡ወይቅትልዎ፡በህየ፡ወይቤሎ፡እስመ፡
ለእመ ፡ ነበረ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ፡
ወያነሥእ፡ሰብአ፡ሀገር፡ላዕሌከ፡ወኢትክል፡
ትግበር፡ምንተኒ፡እምዘትፈቅድ።
፮፤ ወጸሐፈ፡ንጉሥ፡ከመ፡ይሰድዎ፡ለቅዱስ፡አው
ሳብዮስ፡ኀበ፡ብሔረ፡ግብጽ፡ኀበ፡ሉልያኖስ፡
መኰንነ ፡ ቅፍጥ ፡ ከመ ፡ ይኴንኖ ፡ ኵነኔ ፡
ጽኑዐ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡
ሉልያኖስ ፡ ኰነኖ ፡ በመንኰራኵር ፡ ወበ

ጣዖትን ፡ እንዳመለከ ፡ ሰማ ። እጅግ ፡ አዝኖ ፡
ወደ ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ አውሳብዮስ ፡ ልኮ ፡ ይህን ፡
ነገረው ፡ የከበሩ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሰዎች ፡
ዘመዶቹን ፡ ዳግመኛ ፡ ጠራቸው ፡ እነርሱም ፡
የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ዮስጦስ ፡ አባዲር ፡ ገላውዴ
ዎስና ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከእርሳቸውም ፡ ጋር ፡
ያሉትን ፡ ጠርቶ ፡ስለ ፡ ከሀዲው ፡ ንጉሥ ፡
ነገራቸው ። ሁሉም ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ፡
ዳግመኛም፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ እኔ ፡ ስለ ፡
ፈጣሪዬ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ደሜን ፡
አፈሳለሁ፡ ሁሉም፡ በዚህ፡ በጎ፡ ምክር፡ ተስማ
ምተው፡እርስ፡በርሳቸው፡ተማማሉ።
፫፤ ጠላቶቻቸውንም ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡
ሀገራቸው ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡
ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ ወጥቶ ፡ በደስታ ፡ ተቀበ
ሏቸው።
፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቅዱስ ፡ ፊቅጦር ፡ አባት ፡
ህርማኖስ፡ ለቅዱሳኑ፡ ጣዖትን፡ እንዲአቀርብ
ላቸውና ፡ እንዲሰግዱለት ፡ ንጉሡን ፡ መከ
ረው፡ ንጉሡም ፡ ህርማኖስ ፡ እንደ ፡ መከ
ረው ፡ አደረገ ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ቅዱሳንን ፡
ጠርቶ፡እንዲህ፡አላቸው፡እኔ፡እጅግ፡እንደም
ወዳችሁ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችሁ ፡ አሁንም ፡
ለአጵሎን ፡ ሰግዳችሁ ፡ ልቤን ፡ ደስ ፡ ታሰኙ ፡
ዘንድ ፡ ከእናንተ ፡ እሻለሁ ። ቅዱሳንም ፡
ሰምተው ፡ እጅግ ፡ ተቆጡ ፡ አውሳብዮስም ፡
ንጉሡን ፡ ሊገድል ፡ ሰይፉን ፡ መዘዘ ፡
ንጉሡም፡ ሸሽቶ ፡ ተሸሸገ ፡ ከንጉሥም ፡
ባለሟሎች፡ብዙዎችን፡ሠራዊቱንም፡ጭምር፡
ገደለ ፡ የከበረ ፡ ፋሲለደስም ፡ ባይከለክላቸው ፡
ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ ምንም ፡ ሰው፡ ባልቀራቸው ፡
ነበር።
፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አውሳብዮስን ፡ ወደ ፡
ግብጽ ፡ አገር ፡ ወስደው ፡ በዚያ ፡ ይገድሉት ፡
ዘንድ ፡ ህርማኖስ ፡ ንጉሡን ፡ መከረው ፡ እርሱ ፡
በዚች ፡ ሀገር ፡ ከኖረ ፡ ያገር ፡ ሰዎችን ፡ በላይህ ፡
ያስነሣብሃልና ፡ ያሰብከውን ፡ ምንም ፡ ምን ፡
መሥራት፡አትችልም፡አለው።
፮፤ ንጉሡም ፡ ቅዱስ ፡ አውሳብዮስን ፡ ጽኑዕ ፡ ሥቃ
ይን፡ ያሠቃዩት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገር ፡
ወደ ፡ ቅፍጥ ፡ ገዥ ፡ ሉልያኖስ ፡ ዘንድ ፡ እንዲወ
ስዱት ፡ ጻፈ ፡ ወደ ፡ መኰንን ፡ ሉልያኖስም፡
በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በመንኰራኵር ፡ ሕዋሳቱን ፡

www.ethiopianorthodox.org

መቲረ፡መለያልያት፡ወበቅሥፈታት፡ወአብ ሰለዎ፡ካዕበ፡በውስተ፡ጤገን፡ወእግዚእነ፡ ፈነወ፡ሎቱ፡መልአኮ፡ወአድኃኖ፡እምኵሉ፡ ምንዳቤሁ፡ወናዘዞ፡ወአጽንዖ፡ወአንሥአ፡ ዘእንበለ፡ሙስና።

፯፤ ወመሠጣ፡ለነፍሱ፡ኀበ፡ገነተ፡ትፍሥሕት፡ ወርእየ ፡ ማኅደሮሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ወጻ ድቃን፡ ወመካናተ ፡ ዘአስተዳለወ ፡ ሎቱ ፡ ወለአቡሁ ፡ ወአዝማዲሁ ፡ ወተፈሥሐት ፡ ነፍሱ፡ፈድፋደ።

፰፤ ወእምዝ፡አዘዘ፡መኰንን፡ይደይዎ፡ውስተ፡ እቶነ፡እሳት፡አሜሃ፡ወረደ፡መልአከ፡እግዚአ ብሔር፡ወረሰዮ፡ለነድ፡ቈሪረ፡ከመ፡ጠል፡ ወአውጽአ ፡ ለቅዱስ ፡ አውሳብዮስ ፡ እም ውስተ፡እቶን፡ዘእንበለ፡ሙስና።

፱፤ ወአምከርዎ ፡ መኳንንት ፡ ለመኰንን ፡ ወይ ቤልዎ፡አ፡መኰንን፡አዝዝ፡ከመ፡ይምትሩ፡ ርእሶ፡በሰይፍ፡ወተዓርፍ፡እምኔሁ፡ውእቱኒ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡ ቅድስተ ፡ ለአውሳ ብዮስ፡ በሰይፍ ፡ ወመተርዎ ፡ ወነሥአ፡ አክሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፲፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

በመቈራረጥ ፡ በግርፋት ፡ አሠቃዩት ። ዳግ መኛም፡በብረት፡ምጣድ፡ውስጥ፡አበሰሉት፡ ጌታችንም ፡ መልአኩን ፡ ልኮ ፡ ከመከራው ፡ ሁሉ፡አዳነው፡አጽናንቶና፡አረጋግቶ፡ያለ፡ ጉዳት፡አስነሣው።

፯፤ ነፍሱንም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ወዳለበት ፡ ገነት ፡ ወሰዳት፡የጻድቃንና፡የሰማዕታትንም፡መኖ ሪያ፡አየ፡ለርሱና፡ለአባቱ፡ለዘመዶቹም፡ያዘ ጋጀላቸውን፡ቦታዎች፡አይቶ፡ነፍሱ፡እጅግ፡ ደስ፡አላት።

፰፤ ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡እሳት፡ማንደጃ፡ውስጥ፡ ይጨምሩት ፡ ዘንድ ፡ መኰንኑ ፡ አዘዘ ፡ ያን ፡ ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ወርዶ፡እሳቱን፡እንደ፡ጠል፡አቀዝቅዞ፡ያለ፡ ጥፋት፡የከበረ፡አውሳብዮስን፡አወጣው።

፱፤ መኳንንቱም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መከሩት ፡ መኰንን፡ሆይ፡ራሱን፡በሰይፍ፡እንዲቆርጡ፡ እዘዝ ፡ ከእርሱም ፡ ትግል ፡ ታርፋለህ ፡ እርሱም፡ የአውሳብዮስን ፡ የከበረች ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ፡ይቆርጡ፡ዘንድ፡አዘዘና፡ቆረጡት፡ የሰማዕትነት ፡ አክሊልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት፡ተቀበለ።

፲፤ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ወልደ ፡ ፋሲለደስ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ። ወቢጸ ፡ ብፁዕ ፡ መርቆሬ ። አውሳብዮስ ፡ ሰማዕት ፡ ትቤዝወኒ ፡ እመከራ ። አርኢ ፡ ሊተ ፡ ለአምላክ ፡ መሐሪ ፡ ለአባልከ ፡ ምታሬ ። አመ ፡ ለነፍስየ ፡ ይትነበብ ፡ እኩይ፡ምግባራ።

፲፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ስምዐ ፡ ለቅዱስ ፡ አውስግንዮስ ፡ ገብሩ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ ምሥ ራቃዊ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

***

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ፡አመ፡፳ወ፱ ለየካቲት  በዛቲ፡ዕለት፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አጋቢጦስ ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ኮነ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ለዲዮቅልጥያኖስ ፡ ወመክስምያኖስ ፡ ነገ ሥት፡ዐላውያን።

፲፩፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የምሥራቃዊ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አገልጋይ ፡ የአውስግንዮስ ፡ የምስክርነቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

***

፩፤ አንድ ፡አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ሃያ፡አራት፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አጋቢጦስ፡አረፈ።ይህም፡አባት፡በከሀድያን፡ ነገሥታት ፡ በዲዮቅልጥያኖስና ፡ በመክስም ያኖስ፡ዘመን፡ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ አበዊሁ፡ ኄራን፡ መሃይምናን፡ ወመሀርዎ፡ ትምህርተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ወተሠይመ፡ ዲያቆነ፡ ወእምዝ፡ ኀደጎሙ፡ ለአቡሁ፡ ወእሙ፡ ወሖረ፡ ውስተ፡ ፩ ደብር፡ ወተልእኮሙ፡ ለአረጋውያን፡ መነኰሳት፡ ወተምህረ፡ እምኔሆሙ፡ አምልኮ፡ ሠናየ፡ ወተጸምደ፡ በገድል፡እንዘ፡ ይትለአኮሙ፡ ለአረጋውያን፡ ወይተግህ፡ ወትረ፡ በጾም፡ ወበጸሎት፡ ወበሰጊድ፡ ዘእንበለ፡ ጽርዓት፡ ወኮነ፡ ዘይሴሰይ፡ ሀሰረ፡ ተርሙስ፡ ወይጸውም፡እምጽባሕ፡እስከ፡ምሴት።

፲፤ ወሶበ፡ፈቀደ፡ይትዓገል፡ምስለ፡ንዋም፡ነበረ፡ ፴ መዓልተ፡እንዘ፡ይሴሰይ፡ሐመደ፡ምስለ፡ ሀሰረ፡ተርሙስ፡ወኃይሉስ፡ይትዌሰክ፡እንዘ፡ ሀሎ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ተጋድሎ። ወኢያጽርዐ፡ ተልእኮቶ፡ለአረጋውያን፡ወይሰምዮሙ፡አጋእዝቲሁ፡ወፈጸመ፡ኵሎ፡ምግባራተ፡ጽድቅ።

፲፩፤ ወገብረ ፡እግዚአብሔር፡ በእደዊሁ፡ ተአምራተ፡ወመንክራተ፡ዐበይተ፡ብዙኃተ፡ወእምኔሆሙ፡ ለአሐቲ፡ ወለት፡ ፈወሳ፡ ዘነበረት፡ በደዌ፡ዕፁብ፡ብዙኀ፡አዝማነ፡እስከ፡ኮነት፡ ይብስተ፡ ከመ፡ ዕፅ። ወካዕበ፡ ቀተለ፡ ከይሴ፡ ዐቢየ፡ በጸሎቱ፡ ዘአህጐለ፡ ብዙኀነ፡ ሰብአ፡ ወሰደደ፡ እምላዕለ፡ ሰብእ፡ ወእንስሳ፡ ሕማማተ፡ዕፁባተ።

፲፪፤ ወሶበ ፡ ተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ወተጋድሎቱ ፡ ወጽንዐ፡ ኃይሉ፡ ፈነወ፡ ኀቤሁ፡ መኰንን፡ ዘስሙ፡ሉክያኖስ፡ወአብጽሐ፡ወሤሞ፡ሊቀ፡ ላዕለ ፡ ሐራ ፡ ዘእንበለ ፡ ደቃዱ ፡ በኵርህ ፡ ውእቱሰ፡ኢኀደገ፡ተጋድሎቶ፡ዘቀዳሚ፡ኢ፡ ጾመ፡ ወኢ፡ ጸሎተ፡ አላ፡ ይዌስክ፡ ገቢረ፡ ትሩፋት፡ ወበኀዳጥ፡ መዋዕል፡ አጥፍአሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለዲዮቅልጥያኖስ፡ ወመክስምያኖስ፡ ወነግሠ፡ ቈስጠንጢኖስ፡ ጻድቅ፡ መፍቀሬ፡ አምላክ፡ ወኮነ፡ ዝንቱ፡ ቅዱስ፡ ዘየኃሥሥ፡ ምክንያተ፡ ከመ፡ ይጻእ፡ እምውስተ፡ሐራ።

፲፫፤ ወሀሎ፡ ወልድ፡ ወሬዛ፡ ዘሠናይ፡ አርአያሁ፡ ዘያፈቅሮ፡ንጉሥ፡ቈስጠንጢኖስ፡ፈድፋደ፡

፱፤ ወላጆቹም፡ ደጎች፡ ምእመናን፡ ነበሩ፡ የቤተ፡ ክርስቲያንን፡ ትምህርት፡ አስተምረውት፡ ዲቁና፡ ተሾመ። ከዚህም፡ በኋላ፡ እናትና፡ አባቱን፡ ትቶ፡ ወደ፡ አንድ፡ ገዳም፡ ሔዶ፡ የሸመገሉ፡ መነኰሳትን፡ አገለገለ። ከእርሳቸውም፡በጎ፡አምልኮትን፡ተማረ፡አረጋውያኑንም፡ እያገለገለ፡ በገድል፡ ተጠመደ፡ያለ፡ ማቋረጥም፡ በጾም፡ በጸሎትና፡ በስግደት፡ ይተጋል፡ከጥዋትም፡እስከ፡ምሽት፡በመጾም፡ የሽንብራ፡አሠር፡የሚመገብ፡ሆነ።

፲፤ ከእንቅልፍም፡ ጋር፡ ሊታገል፡ በወደደ፡ ጊዜ፡ ከሽምብራ፡አሠር፡ጋር፡አመድ፡እየተመገበ፡ ሰማንያ፡ ቀን፡ ኖረ፡ በዚህም፡ ተጋድሎ፡ ውስጥ፡ እያለ፡ ኃይሉ፡ ግን፡ ይጨመርለት፡ ነበር። ለአረጋውያንም፡ አገልግሎቱን፡ አላስታጐለም፡ ሲጠራቸውም፡ ጌቶቼ፡ ይላቸዋል፡ የጽድቅንና፡ የትሩፋትን፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ፈጸመ።

፲፩፤ እግዚአብሔርም፡ የሚያስደንቁ፡ ብዙዎች፡ የሆኑ፡ ታላላቅ፡ ተአምራቶችን፡ በእጆቹ፡ ገለጠ። ከእርሳቸውም፡ አንዲቷን፡ ብላቴና፡ አዳናት፡እርሷም፡እንደ፡ዕንጨት፡የደረቀች፡ እስከምትሆን፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ጭንቅ፡ በሆነ፡ ደዌ፡ታማ፡የኖረች፡ናት። ዳግመኛም፡ብዙ፡ ሰዎችን፡ያጠፋውን፡ታላቅ፡ከይሲ፡በጸሎቱ፡ ገደለው። ከሰውና፡ ከእንስሳም፡ አስጨናቂ፡ የሆኑ፡በሽታዎችን፡አስወገደ።

፲፪፤ የተጋድሎውና፡ የኃይሉ፡ ጽናት፡ ወሬው፡ በተሰማ፡ ጊዜ፡ ስሙ፡ ሉክያኖስ፡ የሚባል፡ መኰንንን፡ ወደርሱ፡ ልኮ፡ አስመጥቶ፡ ያለ፡ ውዴታው፡በግድ፡የጭፍራ፡አለቃ፡አድርጎ፡ ሾመው፡እርሱ፡ግን፡ተጋሎውን፡አልተወም፡ ጾምንም፡ ጸሎትንም፡ የትሩፋትን፡ ሥራ፡ የሚጨምር፡ሆነ፡እንጂ፡የቀደመ፡ሥራውን፡ አልተወም፡ በጥቂት፡ ቀኖችም፡ ዲዮቅልጥያኖስንና፡ መክስምያኖስን፡ እግዚአብሔር፡ አጠፋቸው፡ አምላክን፡ የሚወድ፡ ጻድቅ፡ ሰው፡ ቈስጠንጢኖስ፡ ነገሠ፡ ይህም፡ ቅዱስ፡ ከጭፍራ፡ውስጥ፡ይወጣ፡ዘንድ፡ምክንያት፡ የሚሻ፡ሆነ።

፲፫፤ ንጉሥ፡ ቈስጠንጢኖስ፡ እጅግ፡ የሚወደው፡ መልከ፡ መልካም፡ የሆነ፡ ወጣት፡ ብላቴና፡

ወተጽዕነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰይጣን ፡ ወኮነ ፡ ዘይኬንኖ ፡ ኮነኔ ፡ ዐቢየ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ፩ ብእሲ ፡ እምእለ ፡ የአምርዎ ፡ ለቅዱስ ፡ አጋቢጦስ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ይቤሎ ፡ ለዘጋኔን ፡ አጋቢጦስ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ እምፌ ወሰከ ፡ ለእመ ፡ መጽአ ፡ ወይቤ ፡ ዘሐመ ፡ ቦኑ ፡ ይክል ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ በሥርዓተ ፡ ሐራ ፡ ንጉሥ ፡ ወአጠየቀ ፡ ኮሎ ፡ ግብሮ ፡ ወተጋድሎቶ ። ወይቤ ፡ ዘጋኔን ፡ በአማን ፡ ይክል ፡ ፈውሶትየ ፡ ወአምጽኡ ፡ ሊተ ፡ ፍጡነ ፡ አጋቢጦስሃ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ከመ ፡ ይፈውሰኒ ፡ እምዝንቱ ፡ ዕፁብ ፡ ደዌ ።

፯፡ ወሶበ ፡ አእመረ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንተ ፡ አዘዘ ፡ ያምጽእዎ ፡ ለቅዱስ ፡ አጋቢጦስ ፡ ወመጺኦ ፡ ውእቱ ፡ ጸለየ ፡ ላዕለ ፡ ወሬዛ ፡ ወአተቦ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ክቡር ፡ ወሐይወ ፡ ሶቤሃ ፡ በኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተፈሥሐ ፡ ንጉሥ ፡ በዝንቱ ፡ ወአክበሮ ፡ ለቅዱስ ፡ አጋቢጦስ ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ምንተ ፡ እግበር ፡ ለከ ፡ ትፈቅድ ። ውእቱኒ ፡ ይቤሎ ፡ ለንጉሥ ፡ ሠዓረኒ ፡ እምውስተ ፡ ሐራ ፡ ወሠዓሮ ፡ ንጉሥ ፡ ወተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ መካኑ ፡ ዘነበረ ፡ ባቲ ፡ ወአኀዘ ፡ ይትጋደል ፡ ፈድፋደ ፡ ብዙኀ ፡ ዓመታተ ።

፰፡ ወእምዝ ፡ አኀዞ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይእቲ ፡ ሀገር ፡ ወሤሞ ፡ ቀሲሰ ፡ ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ ውእቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሰአልዎ ፡ ሕዝብ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከመ ፡ ይሢሞ ፡ ለቅዱስ ፡ አጋቢጦስ ፡ ሎሙ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ ውእቱኒ ፡ ሤመ ፡ ሎሙ ፡ ወዓቀቦሙ ፡ ለመርዔተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነባብያን ፡ ሠናየ ፡ ዕቅበተ ፡ ወወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ ወአእምሮ ፡ ኅቡአት ፡ ወገቢረ ፡ መንክራት ፡ ወይጌሥጾሙ ፡ ለኃጥአን ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ኃጢአተ ፡ በኅቡእ ፡ ወያርኅቆሙ ፡ እምቤተ ፡ መቅደስ ፡ እስከ ፡ ይኔስሑ ።

፱፡ ወዓዲ ፡ ዘተረክበ ፡ ጽሑፈ ፡ ውስተ ፡ ገድሉ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ዐቀሞ ፡ ለማየ ፡ ፈለግ ፡ ዐቢይ ፡ ወሜጦ ፡ በመስቀሉ ፡ ኀበ ፡ ካልዕ ፡ ፍኖት ፡ ወከሠተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለዕውር ፡ ወእለ ፡ ለምጽ ፡ አንጽሐ ፡ ወብዙኀነ ፡ ዱያነ ፡ ፈወሰ ።

ነበር ፡ ክፉ ፡ ጋኔንም ፡ ተጫነበት ፡ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ ታላቅ ፡ ሥቃይን ፡ የሚያሠቃየው ፡ ሆነ ፡ ቅዱስ ፡ አጋቢጦስንም ፡ ከሚያውቁት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ የወታደር ፡ አለቃ ፡ አጋቢጦስ ፡ ቢመጣ ፡ በአዳነህ ፡ ነበር ፡ አለው ፡ የታመመውም ፡ እርሱ ፡ በንጉሥ ፡ ጭፍራ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ በውኑ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ይችላልን ፡ አለ ፡ ሰውዬውም ፡ ገድሉንና ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ አስረዳው ። ጋኔን ፡ ያደረበትም ፡ በእውነት ፡ ሊያድነኝ ፡ ይችላልና ፡ ከዚህ ፡ ከአስጨናቂ ፡ ደዌ ፡ ያድነኝ ፡ ዘንድ ፡ የወታደር ፡ አለቃ ፡ አጋቢጦስን ፡ ፈጥናችሁ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ።

፯፡ ንጉሥም ፡ ይህን ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ አጋቢጦስን ፡ እንዲአመጡት ፡ አዘዘ ፡ በመጣ ፡ ጊዜም ፡ በወጣቱ ፡ ላይ ፡ ጸለየ ፡ በከበረ ፡ መስቀልም ፡ አማተበው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ዳነ ፡ ንጉሡም ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ቅዱስ ፡ አጋቢጦስን ፡ አከበረው ፡ ምን ፡ እንዳደርግልህ ፡ ትሻለህ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ ንጉሡን ፡ ከወታደርነት ፡ ውስጥ ፡ አሰናብተኝ ፡ አለውና ፡ አሰናበተው ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ነበረባትም ፡ ቦታው ፡ ተመለሰ ፡ ብዙ ፡ ዘመናትም ፡ እጅግ ፡ እየተጋደለ ፡ ኖረ ።

፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የዚያች ፡ አገር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይዞ ፡ ቅስና ፡ ሾመው ፡ ይህም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ አጋቢጦስን ፡ ይሾምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ለመኑት ፡ እርሱም ፡ ሾመላቸው ፡ መልካም ፡ ተናጋሪዎች ፡ የሆኑትን ፡ የክርስቶስን ፡ መንጋዎች ፡ በበጎ ፡ አጠባበቅ ፡ ጠበቃቸው ። እግዚአብሔርም ፡ የትንቢትን ፡ ጸጋ ፡ የተሠወረውንም ፡ የማወቅ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችንም ፡ የማድረግ ፡ ሀብትን ፡ ሰጠው ። በሥውር ፡ ኃጢአትን ፡ የሚሠሩትን ፡ ኃጢአተኞች ፡ የሚገሥጻቸው ፡ ሆነ ፡ በንስሐም ፡ እስኪመለሱ ፡ ከመቅደስ ፡ ያርቃቸዋል ።

፱፡ ዳግመኛም ፡ በገድሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ የተገኘ ፡ የታላቅ ፡ ወንዝ ፡ ወራጅ ፡ ውኃን ፡ በመስቀሉ ፡ አቁሞ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ መለሰው ፡ የዕውር ፡ ዐይኖችንም ፡ ገለጠ ፡ ለምጻሞችንም ፡ አነጻ ፡ ብዙዎች ፡ በሽተኞችንም ፡ አዳነ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከ ቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለአጋቢጦስ፡ ለንዋመ፡ ሐኬት፡ ዘአጕየየ ። ምስለ፡ ሀሰረ፡ ተርሙስ፡ ሐመደ፡ እንዘ፡ ይገብር፡ ሲሳዮ ። ነጺሮ፡ ንጉሥ፡ እስከነ፡ አዕበዮ ። ጸገዎ፡ ፈውሰ፡ በጸሎቱ፡ ለዘጋኔን፡ አድወዮ ። ወለዘለምጽ፡ ንጹሐ፡ ረሰዮ።

፲፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ሰማዕት ፡ ዘጋዛ ፡ ወሚናስ ፡ ዘቆጵሮስ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፲፩፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበሩ ፡ በጋዛ ፡ ሰማዕት ፡ የሆኑ፡ጢሞቴዎስና፡የቆጵሮስ፡ሀገር፡ሚናስ፡ መታሰቢያቸው፡ነው፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ ለማትያስ፡ ጽንዐ፡ ቆጵሮስ፡ ወሬዛ። ወለጢሞቴዎስ፡ ዓዲ፡ ዘብሔረ፡ ጋዛ። ትኩላን፡ ዕፀው፡ ለማየ፡ ሃይማኖት፡ ኀበ፡ ሙሐዛ። ይደዩ፡ ውስተ፡ አንፍየ፡ እምፍሬሆሙ፡ መዓዛ። ለጺዓተ፡ ጊጋይ፡ ሕሱም፡ ዘያለስሕ፡ ሕምዛ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፳ወ፫ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱሳን ፡ አውሳንዮስ ፡ ወፊልሞና ፡ ወአሐቲ ፡ ድንግል ፡ ዘስማ ፡ ሉቅያ።

፪፡ ወእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ አምኑ ፡ በእዴሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ አመ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ አፍራቅያ ። ወሶበ ፡ ገብሩ ፡ ክህድያን ፡ በዓለ ፡ ለአርታዳሚ ፡ ጣዖት ፡ ዘሰመይዎ ፡ በስመ ፡ ኮከብ ፡ ዝሑራ ፡ ተጋብኡ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ። ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ወይሣለቁ ፡ ላዕለ ፡ ስሕተቶሙ ፡ ወሶበ ፡ ርእይ ዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ እንዘ ፡ ይሠውዑ ፡ ለጣዖት ፡ ወያዓብይዎ ፡ ሶቤሃ ፡ ነደ ፡ ልቦሙ ፡ ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ በእሳተ ፡ ፍቅሩ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወወጽኡ ፡ እምቤተ ፡ ጣዖት ፡ ወቦኡ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሲሐዊት ፡ ወወሰኩ ፡ ስብሐተ ፡ ወልዕልና ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የከበሩ ፡ አውሳንዮስና ፡ ፊልሞና ፡ ስሟ ፡ ሉቅያ ፡ የሚባል ፡ አንዲት ፡ ድንግልም ፡ በሰማዕ ትነት፡ሞቱ።

፪፡ እሊህ ፡ ቅዱሳንም ፡ በአፍራቅያ ፡ ሀገር ፡ ሳለ ፡ በከበረ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ትምህርት ፡ ያመኑ፡ ናቸው ፡ ከሀድያንም ፡ ዝሑራ ፡ በሚ ባል ፡ ኮከብ ፡ ስም ፡ ለሚጠሩት ፡ ለአርታዳሚ ፡ ጣዖት ፡ በዓልን ፡ በአደረጉ ፡ ጊዜ ፡ አይተው ፡ በስሕተታቸው ፡ ሊዘብቱ ፡ እሊህ ፡ ቅዱሳን ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ጣዖቱ ፡ ቤት ፡ ገቡ ፡ ሰዎችም ፡ ለጣዖቱ ፡ ሲሠዉና ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ሲያ ደርጉት ፡ በአዩአቸው ፡ ጊዜ ፡ በክብር ፡ ባለ ቤት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍቅር፡ እሳትነት ፡ ልባቸው ፡ ነደደ፡ ከጣዖቱም ፡ ቤት ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ክርስቶ ሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔደው ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ክብሩንና ፡ ልዕልናውን ፡ አብዝተው ፡ አመሰገኑ።

www.ethiopianorthodox.org

፫፤ ወሰሚያ፡፩ብእሲ፡እምእለ፡ሀለዉ፡ህየ፡ለበወ፡ ዘተናገሩ ፡ ወዘከመ ፡ ተሣለቁ ፡ ላዕለ ፡ ጣያቶሙ፡ አስተዋደዮሙ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወተጽዕነ ፡ መኰንን ፡ ዲበ ፡ ፈረስ ፡ ወሖረ ፡ ወዓገታ፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡ምስለ፡ሐራሁ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ ጕዩ ፡ እምሰብእ ፡ መሃይምናን ፡ ወአኀዘሙ፡ለእሉ፡፫ቱ፡ቅዱሳን፡ወአርሰኑ፡ አብትረ ፡ ኀጺን ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ወረሰዩ ፡ ውስተ ፡ ገበዋቲሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወእምዝ ፡ ወረውዎ ፡ ለቅዱስ ፡ አውሳንዮስ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት፡ወወገርዎ፡በአዕባን፡እስከ፡መጠወ፡ ነፍሶ።

፬፤ ወለቅዱስሰ፡ፊልሞና፡ወለቅድስት፡ሉቅያ፡ አኃዙ፡ይኰንንዎሙ፡ኵነኔ፡ጽኑዐ፡ብዙኀ፡ ጊዜ፡ወሰአልዎ፡ለእግዚአብሔር፡ይንሣእ፡ ነፍሶሙ ፡ ውእቱኒ ፡ ተወክፈ ፡ ስእለቶሙ ፡ ወነሥአ፡ነፍሶሙ፡ወነሥኡ፡አክሊለ፡ስምዕ፡ በመንግሥተ፡ሰማያት፡ወናሁ፡ጽሑፍ፡ተዝ ካረ ፡ ስምዖሙ ፡ ወሃይማኖቶሙ ፡ ወበረ ከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግዚ አብሔር፡አሜን።

፫፤ ከዚያ ፡ ካሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሰማቸው ፡ ጊዜ፡በጣያታቸው፡ላይ፡እንደ፡ዘበቱ፡የተና ገሩትን፡ልብ፡ብሎ፡በመኰንኑ፡ዘንድ፡ወነ ጀላቸው፡መኰንኑም፡በፈረስ፡ተቀምጦ፡ ሔደ፡ከወታደሮቹም፡ጋር፡ቤተ፡ክርስቲያ ኒቱን ፡ ከበባት ፡ ከምእመናንም ፡ ሰዎች ፡ የሸሹ፡አሉ።እሊህንም፡ሦስቱን፡ቅዱሳን፡ ያዛቸው ፡ የብረት ፡ ዘንጎችን ፡ በእሳት ፡ አግለው ፡ በቅዱሳኑ ፡ ጐኖች ፡ ውስጥ ፡ አደረጉት፡ከዚህም፡በኋላ፡የከበረ፡አውሳን ዮስን፡ወደ፡ጕድጓድ፡ወረወሩትና፡ነፍሱን፡ እስከ፡ሰጠ፡ድረስ፡በደንጊያ፡ወገሩት።

፬፤ የከበረ፡ፊልሞናንና፡የከበረች፡ሉቅያን፡ግን፡ ብዙ፡ጊዜ፡በጸና፡ሥቃይ፡ያሠቃዩአቸው፡ ጀመር፡ነፍሳቸውንም፡ይወስድ፡ዘንድ፡እግ ዚአብሔርን ፡ ለመኑት ፡ እርሱም ፡ ልመና ቸውን፡ተቀብሎ፡ነፍሳቸውን፡ወሰደ።በመ ንግሥተ፡ሰማያትም፡የሰማዕትነት፡አክሊ ልን፡ተቀበሉ፡እነሆ፡የምስክርነታቸውና፡ የሃይማኖታቸው፡መታሰቢያ፡ተጽፎአል። በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚ አብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአውሳንዮስ ፡ ወፊልሞና ፡ ወለድንግል ፡ ሉቅያ ። ዘአመንክሙ ፡ በእዴሁ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ። በእደ፡መኰንን፡ዕልው፡ዘአፍራቅያ።ገበዋቲክሙ፡በርስነ፡ኀጺን፡ዘውዕያ።ይጸልላኒ፡ለዕለተ፡ እምእከያ።

፭፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡ቶና፡ዲያቆን፡ ዘእምሀገረ፡ሮሜ፡ወሚናስ፡እምሀገረ፡ቍስ፡ ወይልማድዮስ ፡ እምሀገረ ፡ ጋዛ ፡ ወተዝ ካሮሙ፡ካዕበ፡ለደማይልናል፡ወርጊኖስ፡ወበ ረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእግ ዚአብሔር፡አሜን።

፭፤ በዚችም፡ዕለት፡ከሮሜ፡አገር፡ዲያቆን፡ቶና፡ ከሀገረ፡ቍስ፡ሚናስ፡ከጋዛ፡ይልማድዮስ፡ በሰማዕትነት፡ሞቱ፡ዳግመኛም፡የደማይል ናልና፡የርጊኖስ፡መታሰቢያቸው፡ነው።በረ ከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአብ ሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ቶና፡ዲያቆን።ወሚናስ፡ብፁዕ፡ሠናየ፡አሚን።ወይልማድዮስ፡ነሣኢ፡አክሊለ፡ ግዕዛን።ሀቡኒ፡አጋእዝትየ፡ለብእሲ፡ምስኪን።ዕሴተክሙ፡ዘኢርእየ፡ዐይን።

፮፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡እንጦኒ፡ ሐዲስ፡ዘውእቱ፡ረውሕ።

፯፤ ወዝንቱ ፡ ቆሮሳዊ ፡ እምክቡራነ ፡ ዐረብ ፡ ወቦ፡ንዋይ፡ብዙኀ፡በሀገረ፡ደማስቆ፡ወይነ

፮፤ በዚችም፡ዕለት፡የከበረ፡ሐዲስ፡እንጦኒ፡በሰማ ዕትነት ፡ ሞተ ፡ ይህም ፡ ረውሕ ፡ የሚባል ፡ ነው።

፯፤ ይህም፡ከከበሩ፡ዐረቦች፡ወገን፡የቆሮስ፡ሰው፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ በሰማ

ብር ፡ ኀበ ፡ ጽንፈ ፡ ፈለግ ፡ ዘእምኔተ ፡ ቅዱስ ፡
ማር ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሰማዕት ። ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡
ወሬዛ ፡ ዘይትዔገል ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡
ወይሰርቅ ፡ ቊርባነ ፡ ቅዱስ ፡ ወይበልዖ ፡
ወደሞ፡ ክቡረ ፡ ይሰቲ ፡ እምውስተ ፡ ጽዋዕ ፡
ወይሰልብ ፡ አልባሰ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወያውዕዮ ፡
በእሳት ፡ ወይሣለቅ ፡ ላዕለ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስ
ቲያን።

፰፤ ወኮነ ፡ ማኅደሩ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ልዑል ፡
ይትረአዩ ፡ ሎቱ ፡ ካህናት ፡ እንዘ ፡ ይትለአኩ ።
ወአሐተ፡ ዕለተ ፡ ርእየ ፡ ርኅወ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ወመጽአ ፡ ተጽዒኖ ፡ በፈ
ረስ ፡ ወነጸረ ፡ ሥዕሎ ፡ ለቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ፡
ወነደፎ፡ በአኀፃ፡ ወተመይጠት፡ አሐቲ፡ ሐፅ፡
ወነደፈቶ ፡ እራኆ ፡ ወበዕፀብ ፡ መልሓ ፡ እም
እራኁ፡ወኢነገረ፡ለመኑሂ፡ዘንተ።

፱፤ ወበካልዕት ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ነቢሮ ፡ ዲበ ፡
መንበሩ ፡ ርእዮሙ ፡ ለካህናት ፡ ፀዊሮሙ ፡ አጸ
ርጊ ፡ እንዘ ፡ ይበውኡ ፡ ውስተ ፡ መቅደስ ። ወር
እየ ፡ ውስተ ፡ ጻሕል ፡ በግዐ ፡ ፀዓዳ ፡ እንዘ ፡ ይሰ
ክብ ፡ ወመልዕልቴሁ ፡ ይጼልል ፡ ርግብ ፡
ፀዓዳ። ወእምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ቅዳሴ ፡ ኮነ ፡
ውእቱ ፡ በግዕ ፡ ክፋለ ፡ በበመለያልይሁ ፡
ወርእዮሙ ፡ ለካህናት ፡ እንዘ ፡ ይትሜጠዉ ፡
ክፍለ ፡ እምሥጋሁ ፡ ወእምደም ፡ ዘውስተ ፡
ጽዋዕ ፡ ወአንከረ ፡ ጥቀ ፡ ወይቤ ፡ በልቡ ፡ ጥቀ ፡
መንክር፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአማን ፡
ክቡር ፡ ውእቱ ። ወርእየ ፡ ካዕበ ፡ እንዘ ፡
ይትመየጥ ፡ በግዕ ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ህላዌሁ ፡
ወእምዝ ፡ ወሪዶ ፡ እመንበሩ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡
አንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወነገሮሙ ፡
ለካህናት ፡ ኵሎ ፡ ዘርእየ ፡ ወሰሚያሙ ፡
ተፈሥሑ፡በእንተ፡ዝንቱ፡መንክር፡ግብር።

፲፤ ወበይእቲ ፡ ሌሊት ፡ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ወይተግህ ፡
አስተርአዮ ፡ ማር ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወውእቱ ፡
ተጽዒኖ ፡ ዲበ ፡ ፈረሱ ፡ ወይቤሎ ፡ ናሁ ፡
አሕሰምከ ፡ ላዕሌየ ፡ እስከ ፡ ረማህከ ፡ ሥዕልየ ፡
ወተሣለቀ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ፡ ንጉሠ፡
ስብሐት፡ወይእዜኒ፡ተመየጥ፡እምዕልወትከ፡
ወእመን፡በእግዚእ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡

ዕታት ፡ አለቃ ፡ በቴዎድሮስ ፡ ገዳም ፡
አጠገብ፡ በወንዝ ፡ ዳርቻ ፡ የሚኖር ፡ ነው ፡
ይህም ፡ ጐልማሳ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡
የሚቃወም ፡ ሁኖ ፡ ቅዱስ ፡ ቊርባንን ፡
በመስረቅ ፡ ኅብስቱን ፡ ይበላዋል ፡ የከበረ ፡
ደሙንም ፡ ከጽዋው ፡ ውስጥ ፡ ይጠጣል ፡ የመ
ሠዊያውንም ፡ ልብስ ፡ ገፎ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥ
ለዋል ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖትም ፡ ላይ ፡
ይዘብታል።

፰፤ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ከከፍታ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
ካህናት ፡ ሲያገለግሉ ፡ ይታዩት ፡ ነበር ። በአን
ዲትም ፡ ዕለት ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ተከፍቶ ፡ አየ ፡ በፈረስም ፡ ተቀምጦ ፡
መጣ ፡ የቅዱስ ፡ ቴዎድሮስንም ፡ ሥዕል ፡
ተመልክቶ ፡ በፍላፃዎች ፡ ወጋው ። አንዲ
ቱም፡ ፍላፃ ፡ ተመልሳ ፡ መሐል ፡ እጁን ፡
ነደፈችው ፡ በጭንቅም ፡ ከእጁ ፡ ላይ ፡
መዘዛት፡ይህንንም፡ለማንም፡አልነገረም።

፱፤ በሌላዪቱም ፡ ዕለት ፡ በወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡
ሳለ ፡ መሥዋዕትን ፡ ተሸክመው ፡ ወደ ፡
መቅደስ ፡ ሲገቡ ፡ ካህናትን ፡ አያቸው ፡
በጻሕሉም ፡ ውስጥ ፡ ነጭ ፡ በግ ፡ ተኝቶ ፡ ከበ
ላዩ ፡ ነጭ ፡ ርግብ ፡ ሲጋርደው ፡ በቅዳሴውም ፡
ፍጻሜ ፡ ያ ፡ በግ ፡ በየመለያያው ፡ የተከፋፈለ ፡
ሆኖ ፡ ካህናቱም ፡ ከተከፋፈለው ፡ ሥጋውን ፡
ሲቀበሉ ፡ ደሙንም ፡ ከጽዋው ፡ ውስጥ ፡
ሲቀበሉ ፡ አየ ፡ እጅግም ፡ አደነቀ ። በልቡም ፡
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡
ነው፡ በእውነትም ፡ የከበረ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡
አለ። ዳግመኛም ፡ ያ ፡ በግ ፡ ተመልሶ ፡ እንደ ፡
ቀድሞው ፡ ኑሮው ፡ ሕያው ፡ ሁኖ ፡ አየ፡
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከመቀመጫው ፡ ወርዶ ፡
ወደ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደጃፍ ፡ ሔዶ ፡
ያየውን ፡ ሁሉ ፡ ለካህናቱ ፡ ነገራቸው ፡
እነርሱም ፡ ሰምተው ፡ ስለዚህ ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡
ደስ ፡ አላቸው።

፲፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ተግቶ ፡ ሲጸልይ ፡ ሊቅ ፡
ቴዎድሮስ ፡ ተገለጠለት ፡ እርሱም ፡ በፈረሱ ፡
ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡
እነሆ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ሥዕሌን ፡ እስከ ፡ ወጋህ ፡
ድረስ ፡ ክፉ ፡ ሠራህ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡
ክርስቶስ፡ ሥጋ ፡ ላይም ፡ ዘበትክ ፡ አሁንም ፡
ከክህደትህ ፡ ተመልሰህ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ስብሐት፡ወዘንተ፡ብሂሎ፡ተሠወረ፡እምኔሁ።

፲፩፡ ወበሳኒታ ፡ ተጽዕነ ፡ ላዕለ ፡ ፈረሱ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ፡ኢየሩሳሌም፡ወቦአ፡ኀበ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሁ ፡ ወሰሚዖ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አእኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር። ወይቤሎ ፡ ለውእቱ ፡ እፈርህ ፡ አጥምቆተከ ፡ በቅድመ ፡ ሕዝብ ፡ ወባሕቱ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ ፈለገ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ይጼግወከ ፡ ዘያጠምቀከ ፡ ወሰሚዖ ፡ ውእቱ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወከዊኖ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ አስተርአየቶ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እመ ፡ ብርሃን ፡ ለቢሳ ፡ ልብሰ ፡ ሜላት ፡ ንጹሐ ፡ ወምስሌሃ ፡ ካልዕት ፡ ብእሲት ፡ ሥርጉተ ፡ ሜላት ፡ ወአንሥአቶ ፡ በእዴሃ ፡ ወትቤሎ ፡ ኢትኀዝን ፡ እስመ ፡ አነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌከ።

፲፪፡ ወጸቢሖ ፡ ሶበ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ፈለገ ፡ ዮርዳኖስ፡ ረከቦሙ ፡ ለ፪ቱ ፡ መነኰሳት ፡ ገዳማውያን ፡ ወእሙንቱ ፡ አጥመቅዎ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሰመይዎ ፡ እንጦንስሃ ፡ ወአልበስዎ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና፡ወአስኬማ፡ወፈነውዎ፡በሰላም፡ ወሖረ፡ሀገረ፡ደማስቆ፡ወቦአ፡ቤቶ።

፲፫፡ ወሶበ ፡ ነጸርዎ ፡ አብያጺሁ ፡ ወአዝማዲሁ ፡ ወይቤልዎ ፡ ምንትኑ ፡ አልባሲከ ፡ ወይቤሎሙ፡ክርስቲያናዊ፡አነ፡ወሶቤሃ፡አኀዝዎ፡ ወሰሐብዎ ፡ ውስተ ፡ አስኳት ፡ ወይዘብጥዎ ፡ እስከ ፡ አብጽሕዎ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ። ወአዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይደይዎ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ወነበረ ፡ ህየ ፡ ፲ወ፯ተ ፡ ለያልየ ፡ በፃማ ፡ ዐቢይ ፡ ወናሁ ፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ ላዕሌሁ ፡ ወሰምዐ ፡ ቃለ ፡ ዘይብል፡ኢትፍራህ፡ኦ፡እንጦንዮስ፡እስመ፡ ተደለወ፡ለከ፡አክሊል፡ወመጽኡ፡ኀቤሁ፡፪ አእሩግ ፡ ዘለብሱ ፡ ብርሃነ ፡ ወአንበሩ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ፡አክሊለ፡ብርሃን፡ወጸቢሖ፡ወሰድዎ፡ ውስተ፡ዐውድ፡ወመተርዎ፡ርእሶ፡በሰይፍ፡ ወሰቀልዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ወበሌሊት ፡ ወረደ ፡ ብርሃን ፡ ላዕሌሁ ። ወርእዮሙ ፡ አውረድዎ ፡ እምዕፅ ፡ ዐቀብት ፡ ወቀበርዎ ፡ ቅሩበ ፡

በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እመን ፡ አለው ፡ ይህንም ፡ ብሎ ፡ ከእርሱ ፡ ተሠወረ።

፲፩፡ በማግሥቱም ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ገብቶ ፡ ከእርሱ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሰምቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነው ፡ እርሱንም ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ አጠምቅህ፡ ዘንድ ፡ እፈራለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ሒድ ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስም ፡ የሚያጠምቅህን ፡ ይሰጥሃል ፡ አለው። እርሱም ፡ ሰምቶ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ሔዶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ የሌሊቱም ፡ እኩሌታ ፡ ሲሆን ፡ የብርሃን ፡ እናት ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ግምጃ ፡ ለብሳ ፡ ተገለጠችለት ፡ ከእርሷም ፡ ጋር ፡ በንጹሕ ፡ ልብስ ፡ የተሸለመች ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ በእጅዋም ፡ ይዛ ፡ አነሣችውና ፡ አትዘን ፡ እኔ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁና ፡ አለችው።

፲፪፡ ሲነጋም ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ገዳማውያን ፡ መነኰሳትን ፡ አገኛቸው ፡ እነርሱም ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አጠመቁት ። ስሙንም ፡ እንጦንስ ፡ ብለው ፡ ሰየሙት ፡ የምንኵስና ፡ ልብስ ፡ አስኬማንም ፡ አልብሰው ፡ በሰላም ፡ አሰናበቱት ፡ ወደ ፡ ደማስቆም ፡ ሔዶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ።

፲፫፡ ባልንጀሮቹና ፡ ወገኖቹም ፡ በአዩት ፡ ጊዜ ፡ የለበስከው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አሉት ፡ እኔ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ አላቸው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ይዘው ፡ በሜዳ ፡ ውስጥ ፡ እየጐተቱ ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ እስኪያደርሱት ፡ ይደበድቡት ፡ ነበር ። መኰንኑም ፡ ወደ ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ እንዲጨምሩት ፡ አዘዘ ፡ በታላቅ፡ ሥቃይም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ሌሊት ፡ በዚያ ፡ ኖረ ፡ እነሆ ፡ በላዩ ፡ ብርሃን ፡ ወረደ ፡ እንዲህም ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማ ፡ እንጦንዮስ ፡ ሆይ ፡ አክሊል ፡ ተዘጋጅቶልሃልና ፡ አትፍራ ፡ ብርሃንን ፡ የለበሱ ፡ ሁለት ፡ አረጋውያንም ፡ መጥተው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የብርሃን ፡ አክሊልን ፡ አኖሩ ፡ በነጋ ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ወስደው ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጡትና ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ። በሌሊትም ፡ በላዩ ፡ ብርሃን ፡ ወረደ ፡ ጠባቆችም ፡ አይተው ፡ ከዕንጨት ፡ ላይ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጤግሮስ፡ወአስተርአዩ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡እመቃብሪሁ። ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

አወረዱት፡ በጤግሮስም፡ አቅራቢያ፡ ቀበሩት፡ከመቃብሩም፡ድንቆች፡ተአምራቶች፡ተገለጡ፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ስሙየ፡እንጦኒ፡ረውሕ።ዘአስተርአየከ፡ክርስቶስ፡አምሳለ፡በግዕ፡የዋህ። ወመንፈስ፡ቅዱስ፡በርግብ፡እንዘ፡ክነፊሁ፡ስፉሕ።በእንተ፡ዝንቱ፡ኢያፍርሆ፡ለክሣድከ፡ሞቅሕ።ወኢያደንገፆ፡ፍጹመ፡አፈ፡ሰይፍ፡በሊሕ።

፲፬፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ አቡፋና፡እምብሔረ፡ግብጽ፡እምአድያመ፡እስሙናይን።

፲፭፡ ወዝንቱ፡ አብ፡ ዘይነብር፡ ውስተ፡ በዓት፡ ዘአልቦ፡ብርሃን፡ግሙራ፡ወይጸውም፡በበ፪ቱ፡ዕለት፡መብልዑኒ፡ወስቴሁኒ፡በመስፈርት፡ወይገብር፡ጸሎተ፡፭፻ተ፡በሌሊት፡ወበመዓልት፡ከማሁ።

፲፮፡ ወበአሐቲ፡ዕለት፡መጽኡ፡ኀቤሁ፡አኃው፡ከመ፡ የሐውጽዎ፡ ወነጥአ፡ ኀብስተ፡ ወአመ፡ረከበ፡፫ተ፡ኀብስተ፡አቅረበ፡ሎሙ፡ለ፷፡ዕደው፡ወእሉ፡በልዑ፡ወጸግቡ፡ወነበረ፡እንዘ፡ይገብር፡ተአምራተ፡ወይፌውስ፡ድውያነ።

፲፯፡ ወእምዝ፡መጽአ፡ኀቤሁ፡ቃል፡እምሰማይ፡ዘይብል፡አቡፋና፡ተርፈከ፡፲ወ፰ወሐለየ፡ቅዱስ፡አቡፋና፡ከመ፡ዐሥርት፡ወስምንቱ፡ዕለት፡ ወቆመ፡ እስከ፡ ይትፌጸማ፡ እሉ፡ ዕለታት።ወእምዝ፡ይቤ፡በልቡ፡፲ቱ፡ወ፰ቱ፡ሱባዔ፡ወቆመ፡ዘንተኒ፡ወዓዲ፡ይቤ፡ለእመ፡ኮነ፡ ፲ ወ ፰ አውራኀ፡ ወዘንተኒ፡ ፈጸመ፡ በቀዊም፡ዘእንበለ፡ጽርዓት።

፲፰፡ ወካዕበ፡ መጽአ፡ ቃል፡ ኀቤሁ፡ ዘይብል፡ አቡፋና፡ጽናዕ፡ወኃይል፡ይቤለከ፡እግዚአብሔር፡፲ወ፰ቱ፡ዓመት፡ይእቲ፡ ወሶቤሃ፡ ጸንዐ፡ወኀየለ።

፲፱፡ ወሀሎ፡ውስተ፡አፈ፡በዓቱ፡ነቅዐ፡ማይ፡ወወገረ፡ማሕቄ፡ውስቴቱ፡ወጸለለ፡ማሕቄ፡መልዕልተ፡ማይ፡በከመ፡ገብረ፡ኤልሳዕ፡ነቢይ።

፳፡ ወፈጸመ፡ ጾመ፡ ፵ዓ፡ ቅድስት፡ እንዘ፡ ኢይበልዕ፡ዘእንበለ፡በ፫ቱ፡ዕለታት።

፲፬፡ በዚችም፡ ዕለት፡ ከግብጽ፡ አገር፡ ከእስሙናይን፡ አውራጃ፡ የሆነ፡ የከበረ፡ አባት፡ አቡፋና፡አረፈ።

፲፭፡ ይህም፡አባት፡ከቶ፡ብርሃን፡በሌለበት፡ዋሻ፡ውስጥ፡ የሚኖር፡ ሁኖ፡ በየሁለት፡ ቀን፡ ይጾማል፡ የሚበላውም፡ የሚጠጣውም፡ በመለኪያ፡ተለክቶ፡ነው፡በሌሊትም፡በመዓልትም፡አምስት፡መቶ፡ጊዜ፡ይጸልያል።

፲፮፡ በአንዲትም፡ዕለት፡ወንድሞች፡ሊጐበኙት፡ወደርሱ፡መጡ፡እንጀራንም፡አጣ፡ሦስት፡እንጀራንም፡በአገኘ፡ጊዜ፡ለሃያ፡ሰዎች፡አቀረበላቸው፡እነርሱም፡በልተው፡ጠገቡ፡ተአምራትንም፡እያደረገ፡በሽተኞችንም፡እየፈወሰ፡ኖረ።

፲፯፡ ከዚህም፡በኋላ፡እንዲህ፡የሚል፡ቃል፡ከሰማይ፡ ወደርሱ፡ መጣ፡ አቡፋና፡ ሆይ፡ ዐሥራ፡ስምንት፡ቀረህ፡የከበረ፡አቡፋናም፡ዐሥራ፡ስምንት፡ዕለታት፡እንደሆኑ፡አስቦ፡እሊህ፡ ዕለቶች፡ እስቲፈጸሙ፡ ቆመ፡ ከዚህም፡በኋላ፡ሱባዔዎች፡ናቸው፡ብሎ፡ይህንንም፡በመቆም፡ፈጸመ፡እንደ፡ገና፡ወሮች፡ይሆናሉ፡ቢሆኑስ፡ብሎ፡ይህንንም፡በመቆም፡ሳያጓድል፡አደረሰ።

፲፰፡ ዳግመኛም፡እንዲህ፡የሚል፡ቃል፡ወደርሱ፡መጣ፡ አቡፋና፡ ሆይ፡ ዐሥራ፡ ስምንት፡ ዓመት፡ናትና፡ጽና፡በርታ፡አለህ፡እግዚአብሔር፡ አለው፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ ፈጽሞ፡ ጸና።

፲፱፡ በዋሻው፡ ደጃፍ፡ የውኃ፡ ምንጭ፡ ነበረ፡ ምሳርንም፡ ወረወረበት፡ ምሳሩም፡ ነቢይ፡ ኤልሳዕ፡ እንዳደረገው፡ በውኃ፡ ላይ፡ተንሳፈፈ።

፳፡ የከበረች፡የአርባ፡ቀንን፡ጾም፡ከሦስት፡ቀኖች፡በቀር፡ሳይበላ፡ፈጸመ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩፤ ወሶበሂ ፡ ይበልዕ ፡ ወይዴቅስ ፡ ኮነ ፡ ይፀወነ፡ ዲበ ፡ አረፍት ፡ ወተጋደለ ፡ ከመዝ ፡ እስከ ፡ ኮና፡እገሪሁ፡ከመ፡አእጋረ፡ነጌ።

፳፪፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ናሁ ፡ ኀለፈ ፡ ዓለም ፡ ወሶበ ፡ ተሰአልዎ ፡ ቴዎ ዶስዮስ፡ንጉሥ፡አዕረፈ፡ይቤ። ወበአሐቲ፡ ዕለት ፡ ኀደረ ፡ እንግዳ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ፩ዱ ፡ ቀሲስ፡ዘምስሌሁ፡፫፻ዲናረ፡ወርቅ፡ወሶበ፡ ኖመ ፡ ቀተሎ ፡ ቀሲስ ፡ በእንተ ፡ ንዋዩ ፡ ወወሰዶ ፡ ወገደፎ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ፩ መነኮስ ፡ ወሶበ ፡ ነገርዎ ፡ አኃው ፡ ለቅዱስ ፡ አቡፋና ፡ ወሀቦሙ፡ ቆብዖ ፡ ከመ ፡ ይገርዎ ፡ ላዕለ ፡ ምውት ፡ ወወገሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ምውት ፡ ወነገሮሙ ፡ ቀሲስ ፡ ከመ ፡ ቀተሎ ፡ በእንተ ፡ ንዋዩ ፡ ወአንከሩ ፡ ጥቀ ፡ ወአሐተ፡ዕለተ፡እንዘ፡ይመጽእ፡ኀቤሁ፡፩ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይትባረክ ፡ እምኔሁ ፡ ሞተ ፡ ወልዱ ፡ በፍኖት ፡ ወፀዊሮ ፡ ወልዶ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ አቡፋና ፡ ወሰጊዶ ፡ ቅድሜሁ ፡ ተባረከ ፡ እምኔሁ ፡ ወተመይጠ ፡ ሶቤሃ ፡ ተን ሥአ፡ሕፃን፡ወተለዎ፡ለአቡሁ።

፳፫፤ወሶበ፡ተፈጸመ፡ሎቱ፡፲ወ፰ዓመት፡እምአመ፡ ቆመ ፡ አእመረ ፡ ዕረፍቶ ፡ ወተመጠወ ፡ ቍር ባነ ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡ ወአድነነ ፡ ርእሶ፡ወመጠወ፡ነፍሶ፡ውስተ፡እዴሁ፡ለእ ግዚአብሔር ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፳፩፤ ሲበላም፡ሲያንቀላፋም፡ግድግዳ፡ተጠግቶ፡ ነው ፡ እግሮቹም ፡ እንደዝሆን ፡ እግር ፡ እስከ ሚሆኑ፡እንዲህ፡ተጋደለ።

፳፪፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እነሆ፡ዓለም፡አለፈ፡አላቸው፡በጠየቁትም፡ ጊዜ፡ንጉሥ፡ቴዎዶስዮስ፡ሞተ፡አለ፡በአን ዲትም፡ዕለት፡ሦስት፡መቶ፡የወርቅ፡ዲናር፡ የያዘ ፡ እንግዳ ፡ በአንድ ፡ ቄስ ፡ ቤት ፡ አደረ ፡ በተኛ ፡ ጊዜ ፡ ስለ፡ ገንዘቡ ፡ ቄሱ ፡ ገደለውና ፡ ወስዶ ፡ ከአንድ ፡ መነኰሴ ፡ ደጅ ፡ ጣለው ፡ ለቅዱስ፡አቡፋናም፡በነገሩት፡ጊዜ፡ከሟቹ፡ ላይ ፡ እንዲጥሉበት ፡ ቆቡን ፡ ሰጣቸው ፡ ሲጥ ሉበትም ፡ ሟቹ ፡ ተነሣ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ ቄሱ ፡ እንደ፡ገደለው፡ነገራቸው፡እጅግም፡አደነቁ። በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቡራኬ ፡ ሊቀበል ፡ ወደርሱ ፡ ሲመጣ ፡ ልጁ ፡ በጒዞ ፡ ላይ፡ሞተ፡ልጁንም፡ተሸክሞ፡ወደ፡ቅዱስ፡ አቡፋና ፡ ሔደ ፡ በፊቱም ፡ ሰግዶ ፡ ተባርኮ ፡ ተመለሰ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሞተው ፡ ብላቴና ፡ ተነሥቶ፡አባቱን፡ተከተለው።

፳፫፤ ከቆመ ፡ ጀምሮ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንቱ ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ፡ጊዜ፡ዕረፍቱን፡አውቆ፡ቅዱስ፡ ቍርባንን ፡ ተቀበለ ፡ ወደ ፡ መኖሪያውም ፡ ሒዶ፡ራሱን፡ዘንበል፡አድርጎ፡ነፍሱን፡በእ ግዚአብሔር፡እጅ፡ሰጠ። በረከቱም፡ከእኛ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለቊመተ ፡ አቡፋና ፡ ዘአልቦ ፡ ኑታጌ ። እስከ ፡ ተመሰለ ፡ እግሩ ፡ ከመ ፡ እግረ ፡ ነጌ ። እንዘ ፡ ቤተ ፡ ጽልመት ፡ ይነብር ፡ ዘምስለ ፡ ብዙኀ ፡ ድግዳጌ ። ኮነ ፡ ተሐራሚ ፡ ወኮነ ፡ ሐጋጌ ። ብርሃነ ፡ ሰማይ ፡ ኢይርአይ ፡ ወዘምድር፡ጽጌ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ፡አመ፡፳ወ፮ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡ አዕረፈ ፡ ጻድቅ ፡ ነቢይ ፡ ሆሴዕ ፡ ዘይሰመይ ፡ ካዕበ፡ዖዝያ፡ወዝንቱ፡ነቢይ፡ተነበየ፡በመዋ ዕሊሆሙ፡ለ፬ነገሥተ፡ይሁዳ።እሉኒ፡ዖዝያን፡ ወኢዮአታም፡ወአካዝ፡ወሕዝቅያስ።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ዖዝያ ፡ ይባል ፡ የነ በረ ፡ ዕውነተኛ ፡ ነቢይ ፡ ሆሴዕ ፡ አረፈ ። ዳግ መኛም ፡ ይህ ፡ ነቢይ ፡ በአራቱ ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥ ታት ፡ ዘመን ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ። እሊህም ፡ ዖዝያን፡ኢዮአታም፡አካዝ፡ሕዝቅያስ፡ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፪፡ ወተናገረ፡በትንቢቱ፡ምግባራተ፡መንክራተ፡
ወገሠጾሙ፡ለደቂቀ፡እስራኤል፡ወሰመዮሙ፡
ውሉደ፡ ዘማ፡ ወአጠየቆሙ፡ ከመ፡ እግዚአ
ብሔር፡ኢይመይጥ፡መዓቶ፡እምኔሆሙ።

፫፡ ወይቤ፡ ለእመ፡ ኮነ፡ ኍልቆሙ፡ ለደቂቀ፡
እስራኤል፡ ከመ፡ ኆፃ፡ ባሕር፡ ዘኢይሰፈር፡
ወዘኢይትኌለቍ፡ ኢይተርፍ፡ እምኔሆሙ፡
ዘእንበለ፡ኅዳጥ።

፬፡ ወተነበየ፡ በእንተ፡ አሚኖቶሙ፡ ለአሕዛብ፡
በእግዚአብሔር፡ወይቤ፡እስመ፡አነ፡እጼው
ዖሙ፡ ለእለ፡ ኢኮኑ፡ ሕዝብየ፡ ወእሙንቱ፡
ይሰምዑኒ።

፭፡ ወተነበየ፡ካዕበ፡በእንተ፡ሕማማቲሁ፡ለመድ
ኃኒነ፡ወድኅነትነ፡በደሙ፡ክቡር፡ወበእንተ፡
ትንሣኤሁ፡ወይቤ።

፮፡ እስመ፡ ውእቱ፡ ቀሠፈነ፡ ወይፌውሰነ፡
ወውእቱ፡ አቍሰለነ፡ ወይሜርየነ፡ ወያሐ
ይወነ፡ በሠኑይ፡ መዋዕል፡ ወአመ፡ ሣለስት፡
ዕለት፡ ንትነሣእ፡ ወነሐዩ፡ በቅድሜሁ፡
ናእምር፡ ወንዴግኖ፡ ለእግዚአብሔር። ወተ
ነበየ፡ በእንተ፡ ሥዕረተ፡ ሥልጣኑ፡ ለሞት፡
ወተመውዖቱ፡ ለሲኦል፡ ወይቤ፡ አይቴ፡
ውእቱ፡ ቀኖትከ፡ ሞት፡ ወአይቴ፡ ሙዓትከ፡
ሲኦል። ወነበረ፡ መጠነ፡ ፸ ዓመት፡ እንዘ፡
ይትኔበይ፡ወአዕረፈ፡በርሥእ፡ሠናይ።

፯፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ወበረከቱ፡
ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፪፡ በትንቢቱም፡ ድንቆች፡ ሥራዎችን፡ ተናገረ፡
የእስራኤልንም ልጆች፡ ገሠጻቸው፡ የአመ
ንዝራ፡ልጆች፡ብሎም፡ጠራቸው፡እግዚአብ
ሔርም፡ ቍጣውን፡ ከእርሳቸው፡ እንደማይ
መልስ፡አስረዳቸው።

፫፡ እንዲህም፡አለ፡የእስራኤል፡ልጆች፡ቍጥራ
ቸው፡ እንደማይሠፈርና፡ እንደማይቈጠር፡
የባሕር፡አሸዋ፡ቢሆን፡ከጥቂት፡በቀር፡አይተ
ርፍም፡አለ።

፬፡ ስለ፡ አሕዛብም፡ በእግዚአብሔር፡ ማመን፡
ተናገረ፡እንዲህም፡አለ፡እኔ፡ወገኖቼ፡ያልሆ
ኑትን፡ እጠራቸዋለሁ፡ እነርሱም፡ ይሰሙ
ኛል።

፭፡ ዳግመኛም፡ ስለ፡ መድኃኒታችን፡ መከራ፡
መቀበልና፡ በከበረ፡ ደሙ፡ ስለ፡ መዳናችን፡
ስለ፡ትንሣኤውም፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናገረ።

፮፡ እሱ፡ በመከራ፡ ገርፎ፡ ይድነናል፡ እርሱም፡
በመከራ፡ አቍስሎ፡ ይቅር፡ ይለናል፡ ሲያድ
ነንም፡ በሁለተኛው፡ ቀን፡ ነው፡ በሦስተ
ኛውም፡ ቀን፡ ድነን፡ በሱ፡ ፊት፡ እንነሣለን፡
እግዚአብሔርንም፡ አውቀን፡ እንከተለው፡
ዘንድ፡ ስለ፡ ሞት፡ ሥልጣን፡ መሻር፡ ስለ፡
መቃብርም፡ መሸነፍ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡
ትንቢት፡ ተናገረ፡ ሞት፡ ይዘህ፡ ማስቀረትህ፡
መቃብርስ፡ ድል፡ መንሳትህ፡ ወዴት፡ ነው፡
ትንቢትን፡ እየተናገረ፡ ሰባ፡ ዓመት፡ ያህል፡
ኑሮ፡ በበጎ፡ ሽምግልና፡ አረፈ።

፯፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ በረከ
ቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለሆሴዕ፡ምጽአተ፡ክርስቶስ፡እንዘ፡ይሰብክ።በቃለ፡ትንቢት፡ቡሩክ።የኀሥሥዎ፡ይቤ፡ለእ
ግዚአብሔር፡አምላክ።እንበለ፡ንጉሥ፡ወኢ፡መልአክ።እምድኅረ፡ነበሩ፡እስራኤል፡በበክ።

፰፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ኮኑ፡ ሰማዕተ፡ ቅዱሳን፡ ሳዶቅ፡
ወእለ፡ምስሌሁ፡፳፻ወ፰ነፍስ።

፱፡ ወለዝንቱ፡ ቅዱስ፡ ሳዶቅ፡ ኃሠሦ፡ብርህም፡
ንጉሠ፡ ፋርስ፡ ከመ፡ ይስግድ፡ ለፀሐይ፡
አውሥአ፡ ቅዱስ፡ ወይቤሎ፡ አንሰ፡ ኢወጻ
እኩ፡እምከርሠ፡እምየ፡ከመ፡እስግድ፡ለዛቲ፡
ፀሐይ፡ እንተ፡ ታስተርኢ፡ አላ፡ ለፈጣሪሃ፡
አውሥአ፡ብርህም፡ንጉሥ፡ወይቤሎ፡ለዛቲ፡
ፀሐይ፡ ሀለዋኑ፡ አምላክ፡ ወይቤሎ፡ ቅዱስ፡

፰፡ በዚችም፡ ዕለት፡ የከበሩ፡ ሳዶቅና፡ ከእርሱ፡
ጋር፡የሆኑ፡ሁለት፡ሺህ፡ስምንት፡ሰዎች፡በሰ
ማዕትነት፡ሞቱ።

፱፡ ይህንንም፡የከበረ፡ሳዶቅን፡ለፀሐይ፡ይሰግድ፡
ዘንድ፡ የፋርስ፡ ንጉሥ፡ ብርህም፡ ፈለገው፡
ቅዱሱም፡ ለፈጣሪዋ፡ እንጂ፡ ለዚች፡
ለምትታይ፡ ፀሐይ፡ ልሰግድ፡ ከእናቴ፡
ማሕፀን፡ አልወጣሁም፡ ብሎ፡ መለሰለት።
ብርህም፡ንጉሥም፡መልሶ፡ለዚች፡ፀሐይ፡አም
ላክ፡አላትን፡አለው፡ቅዱስ፡ሳዶቅም፡ዓለሙን፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳዶቅ፡እስመ፡ክርስቶስ፡ፈጣሬ፡ኵሉ፡ዓለም፡ አምላክ፡ውእቱ፡ወአዘዘ፡ንጉሥ፡ከመ፡ ይምትሩ፡ በሰይፍ፡ ርእሶ፡ ለቅዱስ፡ ሳዶቅ፡ ወቆመ፡ቅዱስ፡ሳዶቅ፡ወጸለየ፡ኀበ፡እግዚአ ብሔር፡ ወእምዝ፡አድነነ፡ርእሶ፡ወመተርዎ፡ አሚሃ፡ ወረደ፡ ብርሃን፡ ላዕሌሁ፡ ወእለ፡ ሀለዉ፡ህየ፡ኵሎሙ፡ርእዮሙ፡ጸርሑ፡እንዘ፡ ይብሉ፡ንሕነ፡ኵልነ፡ክርስቲያን፡ወነአምን፡ በአምላኩ፡ለቅዱስ፡ሳዶቅ፡ወአዘዘ፡ንጉሥ፡ ይምትርዎሙ፡በአስይፍት፡አርእስቲሆሙ፡ ለኵሎሙ፡ወነሥኡ፡አክሊለ፡ስምዕ፡በመን ግሥተ፡ ሰማያት፡ ወእሉ፡ ፳፻ወ፰ ነፍስ። በረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ወስብሐት፡ለእ ግዚአብሔር፡ አሜን።

ሁሉ፡ የፈጠረ፡ ክርስቶስ፡ አምላክ፡ ነው፡ አለው። ንጉሡም፡ የቅዱስ፡ ሳዶቅን፡ ራስ፡ በሰይፍ፡እንዲቆርጡ፡አዘዘ፡የከበረ፡ሳዶቅም፡ ቁሞ፡ ወደ፡እግዚአብሔር፡ ጸለየ፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ራሱን፡ዘንበል፡አድርጎ፡ቆረጡት። ያን፡ ጊዜ፡ከሰማይ፡ብርሃን፡በላዩ፡ወረደ፡ከዚያ፡ ያሉትም፡ሁሉ፡አይተው፡እኛ፡ሁላችንም፡ በቅዱስ፡ ሳዶቅ፡ አምላክ፡ የምናምን፡ ክርስ ቲያን፡ነን፡ብለው፡ጮኹ፡ንጉሡም፡ሁሉ ንም፡ ራሶቻቸውን፡ በሰይፍ፡ እንዲቆርጡ፡ አዘዘ፡ የሰማዕትነት፡ አክሊልንም፡ በመን ግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበሉ፡ ቊጥራቸውም፡ ሁለት፡ሺህ፡ስምንት፡ነፍስ፡ናቸው። በረከታቸውም፡ከኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአብ ሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለሳዶቅ፡ለእግዚአብሔር፡ሰማዕቱ።እንተ፡ተከለለ፡ዮም፡ለንጉሠ፡ፋርስ፡በመጥባሕቱ።ሶበ፡ ነጸሩ፡ብርሃነ፡ ዘወረደ፡ጊዜ፡ዕረፍቱ። ወሰላም፡ለሰማዕታት፡ምስሌሁ፡ዘሞቱ። እስራ፡ምእት፡ወዓዲ፡ ስምንቱ።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፳ወ፯ ለየካቲት፡ በዛቲ፡ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡አንስጣስዮስ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡አንጾኪያ፡በመዋዕሊሁ፡ለቈ ስጠንጢኖስ፡ ንጉሥ፡ ዘየዓቢ፡ ዘመልዐ፡ ትምህርቱ፡ዓለመ።

፪፤ ወሶበ፡ ተጋብኡ፡ማኅበረ፡ቅዱሳን፡አበው፡ በሀገረ፡ኒቅያ፡ኮነ፡ዝንቱ፡አብ፡፩ እምሊቃ ውንተ፡ ዝንቱ፡ ማኅበር፡ ወተሰነዓዉ፡ ማኅበር፡ወአውገዝዎ፡ወሰደድዎ፡ለአርዮስ፡ ምስለ፡ አብያጺሁ፡ እሉ፡ እሙንቱ፡ አውሳ ብዮስ፡ ዘቂሣርያ፡ ወአውሳብዮስ፡ ዘኒቆ ምድያ፡ወአርናሲስ፡ወእሉ፡እሙራን፡በኀበ፡ ኵሎን፡አብያተ፡ክርስቲያናት።

፫፤ ወሶበ፡ገብኡ፡እሉ፡ቅዱሳን፡አበው፡በበሐው ርቲሆሙ፡እምድኅረ፡ሠርዑ፡ቀኖና፡ወጽኡ፡ እሉ፡ምቱራን፡እምሢመተ፡ኤጲስቆጶስና፡ ተመሰሉ፡ ከመ፡ ዘየሐውሩ፡ ኀበ፡ ኢየሩ

* * *

፩፤ አንድ፡ አምላክ፡ በሆነ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ሃያ፡ሰባት፡ በዚች፡ ቀን፡ በታላቁ፡ ንጉሥ፡ በቈስጠን ጢኖስ፡ዘመን፡የከበረ፡አባት፡የአንጾኪያ፡ አገር፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ትምህርቱ፡ በዓለም፡ የመላ፡አንስጣስዮስ፡አረፈ።

፪፤ የከበሩ፡ አባቶችም፡ በኒቅያ፡ ከተማ፡ የአን ድነት፡ስብሰባ፡በአደረጉ፡ጊዜ፡በዚህ፡ጉባኤ፡ ከተሰበሰቡት፡ ሊቃውንት፡ አንዱ፡ እርሱ፡ ነው፡ በዚህም፡ ጉባኤ፡ ተስማምተው፡ አርዮስን፡ ከባልንጀሮቹ፡ ጋር፡ አውግዘው፡ ለይተውታል፡ባልንጀሮቹም፡የቂሣርያ፡አው ሳብዮስ፡ የኒቆምድያ፡ አውሳብዮስና፡ አርና ሲስ፡ ናቸው። እሊህም፡ በአብያተ፡ ክርስቲ ያናት፡ሁሉ፡ታውቀዋል።

፫፤ እሊህም፡ የከበሩ፡ አባቶች፡ ሥርዓትን፡ ሠርተው፡ወደየሀገራቸው፡በተመለሱ፡ጊዜ፡ እሊህ፡ከኤጲስቆጶስነት፡ሹመት፡የተሻሩት፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ የሚሔዱ፡ መስለው፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳሌም፡ወቦኡ፡ሀገረ፡አንጾኪያ፡ወተጋብኡ፡
ኀበ፡እሐቲ፡ብእሲት፡ዘማ፡ወተካየድዋ፡ከመ፡
የሀብዋ፡ንዋየ፡ብዙኀ፡ወመሀርዋ፡ከመ፡ትባእ፡
ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወትትናገር፡ላዕለ፡
ቅዱስ፡አብ፡አንስጣስዮስ፡ወትበሎሙ፡ለካህ
ናት፡ወሕዝብ፡ከመ፡ዝንቱ፡አብ፡ዘመወ፡ምስ
ሌሃ፡ወወልድኒ፡ዘወለደቶ፡ዘዚአሁ፡ውእቱ።

፲፩ ወይቤልዋ፡ሕዝብ፡አንቲሰ፡ሐሳዊት፡ወተና
ገርኪ፡ሐሰተ፡ላዕለ፡ዝንቱ፡አብ፡ቅዱስ፡
ኢነአምን፡ቃለኪ፡ዘእንበለ፡ትምሐሊ፡
በወንጌል፡ቅዱስ፡ወይእቲ፡መሐለት፡
በሐሰት፡በእንተ፡ፍቅረ፡ንዋይ፡ወእምዝ፡
ነገርዎ፡ለንጉሥ፡ወሰደድዎ፡እመንበረ፡
ሢመቱ፡ኀበ፡ሀገረ፡አጥራክያ፡ወአዕረፈ፡
ባቲ፡በስደት።

፲፪ ወባሕቱ፡አሌ፡ሎሙ፡ለእሙንቱ፡ዐላውያን፡
እስመ፡ፈለጠዎ፡ለወልደ፡እግዚአብሔር፡
እምባሕርየ፡መለኮቱ፡ወረሰይዎ፡ፍጡረ፡ወለ
ዝንቱኒ፡አብ፡ቅዱስ፡አውጽእዎ፡እመንበረ፡
ሢመቱ፡በጕሕሉት፡በከመ፡መሀሮሙ፡
አቡሆሙ፡ሰይጣን፡ወኮኑ፡ሱቱፋነ፡ምስለ፡
ዘማ።

፲፫ ዳዕሙ፡ኢተዐወረ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡
እምድኅረ፡ሰደድዎ፡ለዝንቱ፡አብ፡ደወየት፡
ይእቲ፡ዘማ፡ደዌ፡ዕፁበ፡ወተመንደበት፡
ብዙኀ፡ወቀርበት፡ለመዊት፡ወለበወት፡
አሚሃ፡ከመ፡ዝንቱ፡ዘበጽሐ፡በእንተ፡
ዘመሐለት፡በሐሰት፡በወንጌል፡ቅዱስ፡ወተ
አመነት፡አበሳሃ፡በቅድመ፡ኵሎሙ፡ሰብአ፡
አንጾኪያ፡ወትቤሎሙ፡እስመ፡ቅዱስ፡አንስ
ጣስዮስ፡ንጹሕ፡ውእቱ፡እምዝሙት፡ዳዕሙ፡
ዐላውያን፡ወሀቡኒ፡ንዋየ፡ብዙኀ፡ወረሰዩኒ፡
እትናገር፡ሐሰተ፡ላዕሌሁ፡ወእምሐል፡
በሐሰት፡በወንጌል፡ቅዱስ።

፲፬ ወሶበ፡ሰምዑ፡ተአምኖታ፡ኀዘኑ፡ፈድፋደ፡
ኵሎሙ፡ሰብአ፡ሀገረ፡አንጾኪያ፡ወኮኑ፡
ካህናት፡ዘይዜክርዎ፡ስሞ፡በጊዜ፡ጸሎት፡
ወቅዳሴ፡ወወደሶ፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡
ወቃላተ፡ብዙኃተ፡ደረሰ፡በእንቲአሁ፡
በዕለተ፡ተዝካሩ።

፲፭ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡
ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡አብ፡ወበረከቱ፡

ወጡ፡ ወደ፡አንጾኪያም፡ከተማ፡ገብተው፡
ከአንዲት፡አመንዝራ፡ሴት፡ዘንድ፡
ተሰበሰቡ፡ብዙ፡ገንዘብም፡ሊሰጧት፡ቃል፡
ገቡላት፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡እንድትገባ፡
ይህ፡አባት፡ከእርሷ፡ጋር፡እንዳመነዘረ፡የወለ
ደችውም፡ልጅ፡የእርሱ፡እንደሆነ፡በዚህ፡
ቅዱስ፡አባት፡አንስጣስዮስ፡ላይ፡ለካህናቱና፡
ለሕዝቡ፡እንድትናገር፡አስተማሩዋት።

፲፩ ሕዝቡም፡እንዲህ፡አሏት፡አንቺ፡ሐሰተኛ፡
ነሽ፡በዚህ፡ቅዱስ፡አባትም፡ላይ፡ሐሰትን፡
ተናግረሻል፡በከበረ፡ወንጌል፡ካልማልሽ፡
በቀር፡ቃልሽን፡አንቀበልም፡አሏት፡
እርሷም፡ስለ፡ገንዘብ፡ፍቅር፡በሐሰት፡
ማለች። ከዚህም፡በኋላ፡ለንጉሥ፡ነግረው፡
ከመንበረ፡ሢመቱ፡ወደ፡አጥራክያ፡ደሴት፡
አሳደዱት፡በስደትም፡ሳለ፡በርሷ፡አረፈ።

፲፪ ነገር፡ግን፡ለእሊህ፡ከሀድያን፡ወዮላቸው፡የእ
ግዚአብሔርን፡ልጅ፡ከመለኮቱ፡ባሕርይ፡
ለይተው፡ፍጡር፡ነው፡ብለውታልና፡
ይህንንም፡ንጹሕ፡አባት፡ሰይጣን፡
አባታቸው፡እንዳስተማራቸው፡ከአመንዝራ፡
ጋር፡አንድ፡ሁነው፡በተንኰል፡ከመንበረ፡
ሢመቱ፡አውጥተውታልና።

፲፫ እግዚአብሔር፡ግን፡ቸለል፡አላለም፡ይህን፡
አባት፡ከአሳደዱት፡በኋላ፡ያቺ፡አመንዝራ፡
ሴት፡ጭንቅ፡በሆነ፡ደዌ፡ተይዛ፡ብዙ፡
ተሠቃየች፡ለሞትም፡ተቃረበች፡ያን፡
ጊዜም፡ይህ፡ሁሉ፡የደረሰባት፡በከበረ፡
ወንጌል፡በሐሰት፡ስለማለች፡እንደሆነ፡ተገነ
ዘበች፡በአንጾኪያም፡ሰዎች፡ሁሉ፡ፊት፡
በደሏን፡አመነች፡እንዲህም፡አለቻቸው፡
ይህ፡ቅዱስ፡አንስጣስዮስ፡ከዝሙት፡ንጹሕ፡
ነው፡እነዚያ፡ከሀድያን፡ብዙ፡ገንዘብ፡
ሰጥተውኝ፡በእርሱ፡ላይ፡ሐሰት፡እንድናገር፡
በከበረ፡ወንጌልም፡በሐሰት፡እንድምል፡
አደረጉኝ፡እንጂ።

፲፬ የአንጾኪያ፡አገር፡ሰዎችም፡ኃጢአቷን፡
ማመኗን፡በሰሙ፡ጊዜ፡እጅግ፡አዘኑ፡
ካህናቱም፡በጸሎትና፡በቅዳሴ፡ጊዜ፡ስሙን፡
የሚያነሱ፡ሆኑ፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅም፡አመ
ሰገነው፡በመታሰቢያውም፡ቀን፡ስለርሱ፡
ብዙ፡ቃላትን፡ደረሰ።

፲፭ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ፡አባት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከቱም፡

www.ethiopianorthodox.org

ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም፡እብል፡አንስጣስዮስሃ፡ፍጹመ።ትምህርታቲሁ፡ዘመልዐ፡ኵሎ፡ዓለመ።እኩያን፡ዕደው፡እለ፡ተዓጽፉ፡መርገመ።ነገረ፡ሐሰት፡ላዕሌሁ፡እንዘ፡ይነቡ፡ሕሱመ።ኀበ፡ሰደድዎ፡አዕረፈ፡ወኖመ።

፱፡ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካረ፡ስቅለቱ፡ለመድኃኒነ፡ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

* * *

፩፡በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩
አምላክ፡አመ፡፳ወ፰ለየካቲት፡በዛቲ፡ዕለት፡
ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡ቴዎድሮስ፡ሮማዊ፡
ዝንቱኒ፡ኮነ፡እምሀገ፡ ኣስጢር፡እምደወለ፡
እስያ፡በመዋዕሊሆሙ፡ለነገሥት፡መክሲ
ሞስ፡ወመክስምያኖስ።

፪፡ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡አስተዋደይዎ፡ሰብእ፡ኀበ፡
ነገሥት፡ከመ፡ውእቱ፡ኢይሰነዐው፡
በአምልኮ፡አማልክት፡ወጸውዕዎ፡ሶቤሃ፡
ወይቤልዎ፡ለምንት፡ኢትሠውዕ፡ለአማ
ልክት፡አውሥአ፡ወይቤሎሙ፡አንሰ፡ክርስ
ቲያናዊ፡ወኢያመልክ፡ባዕደ፡ዘእንበለ፡
እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ሕያው።

፫፡ወይቤሎ፡ንጉሥ፡ወልደ፡በርብዮስጦስ፡
ለእመ፡አንተ፡ተቀነይከ፡ለአማልክትየ፡
እሠይመከ፡ወእሬስየከ፡ሊቀ፡ሐራ፡ወላዕለ፡
ኵሎሙ፡መኳንንትየ፡ወእሁበከ፡ወርቀ፡
ወብሩረ፡ብዙኀ፡ወአልባሰ፡ክቡራተ።
ወይቤሎ፡ቅዱስ፡ቴዎድሮስ፡ወርቅከ፡
ወብሩርከ፡ይኩንከ፡ለሀጕል፡አንሰ፡ሊቅ፡
ወባዕል፡በኀበ፡ንጉሥየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ወልደ፡እግዚአብሔር፡ሕያው።

፬፡ወይቤሎ፡ንጉሥ፡ቦኑ፡ለአምላክከ፡ወልድ፡
አውሥአ፡ወይቤሎ፡ቅዱስ፡ቴዎድሮስ፡እወ፡
በአማን፡ቦቱ፡ወልድ፡እምባሕርየ፡መለኮቱ፡
ዘፈጠረ፡ምስሌሁ፡ኵሎ፡ዓለመ፡ወይቤሎ፡
ንጉሥ፡ለእመ፡አእመርናሁ፡ለአምላክከ፡
ንክልኑ፡ረኪቦቶ፡ወይቤሎ፡ቅዱስ፡ቴዎድ
ሮስ፡ለእመ፡ተመየጥከ፡ኀቤሁ፡ትከውን፡

፱፡ በዚችም፡ዕለት፡የመድኃኒታችን፡የስቅለቱ፡መታሰቢያ፡ነው፡ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ይኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

* * *

፩፡ አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የካቲት፡ሃያ፡
ስምንት፡በዚች፡ዕለት፡በነገሥታት፡መክሲ
ሞስና፡መክስምያኖስ፡ዘመን፡ሮማዊ፡ቅዱስ፡
ቴዎድሮስ፡በሰማዕትነት፡አረፈ።እርሱም፡
ከእስያ፡አውራጃ፡አስጢር፡ከሚባል፡አገር፡
ነው።

፪፡ይህንንም፡ቅዱስ፡በነገሥታት፡ዘንድ፡አማል
ክትን፡በማምለክ፡እርሱ፡እንደማይስማማ፡
ወነጀሉት፡በዚያንም፡ጊዜ፡አስጠርተው፡
ለአማልክት፡ለምን፡አትሰግድም፡አሉት፡
እርሱም፡እኔ፡ክርስቲያን፡ነኝ፡ከሕያው፡እግ
ዚአብሔር፡ልጅ፡ከጌታዬ፡ከኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡በቀር፡ሌላ፡አላመልክም፡ብሎ፡
መለሰላቸው።

፫፡ የበርብዮስጦስ፡ልጅ፡ንጉሥም፡ለአማል
ክቶቼ፡ብትገዛ፡በጭፍራዎቼና፡በመኳን
ንቶቼ፡ሁሉ፡ላይ፡አለቃ፡አድርጌ፡እሾም
ሃለሁ፡ብዙ፡ወርቅና፡ብር፡የከበሩ፡ልብሶ
ችንም፡እሰጥሃለሁ፡አለው፡ቅዱስ፡ቴዎድ
ሮስም፡ወርቅህና፡ብርህ፡ለጥፋት፡ይሁንህ፡
እኔስ፡በንጉሤ፡በሕያው፡እግዚአብሔር፡
ልጅ፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ባለጸጋና፡አለቃ፡
ነኝ፡አለው።

፬፡ንጉሡም፡ለአምላክህ፡ልጅ፡አለውን፡አለው፡
የከበረ፡ቴዎድሮስም፡አዎን፡ከመለኮቱ፡
ባሕርይ፡የተገኘ፡ከእርሱ፡ጋር፡ዓለምን፡
የፈጠረ፡በእውነት፡ልጅ፡አለው፡ብሎ፡
መለሰለት፡ንጉሡም፡አምላክህን፡ብናው
ቀው፡ልናገኘው፡እንችላለን፡አለው፡ቅዱስ፡
ቴዎድሮስም፡ወደርሱ፡ከተመለስክ፡እንደ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሐራ፡ ከማየ፡ ወይሬስየከ፡ በቅድሜሁ፡ መሥዋዕተ፡ውኩፈ።

፳፡ ወይቤሎ፡ንጉሥ፡ኢታብዝኅ፡ነገረ፡አላ፡ሡዕ፡ ለአማልክትየ፡ ከመ፡ አሀብከ፡ ንዋየ፡ ብዙኀ፡ ቅዱስሰ፡ ቴዎድሮስ፡ ረገሞ፡ ለንጉሥ፡ ወጸረፈ፡ ላዕለ፡ አማልክቲሁ፡ ወሶቤሃ፡ ተምዐ፡ ንጉሥ፡ ወአዘዞሙ፡ ለሐራሁ፡ ከመ፡ ይንሥእዎ፡ አልባሲሁ፡ ወይእሥርዎ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ጽልመት፡ ምስለ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ እለ፡ አምኑ፡ በትምህርቱ፡ ወጸለየ፡ ቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ ወወጽአ፡ በሌሊት፡ ወአስተጋብአ፡ ዕፀወ፡ ወአውዓዮሙ፡ ለኵሎሙ፡ አማልክት፡ እስከ፡ ኮኑ፡ ሐመደ፡ እስመ፡ ወሀቦሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለገነውቶሙ፡ ንዋመ፡ክቡደ፡ከመ፡ኢይስምዑ።

፳፩፡ ወሶበ፡ ነገርዎ፡ ለንጉሥ፡ ዘንተ፡ አሠሮ፡ በጽኑዕ፡ ወወሀቦ፡ ለመኰንን፡ ከመ፡ ይኰንኖ፡ ፈድፋደ፡ በዘዘዚአሁ፡ ኵነኔ፡ ወእምዝ፡ ይቤሎ፡ መኰንን፡ ለምንት፡ ኢትትኤዘዝ፡ ለንጉሥ፡ ወኢትሠውዕ፡ ለአማልክት፡ አውሥአ፡ ቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ ወይቤሎ፡ አንሰ፡ ኢይሠውዕ፡ ለአማልክት፡ ርኵሳን፡ ወኢይትኤዘዝ፡ ለንጉሥ፡ ዓላዊ። ወሶበ፡ ሰምዐ፡ ዘንተ፡ መኰንን፡ ተምዐ፡ ጥቀ፡ ወተንሥአ፡ እመንበሩ፡ ወሠረረ፡ ከመ፡ ነምር፡ ወሐነቆ፡ ክሣዶ፡ ለቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ ወአውደቆ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ወጸፍዖ፡ ገጾ፡ ወረጋፆ፡ በእገሪሁ፡ ወርእዮ፡ እግዚአብሔር፡ ትዕግሥቶ፡ ፈነወ፡ ሎቱ፡ገብርኤልሃ፡ሊቀ፡መላእክት፡ ወቀተሎ፡ ለመኰንን፡ወአስጠሞ፡ውስተ፡ማዕምቅቲሃ፡ ለምድር፡ወለቅዱስ፡ቴዎድሮስ፡ወሀቦ፡ፈረሰ፡ ፀዓዳ፡ መንፈሳዌ፡ ከመ፡ ይጸዓን፡ ዲቤሁ፡ ወያንሶሱ፡ ውስተ፡ ሀገረ፡ እስያ፡ እንዘ፡ ያንሶሱ፡ከመ፡ይምህር፡ሃይማኖተ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፳፪፡ ወሶበ፡ ሰምዐ፡ ንጉሥ፡ ዘንተ፡ ፈነወ፡ ሐራሁ፡ ምእተ፡ መስተጽዕናነ፡ አፍራስ፡ ከመ፡ የአኀዝዎ፡ ለቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ ምስለ፡ ፈረሱ፡ ወይቅትሉ፡ ኵሎ፡ እለ፡ አምኑ፡ በትምህርቱ፡ ወቀተሉ፡ ፳፻ተ፡ወ፹ወ፳ተ፡ ነፍሰ፡ ዘእንበለ፡ አንስት፡ ወደቅ፡ ወሶበ፡ በጽሑ፡ ኀበ፡ ቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ የአኀዝዎ፡ ሠረረ፡ ፈረሱ፡ ላዕሌሆሙ፡ ወአውጽአ፡ እምአፉሁ፡ እሳተ፡ ወአው

እኔ፡ ጭፍራ፡ ትሆናለህ፡ የተወደደ፡ መሥዋዕትም፡ያደርግሃል፡አለው።

፳፡ ንጉሡም፡ ነገር፡ አታብዛ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ እሰጥህ፡ዘንድ፡ለአማልክቶቼ፡መሥዋዕትን፡ አቅርብ፡ እንጂ፡ አለው፡ የከበረ፡ ቴዎድሮስም፡ ንጉሡን፡ ረገመው፡ ጣዖታቱንም፡ ሰደበ፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ ንጉሡ፡ ተቆጣ። ልብሱንም፡እንዲገፉት፡በትምህርቱም፡ከአመኑ፡ አሕዛብ፡ ጋር፡ በጨለማ፡ ቤት፡ ያሥሩት፡ ዘንድ፡ አዘዘ። የከበረ፡ ቴዎድሮስም፡ ጸለየ፡ በሌሊትም፡ ወጣ፡ ዕንጨቶችንም፡ ሰብስቦ፡ ጣዖቶችን፡ ሁሉ፡ አመድ፡ እስኪሆኑ፡ ድረስ፡ አቃጠላቸው፡ እንዳይሰሙ፡ በአገልጋዮቻቸው፡ ላይ፡ እግዚአብሔር፡ ከባድ፡ እንቅልፍ፡ አሳድሮባቸዋልና።

፳፩፡ ለንጉሡም፡ በነገሩት፡ ጊዜ፡ አጽንቶ፡ አሠረው፡ ልዩ፡ ልዩ፡ በሆነ፡ በጽኑ፡ ሥቃይ፡ አብዝቶ፡ ያሠቃየው፡ ዘንድ፡ ለመኰንኑ፡ ሰጠው፡ መኰንኑም፡ እንዲህ፡ አለው፡ ለንጉሥ፡ ለምን፡ አትታዘዝም፡ ለአማልክቶችስ፡ ለምን፡ አትሠዋም፡ የከበረ፡ ቴዎድሮስም፡ እኔስ፡ ለረከሱ፡ አማልክት፡ አልሠዋም፡ ለከሀዲ፡ ንጉሥም፡ አልታዘዝም፡ ብሎ፡ መለሰለት። መኰንኑም፡ ይህን፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ እጅግ፡ ተቆጣ፡ ከወንበሩም፡ ላይ፡ ተነሥቶ፡ እንደ፡ ነብር፡ ተወርውሮ፡ አንገቱን፡ አነቀውና፡ የከበረ፡ ቴዎድሮስን፡ በምድር፡ ላይ፡ ጥሎ፡ ፊቱን፡ ጸፋው፡ በእግሮቹም፡ ረገጠው፡ እግዚአብሔርም፡ ትዕግሥቱን፡ አይቶ፡ የመላእክት፡ አለቃ፡ ገብርኤልን፡ ላከለት፡ መኰንኑንም፡ ገድሎ፡ ከምድር፡ ዐዘቅት፡ አሠጠመው፡ ለከበረ፡ ቴዎድሮስም፡ በእስያ፡ ሀገር፡ ውስጥ፡ እየተዘዋወረ፡ የጌታ፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ሃይማኖት፡ እንዲአስተምር፡ መንፈሳዊ፡ ፀዓዳ፡ ፈረስን፡ ሰጠው።

፳፪፡ ንጉሡም፡ ይህን፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ የከበረ፡ ቴዎድሮስን፡ ከነፈረሱ፡ እንዲይዙት፡ በትምህርቱም፡ የአመኑትን፡ ሁሉ፡ እንዲገድሉ፡ መቶ፡ ፈረሰኞች፡ ወታደሮቹን፡ ላከ። ከሴቶችና፡ ከልጆች፡ በቀር፡ ስድስት፡ ሺህ፡ አርባ፡ ስምንት፡ ሰውን፡ ገደሉ። ሊይዙትም፡ ወደ፡ ቅዱስ፡ ቴዎድሮስ፡ በደረሱ፡ ጊዜ፡ ፈረሱ፡ በላያቸው፡ ተወረወረ፡ ከአፉም፡ እሳትን፡

www.ethiopianorthodox.org

ዓዮሙ፡እስከ፡ኮኑ፡ሐመደ፡ወባሕቱ፡ካልዓን፡
ረከብዎ፡ወአኀዝዎ፡ወወሰድዎ፡ኀበ፡ንጉሥ፡
ወአዘዘ ፡ ይደይዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ምቅሕ ፡
ወይኅትሙ ፡ አናቅጺሁ ፡ ከመ ፡ ኢይብላዕ ፡
ወኢይስተይ።
፰፤ ወእምዝ ፡ አስተርአዮ ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወወሀቦ ፡ ኪዳነ፡
ወሶቤሃ ፡ አውጽእዎ ፡ እምህየ ፡ ወሰቀልዎ ፡
ቍልቍሊተ፡ወቀሠፍዎ፡በጥብጣቤ፡ዘላሕም፡
እስከ፡ ተክዕወ ፡ ደሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ወእለ ፡
ለከፎሙ፡ደሙ፡ሐይዉ፡ብዙኃን፡ድውያን፡
ወእለሰ ፡ ሰምዑ ፡ ወርእዩ ፡ ተአምራቲሁ ፡
አምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ወተቀትሉ ፡ በይእቲ ፡
ዕለት፡፻ት፡ወ፹ወ፰ቱ፡ነፍስ።
፱፤ ወወረውዎሙ፡ ለእሙንቱ ፡ እለ ፡ ተቀትሉ ፡
ውስተ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ምስሌሁ ፡ ወሶቤሃ ፡
ነፍሐ፡ነፋስ፡ወኮነ፡መብረቅ፡ወነጐድጓድ፡
ወአቍረሮ፡ ለእሳት ፡ ወወጽአ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎ
ድሮስ፡እንዘ፡አልቦ፡ዘለከፎ።

፲፤ ወእምዝ፡ሶበ፡ኃጥአ፡ንጉሥ፡ዘይገብር፡ቦቱ፡
አዘዘ፡ያምጽኡ፡ለጓመ፡ዘድልወቱ፡፵ወ፩ቱ፡
ልጥር፡ወይልጕምዎ፡አፉሁ፡ወይቅንውዎ፡
እገሪሁ፡ወእደዊሁ፡ወይውግርዎ፡ለአንበሳ።
ወበከየ፡ አንበሳ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ እንዘ፡ ያንጸ
ፈጽፍ፡አንብዖ፡ወኢለከፎ፡ምንተኒ፡ወአስተ
ርአዮ፡እግዚእነ፡ወወሀቦ፡ኪዳነ፡ለዘይጼው
ዕ፡ ስሞ ፡ ወይገብር ፡ ተዝካሮ ፡ ወይጽሕፍ ፡
ገድሎ፡ከመ፡ይረሲ፡ክፍሎ፡ምስሌሁ፡በመን
ግሥተ፡ሰማያት።

፲፩፤ ወእምዝ፡አምጽኡ፡ዕፀወ፡ያረ፡፪፻ብእሲ፡ወ
፻ተ፡ልጥረ፡ፒሳ፡ወ፻ተ፡ልጥረ፡መዓረ፡ግራ፡
ወ፻ተ፡ልጥረ፡ብርት፡ወወደይዎሙ፡ውስተ፡
እቶነ፡እሳት፡ ወአንደድዎ፡እስከ፡ይረስን፡
ጥቀ፡ወእምድኅረ፡ፈጸመ፡ጸሎቶ፡ወረውዎ፡
ለቅዱስ፡ቴዎድሮስ፡ውስተ፡እቶነ፡እሳት፡
ወፈጸመ ፡ ስምዖ ፡ ወተቀበሉ ፡ ነፍሶ ፡ሚካ
ኤል፡ወገብርኤል፡ ሊቃነ፡መላእክት፡ወከለ
ልዎ ፡ በ፫ አክሊላት ፡ ወነሥአት ፡ ሥጋሁ ፡
አውሳብያ ፡ ብእሲተ ፡ መኰንን ፡ ወገነዘቶ ፡
በአፈዋት፡ዘብዙኅ፡ሤጡ፡ወወሰደቶ፡ሀገረ፡

አውጥቶ ፡ አመድ ፡ እስኪሆኑ ፡ አቃጠላቸው ፡
ነገር፡ግን፡ሌሎች፡አግኝተው፡ያዙትና፡ወደ፡
ንጉሥ፡ወሰዱት፡እርሱም፡ወደ፡እሥር፡ቤት፡
እንዲአስገቡት፡እንዳይበላና፡እንዳይጠጣም፡
ደጃፎችን፡እንዲዘጉበት፡አዘዘ።
፰፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የክብር፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ተገለጸለትና ፡ ቃል ፡ ኪዳን፡
ሰጠው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከእሥር ፡ ቤት፡ አው
ጥተው ፡ ዘቅዝቀው ፡ ሰቀሉት ፡ ደሙም ፡ እንደ
ውኃ፡እስቲፈስ፡ከላም፡ቆዳ፡በተሠራ፡ጅራፍ፡
ገረፉት፡ደሙ፡የነካቸውም፡ብዙ፡በሽተኞች፡
ዳኑ፡ተአምራቱንም፡ያዩና፡የሰሙ፡በጌታችን፡
አመኑ፡በዚያችም፡ቀን፡መቶ፡አርባ፡ስምንት፡
ሰዎች፡ተገደሉ።
፱፤ እሊህን፡ የተገደሉትንም ፡ ሰማዕታት ፡ ወደ፡
እሳት፡ማንደጃ፡ውስጥ፡ከእርሱ፡ ጋር፡ ጨመ
ሩአቸው፡ በዚያንም፡ ጊዜ ፡ ነፋስ ፡ ነፈሰ፡ መብረ
ቅና ፡ ነጐድጓድም ፡ ሆነ ፡ እሳቱንም ፡ አቀዝ
ቀዞት፡የከበረ፡ቴዎድሮስ፡ምንም፡ሳይነካው፡
ከእሳት፡ውስጥ፡ወጣ።
፲፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ የሚያደርግበትን ፡
በአጣ ፡ ጊዜ ፡ ኃምሣ ፡ አራት ፡ ልጥር ፡
የሚመዝን፡ልጓም፡አምጥተው፡አፉን፡እንዲ
ለጕሙት፡እግሮቹንና፡እጆቹንም፡በችንካር፡
ቸንክረው፡ለአንበሳ፡እንዲጥሉት፡አዘዘ። አን
በሳውም ፡ ዕንባውን ፡ እያንጠባጠበ ፡ እንደ ፡
ሰው ፡ አለቀሰለት ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልነ
ካውም። ጌታችንም ፡ ተገለጠለትና ፡ ስሙን ፡
ለሚጠራ፡መታሰቢያውንም፡ለሚያደርግ፡ገድ
ሉንም፡ለሚጽፍ፡ዕድል፡ፈንታውን፡ከርሱ፡
ጋር፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ያደርግ፡ዘንድ፡
ቃል፡ኪዳንን፡ሰጠው።
፲፩፤ ከዚህም፡በኋላ፡የሁለት፡መቶ፡ሰው፡ሸክም፡
ዕንጨት፡መቶ፡ልጥር፡ባሩድ፡መቶ፡ልጥር፡
የዶሮማር ፡ መቶ ፡ ልጥር ፡ ነሐስ፡ አመጡ ፡
ከማንደጃውም ፡ ጨምረው ፡ እጅግ ፡ እስከ
ሚግል፡ አነደዱት ፡ ጸሎቱንም ፡ ከፈጸመ፡
በኋላ፡ቅዱስ፡ቴዎድሮስን፡ወደ፡ነደደው፡
እሳት፡ወረወሩት፡ምስክርነቱንም፡ፈጸመ፡
የመላእክት፡ አለቆች ፡ሚካኤልና ፡ ገብር
ኤል፡ ነፍሱን ፡ ተቀበሉ ፡ በሦስት ፡ አክሊ
ላትም፡አቀዳጁት፡ሥጋውንም፡አውሳብያ፡
የተባለች ፡ የመኰንኑ ፡ ሚስት ፡ ወሰደች ፡

www.ethiopianorthodox.org

ገላትያ ፡ ወቀበረቶ ፡ ህየ ፡ በማዕን ፡ ዘዕብነ፡ ርኳም ፡ ወሐነፀት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአስ ተርአዩ ፡ እምሥጋሁ፡ ተአምራት ፡ ወመን ክራት፡ዐበይት።

ዋጋው ፡ ብዙ ፡ በሆነ ፡ ሹቱም ፡ ገነዘችውና ፡ ወደ፡ ገላትያ ፡ ወሰደችው ፡ በዕብነ ፡ በረድ፡ ማጥንም ፡ አድርጋ ፡ በዚያ ፡ ቀበረችው፡ ቤተ፡ ክርስቲያንም፡ሠራችለት፡ከሥጋውም፡ታላ ላቆች፡ድንቆች፡ተአምራቶች፡ተገለጹ።

፲፪፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐ ረነ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፈለጋ። ለማየ፡ሃይማኖት ፡ እንበለ ፡ ንትጋ። እንዳኢ ፡ ኤልያስ ፡ ለቤተ ፡ አክዓብ፡ ዘላፌ፡ ሕጋ። ከማከ፡ አልቦ፡ እምእለ፡ አድምዑ፡ ጸጋ። መንፈሳዌ፡ ፈረሰ፡ ዘተጽዕነ፡ በሥጋ።

፲፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ፫ ፻ወ ፫፻ ወ፩ቱ ፡ ሰብእ፡ ማኅበራነ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፲፫፡ በዚችም፡ ቀን ፡ የቅዱስ፡ ቴዎድሮስ ፡ ማኅበር፡ የሆኑ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ አራት፡ ሰዎች ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ፡ በረከታ ቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ዘላለሙ፡ ለእግ ዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለክሙ ፡ አምዓት፡ ስሳ። ወበበዐሥርቱ ፡ ሠላሳ፡ ማኅበራነ፡ ቴዎድሮስ፡ ማር ፡ መቸሴ፡ ቴዎድሮስ፡ ዕጓለ፡ አንበሳ። እምኒሩትክሙ፡ ብየ፡ ኃሠሣ። ታናሕስዩ፡ ሊተ፡ ክቡደ፡ አበሳ።

* * *

፩፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አመ ፡ ፳ወ፱ ለየካቲት ፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ተዝካረ ፡ በዓለ ፡ ልደቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በሥጋ ፡ እምእግዝ እትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ኄር ፡ ወምስለ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ መስተሣህል፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ የካቲት፡ ሃያ፡ ዘጠኝ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በሥጋ ፡ ለመወለዱ ፡ ለክብር፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ፡ የልደቱ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ነው። ከቸር፡ አባቱና ፡ ይቅር፡ ባይ ፡ ከሆነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ጋር ፡ ለእርሱ ፡ ክብር፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘላ ለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ እብል፡ ለልደትከ፡ መድምም። እምድንጋሌ ፡ ሥጋ፡ ኅቱም። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኔ፡ ዓለም። ልብየ፡ አንቅሕ፡ ለስብሐቲከ፡ አዳም። ለሥጋየሰ፡ አኀዞ፡ ድካም።

፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ቢላካ ርዮስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ዘሀገረ፡ አርሞኒ።

፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የአርሞኒ፡ ሀገር፡ ኤጲስቆጶስ፡ የከበረ፡ ቢላካርዮስ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ።

፫፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ሢመቱ፡ ብዙኀ ፡ አዝማነ ፡ እስከ ፡ ልሕቀ ፡ ወረሥአ ፡ ፈድፋደ፡ ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ወተግሣጻተ፡ ብዙኃተ፡ ወእሉኒ፡ በእንተ፡ በዓለ ፡ ልደት፡

፫፡ ይህም ፡ አባት ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ፡ አረጀ ፡ ድረስ ፡ በተሾመበት ፡ ወንበር ፡ ብዙ፡ ዘመናት ፡ ኖረ ፡ ብዙ፡ ድርሳናትንና ፡ ተግሣጻትንም ፡ ደረሰ ፡ እሊህም፡ ስለከበረች ፡ የልደት ፡ በዓልና ፡ ስለ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቅድስት፡ ወበእንተ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል፡ማርያም፡ወበእንተ፡ሞት፡ወሲኦል፡ ወዅነኔ፡ዘይበጽሖሙ፡ለኃጥአን፡ወበእንተ፡ ኪነ፡ጥበቡ፡ለመድኃኒነ፡ወበእንተ፡በዓላት፡ ክቡራት፡ ወሦዐ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ነፍሳተ፡ ብዙኃተ፡በትምህርታቲሁ፡ማሕያውያት።

፬፣ ወሶበ፡ኮነ፡መዋዕለ፡ስደት፡ወምንዳቤ፡ላዕለ፡ ሕዝበ፡ ክርስቲያን ፡ ፈተወ ፡ ከመ ፡ ይክዓው ፡ ደሞ፡በእንተ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አዘዞሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ከመ፡ ይጽንዑ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወመሀ ሮሙ፡ወነገሮሙ፡ከመ፡እሙንቱ፡ኢይሬእዩ፡ ገጾ፡እስመ፡ውእቱ፡ይፈቅድ፡ከመ፡ይክዓው፡ ደሞ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ። ወሰሚ ዖሙ፡እሙንቱ፡በከዩ፡ወኀዘኑ፡ጥቀ፡በእንተ፡ ተፈልጠቶሙ፡ወይቤልዎ፡ለምንት፡ተኃድገነ፡ ዕጓለ፡ማውታ፡ንኩን፡ወሶበ፡ኢተክህሎሙ፡ ያኅድግዎ፡ወጽአ፡እምኅቤሆሙ፡ወሖረ፡ኀበ፡ መኰንን፡ወቆመ፡ቅድሜሁ፡ወተአመነ፡በእ ግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት። መኰንንኒ፡ኰነኖ፡ብዙኀ፡ወሰአልዎ፡ሕዝብ፡ ብዙኀ፡ ስእለተ ፡ ወይቤልዎ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ አረጋዊ ፡ መሐክ፡ ርእሰከ ፡ ወጻእ ፡ እምሀገር ፡ ውእቱኒ ፡ ከመ፡ ያሠኒ ፡ ልቦሙ ፡ ይቤሎሙ ፡ እወጽእ፡በኀቡእ።

፭፣ ወበይእቲ፡ሌሊት፡ርእየ፡ራዕየ፡ከመ፡ብእሲ፡ ዘይቤሎ ፡ ለምንት ፡ ረሳዕከ ፡ ውእተ ፡ ምክረ ፡ ሠናየ ፡ ዘፈተውከ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ሰማዕተ ፡ ወእምዝ፡ተመይጠ፡ወአስተርአዮ፡ለመኰንን፡ ወሶቤሃ፡አዘዘ፡መኰንን፡ከመ፡ይምትሩ፡ርእሶ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመን ግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወነሥኡ ፡ ሥጋሁ ፡ መሃይ ምናን ፡ ወገነዝዎ ፡ በክብር ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ወአንበርዎ ፡ ውስተ ፡ መቃ ብር።

፮፣ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐ ረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓ ለመ፡ዓለም፡አሜን።

እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ስለ፡ሞትና፡ስለ፡መቃብር፡በኃጥአንም፡ላይ፡ ስለ፡ሚደርስባቸው፡ሥቃይ፡ስለ፡መድኃኒታ ችንም ፡ የረቀቀ ፡ ጥበብ ፡ ስለ ፡ ከበሩ ፡ በዓላ ትም ፡ ናቸው ፡ ሕይወት ፡ በሆኑ ፡ ትምህር ቶቹም ፡ ብዙ፡ ነፍሳትን ፡ መሥዋዕትን ፡ አድርጎ፡ለእግዚአብሔር፡አቀረበ።

፬፣ በክርስቲያንም ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ የስደትና ፡ የመከራ ፡ ወራት ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ በክብር ፡ ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ ደሙን፡ሊያፈስ፡ወደደ፡ሕዝቡንም፡ሰብስቦ፡ በቀናች፡ሃይማኖት፡ይጸኑ፡ዘንድ፡አዘዛቸው፡ ስለ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ደሙን ፡ ሊያፈስ ፡ ይሻልና ፡ እነርሱ፡ እንግዲህ፡ ፊቱን ፡ እንደማ ያዩት፡ነገራቸው።ሰምተውም፡አለቀሱ፡ስለ፡ መለየታቸውም ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ፡ የሙት ፡ ልጆች፡እንሆን፡ዘንድ፡ለምን፡ትተውናለህ፡ አሉት ፡ ማስቀረትና ፡ ማስተውም ፡ ባልተቻ ላቸው ፡ ጊዜ ፡ ከእርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ፡መኰንኑ፡ሔደ፡በፊቱም፡ቁሞ፡በክብር፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ታመነ ፡ መኰንኑም ፡ ብዙ ፡ አሠቃየው ። ሕዝቡም ፡ ብዙ ፡ ልመናን ፡ አብዝተው ፡ ለመኑት፡ራስህን፡አድን፡ከከተማም፡ውጣ፡ አሉት ፡ እርሱም፡ ልባቸውን ፡ ደስ፡ ያሰኝ፡ ዘንድ፡በሥውር፡እወጣለሁ፡አላቸው።

፭፣ በዚያችም፡ሌሊት፡ሰማዕትን፡ትሆን፡ዘንድ፡ የተመኘኸውን፡በጎ፡ምክር፡ለምን፡ረሳህ፡እን ደሚለው፡ሰው፡ሁኖ፡ራእይን፡አየ።ከዚህም፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ለመኰንኑ ፡ ተገለጠለት ፡ በዚያንም፡ጊዜ፡ራሱን፡በሰይፍ፡ይቆርጡት፡ ዘንድ፡ መኰንኑ፡አዘዘ፡የሰማዕትነት፡አክሊ ልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተቀበለ፡ ሥጋውንም ፡ ምእመናን ፡ አንሥተው ፡ ወሰ ዱት፡ለኢጲስቆጶሳትም፡እንደሚገባ፡አክብ ረው፡ገንዘው፡በመቃብር፡አኖሩት።

፮፣ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቱ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለቢላካርዮስ፡ ሰማዕት፡ወካህን።በእንተ፡ሲኦል፡ወሞት፡ነባቤ፡ድርሳን።እንዘ፡ትበኪ፡ኪያከ፡ ሀገረ፡አርሞን።አጥባዕከ፡በዓውደ፡ስምዕ፡አምሳለ፡ወሬዛ፡ሕፃን።አድክሞተከኒ፡ኢክህለ፡ርሥአን።

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ፡ ፴ሁ ፡ ለየካቲት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ ተረክበት ፡ ርእሱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥ ምቅ።

፪፤ ውእቱኬ፡እስመ፡ኄሮድስ፡ከሐዲ፡ሶበ፡አዘዘ፡ ይምትሩ፡ርእሶ፡ለቅዱስ፡ዮሐንስ፡ መተርዎ፡ በቤተ፡ሞቅሕ፡ወአብጽሕዋ፡ኀበ፡ኄሮድስ፡ ውእቱሰ፡አርአዮሙ፡ለእሊአሁ፡ከመ፡የኀዝን፡ በእንተ፡ ዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ላዕለ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐ ንስ፡ ወአትረፋ ፡ ለርእሰ ፡ ዮሐንስ ፡ ክቡር ፡ ውስተ፡ቤቱ።

፫፤ ወብእሲቱሰ፡ዘቀዳሚ፡ወለተ፡አርጣ፡ንጉሥ፡ ሶበ፡ሰደዳ፡መጽአት፡ኀበ፡አቡሃ፡ወበከየት፡ ቅድሜሁ፡ወነገረቶ፡ኵሎ፡ዘገብረ፡ላዕሌሃ፡ ኄሮድስ ፡ ዘከመ ፡ ሰደዳ ፡ ኪያሃ ፡ ወዘከመ ፡ ነሥአ፡ለኄሮድያዳ፡ብእሲተ፡እኁሁ።

፬፤ ወተንሥአ ፡ ሶቤሃ ፡ አርጣ ፡ ንጉሥ ፡ ወአስተ ጋብአ ፡ ሠራዊቶ ፡ ወበጽሐ ፡ ብሔረ ፡ ገሊላ ፡ ወአመዝበረ ፡ ኵሎ ፡ አህጉረ ፡ ወአውዓየ ፡ በእሳት።

፭፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ጢባርዮስ ፡ ቄሣር ፡ ዘንተ፡ ነገረ ፡ ወአጠየቅዎ ፡ ከመ ፡ አርጣ ፡ ንጉሥ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ ወለቱ ፡ ሶበ ፡ ሰደዳ፡ኄሮድስ፡ወበእንተዝ፡ተምዐ፡ንጉሥ፡ ጢባርዮስ ፡ ቄሣር ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀቤሁ ፡ ለኄሮድስ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ወሠዓሮ ፡ እምሢመቱ ፡ በእንተ ፡ ዘቀተሎ ፡ ለነቢይ ፡ ዐቢይ ፡ ወበእንቲአሁ ፡ ዘኮነ ፡ ምዝባሬ ፡ አህጉር፡ ወሰደዶ ፡ ብሔረ ፡ እንድልኩ ፡ ወበ ህየ፡ሞተ፡በእኩይ፡ሞት።

፮፤ ወርእሱሰ፡ለቅዱስ፡ዮሐንስ፡ ሀለወት፡ውስተ፡ ቤቱ ፡ ለኄሮድስ ፡ ቅብርተ ፡ ወእምዝ ፡ ፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ጢባርዮስ ፡ ሐራሁ ፡ ወአመዝበረ ፡ ቤቶ፡ ለኄሮድስ ፡ ወነሥአ ፡ ኵሎ ፡ ጥሪቶ ፡ ወኮነ፡ አርአያ ፡ ወመሐድምተ ፡ ለኵሉ ፡ ዘይኔጽሮ፡እስመ፡ተርፈ፡ዘእንበለ፡ተድባብ፡ ወአናቅጽ፡ወነጋድያን፡የኀድሩ፡ውስቴቱ።

፯፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ኮኑ፡ ፪ዕደው ፡ ነዳያን ፡ በንዋይ፡ወብዑላን፡በሃይማኖት፡ወእሙንቱ፡ ሖሩ፡ኢየሩሳሌም፡ከመ፡ይስግዱ፡ወይጹሙ፡ ጾመ፡፵፡ቅድስተ፡ውእቱኬ፡እምብዙኅ፡ዓመ ታት።ወሶበ፡ኮነ፡ምሴተ፡ኀደሩ፡ውስተ፡ቤቱ

፩፤ አንድ ፡ አምላክ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ የካቲት ፡ ሠላሳ ፡ በዚች፡ዕለት፡የመጥምቁ፡ዮሐንስ፡የከበረች፡ ራሱ፡ተገኘች።

፪፤ ይህም፡እንዲህ፡ነው፡ከሐዲ፡ኄሮድስ፡የከበረ፡ ዮሐንስን፡ ራሱን፡ይቆርጡት፡ዘንድ፡በአዘዘ፡ ጊዜ፡ በእሥር፡ቤት፡ራሱን፡ቆርጠው፡ወደ፡ ኄሮድስ ፡ አቀረቧት ፡ እርሱም ፡ ለወገኖቹ ፡ በማሳየት ፡ በቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ አደረገው፡ሥራ፡እንደሚያዝን፡ገለጠላቸው፡ የክቡር፡ዮሐንስንም፡ ራስ፡ በቤቱ፡ ውስጥ፡ አስቀራት።

፫፤ የፊተኛዪቱ ፡ ሚስቱ ፡ የንጉሥ ፡ አርጣ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ በአበረራት ፡ ጊዜ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ መጥታ ፡ በፊቱ፡አለቀሰች፡ኄሮድስ፡በእርሷ፡ላይ፡ያደ ረገውን፡ሁሉ፡እርሷን፡አሳዶ፡የወንድሙን፡ ሚስት፡ኄሮድያዳን፡እንዳገባ፡ነገረችው።

፬፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ አርጣ ፡ ተቆጥቶ ፡ ተነሣ ፡ ሠራዊቱንም ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ዘመተ ፡ የገሊላንም፡ ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ፡ በእሳትም፡አቃጠለ።

፭፤ ንጉሥ፡ጢባርዮስ፡ቄሣር፡ይህን፡ነገር፡በሰማ፡ ጊዜ ፡ ኄሮድስ ፡ በአባረራት ፡ በልጁ ፡ ምክን ያት፡ ንጉሥ፡አርጣ፡ይህን፡እንዳደረገም፡በአ ስረዱት ፡ ጊዜ ፡ ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ጢባርዮስ ፡ ቄሣር ፡ ተቆጣ ፡ ኄሮድስንም ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ከተማ ፡ ወደርሱ ፡ አስቀረበው ፡ በእርሱም ፡ ምክንያት ፡ የሀገሮች ፡ ጥፋት ፡ በመደረጉና ፡ ታላቁን፡ነቢይም፡ስለ፡መግደሉ፡ከሹመቱ፡ ሻረውና ፡ እንድልኩ ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ አጋዘው፡በዚያም፡በክፉ፡አሟሟት፡ሞተ።

፮፤ የቅዱስ፡ዮሐንስ፡ ራስ፡ግን፡በኄሮድስ፡ቤት፡ ተቀብራ ፡ ትኖር ፡ ነበር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ጢባርዮስ ፡ ጭፍሮቹን ፡ ልኮ ፡ የኄሮ ድስን፡ቤት፡አስፈረሰ፡ጥሪቱን፡ሁሉ፡ወሰደ፡ ለሚያየውም ፡ ሁሉ ፡ አርአያና ፡ ተረት ፡ ሆነ ፡ ያለ ፡ ጣሪያና ፡ ያለ ፡ ደጃፍ ፡ ቀርቷልና ፡ ነጋዴ ዎችም ፡ መነሃሪያ ፡ አድርገው ፡ ያድሩበት ፡ ነበር።

፯፤ በዚያንም ፡ ወራት ፡ በገንዘብ ፡ ድኆች ፡ በሃይ ማኖት ፡ ባለጸጎች ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ፡እነርሱም፡ሊሰግዱ፡የከበረች፡የአርባ፡ ቀን ፡ ጾምንም ፡ ሊጾሙ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተጓዙ ፡ ይህም ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ለኄድሮስ ፡ ዘኮነ ፡ በድወ ፡ ወአስተርአዮ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ በንዋም ፡ ለአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወአጠየቆ ፡ መካነ ፡ ርእሱ ፡ ቅድስት ፡ ወአዘዘ፡ከመ፡ይፁራ፡ወይሰዳ፡ውስተ፡ቤቱ፡ ወነቂሖ፡እምንዋሙ፡ነገሮ፡ለቢጹ፡ዘከመ፡ ርእየ፡ራእየ፡ወተንሥኡ፡ወበጽሑ፡ኀቡረ፡ ኀበ፡ውእቱ፡መካን፡ዘአመሮ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ ወሶበ ፡ ከረዩ ፡ ረከቡ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ፡ ወከሠትዋ ፡ አሜሃ ፡ ወጽአ ፡ መዓዛ ፡ ሠናይ ፡ ዘይምዕዝ ፡ ፈድፋደ ። ወረከብዋ ፡ ለርእሰ ፡ ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ወተባረኩ፡እምኔሃ፡ወሜጥዋ፡ ውስተ ፡ ውእቱ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ፡ ወፈጸሙ ፡ አፉሁ ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ቀዳሚ ፡ ወነሥአ ፡ ምስሌሁ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወአክበራ፡ክብረ፡ዐቢየ፡ወሜመ፡ቅድሜሃ፡ መኃትወ፡ዘያበርሁ፡ወትረ።

፰፡ ወሶበ፡ቀርበ፡ጊዜ፡ዕረፍቱ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ ነገራ ፡ ወአዘዛ ፡ ለእኅቱ ፡ እስመ ፡ ቅድስት ፡ ይእቲ ፡ ከመ ፡ ትግበር ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ይገብር ፡ ይእቲኒ ፡ ኮነት ፡ ዘታከብራ ፡ ለርእሰ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ወታኀቱ ፡ ቅድሜሃ ፡ ማኅቶተ፡ወትረ።

፱፡ ወኮነት ፡ ርእሱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘትፈልስ ፡ እምብእሲ ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ እስከ ፡ በጽሐት ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ አርዮሳዊ ፡ ውእቱኒ ፡ ይሔሊ ፡ ከመ ፡ ርእሱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ትገብር ፡ ተአምራተ፡ ወመንክራተ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ፡ውስተ፡ሃይማኖተ፡አርዮስ፡ክሀዲ።

፲፡ ወአንሥአ፡ላዕሌሁ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡አሐደ፡ ብእሴ ፡ ዘየዓቢ ፡ እምኔሁ ፡ ወሰደዶ ፡ እምውእቱ፡ መካን ፡ ወኮነ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ በድወ ፡ ዘኢይነብሮ ፡ ሰብእ ፡ ፍጹመ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ተሠይሙ፡አባ፡ቄርሎስ፡ኤጲስቆጶስ፡ላዕለ፡ ሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡ወአባ፡አንያኖስ፡ላዕለ፡ ሀገረ፡ኅምዳ።ወአስተርአዮ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ ለአባ፡አንያኖስ፡በንዋም፡ወነገሮ፡ወአመሮ፡ መካነ ፡ ዘውስቴቱ ፡ ርእሱ ፡ ቅድስት፡ ወሖረ ፡ አባ ፡ አንያኖስ ፡ ወአዕረጋ ፡ እምህየ ፡ በከመ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ አመ ፡ ፴ሁ ፡ ለግንቦት ፡ ውእቱሰ ፡ በዘረከብዋ፡ዳግመ፡እምድኅረ፡ረከብዋ፡አመ፡ ፴ሁ፡ለየካቲት።

ምሽትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በሆነ ፡ በኄሮድስ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አደሩ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስም ፡ ከእርሳቸው ፡ ለአንዱ ፡ በሕልም ፡ ተገለጠለትና ፡ የከበረች ፡ ራሱ ፡ ያለችበትን ፡ ቦታ ፡ አስረዳው ፡ ወደቤቱም ፡ ተሸክሞ ፡ ይወስዳት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ፡ በነቃም ፡ ጊዜ ፡ ራእይን ፡ እንዳየ ፡ ለባልንጀራው ፡ ነገረው ። ቅዱስ ፡ ዮሐንስም ፡ ወደአመለከተው ፡ ወደ ዚያ፡ ቦታ ፡ ተነሥተው ፡ በአንድነት ፡ ሔዱ፡ በቆፈሩም ፡ ጊዜ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ አግኝተው ፡ ከፈቷት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ የሚመስጥ ፡ በጎ ፡ መዓዛ ፡ ወጣ ፡ የቅዱስ ፡ ዮሐንስንም ፡ ራስ ፡ አገኙዋት ፡ ከእርሷም ፡ ተባረኩ ፡ ወደ ፡ ሸክላውም ፡ ዕቃ ፡ መለሱዋትና ፡ በፊት ፡ እንደ ነበረ፡ አፉን ፡ ዘጉ ፡ ያም ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወሰዳት ፡ ታላቅ ፡ ክብርንም ፡ አከበራት ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ የሚያበሩ ፡ መብራቶችን፡በፊቷ፡አኖረ።

፰፡ የዚያም፡ሰው፡ዕረፍቱ፡በቀረበ፡ጊዜ፡ለእኅቱ፡ ነገራት ፡ እርሷ ፡ ቅድስና ፡ ስለአላት ፡ እርሱ ፡ ሲሠራው ፡ እንደነበረ ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ አዛዛት፡ እርሷም ፡ የምታከብራትና ፡ ሁል ፡ ጊዜ፡መብራትንም፡የምታበራ፡ሆነች።

፱፡ የቅዱስ ፡ ዮሐንስም ፡ ራስ ፡ ወደ ፡ አርዮሳዊ ፡ ሰው፡ እስከ ፡ ደረሰች ፡ ድረስ ፡ ከአንዱ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ የምትፋለስ ፡ ሆነች ፡ ይህም፡ ሰው ፡ በከሀዲው ፡ አርዮስ ፡ እምነት ፡ ውስጥ ፡ እያለ ፡ የቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ራስ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ እንደምታደርግ ፡ ያስብ፡ነበር።

፲፡ የከበረ፡ ዮሐንስም፡ከእርሱ፡የሚበልጥ፡ሰው፡ በላዩ፡አስነሣበትና፡ከዚያ፡ቦታ፡አሳደደው፡ ያም ፡ ቦታ ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሀገር፡ አባ፡ አንያኖስ፡ በሀገረ፡ ኅምዳ፡ ኤጲስ፡ ቆጶስነት ፡ እስከ ፡ ተሾሙ ፡ ድረስ ፡ ፈጽሞ ፡ ሰው፡የማይኖርበት፡ምድረ፡በዳ፡ሆነ።ቅዱስ፡ ዮሐንስም፡ለአባ፡አንያኖስ፡በሕልም፡ተገልጦ፡ የከበረች፡ራሱ፡ያለችበትን፡ቦታ፡ነግሮ፡አመለከተው፡አባ፡አንያኖስም፡ሒዶ፡እንደ፡ዛሬው፡ ግንቦት ፡ ሠላሳ ፡ ከዚያ ፡ አወጣት ፡ ይህም ፡ የካቲት ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ከአገኙዋት ፡ በኋላ፡ ዳግመኛ፡ያገኙበት፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፡ ወቦ፡ ዘይቤ፡ ከመዝ፡ ወይቤ፡ ቅዱስ፡ ዮሐንስ፡
አፈ፡ ወርቅ፡ ውእቱኬ፡ ሶበ፡ አዘዘ፡ ኄሮድስ፡
ከሀዲ ፡ መተሩ ፡ ርእሶ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡
በሰይፍ፡ እንዘ፡ ሀሎ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ሞቅሕ፡
ወአምጽኡ፡ ርእሶ፡ በጻሕል፡ ኀበ፡ ኄሮድስ፡
ውእቱኒ ፡ ወሀባ ፡ ለወለተ ፡ ኄሮድያዳ ፡
ወይእቲ፡ ወሰደት፡ ለእማ።

፲፮፡ ወይእቲ ፡ ዘማ ፡ ርኵስት ፡ ሶበ ፡ ፈቀደት ፡
ትግሥሣ ፡ ተሰፍሐ ፡ ሥዕርታ ፡ በውስተ ፡
ጻሕል፡ ወሠረረት፡ ውስተ፡ አየር፡ ወኮነት፡
ዘትጸርሕ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ኢይደልወከ ፡
ከመ፡ ትንሣእ፡ ብእሲተ፡ እኁከ፡ ወነበረት፡
እንዘ፡ ትሠርር፡ ወትብል፡ ከመዝ፡ መጠነ፡
፲ወ፫ቱ፡ ዓመት፡ ወእምዝ፡ አዕረፈት፡ ወተቀ
ብረት፡ ብሔረ፡ ዓረቢያ።

፲፯፡ ወኮኑ፡ ነጋድያን፡ የኀድሩ፡ ውስተ፡ ውእቱ፡
መካን፡ ወበፈቃደ፡ እግዚአብሔር፡ በጽሑ፡
ኀበ፡ ውእቱ፡ መካን፡ ፪ዕደው፡ መሃይምናን፡
ነጋድያን፡ ወኀደሩ፡ ወአስተርአዮሙ፡ ቅዱስ፡
ዮሐንስ፡ ወአዘዞሙ፡ ከመ፡ ያዕርጉ፡ ርእሶ፡
ቅድስተ፡ ወእሙንቱ፡ አዕረግዋ፡ ወወሰድዋ፡
ምስሌሆሙ፡ ውስተ፡ ቤቶሙ፡ ወአክበርዋ፡
ክብረ፡ ዐቢየ።

፲፰፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡
መጥምቀ ፡ መለኮት ፡ ወበረከቱ ፡ ቅድስት ፡
ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፲፭፡ እንዲህም፡ የሚል፡ አለ፡ የከበረ፡ ዮሐንስ፡ አፈ፡
ወርቅ ፡ ተናገረ ፡ ይህም ፡ ኄሮድስ ፡ በአዘዘ ፡
ጊዜ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ በእሥር ፡ ቤት፡ ሳለ ፡
ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ቆርጠው ፡ በጻሕል ፡ አድር
ገው ፡ ወደ ፡ ኄሮድስ ፡ አመጡለት ፡ እርሱም ፡
ለኄሮድያዳ ፡ ልጅ፡ ሰጣት ፡ እርሷም ፡ ለእናቷ፡
ወስዳ፡ ሰጠች።

፲፮፡ ይቺም ፡ የረከሰች ፡ አመንዝራ ፡ ልትዳስሣት ፡
በወደደች ፡ ጊዜ ፡ በወጭቱ ፡ ውስጥ ፡ ጠጕ
ሩዋ፡ ተዘርግቶ ፡ ወደ ፡ አየር ፡ በረረች ፡
በአየርም ፡ ሁና ፡ የወንድምህን ፡ ሚስት ፡
ልታገባ፡ አይገባህም፡ እያለች፡ የምትጮኽ፡
ሆነች ፡ እንዲህም ፡ እያለች ፡ ዐሥራ ፡ አም
ስት፡ ዓመት፡ ኑራ፡ በዓረቢያ፡ ምድር፡ ዐርፋ፡
በዚያ፡ ተቀበረች።

፲፯፡ ነጋድያንም ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ የሚያድሩ ፡ ሆነ ፡
በእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ ሁለት ፡ አማን
ያን ፡ ነጋዴዎች ፡ ወደዚያ ፡ ቦታ ፡ ደርሰው ፡
አደሩ፡ ቅዱስ፡ ዮሐንስም፡ በሕልም፡ ተገለጠ
ላቸውና ፡ የከበረች ፡ ራሱን፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡
አዘዛቸው ፡ እነርሱም፡ አወጡዋት ፡ ከእርሳ
ቸውም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ወስደው ፡
ታላቅ፡ ክብርን፡ አከበሩዋት።

፲፰፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡
መለኮትን ፡ በአጠመቀ ፡ በከበረ ፡ ዮሐንስ ፡
ጸሎት ፡ ይማረን ፡ ልዩ ፡ የሆነች ፡ በረከቱም ፡
ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ እብል፡ ለርእስከ፡ ክቡር። ዘተረክበ፡ ዮም፡ በንዋየ፡ ጽቡር። ዮሐንስ፡ ሠራሬ፡ ንጉሠ፡ አዕዋፍ፡ ንስር። ንሥአኒ፡ በክነፊከ፡ ወአዕድወኒ፡ ለገብር። ከመ፡ ኢያስቆቁ፡ ቀዊምየ፡ በጽንፉ፡ ለባሕር።

፲፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሩ ፡ ለክቡር ፡ አባ ፡
ሚናስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡
ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡
አሜን።

ተፈጸመ ፡ ምንባብ ፡ ዘወርኀ ፡ የካቲት ፡ በሰላመ፡ እግዚአብሔር፡ ወስብሐት፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡ ለነቢያት ፡ ወሐዋ ርያት ፡ ወጻድቃን ፡ ወሰማዕት ፡ ወደናግል ፡ ወመነኮሳት፡ ወበረከቶሙ፡ ለቅዱሳን፡ መላ እክት ፡ ወበረከታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡

፲፱፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ የእስክንድርያ ፡
ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ መታሰቢያው ፡
ነው ። በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡
ለዘላለሙ፡ አሜን።

በእግዚአብሔር፡ ቸርነት፡ በየካቲት፡ ወር፡ የሚነበብ፡ ምንባብ፡ ደረሰ፡ ተፈጸመ። ለእግ ዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ የነቢ ያት ፡ የሐዋርያት ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታት ፡ የደናግልና ፡ የመነኰሳትም ፡ የቅዱሳን ፡ መላ እክትም ፡ በረከታቸው ፡ አምላክን ፡ የወለ ደች፡ የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ይኅድር ፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ወላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወላዕለ ፡ ኵልነ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | ማርያምም ፡ በረከቷ ፡ በርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ላይ ፡ ይደር ፡ በሁሉም ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳተና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሃይማኖታቸው ፡ በቀና ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ በሁላችንም ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ ላይ፡ይደር፡ለዘላለሙ፡አሜን። |

ዘአቅረብኩ ፡ ማኅሌተ ፡ አዘኪርየ ፡ አእላፈ ። እምእለ ፡ ተጸምዱከ ፡ ዘልፈ ። ለለአነብብ ፡ ተወከፍ ፡ ዘንዶትየ ፡ መጽሐፈ ። እንተ ፡ ረሰይከ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሪቀ ፡ መበለት ፡ ውኩፈ ። እምእለ ፡ አብኡ ፡ ብዑላን ፡ ዘተርፈ።

ነቢያት ፡ ቅዱሳን ፡ ወሐዋርያት ፡ ሰባክያን ። ሰማዕት ፡ ወጻድቃን ። ደናግል ፡ ዓዲ ፡ ወመነኰሳት ፡ ኄራን።ባርኩ፡ባርኮ፡ጉባኤ፡ዛቲ፡መካን።እስከ፡አረጋዊ፡ልሒቅ፡ወንኡስ፡ሕፃን።

ለዘጸሐፎ፡በክርታስ፡ወለዘአጽሐፎ፡እንዘ፡ይደርስ።ለዘአንበቦ፡ወለዘተርጐሞ፡በልሳን፡ሐዲስ። ወለዘሰምዐ ፡ ቃሎ ፡ በዕዝነ ፡ መንፈስ ። በጸሎተ ፡ እሙ ፡ ማርያም ፡ ዐራቂተ ፡ ኵሉ ፡ እምባእስ ። ኅቡረ ፡ ይምሐረነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

www.ethiopianorthodox.org